# ያልተኖረ ልጅነት

## እውነተኛ ታሪክ

ኢዮብ ጌታሁን

Sample output to test PDF Combine only

© መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
2001 ዓ.ም.

አሳታሚ፡- ኤሆፕ ኢትዮጵያ

የመጀመሪያ ዕትም ጥር 2001 ዓ.ም.
ሁለተኛ ዕትም ሚያዝያ 2001 ዓ.ም.
ሶስተኛ ዕትም መስከረም 2002 ዓ.ም.
አራተኛ ዕትም ጥቅምት 2003 ዓ.ም.
አምስተኛ ዕትም መስከረም 2004 ዓ.ም.
ስድስተኛ ዕትም ሐምሌ 2004 ዓ.ም.
ሰባተኛ ዕትም ህዳር 2006 ዓ.ም.
ስምንተኛ ዕትም መጋቢት 2007 ዓ.ም
ዘጠነኛ ዕትም ግንቦት 2007 ዓ.ም
አስረኛ ዕትም ሐምሌ 2007 ዓ.ም

የሽፋን ዲዛይን
አገኘሁ አዳነ

ስለመጽሐፉ ለፀሐፊው አስተያየት መስጠት ካሰኝዎ፡-

ፖ. ሣ.ቁ. 989 ኮድ 1250
አዲስ አበባ
ኢሜይል፡-egetahun2005@yahoo.com

በኢዮብ ጌታሁን ተጽፈው የታተሙ መጻሕፍት፡-

*ከሞናሊዛ ጀርባ—1997 ዓ.ም.*
*(የአጫጭር ልብ ወለዶች ስብስብ)*
*አለላ መልኮች—2005 ዓ.ም.*
*(በእውነተኛ ገጠመኞች ላይ የተመሠረተ)*

Sample output to test PDF Combine only

*ይህ መጽሃፍ፡ የአመለዘሙድ መታሰቢያ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣*
*የዕድሜዋን ግማሽ በስኳር በሽታና በጭንቅላት ዕጢ ስትሰቃይ ኖራ በአስር ዓመቷ ላረፈችው*

**ለሳሮን ይልማ**
**እና**
**በለጋ ዕድሜያቸው በቀላሉ ሊድኑ በማይችሉ በሽታዎች ለተቀጠፉ ህጻናት መታሰቢያ ይሁንልኝ።**

# መግቢያ

ይህን መጽሃፍ ለመጻፍ የሞከርኩት ፈጠራዊ ኢ-ልብወለድ የሚባሉ መጽሃፍት በሚጻፉበት የአጻጻፍ ዘዴ ነው። በፈጠራዊ ኢ-ልብወለድ መጽሃፍት አጻጻፍ ዘዴ የሚቀርብ እውነተኛ ታሪክ እንዲነገር ሳይሆን እንዲታይ ተደርጎ ነው የሚተረከው። መጽሃፉን ለመጻፍ ዋናዋን ባለታሪክ፣ አመለዘውድን ከሚያውቁ አርባ አንድ ሰዎች ጋር በአካልና በስልክ እንዲሁም በኢ-ሜይል ቃለመጠይቅ አድርጌአለሁ። ቃለመጠይቅ የቀረበላቸው ሰዎች የነገሩኝን በቴፕ የተቀዳና በማስታወሻ የተመዘገበ እውነታ የጊዜ ቅደም ተከተሉን ጠብቄ ምስል ከሳች በሆነ መልኩ ለማቅረብና የታሪኩ ባለቤቶች እንዲታዩ ለማድረግ አቅሜ የፈቀደልኝን ያህል ጥሬአለሁ።

መጽሃፉ ሶስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን፣ የመጀመሪያዎቹን ሁለት ክፍሎች የጻፍኳቸው በይበልጥ ከቃለመጠይቅ ባገኘሁት መረጃ ተመርኩዤ ነው። በሶስተኛው ክፍል ግን ከቃለመጠይቁ መረጃ በተጨማሪ የአመለዘውድን ደብዳቤዎች አካትቻለሁ። በመጽሃፉ የተካተቱት በቁጥር አርባ ገደማ የሚሆኑ የአመለዘውድ ደብዳቤዎችና አጫጭር መልዕክቶች ልክ እሷ እንደጻፈቻቸው ቃላቶቹም ሆነ ፊደሎቹ ሳይታረሙ የተቀመጡ ሲሆን፣ ለማንበብ ምቹና ግልጽ እንዲሆኑ ግን ስርዓተ ነጥቦቹን ለማስተካከል ተገድጃለሁ። ከአመለዘውድ ደብዳቤዎችና አጫጭር መልዕክቶች ጎን ለጎንም ለታሪኩ ፍሰት ይጠቅማሉ ብዬ ያመንኩባቸውን በሚያውቋትና በሚቀርቧት ሰዎች ለአመለዘውድ የተጻፉ አራት ደብዳቤዎችን ጨምሬአለሁ። በአንድ ደብዳቤ ውስጥ ያሉ የህዳግ ምልክት የተደረገባቸው መግለጫ የሚፈልጉ ስሞች ወይም ጉዳዮች የመጽሃፉ አካል ሆነው በቀላሉ እንዲነበቡ በሚል የተብራሩት ከገጹ በታች ሳይሆን ከደብዳቤው በታች ነው።

አሁንም አብዛኛው የህብረተሰባችን ክፍል ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ሰዎችን የማግለል ችግር ስላለበት፣ በህይወት ላሉት ወንድሞቿ ደህንነት ሲባል፣ እንዲሁም የአመለዘውድ ታላቅ ወንድም ስማቸው እንዲደበቅ ስለጠየቁ፣ ከሷ ስም በስተቀር የአመለዘውድ ቤተሰብ አባላት ስም በሙሉ ተቀይሯል። ከአንዲት ከጉዲፈቻ አሳዳጊዎቿ ጋር አሜሪካ ከምትኖር እውነተኛ ስሟ የግድ መጠቀስ ካለበት የአመለዘውድ ጓደኛ በስተቀር የሁሉም ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ህጻናትና አመለዘውድ በክፉ ያነሳቻቸው ግለሰቦች

Sample output to test PDF Combine only

ወይም በታሪኩ ውስጥ ካላቸው ሚና አንጻር በእውነተኛ ስማቸው ቢጠሩ ቅር ሊላቸው ይችላል ተብለው የተገመቱ ሰዎች ስምም ተቀይሯል።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ በትምህርተ ጥቅስ ውስጥ የተቀመጡት ጥቅሶች ቃለመጠይቅ ያቀረብኩላቸው ሰዎች በራሳቸው አንደበት የተናገሯቸው ናቸው። በአመለዘውድ ስም የተቀመጡት ደግሞ ከደብዳቤዎቿ የተቀነጨቡ ናቸው። በምዕራፉ መጀመሪያ ላይ የተናገሩት ተቀምጦ በታሪኩ ውስጥ ስማቸው ያልተጠቀሰ ሰዎች በቅንፍ ማንነታቸው ተገልጿል።

ኢዮብ ጌታሁን

መጨረሻውን ያወቅነው የመሰለን ታሪክ በየምዕራፉ አጅሬን ልብ አንጠልጣይ ሆኖ እናገኘዋለን። እንዲሆን የፈለግነውን እየተመኘን ገጽ መገለባበጣችንን አናቋርጥም። ... ኢትዮጵያዊ የሆኑ ነገሮቻችንና ማንነታችንን ፈትሸው ሚገልጹ ኢ-ልብወለድ መጻሕፍትን እንደልብ ማየት ባልቻልንበት ዘመን ኢዮብ ጌታሁን እንዲህ ያለ «ያልተኖረ ልጅነት» በሥነጽሑፋዊ አቀራረቡም ሆነ በተነሳበት ርእስ ጉዳዮች ይዘት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ነው።

-አዲስ ዘመን

ደራሲው እውነታውን ለማዝነብ በሚጋብዝ መልኩ አስተምሮታል።

-ሪፖርተር

ኢዮብ ጌታሁን «ያልተኖረ ልጅነት» በሚል ርዕስ ለንባብ ባበቃው እውነተኛ ታሪክ፣ ከቋንቋ አንጻር ደብል የሚያሰኝ ችሎታውን አስዩቶናል። ደራሲው በታሪኩ የተጠቀመው ቋንቋ ለአንባቢያን የማይጎረብጥና በሥዕል ከሳች ገለጻዎች የተሞላ መሆኑን እንረዳለን።

-ነጋድራስ

መጽሐፉ የአንድን ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ሕይወት ፍንትው አድርጎ ያሳያል። ... አንባቢው ከቤተሰቡ ጋር አብሮ የሚኖር እንዲመስለው ያደርጋል። ስሜቶችንን በጥልቀት ይነካል።

-ኢትዮጵያን ሄራልድ

ደራሲው ኢዮብ ከደብዳቤዎቿና ከቃለ ምልልስ የሰበሰበውን መረጃ በሥነጥበብ አዋቅሮ፣ በተዋበ ቋንቋ በወጉ ባይተርከው የእነዚህ ተቃጣላ ታላቅ ነፍስ ከራሳ ጩኸት እንኳ እንዴት ይሰማ ነበር!?

-አዲስ አድማስ

## በኢ-ሜይል ለመጽሐፉ ፀሐፊ ከደራሲያን የተላኩ አስተያየቶች

በንባብ ቆይታዬ ውስጥ የተለያዩ ግዜያት ስሜቶች ያሰቃዩኝ ነበር። ... (ለአመለዘውድ) አቻዋን መፈለግ ጀመርኩ፤ ሌላው አንባቢ ሌላ አቻ ይፈልግላት። እኔ ግን አና ፍራንክን አገኘኋላታለሁ፤ አና ፍራንክ ነጻነት፣ አመለዘውድ ደግሞ ጤና አጥተዋል። ሁለቱም እጅግ ዋናውን የሰው ልጅ ሀብት ማረጋገጫ አጥተው፣ ነገር ግን በመንፈስ ጠንካራነታቸውና በመኖር ፍቅራቸው፣ በሰው ልጅ ተበድለው ግና ለሰው ልጅ ባላቸው እጅግ የበዛ ፍቅር፣ ከበሽታና ከግፍ ጋር ታግለው ታላቅነታቸውን አስመሰከሩ።

-ጽጌረዳ አስራት

ተሰጥዎ ባለው ምግብ አብሳይ ድንቅ በሆነ ክህሎት ተከሽኖ እንደተዘጋጀ ምግብ «ያልተኖረ ልጅነት» የሥነጽሑፍ ቅመሞችን በሚገባ በመቀላቀል የተሠራ መጽሐፍ ነው። ታሪኩ በራሱ ስሜትን የሚነካና አንጀትን የሚያላውስ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን፣ አቀራረቡ ጣፋጭ በመሆኑ አንባቢያን ከዚህ ልብ ሰቃይ መጽሐፍ ራሳቸውን መነጠል ከባድ ይሆንባቸዋል።

-ዓለም ኃይሉ

Sample output to test PDF Combine only

«ክብነሽ! . . . ክብነሽ!»

ገና በግንብ የታጠረው ግቢ ትልቅ የብረት በር ተከፍቶልን ወደ ህጻናት ማሳደጊያው ስንገባ፣ ቁጥራቸው ከሃያ የማያንስ ህጻናት እየሮጡና እየተንጫጩ ወደ ክብነሽ መጡ። ቀድመው የደረሱት ሦስት፣ አራት ህጻናት እግሮቿ ላይ ተጠመጠሙ። ጎንበስ ብላ ብዙ ፍቅር በፈገግታዋ እያፈሰሰችላቸው ስማቸውን እየጠራች ሳመቻቸው፣ ጨበጠቻቸው።

ክብነሽን ለጊዜው ማግኘት ያልቻሉ ሌሎች ህጻናት ደግሞ ወደ እኔ መጡ። ጎንበስ ብዬ እጆቻቸውን እየጨበጥኩ ጉንጮቻቸውን እየደባበስኩ ስሞቻቸውን ጠየቅኳቸው። ብዙዎቹ ሕፃናት መታቀፍ ይፈልጋሉ። ሽቅብ እያዩኝ እጆቻቸውን ወደ ጎን ይዘረጋሉ።

በአጠቃላይ ሕፃናቱ የነበሩበት ሁኔታ ለኔ ከጠበቅኩት በላይ አስደንጋጭ ነበር። ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በተለያዩ የሚታዩ የቆዳ በሽታዎች ተጠቅተዋል። ሁለት ወይም ሶስት ሰውነታቸው የመነመነ ህጻናትም ነበሩ።

አንዱን ህፃን ሳቅፈው ጎንበስ ስል፣ «ባታቅፈው ይሻላል» አለችኝ ክብነሽ፣ «እንዴ ካቀፍከው ለማውረድ ትቸገራለህ።»

ልጆቹ የወላጅ ፍቅር የተጠሙ ስለሆኑ ያቀፋቸውን ሰው የራሳቸው ብቻ ማድረግ ይፈልጋሉ። በዚህ ምክንያት አንድ ህጻን ያቀፈ ሰው ለሌሎቹ ፍቅር ለመስጠት ይቸገራል።

የሁለት ሕፃናትን እጅ ያዝኩኝ። ግቢው ውስጥ ስዘዋወር አብረውኝ ይዞሩ ጀመር። ግቢው ጠባብ የሚባል ዓይነት ነው። ረጅም ቁመት ካለው የግቢው የብረት በር አስር እርምጃም ሳይራመዱ የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅቱ እንደ ቢሮ የሚጠቀምበት በረንዳ ያለው በሸክላ የተሰራ አነስተኛ ቤት ይታያል። ከዚህ ሸክላ ቤት ጀርባ ያለው ግቢ ከፊት ካለው ይልቅ ሰፋ ያለ ነው። ዙሪያውን የሚታዩት እንደ ዋናው ቤት በሸክላ የተሠሩ ሰርቪስ ክፍሎች አጥሩን ታከው የተገነቡ ናቸው። ግቢው ከፊትም ከኋላም በሲሚንቶ ሊሾ የተሸፈነ ነው። በስተግራ ከሚታየው አንድ ሰርቪስ ክፍል ፊት ለፊት አንዲት ሴት በጎማ የተሰራ ጥቁር ጓንት አድርጋ የህጻናቱን ልብስ ታጥባለች። ከእሷ አጠገብ ደግሞ ሌላ ሴት በእግሮቿ መሃል ያስቀመጠቻትን የአንዲት ህጻን ፀጉር ሽሩባ ትሰራለች።

«እንዴት ናችሁ?» ክብነሽ በሩቁ ሰላምታ አቀረበችላቸው።
«ደህና። እንዴት ነሽ?»

ከያዝኳቸው ህጻናት አንዱ ጨዋታ አታሎት ሄደ። ሌላኛው ግን እጁን በእጄ በመያዜ ከፍተኛ ደስታ ተሰምቶታል። ትንሽ ፊቱ ላይ ደስታና እርካታው በግልጽ ይነበባል። ዓይኖቹ ጤነኛ አልነበሩም። ደም ጎርሰዋል።



Sample output to test PDF Combine only

ወፍራም ቀለም አልባ ፈሳሽ ያመነጫሉ:: ፈሳሹ ጉንጮቹ ላይ ወርዶ ደርቋል:: በጣም የሚያሳዝን ሕፃን ነው:: ጤናውን ብቻ ሳይሆን ከወላጆቹ ማግኘት ያለበትን ፍቅር ማግኘት ያልቻለ ምስኪን! ያለኃጢአቱ የሚሰቃይ ንፁህ ሕፃን መሆኑን ሳስብ፣ ግራ ደረቴ አካባቢ ህመም ተሰማኝ:: ጉሮሮዬን የሚያንቀኝን ሳግ በየደቂቃው መዋጥ ነበረብኝ::

በስተቀኝ ካሉ ሰርቪስ ክፍሎች ወደ አንዱ ውስጥ ገባን:: የህጻናቱ መኝታ ክፍል ነው:: አልጋ ላይ ከተኛ ዕድሜው አራት ወይም አምስት ዓመት ከሚሆን አንድ ልጅ በስተቀር በክፍሉ ውስጥ ማንም አልነበረም:: ጠጋ ብለን ስናየው ዓይኖቹ አልተከደኑም:: አልጋው ላይ ብርድልብስና አንሶላ ሳይለብስ ጉልበቶቹን ወደ አገጩ አስጠግቶ ራሱን ከአደጋ ለመከላከል እንደሚሞክር ትል ጥቅልል ብሏል:: እንደ ሌሎቹ ህጻናት ፀሐይ ለመሞቅ ውጪ ያልወጣው ስለታመመ ነው::

«ዳንኤል*! ዳኒ!» ክብነሽ ስሙን ጠራችው:: «ምነው? ምን ሆንክ?» መገረሟንና ማዘኗን ከድምጿ ተረዳሁ::

ዳንኤል ዞር ብሎ አላየንም:: ክብነሽ ያለችውንም የሰማ አይመስለኝም:: ዓይኖቹ ቢገለጡም የሚያዩ አይመስሉም:: ዛል፣ ፍዝዝ፣ ድንዝዝ ብሏል::

«ዳንኤል ከመቼ ጀምሮ ነው የታመመው?» ወደ ክፍሉ ገብታ የሚታጠቡ ልብሶች ይዛ የምትወጣውን ውጪ ያየናትን ሴት ክብነሽ ጠየቀቻት::

ሴትየዋ ቆም ብላ፣ «ከትላንት ጀምሮ ነው::» አለችና ከክፍሉ ወጣች::

ክብነሽ አልጋውን ደገፍ ብላ ለአፍታ በዝምታ አየችውና፣ «አይገርምም! ከሁለት ቀን በፊት ደህና ነበር::» አለችኝ:: «ዛሬ ደህና የመሰለህ ልጅ ነገ ታሞ፣ በአደገኛ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ታገኘዋለህ::»

ምንም መናገር አልቻልኩም:: ጉሮሮዬን የለቅሶ ሳግ ደፍኖት ነበር::

በወቅቱ ከክብነሽ ጫላ ጋር አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ አንድ ክፍል እንማር ነበር:: «ከሞናሊዛ ጀርባ» የተባለው የአጫጭር ልብወለዶች መድብል መጽሐፌን ካነበበች በኋላ፣ «የዝምታ ስለባዎች» የሚል ርዕስ በሰጠሁት አጭር ልብወለድ ውስጥ ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ጋር ስለሚኖሩ ሕፃናት መፃፌ እንዳስደሰታት ነገረችኝ:: በታሪኩ ውስጥ ከተጠቀሱት ከቫይረሱ ጋር ከሚኖሩ ሕፃናት ጋር የመገናኘት ዕድል አጋጥሞኝ እንደነበረ ስትጠይቀኝ መልሴ አጭር ነበር::

* የተቀየረ ስም፤ በመግቢያው ላይ እንደተገለጸው ከአንዲት ልጅ ስም በስተቀር የሁሉም ከኤች.አይ.ቪ ጋር የሚኖሩ ህጻናት፣ የአመለዘውድ ቤተሰብ አባላትና ስማቸው በበጎ መልኩ ያልተነሳ ግለሰቦች ስም ተቀይሯል::



Sample output to test PDF Combine only



«አላጋጠመኝም::» አልኳት:: «ህፃናቱ የፈጠርኳቸው ገፀ ባህሪያት ናቸው::»

በታሪኩ ከራሴ ገጠመኝ ጋር የተያያዙ እውነታዎች ቢንፀባረቁም ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ህጻናትን በቴሌቪዥን ካልሆነ በአካል አይቼ አላውቅም ነበር::

ክብነሽ በትርፍ ጊዜዋ ከትምህርቷ ጎን ለጎን የምትሰራበት ድርጅት በአጭር ልብወለዱ እንደተጠቀሱት ልጆች ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ሕፃናት የሚያድጉበት መሆኑን ነገረችኝ::

«ድርጅቱን አንድ ቀን መጎብኘት ብችል ደስ ይለኛል::» አልኳት::
«እሺ፣ በሚመችህ ቀን ላስጎበኝህ እችላለሁ::» አለችኝ::

ዛሬ እሁድ፣ ነሐሴ 28 ቀን፣ 1997 ዓ.ም. ድርጅቱን ለመጎብኘት የመጣሁት ከወራት በኋላ የትምህርት ውጥረት ረገብ ሲልልኝ ነበር:: የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት ይባላል ድርጅቱ:: እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ ድርጅቱን ስጎበኝ በሁለት የተለያዩ ግቢዎች ውስጥ ወደ ስድሳ ገደማ ልጆችን ያሳድግ ነበር:: በጣት ከሚቆጠሩ ሕፃናት በስተቀር በሙሉ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ በደማቸው ተገኝቷል:: ሁሉም ማለት ይቻላል ወላጆቻቸውን በበሽታው ተነጥቀዋል:: አሁን ያለንበት ከሁለቱ ግቢዎች አንዱ ሲሆን የድርጅቱ የአስተዳደር ሠራተኞች ቢሮና ከስድስት ዓመት በታች ያሉ ሕፃናት መኖሪያ ነው::

ዓይኑ የሚያዝው፣ ያ እጁን የያዝኩት ፍቅር የተጠማ ሕፃን አብሮኝ በግቢው ውስጥ ይዞር ነበር:: ከክብነሽ ጋር ወደ ቢሮ እስክንገባ እጁን አለቀቀም::

የድርጅቱ የአስተዳደር ሠራተኞች ቢሮ ገብተን ቁጭ ከማለታችን አንድ ሚኒ ባስ ወደ ግቢው ዘለቀ:: አንዲት መነጽር ያደረገች ወጣት ከመኪናው ወርዳ ወደ ቢሮው ገባች:: ወጣቷ የድርጅቱ ዳይሬክተር ወ/ሪት (አሁን ወ/ሮ) ስድሴ ቡሊ ነበረች:: ስራው እንደ ሌላ ስራ ያዝ ለቀቅ የሚያደርጉት ዓይነት አይደለም:: ከፍተኛ ጽናት ይጠይቃል:: እሁድ ስራ መግባት ለስድሴ አዲስ ነገር አይደለም:: ተዋወቅን::

ሳመነታ ቆይቼ፣ «እንዴት ነው ብዙ ልጆች ይሞቱባችኋል?» ብዬ ግቢው ውስጥ ከገባሁ ጀምሮ በአእምሮዬ ሲመላለስ የነበረውን ጥያቄ ስድሴን ጠየቅኳት::

እሷ የድርጅቱ ዳይሬክተር ከሆነችበት ከነሐሴ 1996 ዓ.ም. ጀምሮ ባለፈው አንድ ዓመት ምንም ሕፃን እንዳልሞተና የሕፃናቱ ጤንነት እየተሻሻለ እንደሆነ ስትነግረኝ መጠነኛ ዕረፍት አገኘሁ::

«አሁን በቅርቡ እንዲያውም የተወሰኑት ፀረ-ኤድስ መድኃኒት መውሰድ ጀምረዋል።» አለችኝ ስድሴ። ይህን ጥሩ ዜና ስሰማ ልቤን ቁልቁል የተጫነው ከባድ ሐዘን ቀለል አለልኝ።

ድርጅቱ አሁን ካለንበት ግቢ በተጨማሪ ሌላ ዕድሜያቸው ከስድስት ዓመት በላይ የሆኑ ህጻናት የሚኖሩበት ግቢ አለው። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የድርጅቱ ሹፌር ይድነቃቸው አከለ እኔና ክብነሽን በሚኒባሱ ወደ ሁለተኛው ግቢ ይዞን ሄደ።

ሁለተኛው ግቢ ውስጥ ገባን። በሲሚንቶ የተያያዙ ትልልቅ ፍልጥ ድንጋዮች የተነጠፉበት ግቢ ነው። ስፋቱ የሚደነቅ ዓይነት ባይሆንም ጠባብ የሚባል ግን አይደለም። ድንጋይ ሳይነጠፍባቸው በተተዉ ክፍት ቦታዎች ላይ የተተከሉት አበቦችና ዛፎች በድንጋይ፣ በሲሚንቶና በግንብ ለተሰላቸ ዓይን መጠነኛ ሩታ ይሰጣሉ። ከግቢው የብረት በር ፊት ለፊት ፈንጠር ብሎ በረንዳ ያለው ተለቅ ያለ ቤት ይታያል። የግቢውን የግንብ አጥር ተጠግቶ የተገነባ ነው። በስተግራ እንደ ዋናው ቤት አጥሩን ታከው መደዳውን የተገነቡ ሰርቪስ ክፍሎች አሉ። መኪናው እንደቆመ በዙሪያው አራት ወይም አምስት ልጆች ተሰበሰቡ። ሁሉም ፍፁም ጤነኞች የሚመስሉ ናቸው።

«ይድኔ!»
«ክብነሽ!»

ልጆቹ የሚያውቋቸውን ሰዎች በማየታቸው ተደስተዋል። ክብነሽ ልጆቹን ተራ በተራ ሳመቻቸው። እኔም ጨበጥኳቸው። ነፍስ ስላወቁ እንደትንንሾቹ ህጻናት የማያውቁት ሰው ላይ ለመንጠላጠል አይቸኩሉም።

እዚህም፣ እዚያኛውም ግቢ ተገቢ ጥንቃቄ እንጂ አላስፈላጊ ፍርሃትና ማግለል እንደሌለ ለመረዳት ክብነሽን ማየት ብቻ በቅቶኛል። ከእሷ ለመማር ጊዜ አልወሰደብኝም። በየቀኑ ከምናቅፋቸው፣ ከምንስማቸውና ከምንጨብጣቸው፣ በኮንዶምም ሆነ ያለኮንዶም የወሲብ ግንኙነት አብረናቸው ከምንፈጽም ሰዎች ጥቂቶቹ ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ስለማናውቅ አናገላቸውም። ብዙዎቻችን አንድ ሰው ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ እንደሆነ ካወቅን ግን በደም ንክኪና ጥንቃቄ በጎደለው የወሲብ ግንኙነት ብቻ እንደሚተላለፍ እያወቅንም እንፈራዋለን፣ እናገለዋለን፣ እንሸሸዋለንም። በዚህ የህጻናት ማሳደጊያ ግን እንዲህ ዓይነት መሠረት የለሽ ፍርሃት የለም።

እዚህኛው ግቢ የፊቱ ቆዳ ከተኾሳረሳረ አንድ ዕድሜው አሥር ወይም የአሥራ አንድ ዓመት ከሚሆን ልጅ በስተቀር ከውጪ የሚታይ ቁስል ያለበት ወይም የተጎሳቆለ ልጅ አላየሁም።





በዋናው ቤት ውስጥ ወደሚገኘው በሕፃናት ማሳደጊያው እንደ ሳሎንና መመገቢያ ክፍል ወደሚያገለግለው ሰፊ ክፍል ገባን። አንድ ጥግ ላይ ሶፋዎች ከጠረጴዛ ጋር ይታያሉ። አንዲት ረዘም ያለች፣ ጠይም፣ ቀጭን ልጅ ረጅሙ ሶፋ ላይ ጋደም ብላለች።

ክብነሽ፣ «እንዴት ነሽ አመለዘውድ?» ብላ አገላብጣ ሳመቻት።

እኔም ጨብጫት አጠገቧ ተቀመጥን። አመለዘውድ ዕድሜዋ አስራ ሁለት፣ ከዚያ ካለፈም አስራ ሶስት ዓመት ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ።

«እንዴት ነሽ? ተሻለሽ?» ብላ ክብነሽ በአፏ እንቅስቃሴ የምትለው እንዲገባት እየጣረች ጠየቀቻት።

አመለዘውድ የመስማት ችግር አለባት። ከሷ ጋር መግባባት የሚፈልግ ሰው በጣም ጮክ ብሎ ማውራት አለበት። ወይም የከንፈሩ እንቅስቃሴ የሚነበብ መሆን ይኖርበታል።

«እዚህ'ጋ ይወጋኛል።» አለች አመለዘውድ ግራ ጎኗን እያሳየቻት፣ «ጉሮሮዬም ቆስሏል።» ወደ አፏ በጣቷ እያመለከተች።

ድምጿ በለቅሶ ሳግ የታፈነ የሚመስል፣ ወፍራም ሆኖ ድክም ያለ ነበር። ምንም የማልቀስ ፍላጎት እንደሌላት ግን ፊቷን አንብቤ ተረዳሁ። ድምጿ ሻካራና ደካማ የሆነው ዝም ብላ ስለዋለችና አቅም ስለሚያንሳት ሊሆን እንደሚችል ገመትኩ።

ከቅቤ ጋር የተቀላቀለ በርበሬ የተቀባ የቂጣ ቁራሽ በዝርግ ሰሀን ጠረጴዛው ላይ ይታያል።

«ምግብ አትበዪም?» ክብነሽ ጠየቀቻት።
«አይበላልኝም» ሌላ የሚያሳዝን ድምፅ፣ ከቀጭኗ ልጅ አንደበት ወጣ።
«መብላት አለብሽ»
«እም፣ ቂጣ ተጋግሮልኝ ትንሽ በልቻለሁ።»

ሁለት ወይም ሶስት ትልልቅ ኪንታሮቶች በአንድ እጇ አይበሉባ ላይ ይታያሉ። ሌላ ሰውነቷ ላይ የሚታይ ምንም ዓይነት ቁስል ወይም የቆዳ በሽታ አልነበረም።

ክብነሽ ለጥቂት ደቂቃዎች ስታጫውታት ቆይታ እኔና እሷን ትታን ወደ ሌላ ክፍል ሄደች።

«መብላት አለብሽ፣ እንድትበረቺ።» አልኳት ፈገግ ብዬ።
«ምን አልክ? አይሰማኝም።»
በእጄ የጉርሻ ምልክት እያሳየኋት፣ «ቶሎ እንድትድኚ መብላት አለብሽ!» አልኳት።



Sample output to test PDF Combine only

«ምግብ አይበላልኝም» አለችኝ::
«ጆሮሽን መቼ ነው ያመመሽ?»
«እ ... አይሰማኝም»
ትንሽ ጮክ ለማለት እየሞከርኩ ጥያቄውን ደገምኩላት::
አልሰማችኝም::
«ቆይ ማዳመጫ አለኝ» ጋደም ካለችበት ተነስታ ቁጭ አለች::
«እናታችን! እናታችን!» ጮክ ብላ ተጣራች::

አንዲት መልከ መልካም ወጣት ሴት ከሌላኛው ክፍል ወጣች::

«ማዳመጫዬን አምጪልኝ» አለቻት አመለዘውድ::

ከፕላስቲክ የተሰራች ማዳመጫዋን ከሚቀጥለው ክፍል አመጣችላት:: አንድ ጆሮዋ ላይ እየሰካች፣ «አሁን ይሰማኛል» አለችኝ::

«ጆሮሽን ከመቼ ጀምሮ ነው ያመመሽ?»
«ቆይቷል:: አንድ ጆሮዬን አሞኝ አባቴ ሐኪም ቤት ወስዶኝ ነበር:: ቆይቷል::»

ቁጭ እንዳለች ነበር የምታናግረኝ::
«ተኚ! ጋደም በይ::» አልኳት::
«አይ ግድ የለም፤ ቁጭ እላለሁ::»

ጋደም ማለቱ ቢሻላትም እኔን ያስደሰተች መስሏት መቀመጥ እንደመረጠች ገባኝ::

«ምግብ መብላት አለብሽ፣ እሺ!» ድምጼ እንደመታፈን ብሎ ነበር:: ፍንድት ብዬ ባለቅስ ደስ ይለኝ ነበር:: ህመሟ ቢያደክማትም እኔን ለማስደሰት ያላትን አቅም እያሟጠጠች እንደሆነ ሳስተውል ነበር በጣም ያሳዘነችኝ::

«እሺ» አለችኝ በሕፃናት ንፅህና::

አመለዘውድ ምግብ መብላት ባለመቻሏ ነው ታማሚ የሆነችው:: ብዙዎቹ በዚያ ግቢ የሚኖሩ እንደ አመለዘውድ ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ህፃናት ጤነኞችና ያማረባቸው ናቸው:: የእንቁላል ቅርፅ ያለው የአመለዘውድ ጠይም ፊትና ወደኋላ የታሰረው ፀጉሯ ወዝ አይታይባቸውም::

ብዙም ሳናወራ ክብነሽ መጣች::
«እንሂድ!»

እኔም አመለዘውድም ትንሽ አብረን ብንቆይ ደስ ይለን ነበር:: ክብነሽ ለስራ ወደ ቢሮ መመለስ ስለነበረባት ቶሎ መነሳት የግድ ነበር::



Sample output to test PDF Combine only



ወደ አመለዘውድ ዞር ብዬ ፈገግ አልኩና፣ «ቻው፣ ደህና ሁኚ» አልኳት፣ እጄን እየዘረጋሁ:: ቀጭን ትንሽ እጇን ዘረጋችልኝና ተጨባበጥን:: ከትንሽ እጇ አንጻር አለንጋ የሚባሉ ጣቶች አሏት::

«ምግብ በደንብ መብላት አለብሽ እሺ!»
«እሺ»

ከተቀመጥኩበት ሶፋ ተነስቼ ሦስት፣ አራት እርምጃ ተራመድኩና ዞር ብዬ በፈገግታ እጄን ለመጨረሻ ስንብት ወዘወዝኩላት:: ቀጭን እጇን እሷም ወዘወዘችልኝ:: ከመቅጽበት ፊቷን ፍፁም ልዩ በሆነ፣ ብሩህነቱ በጨፍጋጋ ቀን ጥቅጥቅ ደመናን በርቅሶ ከሚወጣ የፀሐይ ጮራ በሚልቅ አስደሳች ፈገግታ ሞላችው:: እውነተኛና ንፁህ ፈገግታ ነበር:: በዚያ ልዩ ፈገግታ ውስጥ የልጅነት ዓይን አፋርነት፣ የዋህነትና ፍቅር ይንፀባረቅ ነበር:: ከታመመችና አቅም ከሌላት ደቃቃ ሕፃን ላይ እንደዚያ ዓይነት ኃይለኛ ጉልበት ያለው ፈገግታ ማየቴ እጅግ አስደነቀኝ:: እስከ ሕይወቴ መጨረሻ ሊረሳኝ የማይችል፣ ትዝታው ልብን በደስታ እያሞቀ፣ ከስር፣ ከጥልቁ ደግሞ ከባድ ሐዘን የሚጭር ዕፁብ ድንቅ ፈገግታ ነበር:: አጠገቧ ቁጭ ብዬ ለጥቂት ደቂቃዎች ለሷ አዝኜና ተጨንቄ ስላናገርኳት ስለኔ ጥሩ ስሜት የተሰማት ይመስለኛል::

☆ ☆ ☆

ከአመለዘውድ ጋር ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ የተገናኘነው በዚያች ዕለት ነበር:: አመለዘውድ በሚያሳድጋት ድርጅት ውስጥ ለሚሰሩ ሰዎች፣ ለሌሎች ለምታውቃቸው ሰዎች እንዲሁም ለአሜሪካውያን የብዕር ጓደኞቿ ደብዳቤ ሥጣፍ በጣም እንደምትወድ ሰምቼ ጥቂት ደብዳቤዎቿን የማንበብ ዕድል አገኘሁ:: ደብዳቤዎቿን ሳነብ የቃላት አጠቃቀሟ፣ በደብዳቤው የገለጸችው ለሰው ያላት ፍቅር፣ ፈጣሪን አንድም ቀን አለማማረሯ . . . እጅግ አስደነቀኝ::

ደብዳቤዎቿን መነሻ አድርጌ በእሷ ህይወት ዙሪያ መፅሀፍ ለመጻፍ አሰብኩ:: የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት የእንክብካቤ ፕሮጀክት ዳይሬክተርና ሠራተኞች ሊተባበሩኝ ዝግጁ ነበሩ:: ደብዳቤዎቿን አሰባሰብኩ:: አመለዘውድን ወይም ቤተሰቦቿን ለሚያውቁ ለአርባ አንድ ሰዎች ቃለ መጠይቅ አቀረብኩ:: ከቃለመጠይቆቹ በኋላ ከጠበቅኩት በላይ ብዙ ሰዎች ሊያውቁት የሚገባ ታሪክ እንዳላት የበለጠ አመንኩ:: እነሆ!

የመጽሃፉ ፀሐፊ

# ክፍል አንድ

*«እንደፈለኩ ሣልሆን ጥሩ ሆኜ ማደግ ነው የመረጥኩት::»*
*አመለዘውድ*

Sample output to test PDF Combine only

# -1-

*«አባታችን በጣም ይወደን ነበር።»*
*አመለዘውድ*
*«'ቆይ አንጂ ትንሽ አምሽተህ ትሄዳለህ' ስንለው፣ 'ኧረ ልሂድ! ልጆቼን ጅብ እንዳይበላብኝ' ብሎን ወደ ቤቱ ሲሮጥ ይሄድ ነበር።»*
*ወ/ሮ ልኬ ጉደታ*

አቶ ግርማ ይመር ሥራ ሲጨርሱ ደንገዝገዝ ብሎ ነበር። የቀን ሠራተኛ ናቸው። በዕለቱ የተከፈላቸውን ምንዳ በኪሳቸው እንደያዙ ወደ ቤት በፍጥነት ተራመዱ። ለልጆቻቸው አንድ ነገር ይዘው ሊገቡ ወሰኑና ወደ አንድ የአትክልትና ፍራፍሬ መሸጫ ሱቅ ጎራ አሉ። ገንዘብ ካላቸው ለልጆቻቸው አንድ የሚበላ ነገር በጉያቸው ሸጉጠው መግባት ልማዳቸው ነው። በዚህ ዓለም የልጆቻቸውን ደስታና ፈንጠዝያ ከማየት በላይ የሚያስደስታቸውና የሚያረካቸው ነገር የለም።

በወ/ሮ ልኬ ጉደታ ቤት ሲያልፉ ባለፉት ሁለት ቀናት እንዳልጠየቋቸው አስታወሱ። ቆም ብለው፣ 'ለምኑን እኮ ጠፍቼባቸዋለሁ። እስቲ ዛሬ እንኳን አንድ አፍታ ብቅ ብዬ ልያቸው።' ሲሉ አሰቡና ወ/ሮ ልኬ ቤት ጎራ አሉ።

ወ/ሮ ልኬ በዕድሜ ከአቶ ግርማ ብዙም ከማያንሱት ከልጃቸው ከወ/ሮ አበበች ገመቹ ጋር በመኖሪያ ቤታቸው በረንዳ ላይ ቁጭ ብለው እያወሩ ነበር።

«እንዴት አመሻችሁ?» አሉ አቶ ግርማ ገና ገርበብ ያለውን የግቢውን የቆርቆሮ በር ገፋ አድርገው ገብተው እናትና ልጅን እንዳዩ።
«ግርማ! አንተ ነህ እንዴ? እንዴት ነህ?» አሉ ወ/ሮ ልኬ።
«እንደምን ነህ ግርማ?» አሉ ወ/ሮ አበበችም።

አቶ ግርማ ሴቶቹን ጨብጠዋቸው፣«ደህና ነኝ። እናንተ እንዴት ናችሁ?» አሏቸው።
«ደህና ነን። ምነው ለምኑን ጠፋህ?» አሉ ወ/ሮ ልኬ።
«ጠፋሁ አይደል? ሥራ ስሰራ እየመሸብኝ ለልጆቼ ቶሎ ልግባላቸው እያልኩ ስሮጥ ወደ ቤት እሄዳለሁ። ዛሬም ጠፋሁ ብዬ'ኮ ነው 'ልቀመጥም ሰላም ብያችሁ ላልፍ ጎራ ያልኩት።»
«እና አሁን ቁጭ አትልም?» አሉ ወ/ሮ ልኬ።
«አይ ልሂድ እማማ»
«እንዲያው አንድ ብርሌ እንኳን ሳትል?»



Sample output to test PDF Combine only

ወ/ሮ ልኬ ቤታቸው ጠጅ ቤት ነው። አቶ ግርማ ወ/ሮ ልኬ ቤት ጎራ ካሉ አንዳንዴ አንድ ወይም ሁለት ብርሌ ጠጅ የመጠጣት ልምድ አላቸው።

«አይ መሽቷል። ሌላ ቀን። ልጆቼን ጅብ እንዳይበላብኝ አሁን ቶሎ ልግባ።»

«ጅብ?!» አሉ ወ/ሮ አበበች ተገርመው።

«አዎ፣ ከእኛ ሰፈር በላይ ያው ጫካና ዱር አይደል? አንዳንዴ ገና ጨለም ሲል ነው ጅብ የሚመጣው።»

«ታዲያ ልጆቹን የት ያገኛቸዋል?» ጠየቁ ወ/ሮ አበበች።

«የልጅ ነገር አይታወቅም። ለጨዋታ ብለው ውጪ ወጥተውስ ቢሆን?»

«ታዲያ እናታቸው አትጠብቃቸውም?» አሉ ወ/ሮ አበበች።

«እናታቸውማ ራሷ ጠባቂ ያስፈልጋታል።»

አቶ ግርማ ለመቀለድ አስበው ባይናገሩም፣ እናትና ልጅ ሳቁ።

«አይ ግርማ!»

«በሉ እስቲ ደህና እደሩ!» አሉ አቶ ግርማ ወደ ግቢው በር እየተራመዱ።

«በል ደህና እደር!» አሉ ወ/ሮ ልኬ።

«ወቸ ጉድ! መውለድ እንዲህ እንደ ወፍ በጊዜ ወደ ጎጆ ያስሮጣል ማለት ነው!?» አሉ ወ/ሮ አበበች አፋቸውን በመዳፋቸው ከልለው እየተገረሙ።

አቶ ግርማ ከወ/ሮ,ልኬ ግቢ ወጥተው ወደ ቤት ተጣደፉ። ከአስፋልት መንገዱ በስተግራ እንደተገነጠሉ ዳገታማ የጠጠር መንገድ ተቀበላቸው። በፍጥነት ለሚወጣው ሰው የሚያደክም ረጅም ዳገት ነው። አቶ ግርማ የእቀበቱ አድካሚነት ታስቧቸውም አያውቅ። ዕድሜያቸው አርባዎቹን አጋምሶ ወደ ሃምሳዎቹ እየገሠገሠ ቢሆንም፣ አሁንም ጠንካራ ናቸው። ጉልበታቸው የሚፈተሸበት ሥራ ሲሰሩ መዋላቸው ብርቱና ሸንቃጣ አድርጓቸዋል። በሚዳቆ ቅልጥፍና ዳገቱን ወጥተው፣ ቀሪውንም መንገድ ተጉዘው ሰፈራቸው ደረሱ።

አዘውትረው የሚመጡበትን ሰዓት የሚያውቁት ሁለቱ ልጆቻቸው ተሾመና አመለዘውድ ከቤት ውጪ ግቢው ውስጥ ሆነው በጉጉት እየጠበቋቸው ነበር። ገና የግቢውን የቆርቆሮ በር ገፋ አድርገው ሲገቡ፣ «ግርማ! ግርማ!» እያሉ ወደ እሳቸው ሲሮጡ መጡ። ልጆቹ ወላጆቻቸውን የሚጠሩዋቸው አባባ፣ እማማ ወይም አባዬ፣ እማዬ ብለው ሳይሆን በስማቸው ነው።

«ተሼ! አመለ! የኔ አመለዘውድ!» አቶ ግርማ ጎንበስ ብለው የልጆቻቸውን ለስላሳና ጠይም ጉንጮች ሳሙ። ፀሐይና ውርጭ ያጠየመው ቀይ ፊታቸው ከልባቸው በሚገነፍል ፍቅርና ደስታ በፈገግታ ፈካ።





የያዙትን በኪስ ወረቀት የተጠቀለለ ብርቱካን ለተሾመ አስያዙና አመለዘውድን አቀፏት። ተሾመ የታቀፈው ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጓ። ጉያው ስር በአንድ እጁ እቅፍ እንዳደረገው ወረቀቱን ገለጥ አድርጎ ውስጡ ምን እንዳለ አየ።

«ድንቄ! ድንቄ! ግርማ ብርቱካን ገዛልን! ብርቱካን!» እያለ አባቱ የገዙትን ብርቱካን ለእናቱ ለማሳየት ወደ ቤት ተንደረደረ። ሎተሪ የወጣለት ነበር የሚመስለው።

አቶ ግርማ አመለዘውድን እንዳቀፉ ወደ ቤት ገቡ።

«ደህና ዋልክ?» አለች ድንቄ ለአፍታ ከሥራዋ ቀና ብላ ባለቤቷን እያስተዋለች።

አቶ ግርማ ለባለቤታቸው መልስ ሳይሰጧት ሴት ልጃቸውን ከእቅፋቸው አወረዱና ፍራሽ ላይ ቁጭ ብሎ ሁለት እጆቹን ወደ እሳቸው ወደዘረጋው ሦስተኛ ልጃቸው ወደ ትንሹ ሚካኤል ተራመዱ። ከፍራሹ ላይ አንስተው ሳሙትና አንድ ጥግ ላይ ጭኖቻቸው ላይ አድርገውት ተቀመጡ። አመለዘውድ አጠገባቸው መጥታ ትከሻቸውን ደገፍ ብላ ቆመች።

ተሾመ አንድ ብርቱካን ሲያወጣ እናቱ፣ «ቆይ አሁን አይደለም ተሼዬ! ከራት በኋላ ትበላዋለህ።» አለችው።

«ትምህርት ቤት መቼ ነው ምገባው?» አመለዘውድ አባቷን ጠየቀቻቸው።

«ትምህርት ቤት መግባት ፈለግሽ?»

«አዎ»

«እንደ ታላቅ ወንድምሽ?»

«አዎ»

«በቃ ስታድጊ ትገቢያለሽ።»

«መቼ ነው የማድገው?»

አቶ ግርማ ሳቁ። «አሁን፣ ብዙም ሳትቆዪ ታድጊያለሽ። ምን አስቸኮለሽ?»

ቤቷ አባት ሲገቡና ሁሉንም ነዋሪዎቿን በአራት የጭቃ ግድግዳዎቿ ስትከልል ሞቀች። አባትና እናት ለልጆቻቸው፣ ልጆቹ ለአባትና ለእናታቸው በሚያሳዩት ፍቅር ጋለች፣ ደመቀች።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አባትና እናት ከልጆቻቸው ጋር በአንድ ትሪ ዙሪያ ተቀምጠው ራታቸውን መመገብ ጀመሩ። ልጆቹ ከመብላት ባይቦዝኑም አባትና እናት ለትንንሽ አፎቻቸው የሚመጥን ጉርሻ እየጠቀለሉ ያጎርሷቸዋል።



Sample output to test PDF Combine only

«ብዬ! . . . ብላ!» ይላሉ አቶ ግርማ ልጆቻቸውን በፍቅር እያዩ።
«አንተም ብላ እንጂ!» ትላለች ድንቂ ባለቤቷን።

መልስ አይሰጧትም። ሙሉ ትኩረታቸው ልጆቻቸው ላይ ነው። ዘምታቸውን ስለለመደችው ድንቂ ምንም አይመስላትም።

ማታዉ ከፍ ካለም በኋላ አቶ ግርማ ከልጆቹ ጋር ሲጫወቱ አመሹ። ምስት ሰዓት ገደማ ልጆቹ እንቅልፍ ያዛቸው። እናትና አባትም ልጆቻቸው ከተኙ በኋላ ወደ መኝታቸው አመሩ።





## -2-

*«ጠባዩ ጥሩ፣ ታዛዥና ትሁት ስለነበር፣*
*የቀን ሠራተኝነቱ ቀርቶ በደሞዝ ቀጠርነው።»*
*ወ/ሮ ማርታ ገብረጻድቅ*
*«ጎበዝ! ጎበዝ! ጎበዝ ነበር።»*
*አቶ ተክሉ መታፈሪያ*

«እንዴት ነው ይሄ ቀዩ ልጅ ግርማ የሚባለው?» ብለው ጠየቁ አቶ ገብረጻድቅ።

«ጎበዝ! ጎበዝ! ጎበዝ ነው።» አሉ ተክሉ ለግርማ ያለው አድናቆት በአምጹም በፊቱም በጉልህ እየተንጸባረቀ።

«እኔን ሲያይ ብቻ የሚታትር እንደሆነ ብዬ ነው።»

«እረ ሰው አሉ፣ የለም ብሎ ነገር እሱ ጋ የለም። የሰጠሁትን ሥራ ቶሎ ጨርሶ ሌላ ሥራ ካለ ሊጠይቀኝ ይመጣል። እንደው አስተውለው ከሆነ'ኮ ቅልጥፍናው፣ ታዛዥነቱ፣ . . . ትህትናውስ ቢሆን። እንዴት ዓይነት ጥሩ ልጅ መሰለዎ!»

የአቶ ገብረጻድቅ አሊ ልጅ ወ/ሮ ማርታና ባለቤታቸው አቶ ደመቀ ተክለወልድ ኮተቤ አካባቢ ባለአንድ ፎቅ ቤታቸውን ሲያስገነቡ ከቀጠሯቸው የቀን ሠራተኞች አንዱ ወጣቱ ግርማ ደመር ነው። ትጉህና ፈጣን ነው። እንደአንዳንድ ሠራተኞች የት ወጣህ? የት ገባህ? የሚል ተቆጣጣሪ አያስፈልገውም። ለግርማ ተቆጣጣሪው ህሊናው ነው። ከልቡ ይሠራል።

ባለጡንቻና ፈርጣማ አይደለም። እረ እንዲያውም አጭርና ቀጭን ነው። ግን እንደ ጉንዳን ጠንካራ፣ እንደንብ ታታሪ ነው። ጉልበቱን ሳይሰስት ዶማ ያነሳል፣ ይቆፍራል። ጉድጓድ ያጠልቃል፣ ያስፋል። አካፋ ይጨብጣል፣ አፈር ይዝቃል፣ ይወረውራል። ሮጥ ብሎ ውሃ ለማምጣት፣ ደፋ፣ ቀና ብሎ ሲሚንቶ ለማቡካት፣ በባሬላ ድንጋይና ሌላ ከባድ ነገር ለመሸከምም አይሰንፍም። . . .

ታታሪ ብቻ ሳይሆን ታዛዥም ነው። ትዕዛዝ አቀላጥፎ ለመፈፀም የተፈጠረ እስኪመስል ለተክሉና ለሌሎች አብረውት እየሰሩ ለሚያስሩት አንጀት እርስ ነው።

የሁለት ፎቅ ርዝመት ያለው የሚመስለው ባለአንድ ፎቁ ውብ ሕንፃ ግንባታው ሲጠናቀቅ የግንባታ ስራውን በቅርበት ይከታተሉ የነበሩት አቶ ገብረጻድቅ ብቻ ሳይሆኑ ልጃቸው ወ/ሮ ማርታና ባለቤታቸው አቶ ደመቀም የግርማን ትጋትና ትህትና አስተውለው ነበር። አቶ ገብረጻድቅ ሌሎች የቀን



Sample output to test PDF Combine only

ሠራተኞችን ሲያስናብቱ ግርማን ጠርተው፣ «ከእኛ ጋር ለመኖር ፈቃደኛ ከሆንክ በደመወዝ እንቅጠርህ?» አሉት።

ግርማ ደስታ በልቡ ሞልቶ ገነፈለ። ጉልበቱን ለመሳም ጋት እስኪቀረው እጅ ነስቶ፣ ተሽቀዳድሞ «እሺ!» አለ።

ጠባቱ በአቶ ገብረጻድቅ ቤት ኑሮ ጀመረ። ትጋቱና ታዛዥነቱ ተመልካች አግኝቶ፣ «ዛሬንስ ስሰራ ዋልኩ፣ ነገስ እንዴት ልሆን ነው?» ከሚል የቀን ሠራተኛ የዕለት ተዕለት ሥጋትና ጭንቀት በመገላገሉ ግርማ ደስታው ወሰን አልነበረውም። የቤተሰቡ ከብቶችና ፈረሶች ነበሩ። እነርሱን መንከባከብ የሱ ኃላፊነት ሆነ። ሌላ ሥራም ካለ የግርማ እጆች መቶ ናቸው።

ከአንድ የእግር ኳስ ሜዳ በመጠኑ በሚያንሰው፣ በግንብ በታጠረው ውብ አጥር ግቢ ውስጥ ተክሉም ከግርማ ጋር አብሮ ይሠራል። ተክሉ በግርማ ታታሪነት ዘወትር ይደነቃል። እንደጋራ የተቆለለ የሥራ ክምር ቢሰጠው ቅንጣት ድካምና መታከት በልበ ሙሉው ወጣት አጠገብ አያልፍም። ቁልሉን ሥራ ደረማምሶ ቀጣሪዎቹን ያስደስታል።

ከ1950ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ ወታደራዊው የደርግ መንግስት በህዝባዊ አመጽ ዙፋናቸው የተነቀነቀውን አፄ ኃይለሥላሴን ከስልጣን አውርዶ አገሪቷን በይፋ ማስተዳደር እስከጀመረበት እስከ 1967 ዓ.ም. ድረስ ግርማ እዚያው ቤት ሲሰራ ቆየ።

ደርግ ስልጣን ላይ ከወጣ ከጥቂት ወራት በኋላ የሚከተለው ርዕዮተዓለም ሶሻሊዝም መሆኑን አወጀ። በገጠር፣ መሬት ላራሹ ተሰጠ።

የአቶ ገብረጻድቅ ልጅ ወ/ሮ ማርታ አሜሪካ ተምረው የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ይዘው ከተመለሱ በኋላ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቀጥረው ሠርተዋል። በ1960 ዓ.ም. በዘመኑ ከነበሩት ሁለት ፓርላማዎች አንዱ በሆነው፣ አጼ ኃይለሥላሴ የመረጧቸውን ግለሰቦች ብቻ በሚያስገቡበት የህግ መወሠኛ ምክር ቤት ውስጥ በኢትዮጵያ የመጀመሪያዋ ሴት የምክር ቤቱ አባል ሆነው የተመረጡት ወ/ሮ ማርታ ገብረጻድቅ ለንጉሳዊው ቤተሰብ የቅርብ ሰው ነበሩ።

ስድሳ ዋና ዋና የንጉሳዊው አስተዳደር ባለስልጣናትን መረሸኑን በይፋ በብዙሀን መገናኛ ያወጀ መንግስት ለእሳቸውና ለባለቤታቸው እንደማይመለስ አስበው ወ/ሮ ማርታ መስጋት ከጀመሩ ከራርመዋል።

ጭሰኛው የመሬት ባለቤት ከሆነ ከጥቂት ወራት በኋላ፣ ወታደራዊ መንግስት ሐምሌ 19 ቀን፣ 1967 ዓ.ም. የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶችን



Sample output to test PDF Combine only



የሕዝብ ያደረገውን አዋጅ አወጀ። አዋጁ ከታወጀ ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ወ/ሮ ማርታ ከባለቤታቸው ከአቶ ደመቀ ተክለወልድና ከልጆቻቸው ጋር ለአጭር ጊዜ ሽርሽር ወደ ላንጋኖ እንደሚሄዱ አሳውቀው ወደ ኬንያ ተሰደዱ። ቤት ውስጥ ላሉት ሠራተኞች የሚከፈል የስድስት ወር ደመወዝ ትተው ነው ባልና ሚስቱ የሄዱት።

የደርግ መንግስት ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ኢትዮጵያ ውስጥ መኖር ለደህንነታቸው አስጊ ስለሆነ፣ ወ/ሮ ማርታና ቤተሰባቸው በስደት ውጪ አገር መኖሩ እንደሚሻል አምነው፣ ከኬንያ ወደ ግሪክ፣ ከዚያም ወደ አሜሪካ ተሻግረው ኑሯቸውን በዚያው አደረጉ።

በእነግርማ ጉልበትና ላብ የታነፀው ቤተመንግስታዊ ግርማ ያለው ባለአንድ ፎቅ መኖሪያ ቤታቸው በደርግ ተወረሰ። አቶ ገብረጻድቅ ከዋናው ቤት ጀርባ በተሠሩት ሰርቪስ ክፍሎች ውስጥ ለመኖር ተገደዱ።

አቶ ገብረጻድቅ ለነዚያ ከደርግ ከመወረስ ለተረፉ ጥቂት ክፍል ቤቶችና ከበፊቱ ጠበብ ላለ ግቢ ብዙ ሠራተኞች ስለማያስፈልጓቸው የተወሰኑትን ማሰናበት ነበረባቸው። ተክሉ ከግርማ ቀድሞ የተቀጠረ ሠራተኛ ስለነበረ እሱንና ሌሎች ነባር ሠራተኞችን ሲያስቀሩ ግርማንና ሌሎች ሠራተኞችን ግን አሰናበቱ።

## -3-

*«ግርማ ከብቶቹ እንኳን ሲጠፉ፣ 'የት ገቡ?' ብሎ ፈልጎ ያመጣል:: ዛሬ ልጅስ ይታዘዛል?»*
*ወ/ሮ ልኬ ጉደታ*

በወቅቱ በደሀ ዕንባ አባሽነቱ የሚታወቀው የደርግ መንግስት የእሱን ሊረጋጋ የጀመረ ሕይወት በተቃራኒው ቢረብሸውም፣ ግርማ «ጉልበትና ጤና እስካለኝ፣ ሠርቼ መብላት አያቅተኝም::» ብሎ እዚያው ኮተቤ አካባቢ የቀን ሥራ እየሰራ ኑሮን ለማሸነፍ ደፋ፣ ቀና ማለቱን ተያያዘው::

የዚያን ጊዜው ኮተቤ እንዳሁኑ በቤቶችና በሕዝብ የተጨናነቀ፣ በመኪናና በሰው ግርግር የተረበሸ አካባቢ አልነበረም:: የኮተቤ መምህራን ኮሌጅና ጥቂት ቤቶች ብቻ ፈንጠርጠር ብለው የሚታዩበት፣ እርሻ፣ ደንና የግጦሽ መሬት ያወዙት፣ ወፎች በነፃነት የሚዘምሩበት ውብ ገጠራማ ቀበሌ ነበር:: ቀበሌው በገበሬ ማኅበር ሥር እንጂ እንደሌሎች የአዲስ አበባ ከተማ ሰፈሮች በቀበሌ የሚተዳደር አልነበረም::

በኮሌጁ አቅራቢያ ዓይን ከሚገቡ ቤቶች አንዱ የወ/ሮ ልኬ ጉደታ ጠጅ ቤት ነው:: ግርማ መጠጥ አብዝቶ ባይጠጣም፣ አንድ፣ ሁለት ብርሌ ጠጅ ወርወር ለማድረግና ከመሰሎቹ ጋር ለመጫወት አዘውትሮ ወደ ወ/ሮ ልኬ ጠጅ ቤት ጎራ ይላል:: እዚያው አካባቢ ለተለያዩ ሰዎች ሥራ ስለሚሰራ ከጠጅ ቤቱ ባለቤት ከወ/ሮ ልኬም ጋር ለመተዋወቅና ለመግባባት በቃ::

አቶ ገብረጻድቅን፣ ወ/ሮ ማርታንና ባለቤታቸውን አቶ ደመቀን የማረከው ታታሪነቱና ታዛዥነቱ በወ/ሮ ልኬም ዓይን ሞልቶ ታየ:: በተለያየ ጊዜ ያዘዙትን በቅንነትና በብቃት ሲሰራላቸው ወደዱትና በግቢያቸው ባለች አንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ ኪራይ ሳይከፍል እንዲኖር ፈቀዱለት::

ንቅሳት አንገታቸውን ያዥጎረጎረው፣ ጠይም፣ ሸንቀጥ ብለው መካከለኛ ቁመት ያላቸው፣ ኩሩ ሴት ናቸው፣ ወ/ሮ ልኬ:: የሌሎች ሰዎችን ሥራ እየሠራ፣ ወ/ሮ ልኬ የእሱን ድጋፍ በሚፈልጉ ጊዜ፣ «አለሁልዎት» እያለ ግርማ ለወ/ሮ ልኬና ለቤተሰባቸው አለኝታ ሆኖ ለጥቂት ዓመታት አብሯቸው ኖረ::

አንድ ቀን ግርማ ከዓመታት በፊት ትቶት ከመጣው ከትውልድ ቀዬው ከደቡብ ወሎ ውጫሌ በመጣ ሰው የአባቱን በፅኑ መታመም ተረዳ::



Sample output to test PDF Combine only



«አባቴ በጣም ታሟል አሉ:: ወደ አገሬ ሄጄ ላየው ነው::» አላቸው ወ/ሮ ልኬን::

«ምነው?»

«እንጃ፣ ብቻ በጣም ታሟል አሉኝ::»

«ትመለሳለህ አይደል?»

«አዎ እመለሳለሁ:: እዛ ምን አለኝ ብለው ነው? ሚስት የለኝ፣ ድስት የለኝ::» አለ ግርማ እርግጠኛ ሆኖ::

ወ/ሮ ልኬና ቤተሰባቸው መልካም ነገር እንዲገጥመው ተመኝተው ሸኙት::

ግርማ አባቱን ለማየት ወደ ውጫሌ ተጓዘ::

ወራት አለፉ:: ወ/ሮ ልኬ ጉደታና ቤተሰባቸው ከዛሬ ነገ ይመጣል ብለው ቢጠብቁትም ግርማ እንደወጣ የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ::

ወ/ሮ ልኬ፣ «ግርማ አገሩ ደርሶ ተመልሶ ሊመጣ ነበር የሄደው:: ምነው ቀረ? ወታደር ሆኖ ይሆን እንዴ?» ይላሉ፣ ከመላምት ያለፈ እርግጠኛ መልስ የሚሰጣቸው ሰው ባያገኙም:: ሥልጣን ላይ ያለው መንግስት በየአቅጣጫው በጦርነት የተወጠረበት፣ ወታደር በውዴታ ብቻ ሳይሆን በግዴታ የሚመለመልበት፣ የአፈሳ ዘመን ስለነበር ትጉሁንና አመለሸጋውን የባዳ ዘመድ በማጣታቸው ወ/ሮ ልኬ ቅር ተሰኙ::

ከሦስት ዓመት በኋላ ግን አንድ ቀን ግርማ ወ/ሮ ልኬ ቤት መጣ:: ወ/ሮ ልኬና ቤተሰባቸው ዳግመኛ ሲያገኙት በጣም ተደሰቱ::

«ምነው? የት ጠፍተህ ከረምክ?» ብለው ጠየቁት ወ/ሮ ልኬ::

«አባቴ ሞቶ ነበር የደረስኩት::»

«አዬ!. . . ሞቱ?»

«አዎ፤ እርሜን ላውጣ ብዬ ትንሽ ልቆይ ብል፣ የእርሻ ሥራ አስጀመሩኝ:: ቀስ ብለው አባብለውም ሚስት ዳሩልኝ:: አሁን ሚስቴን ትቼ፣ ያው ፈትቼ ብል ይሻላል፣ ነው የመጣሁ::» አለ ግርማ::

ወ/ሮ ልኬ በፊት ሰጥተውት የነበረውን አንድ ክፍል ቤት አሁንም ለግርማ አልነፈጉትም:: ግርማ ለሦስት አመታት አቋርጦት የነበረውን የአዲስ አበባ ኑሮውን ቀጠለ::

ለግርማ ህይወት መሻሻል ምንም ሳይፈይዱ ዓመታት ነጎዱ:: ኑሮው ከእጅ ወደ አፍ ነበር::

## -4-

*«ድንቄ መሳቅ መጫወት ነው ምታውቀው።»*

*ወ/ሮ ልኬ ጉደታ*

*«ድንቄ ግርማን በጣም ትወደው ነበር።»*

*ወ/ሮ አበበች ገመቹ*

ከዕለታት አንድ ቀን ወ/ሮ ልኬ አንዲት ጠይም፣ ወፈር ብላ ዘለግ ያለ ቁመት ያላት ወጣት ሴት በቤት ሠራተኛነት ቀጠሩ። ጠይሟ ሸጋ ድንቄ ዳምጠው ትባላለች። ሳቂታና ደስተኛ ጉብል ነች። በተለይ ትንሽ ጠጅ ከቀማመሰች ማንጎራጎር፣ በዜማ የምትወዳቸውን ማወደስ ያስደስታታል። ተጫዋችና ተግባቢ ብትሆንም አንዳንዴ ስትቆጣ ቶሎ፣ቶሎ ስድብ የሚያቀብሏት ሰይጣኖች ይከቧታል። የዋህ ስለሆነች ግን ማንም በእሷ ቁጣና ስድብ ተማርሮ አያቄምባትም። ዛሬ የተናደደችበትን ሰው፣ ነገ ቁጣዋን ረስታ ስታናግረውና ስታጫውተው ምን ነካኝ ብሎ ያመርባታል?

ግርማ ድንቄ ላይ ዓይኑን ጣለ። ፈገግታዋን፣ ጨዋታ ወዳድነቷን፣ የዋህነቷን፣ የምታንጎራጉረውን ዜማ፣ ዘለግ ያለ ቁመናዋን . . . ወደደላት። በዚያ ላይ ባለሞያ ናት። ወጧ ይጣፍጣል። ግርማ ከሥራ መልስ ቤቱ ሲገባ ሲያያት ልቡ ወከክ፣ አእምሮው ዘና ማለት ጀመረ። ክፍሉ ውስጥ ጋደም ብሎም ከቀንና ከሌሊት ህልሙ ጋር የሚሸምናት ውብ ጥበብ ሆነች፣ የወረ ኢሉኑዋ ቆንጆ፣ ድንቄ!

ወረ ኢሉኑና የግርማ የትውልድ ቦታ ውጫሌ ወሎ ውስጥ እንደመገኘ ታቸው የአገር ልጅነቱን ሰበብ አድርጎ ለመግባባት ለግርማ ተመቸው። ስለልጅነት ዘመናቸው፣ ስለሚያውቁት ባህል፣ ወንዝና ተራራ ያወጋታል። ደስ ብሏት ታዳምጠዋለች። ብቻዋን ሲያገኛት ይላፋታል፣ ይጎነታትላታል።

«ኧረ! እረፍ አንተ!» እያለች ትስቅና ትፈነድቃለች እንጂ አትቆጣውም።

ቀናት ሳምንታትን፣ ሳምንታት ወራትን እየወለዱ ሲያልፉ ይበልጥ ተቀራረቡ። ተግባቡ። ሲላፋትና፣ ሲጎነታትላት ድንቄ «ተው! እረፍ!» ማለት አቆመች። ለአፍቃሪዋ የየዋህ ልቧን በር ወለል አድርጋ ከፈተችለት። ግርማ እሷን ከሚወዳት የበለጠ፣ እሷ እሱን ወደደችው።

ድንቄ የሚጥል በሽታ አለባት። ወ/ሮ ልኬ ቤት ስትሰራ ሁለት ጊዜ ራሷን አስቶ ጥሏታል። በሰውነት ውስጥ የሚገኘው የነርቭ ኤሌትሪካዊ ቅብብሎሽ ስርዓት ሲዛባ በሚከሰት በዚህ የጤና ችግር የሚቸገሩትን ሰዎች ብዙዎች ክፉ መንፈስ እንደተጠናወታቸው ያስባሉ። ይፈሯቸውማል። ግርማን ግን ይህ የጤና ችግሯ ድንቄን ከማፍቀር ሊገታው አልቻለም።



Sample output to test PDF Combine only



ይውደዳት እንጂ ገጠር አግብቶ ትዳርን ስላየውና ብዙም ስላልወደደው፣ ድንቄን የማግባት ጉጉት አልነበረውም። ድንቄ ግን በፍቅሩ ነድዳ ስለነበር ባሏ እንዲሆን ትመኝ ነበር። . . .

ድንቄ ወ/ሮ ልኬ ቤት ተቀጥራ ለሦስት ዓመታት ያህል ሠራች። የሁለቱ ፍቅር በወ/ሮ ልኬና በልጆቻቸውም የሚታወቅ የአደባባይ ምስጢር ሆነ። ግርማን እንደሚቀሟት የሚቀልዱ ሴቶች እንኳን የቅናት እሳት በድንቄ ልብ ውስጥ ይለኩሳሉ።

«እማማ እስቲ ለቤት መሥሪያ መሬት ያሰጡኝ።» እያለ ግርማ በተደጋጋሚ ወ/ሮ ልኬን ይወተውታቸው ነበር።

ከጠጅ ቤቱ ፊት ለፊት ከአስፋልት መንገዱ ወረድ ብሎ ከተንጣለለው ፣ የወ/ሮ ልኬ ከብቶች ከሚሰማሩበት፣ ሰፊ የግጦሽ መሬት ገበሬ ማኅበሩ እየሸነሸነ ለአንዳንድ ቤተ ሠሪዎች ቦታ መስጠት ጀምሮ ነበር። ወ/ሮ ልኬ አንድ ቀን ወደ ገበሬ ማኅበሩ ጽ/ቤት ሄዱ። ከእርሳቸው ጋር ቦጥገኝነት ለሚኖረው ለአቶ ግርማ ይመርም ከግጦሽ መሬታቸው የቤት መስሪያ ቦታ ተከልሎ እንዲሰጠው ጠየቁ።

የገበሬ ማኅበሩ ምላሽ ቀና ነበር። ምንም ቢሆን የገበሬ ማኅበሩ አመራሮች የወ/ሮ ልኬ ጉደታን ጠጅ ይጠጡ አይደል?! እንዴት እኚህ በአካባቢው የተከበሩ ሴት ወይዘሮ የጠየቁት እንቢ ይባላል?! ለአቶ ግርማ የቤት መስሪያ ቦታ ተሰጠው።

አቶ ግርማ በተሰጠው ቦታ ላይ አንዲት አነስ ያለች ደሳሳ ቤት ቀለሰ። ለሱ ከፍተኛ ፍቅር ስላላት፣ የእሷን ያህልም ባይሆን እሱም ስለሚወዳት፣ የሁለቱን ግንኙነትም ወ/ሮ ልኬን ጨምሮ ብዙ ሰው ስለሚያውቅ ድንቄን ሊያገባት ወሰነ። ሠርግ መልስ የሚል ጣጣም ሳያበዛ፣ (ለነገሩ ቢመኝስ በምን አቅም?) አዲስ አበባ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ «የኔ» የሚለው ቤት ድንቄን ይዟት ገባ።

ኑሮዋቸው ከእጅ ወደ አፍ ነበር። ድንቄ ደግሞ ስለገንዘብም ሆነ ስለገንዘብ አጠቃቀም ያላት ዕውቀት አናሳ ነው። የትኛውን ምግብ በምን ያህል መጠንና ብር መግዛት እንዳለባት አታውቅም። እንደ ጤፍ፣ ዘይትና ሽንኩርት ያሉ በየቀኑ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ነገሮች በበቂ ሁኔታ ሳይኖሩ ሥጋ በመግዛት ገንዘብ ታባክናለች። ጉልት ሄዳ አላዋቂነቷን በተረዱ ነጋዴዎች ተጭበርብራ የአንድ ብሩን ድንች በሁለት ብር ገዝታ ትመጣለች። ደስ ካላትም ገንዘብ በእጇ እስካለ ድረስ መንገድ ላይ ያየችውን ኮንጎ ጫማ ወይም ሻሽ ያለዕቅድ ትገዛለች። ገንዘቡ ታዲያ ከወር እስከ ወር እንዴት ያድርሳቸው!? እምብርት ላይ በሚቀር ካናቴራ ራቁት ኃፍረተ ሥጋን ለመሸፈን እንደመጣጣር ለግርማ ኑሮ እጥረትና ክፍተት የሞላበት

የሚያበሳጭና አሳፋሪ ትግል ሆነበት:: ጭቅጭቅና ንትርክ በደሳሳዋ ቤት ከተሙ:: ገና ከጅምሩ ሁለት ወር እንኳን አብረው ሳይኖሩ ባልና ሚስቱ ተጣሉ:: ድንቄ ጭንቅ አትችል፤ ቤቱን ጥላለት ወጣችና ሌላ ሰው ቤት በቤት ሠራተኛነት ተቀጥራ መስራት ጀመረች::

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ አንድ ቀን መንገድ ላይ ተገናኙ::

«ሰማህ!» አለችው ድንቄ፣ «እኔ ልጂት እንዳንተ የጭድ ፍራሽ ላይ ሳይሆን ባማረ የብረት አልጋ ላይ ነው የምተኛው:: መናጢ ደሀ! አንድ የረባ ወንበር እንኳ በቤትህ የለ፤ ደግሞ አንተን ብሎ ባለ ቤት:: ልንገርህ! እኔ ቤተመንግስት ውስጥ ነው የምኖረው:: እንዳንተ የጭቃ ጎጆ ውስጥ እንዳይመስልህ::. . .» ድንቄ ሰይፍ ምላሷን መዘዘችበት:: ደሃ መሆኑን እስኪበቃው አስታወሰችው:: የቀጣሪዎቿ ንብረት የራሷ የሆነ ያህል እስኪበቃት፣ ምራቋ እስኪመራት ጉራዋን ነዛችበት::

ግርማ በጣም ተናደደባት:: በዚህ ወቅት ብቻ ሳይሆን በሌላም ጊዜ ከእሷ ጋር አፍ ለመካፈት ፍላጎቱ እንኳን ቢኖረው እንደማይችላት ያውቀዋል:: አንገቱን አቀርቀሮ በፍጥነት ከአጠገቧ ራቀ እንጂ አልተጋፈጣትም::

ድንቄ ያልተረዳችው እውነታ ነበር:: ለካ እርጉዝ ነበረች!

ከወራት በኋላ መውለዷ ተሰማ:: የተወለደው ልጅም የግርማ እንደሆነ ተወራ:: ይኸው ወሬ ግርማ ጆሮ ለመድረስ ጊዜ አልወሰደበትም::

«የኔ ልጅ አይደለም!» ብሎ ካደ::

ወ/ሮ ልኬ ልጃቸውን መስፍንን ድንቄ ስላለችበት ሁኔታ እንዲያጣራ ላኩት::

«ልጁ አባቱን ቁርጥ ነው!» አለ መስፍን የሩቅ ዘመዷ ቤት ተጠግታ ወንድ ልጅ የወለደችውን ድንቄን ጠይቆ ሲመጣ:: «ጆሮው ልክ እንደአባቱ ጆሮ ትንሽ ነው!»

መስፍን ይህንኑ ለግርማ ሲነግረው፣ «ከማንም የወለደችው ቢሆንስ? የኔ ላይሆን ይችላል::» ብሎ ተከራከረ::

«ቁርጥ አንተን ነው ስልህ!» አለው መስፍን::
«አልክ መስፍን? በኔ ፈረድክ?!»
«አዎ፣ ፉንተ ልጅ ነው!»

ወ/ሮ ልኬና ልጆቻቸው ሌሎች ወዳጆቹም ህጻኑን ሄዶ እንዲያይ ግርማን ወተወቱት::





ግርማ መስፍን በፈጠረበት ጉጉትና በወ/ሮ ልኬ ቤተሰብ ውትወታ ተገፋፍቶ ድንቄ ወዳለችበት ሄደ:: ህጻኑን ሲያየው ሊቆጣጠረው ባልቻለው ደስታ ተሞላ:: መስፍን አጋኖ እንደተናገረው ከአባቱ ጋር ባይመሳሰልም ግርማ ከሱ ጋር እንደሚመሳሰል ማሰብ ፈለገ:: ልጁ እንደሆነም በፀጥታ አመነ::

ዕድሜ ለህጻኑ ባልና ሚስቱ ታርቀው ከበኩር ልጃቸው ጋር አብረው መኖር ጀመሩ:: ሕፃኑንም ተሾመ አሉት::



Sample output to test PDF Combine only

## -5-

*«ቤቱን ሸጦ ኪራይ ቤት ገባ። . . . 'ቦታ ግዛ እንጂ!*
*እስከ መቼ ተከራይተህ ትኖራለህ?' አልኩት።»*
*ወ/ሮ ልኬ ጉደታ*

ጥቂት ዓመታት አለፉ። የአቶ ግርማ ቤተሰብ ኑሮ አሁንም ውሃ ቅዳ፣ ውሃ መልስ ነበር። እንደ ሆድ ነው፤ የሞላ ቢመስልም፣ ወዲያው ይጎድላል። አቶ ግርማ በአብዛኛው የቀን ሥራ፣ ሲቀናቸው ደግሞ የኮንትራት ሥራ ይሰራሉ። ድንቄም ወ/ሮ ልኬ ቤት እየተመላለሰች የወጥ ቤት ሥራ ትሰራለች። አንዳንዴ አቶ ግርማ ሥራ ሲያጡ፣ ባይራቡም የረባ ምግብም ማግኘት እንኳን አስቸጋሪ ይሆናል። ደግነቱ የራሳቸው ቤት አላቸው።

ጥንብ አንሳ ለሞት ከተቃረበ እንስሳ አጠገብ ሆኖ በትዕግስት ሞቱን እንደሚጠብቅ፣ አንዳንድ ደላሎችም ደሀ ባለመሬቶችን በችግራቸው ወቅት ለመፈታተን በቅርበት ያንዣብቡባቸዋል።

«ይሄ አስፋልት ዳር ያለ መሬትህ እኮ ፈላጊው ብዙ ነው። በደህና ዋጋ ብትሸጠው እኮ ትንሽ ከመንገድ ገባ ብለህ ሌላ መሬት በርካሽ ትገዛና የተሻለ ኑሮ መኖር ትችላለህ።» ይሏቸዋል አቶ ግርማን።

ጠግቦ ለማያድርና ለታረዘ ደሀ ይህ ከባድ ፈተና ነው። ለተራበ ነብር ያላያትን ቅርቡ ያለች የሜዳ ፍየል እያሳዩ፣ «ያችንም በቀላሉ ይዘህ ልትበላት ትችላለህ እኮ» እንደ ማለት ነበር።

አቶ ግርማ፣ 'እውነት እኮ ነው። እኔ ይህን መሬት በነጻ ነው ያገኘሁት። ብሸጠው እኮ ትርፍ እንጂ ኪሳራ አይሆንም።' ብለው ማሰብ ጀመሩ። በሃሳብ ብቻ አልቀሩም። የንፋስና የዶፍ ዝናብ ዛቻ የሚያሳቅቃት ደቃቃ ቤታቸው ያረፈችበትን ሰፋ ያለ ቦታ ለመሸጥ ወሰኑ። ደላሎቹ እንዳሉትም ቦታው ለአስፋልት መንገዱ ቅርብ በመሆኑ ገንዘብ ያላቸው ሰዎች ሊገዙት የሚፈልጉት ዓይነት ነበር። አቶ ግርማ ገዢ ፍለጋ ብዙ መድከም አላስፈለጋቸውም። ቦታቸውን ከነደሳሳ ቤታቸው በአምስት ሺህ ብር ሸጡትና ከደላሎች ጭቅጨቃና ማባበል ተገላገሉ!

አቶ ግርማ በሕይወታቸው እንኳን ቆጥረውት፣ ይዘውት የማያውቁት ገንዘብ በእጃቸው ገባ። ከእሳቸው ከተሻሉ ሰዎች እኩል የመሆን ደስ የሚል ስሜት ተሰማቸው። የራሳቸውን ቤት እስኪገዙ፣ ከባለቤታቸው ከድንቄና ከትንሹ ልጃቸው ከተሾመ ጋር የወ/ሮ ልኬ ጎረቤት ቤት አንዲት ክፍል ተከራይተው መኖር ጀመሩ። እንዳሰቡት ግን በአነስተኛ ዋጋ ቤት ቶሎ መግዛት አልቻሉም።





ተሾመ ድሆ፣ ድክ ድክ ብሎ፣ የወተት ጥርሶቹን አብቅሎ በጨረሰበት ዕድሜ፣ ጥቅምት 19 ቀን፣ 1981 ዓ.ም. ሌላ አንዲት ሴት ሕፃን ከቤተሰቡ ጋር ተቀላቀለች። ይህችን ጠይም ሕፃን ወላጆቿ አመለዘውድ አሏት። የኪራይ ቤቷ በአራት ሰው ትንፋሽ ሞቅ፣ ሞቅ አለች።

ብዙ ይመስል የነበረው ከቤት ሽያጭ የተገኘ ብር ይህ ነው የሚባል ቁም ነገር ላይ ሳይውል ከቀን ወደ ቀን መመናመን ጀመረ። ገንዘቡ ከእጃቸው ቀስ በቀስ እየሾለከ ቢሆንም አቶ ግርማ ተዘናግተው ከራረሙ።

የተከራዩት ቤት ከወ/ሮ ልኬ ቤት ጋር ይዋሰናል። በሁለቱ ቤቶች መካከል የረባ አጥር እንኳን የለም። በተለያዩ ቀናት ድንቄ ከአከራዩዋ ጋር ስትሰዳደብና ስትጨቃጨቅ ወ/ሮ ልኬ ይሰማሉ።

ወ/ሮ ልኬ ድንቄ ከአከራዩዋ ጋር ስትጨቃጨቅ በሰሙበት አንድ ቀን አመሻሽ ላይ አቶ ግርማ ሊጠይቋቸው ቤት መጡ። እንደ ዘመድና የቅርብ ወዳጅ ናቸውና አቶ ግርማ አዘውትረው ወ/ሮ ልኬን ይጎበኙዋቸዋል።

«ግርማ ሚስትህ ከአከራያችሁ ጋር በየጊዜው ስትጣላና ስትጨቃጨቅ እየሰማኋት ነው። ዛሬም ስትሳደብ ነበር።» አሉት ወ/ሮ ልኬ ጠይም ግንባራቸውን ቋጥረው።

«ምን እሷ መሳደብ ልማዷ'ኮ ነው። አሁን ተቆጥታ ወዲያው ትረሳዋለች።»

«እንደኛ አብሯት አንድ ቤት የሚኖር ሰው ነዋ ፀባዩዋን የሚያውቅላት። እንዲህ ከአከራይ ጋር የምትጣላ ከሆነማ እንዴት ተከራይታችሁ ትኖራላችሁ?»

«አዎ እሱስ ልክ ነዎት።» አሉ አቶ ግርማ ራሳቸውን በስምምነት እየነቀነቁ። ከልባቸው ግን አልነበረም።

«አንተ ግን ቦታ ግዛ እንጂ! እስከመቼ ነው ተከራይተህ የምትኖረው? ቤት ሸጠህ'ኮ ሌላ ቤትም ሳትገዛ ብሩን ልታጠፋው ነው። ኋላ መውደቂያ አጥተህ የባሰ ችግር እንዳይደርስብህ።»

«እማማ መሬት ውድ ሆኖብኝ'ኮ ነው። ባዶውን ቦታ አምስትና ስድስት መቶ ብር ይላሉ።»

«አይ ቢሆንም፣ ተወደደ ብለህ ባትዘናጋ ጥሩ ነው። ነገርኩህ፣ ኋላ መውደቂያ እንዳታጣ።»

«ልክ ነዎት። እስቲ እርስዎም በሚያውቁት ሰው በእኔ አቅም የምገዛው ቤት ያፈላልጉልኝ።» አሉ አቶ ግርማ የወ/ሮ ልኬን ምክር ከልብ ተቀብለው።

በዚያው ሰሞን ወ/ሮ ልኬ በቅርብ ከሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አቅራቢያ ጣሪያዋ በስምንት ቆርቆሮ የተሰራች ትንሽ የጭቃ



Sample output to test PDF Combine only

ቤት ያረፈችበትን ቦታ ለመሸጥ የተዘጋጀ ሰው እንዳለ ሰሙ:: የሰሙትን ለአቶ ግርማ ነገሯቸው::

አቶ ግርማ ጊዜ ሳያጠፉ ከዋናው መንገድ የአስራ አምስት ደቂቃ የእግር መንገድ ተገብቶ የምትገኘውን ደሳሳ ቤት አዩዋት:: ወለሏ አፈር ነው:: ጣሪያዋ እንደ ምላጭ በሳሳ ርካሽ ቆርቆሮ የተሰራ ነው:: የመሬቱ ባለቤት፣ «ይህ ቦታ ባለቤት አለው» ለማለት ያህል ብቻ ለምልክት የሰሯት፣ የዘበኛ ቤት የምትመስል ጠባብ የጭቃ ቤት ናት:: ጠባብነቷ አቶ ግርማን አላስከፋቸውም:: እሳቸው ባዶ ቦታ መግዛት ነበር የጠሉት:: ቆርቆሮ፣ እንጨት፣ ምስማር፣ . . . ለመግዛት እያሉ ወጪ ማውጣት፣ ቤት ለመሥራት ላይ፣ ታች ማለት አልፈለጉም:: ከቤቷና ከቦታው ባለቤት ጋር ተደራድረው ጠባቧን ቤትና ሁለት መቶ ካሬ ሜትር ገደማ ስፋት ያለውን ግቢ በ750 ብር ገዙ::

የሌላ ተጨማሪ ወር የቤት ኪራይ ሳይከፍሉ፣ በ1981 ዓ.ም. ባልና ሚስቱ ከልጆቻቸው ከተሾመና የጥቂት ወራት ዕድሜ ካላት ከአመለዘውድ ጋር ጠባቧ ጭቃ ቤት ውስጥ ዓይን የማይገባ ንብረታቸውን ጠቅልለው ገብተው መኖር ጀመሩ:: . . .

አመለዘውድን በሶስት ዓመት አስቀድሞ ሚካኤል የተባለ እንደ አባቱ ቀላ ብሎ ጉንጮቹ የተድቦለቦለ ድንቡሼ ሕፃን ተወለደ::



Sample output to test PDF Combine only



## -6-

*«አመለዘውድ ቤት ውስጥ ብዙ ሥራ ትሠራ ነበር::»*
*ብዙነሽ መሃመድ (እሙሽ)*
*«እንደ ልጅ መጫወት፣ አቧራ ማቡነን አመለዘውድ'ጋ የለም::»*
*እመቤት ተፈሪ*

አመለዘውድ ገና በስድስትና ሰባት ዓመቷ በቤት ውስጥ ሥራዎች እናቷን የምታግዝ፣ የምትላላክ ልጅ ሆነች:: ወ/ሮ ድንቂ የልጇ ዕርዳታ ያስፈልጋታል:: ልጅ ተንከባክባ፣ የሰፈሩ ሰዎች በተለምዶ «አስፋልት» ከሚሉት ከኮተቤ መምህራን ኮሌጅ አካባቢ ውሃ አምጥታ፣ የቤት ውስጥ ስራዎችን ሠርታ . . . ከባድ ኃላፊነቷን ብቻዋን መወጣት ቀላል አልነበረም::

ትንሿ አመለዘውድ እንደ ብዙዎቹ የዕድሜ እኩዮቿ በነፃነት ለመጫወትና ለመቦረቅ ብዙም ጊዜ አልነበራትም:: መደረግ ያለበትን አድርጋ ከተላከችበት ስትመለስ፣ ወይም ያዘዘቻትን ሠርታ ስትጨርስ እናቷ ትደሰታለች::

«ጎሽ የኔ ልጅ! ደረስሽልኝ አይደል?! ጎበዝ!» ትላታለች:: አንዳንዴም አገላብጣ ትስማታለች::

አመለዘውድ ይህ የእናቷ ደስታ እጅግ ያረካታል:: እናም ውጪ ወጥታ ከልጆች ጋር ከመጫወት ይልቅ፣ ቤት ውስጥ እናቷን ማገዝ ምርጫዋ ሆነ:: አልፎ፣ አልፎ ዕኩዮቿን ስትቀላቀልም በጨዋታቸው ውስጥ በንቃት የመሳተፍ ጉጉት አታሳይም:: ሲጫወቱ አጠገባቸው ቁጭ ብላ ታያቸዋለች::

«እስቲ አሁን ደግሞ ቁጭ ብለን እናውራ::» ትላለች ጨዋታው ያደከማቸው ሲመስላት::

«ምንድነው የምናወራው?» የሰፈሯ ልጆች ይጠይቋታል::

«በቃ ስለብዙ ነገር:: ኑ ቁጭ በሉ!»

«አንቺ ግን ለምን አትጫወቺም?» ትላታለች እመቤት ተፈሪ የተባለችው የሰፈሯ ልጅ::

«እጫወታለሁ:: ግን ቁጭ ብለን ብናወራ ደስ ይለኛል::»

ልጆቹ እሺ ብለው እንኳ አጠገቧ ቢቀመጡ፣ እሷ እንደምትፈልገው የሷን «ቁም ነገር» እህ ብለው ለማዳመጥ ብዙም ትዕግስት አይኖራቸውም::

የዕድሜ እኩያዋ ብዙነሽ መሃመድ ከእናቷ ከወ/ሮ የሺ ካሰው ጋር ባለቤቶቹ ያልገቡበት አዲስ የጎረቤት ቤት እየጠበቁ እዚያው ከአነርሱ ቤት አጠገብ ይኖራሉ:: አመለዘውድ ብዙነሽን «እሙሽ» ብላ ነው የምትጠራት:: የቅርብ ጓደኛዋ እሙሽ ነበረች:: የመጫወቻ ፍላጎት ካላት በቅርብ ስለምታገኛ

ት እሙሻ'ጋ መሄድ ትመርጣለች። እንቆቅልሽ መጠያየቅ፣ ቁጭ ብላ በጠጠሮች ቅልልቦሽ መጫወት፣ አልፎ አልፎም ገመድ መዝለል ያስደስታታል። የቤተሰቦቻቸው ከሰፈሩ ሰዎች በተለየ ሁኔታ ደሀ መሆን ሁለቱን ህጻናት የበለጠ አቀራርቧቸዋል።

አመለዘውድ በዕድሜ ከፍ እያለች ስትሄድ እንደልብስ ማጠብ ያሉ ከበድ ያሉ ሥራዎችንም መስራት ጀመረች። ምንም የሥራ ጫና ቢበዛባት ግን እናቷ የጨዋታ ጊዜዋን እንደተሻማች፣ የልጅ ጉልበቷን እንደበዘበዘች፣ ልጅነቷን በቅጡ ሳታጣጥም ወደ አዋቂነት እያንደረደረቻት እንደሆነ አንድም ቀን አስባ አታውቅም። ለእሷ ጨዋታ ከትምህርትና ከቤት ውስጥ ሥራ ቀጥሎ በሦስተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ለልጆች ብዙም የማይጠቅም ነገር ነው። በትምህርቷ ጎበዝ ነች። ደብተሮቿንም ሆነ መጻሕፍቷን ባላት ትርፍ ጊዜ ታነባለች።

አመለዘውድ በሆነ ምክንያት ያዘዘቻትን ሥራ ሳትሰራ ከቆየች፣ ድንቄ «ጎሽ!» ማለቷ ቀረና፣ «ምን አባሽ!» ብላ መቆጣት አመጣች። አንዳንድ ጊዜ በጣም ስትናደድ አመለዘውድን በጥፊ ወይም ባገኘችው ነገር ከመማታት ወደ ኋላ አትልም።

እናቷ የዋህ እንደሆነች ስለምታውቅ አንዳንድ ጊዜ አመለዘውድ የእናቷ ንዴት እስኪበርድ አምልጣት ሮጣ ከግቢያቸው ትወጣና ጎረቤት ቤት አንዱ'ጋ ተደብቃ ትቆያለች። ተመልሳ ስትመጣ፣ እናቷ ንዴቷ በርዶላት፣ ምናልባትም ፍፁም ረስታው፣ «አመለዘውድ! እስቲ ቡና አፍዪልኝ።» ትላታለች··

አልፎ፣ አልፎ ግን ከግቢው ተከትላት እያሯሯጠቻት ወጥታ፣ 'ጎረቤት ወይም መንገደኛ ምን ይላል?' የሚል ስጋትና ሃሣብ ጭራሽ ሳያስጨንቃት እየሰደበቻትና እየረገመቻት ስታባርራት ትታያለች።

ድንቄ ቶሎ የምትደሰት፣ ቶሎ የምትከፋና የምትናደድ፣ ከንዴቷ ወዲያው ምልስ የምትል፣ ነገር በሆዷ የማያድር፣ ካደረም በጥሩ ሰላምታ ወይም በትንሽ ውለታ ከሆዷ ጭራሽ የሚጠፋ ፍፁም የዋህ ሴት ነች። የአዋቂ ሰውነት ይኑራት እንጂ ባህሪዋ በአብዛኛው የልጅ ዓይነት\ነው። ይህን ባህሪዋን የማይረዱ፣ ስትቆጣና ስትሳደብ የሰሙ አንዳንድ ሰዎች ለእሷ መጥፎ ግምት ሊኖራቸው ይችላል። ብዙዎች ጤንነቷን ይጠራጠሩም ይሆናል። የፈለጉትን ቢያስቡ ድንቄ ደንታዋ አልነበረም።

እገሊት ከእገሊት ሳትል ሁሉንም በአንድ ዓይን የምታይ፣ ተጫዋች ስለሆነች በሰፈሩ ሴቶች የተወደደች ናት። ቡና ሲጠጡ ይጠሯታል። ድግስ ሲደግሱም ትጋበዛለች። ከሰፈሩ ቤቶች በአንዱ ድግስ ካለ፣ ድንቄ በዚያ



Sample output to test PDF Combine only



አለች። መጠጥ ትደፍራለች። ድግስ ላይ የተዘጋጀውን ጠላም ይሁን ጠጅና አረቄ ትወሳስድና ታንጎራጉራለች። በዘፈን ጋባዧንና ሌሎች ጎረቤቶቿንም ታወድሳለች።

አንዳንድ ቀን ከተበሳጨች፣ የሚቀርቧትን ጎረቤቶች ሳይቀር በስድብ እጥብ ታደርጋቸዋለች። በሚቀጥለው ቀን ምንም የተለየ ነገር እንዳላደረገች ሁሉ የወትሮዋ ድንቄ ትሆናለች፤ ትስቃለች፣ ትጫወታለች። ይህን ባህሪዋን የተረዱ ጥቂት ጎረቤቶቿ ለሷ ይቅርታ ለማድረግ ዘወትር ዝግጁዎች ነበሩ። ስቀው፣ አፋቸውን በመዳፋቸው ከልለው፣ «አይ ድንቄ!» ብለው ተገርመው፣ ከእሷ ጋር ማድረግ ያለባቸውን ያደርጋሉ።

በአብዛኛው ድንቄ፣ «አሁንን መኖር፣ ያለፈውን መርሳትና ስለወደፊቱ አለመጨነቅ» የሚል ያልተፃፈ፣ እሷ እንኳ ልብ የማትለው የሕይወት መመሪያ ነበራት። የዋህነቷን የተረዱት ልጆቿ ተሾመና አመለዘውድ ምንም ብትጮህባቸው፣ ብትቆጣቸው፣ ብትሰድባቸውና ብትደበድባቸው አያዝኑባትም። ለእናታቸው ከፍተኛ ፍቅር ነበራቸው። እሷም ልጆቿን ትወዳለች። በተለይ ለበኩር ልጇ ተሾመ የተለየ ፍቅር ነበራት።

በእናቷ ጥፊ ሰበብ ሊሆን እንደሚችል ቢጠረጠርም፣ መንስኤው በትክክል ባልታወቀ ሁኔታ አመለዘውድ ጆሮዋን መታመም ጀመረች። «ጆሮዬን» ማለት ስታበዛ አባቷ ወደ ጤና ጣቢያ ወሰዷት። የታዘዘላት መድኃኒት ጊዜያዊ እፎይታ ከማስገኘት ውጪ ዘለቄታዊ መፍትሔ አልሰጣትም። ጆሮዋን በጥጥ ጠቅጥቃ መዋል ልማዷ ሆነ። የጆሮዋ ህመም የመስማት አቅሟን በመጠኑ ቢቀንሰውም፣ ሰዎች የሚናገሩትን በደንብ መስማት ስለምትችል እሷም ወላጆቿም እንደትልቅ የጤና ችግር አክብደው አላዩትም።

## -7-

*«ድንቁ ገበያ አትሄድም። ግርማ ሁሉን ነገር ይገዛ ነበር።»*
*ወ/ሮ ሃና መስፍን*
*«ድንቁ ብር አታውቅም፤ አስር ብር ብትሰጣት፣*
*መቶ ብር ነው የሚመስላት።»*
*ወ/ሮ አበበች ገመቹ*

ድንቁ ገንዘብ በእጇ ብዙም አይገባም። አቶ ግርማ ከድንቁ ጋር ትዳር እንደመሠረቱ ድንቁ ገንዘብ በአግባቡ ማውጣትና መጠቀም እንደማትችል ስላዩና ስለተገነዘቡ፣ ተሾመ ተወልዶ ከድንቁ'ጋ አብረው መኖር ከጀመሩ በኋላ ገንዘብ አይሰጧትም። ለቤቱ የሚያስፈልገውን ብዙ ነገር የሚገዙት ራሳቸው ናቸው። ለወር የሚያስፈልጋቸውን ጤፍ ገዝተውና አስፈጭተው ራሳቸው ዱቄቱን ተሸክመው ወደ ቤት ያመጣሉ። ዘይትም፣ ሽንኩርትም፣ ሽሮም . . . ሌላውንም ሸማምተው የሚያመጡት አባወራው ናቸው። አስፈላጊ ከመሰላቸው ለአንዳንድ አነስተኛ ወጪዎች ሁለት ሶስት ብር ብቻ ለሚስታቸው ይሰጣሉ፣ ከብርቱ ማስጠንቀቂያ ጋር።

«ድንቁ ምንም አታውቅ።» ይላሉ በቅርብ የሚያውቋት ሰዎች ሁሉ። «ብር መቁጠር እንኳን አትችልም።»

በእርግጥም ለድንቁ አስር ብርና መቶ ብር ልዩነት የላቸውም። በተፈጥሮዋ የበሰለች አለመሆኗ ስለገንዘብ ያላት ዕውቀት ደካማ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል። ከጥቃቅን ወጪዎች የሚተርፍ ገንዘብ አይኖራትም እንጂ ካላት እዚያው ጎረቤት አረቄ የሚሸጡ አንድ ሴትዮ ቤት ጎራ ትላለች። ስትጠጣ «ይብቃኝ እንዳልሰክር» የሚል ሀሳብ የለባትም፤ ትጠጣለች።

አንዳንድ ቀን ድንቁ ጎረቤት ቤት ሄዳ በዚያው ቀልጣ ትቀይና እንደቤት እመቤት ያለባትን ኃላፊነት ሳትወጣ ትቀራለች። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጣሪያ ሊገነጥል የሚደርስ ጭቅጭቅና ጥል በደሳሳዋ ቤት ይፈነዳል።

አንድ ቀን ድንቁ የጎረቤት ቤት ድግስ ሄዳ አመሸች። አቶ ግርማ ቤት ሲገቡ የለችም። ከምሽቱ አንድ ሰዓት ካለፈ በኋላ ቤት ስትገባ ሞቅ ብሏታል። አቶ ግርማ እጅግ ተበሳጩ። እሳቸው ድህነታቸውን፣ የቤታቸውን ገመና ደብቀው ነው መኖር የሚፈልጉት። ሥራ ጠፍቶ ተቸግረው ብር ከቅርብ ጎረቤት እንኳን ቢበደሩ፣ እመልሳለሁ ባሉበት ቀን ቃላቸውን አክብረው ይመልሳሉ። ሚስታቸው ጎረቤት ቤት ሄዳ እስክትሰክር መጠጣቷ አበገናቸው።

«የት ነበርሽ?» በቁጣ አፈጠጡባት።
«እዚህ ጎረቤት ሃና'ጋ። ዛሬ'ኮ ገብርኤል ነው።»





«እና እስካሁን ለምድነው የቆየሽው?»
«ድግስ አይደል እንዴ?! ያለውን ሳልቀማምስ አልመጣ።»
«መቀማመስ ታዲያ ይህን ያህል ያቆያል? እኔ ከመጣሁ ራሱ ዘመን ጊዜ አለኝ እንዴ?»
«በል አትጨቅጭቀኝ ወጥ ልስራበት» ብላ ድንቁ ነጠላዋን ከትከሻዋ አውርዳ የሚተኙበት ፍራሽ ላይ ጣል አደረገችው።
«ወጥ ሳትሰሪ ነው ጎረቤት ለጎረቤት የምትዞሪው?!» አቶ ግርማ ንዴታቸው ከቁጥጥር ውጪ አደረጋቸው። ከተቀመጡበት ተነስተው በጥፊ ወለወሏት።

«ውይ!» ድንቁ ባላሰበችው ጥፊ ደነገጠች።

የመሳደቢያ ጊዜ እንኳን ሣይሰጧት በቡጢና በእርግጫ ያገኙት ቦታ ንዴት እብድ አድርጓቸው መቷት።

ድንቁ፣ «ኡኡ! ሊገድለኝ ነው! ድረሱልኝ!» ብላ ጮኸች።

ወንድማቸውን ሚካኤልን ይዘው ግቢው ውስጥ ሲጫወቱ የነበሩት ተሾመና አመለዘውድ የእናታቸውን ጩኸት ሲሰሙ ወደ ቤት ሮጡ።

«እንዴ?! ምን አደረገችህ? ምን ነካህ?» ወደ ቤት ገብተው ተንጫጩ።

አቶ ግርማ ዞር ብለው የሚወዷቸው ልጆቻቸው ከበስተጀርባቸው መቆማቸውን አዩ። ለመምታት ያነሱት እጃቸው አየር ላይ ዘግይቶ ድንቁ ላይ አረፈ። ደግመው ሊመቷት እጃቸውን አላነሱም።

«ነገረኛ! ምላሳም!»

ቁጣና እልሃቸውን በስድብ ለማብረድ እየሞከሩ ከቤት ሲወጡ ተሾመ አባቱን በቁጣ ገላመጣቸው።

አመለዘውድ ፍራሽ ላይ በጎኗ ተኝታ ወደምታለቅሰው እናቷ ተንደረደረች።

«አይዞሽ ድንቁ! . . . አይዞሽ በቃ!» እናቷን ለማባበል ሞከረች።

አቶ ግርማ ከቤት ወጥተው በሩ አካባቢ ቆሞ የነበረውን ሚካኤልን ፀጉሩን ዳበስ አድርገው አልፈው ግቢው ውስጥ ያደገው ሳር ላይ እንደተቀመጡ፤ ድንቁ መሳደብ ጀመረች።

«ሂድና ውሽማህን ደብድብ! እኔን ጫፌን መንካት አትችልም። . . . » የስድብ መአት አዥጎደጎደች።



Sample output to test PDF Combine only

አቶ ግርማ በተከፈተው የቤታቸው የቆርቆሮ በር በኩል የምትላቸውን ሲሰሙ ንዴት እንደ አዲስ ሰውነታቸውን አጋለው:: ተመልሰው ዳግመኛ ሊቀጠቅጧት ከጀሉና ልጆቹን አሰቡ:: የተሸመ ግልምጫ ትዝ አላቸው:: በዱላ የመመታት ያህል የሚያም ነበር:: እናም ባሉበት በትዕግስት መቆየት መረጡ::



Sample output to test PDF Combine only



## -8-

*«አግኝተን አላጣንም፤ አጥተንም አላገኘንም::»*
*ተሸመ ግርማ*

«የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ» እንዲሉ ደሳሳ ቤታቸው ቦታውን ለመጠበቅ እንደነገሩ የተቀለሰች ስለነበረች ወደ አንድ ጎን ዘምማ ለመስገድ ያጎነበሰ ምዕመን መሰለች:: አቶ ግርማ ጭቃ አቡክተው፣ ከጭድ ጋር ቀላቅለው አዘጋጁና አንድ ቀን ቤቷን አፍርሰው ከናካቴው ከመውደቅ ገላገሏት:: ካፈረሷት ቤት ሶስት ወይም አራት እርምጃ ያህል ፈንጠር ብለው፣ ወደ ግቢው የኋላ ድንበር አስጠግተው አዲስ ቤት ቀለሱ:: የአሮጌዋን ደሳሳ ቤት ማገርና ቆርቆሮ ዳግመኛ ተጠቅመው፣ በአዲሱ ጭቃ ግድግዳዋን መርገው የሠሯት ስፋቷ ከበፊቷ ቤት ያልተለየች ትንሽ ቤት ባንዲራ ለመስቀል በተጠንቀቅ እንደቆመ ወታደር ቀጥ ያለች ነበረች::

አቶ ግርማ የቀን ሠራተኛ እንደመሆናቸው አንዳንድ ጊዜ ሥራ ይጠፋና ለቀናት ላይሰሩ ይችላሉ:: ገንዘብ ከኪሳቸው ይጠፋል:: ማታ ቤት ሲገቡ ድንቄ፣ «ዘይት አልቋል:: . . . የውሃ መግዣ የለኝም:: . . . ጤፍ መገዛት አለበት:: . . . ልብስ የማጥብበት ሳሙና የለም:: . . . » እያለች የቤቱን በጀት ሙሉ በሙሉ ለሚቆጣጠሩት አባወራ ያልተጻፈ ማመልከቻ ታቀርባለች::

ታዲያ የጠየቀችው ካልተገዛላት ትነጫነጫለች:: ሥራ በጠፋበት አንድ ሰሞን አመሻሽ ላይ አቶ ግርማ ቤት ገብተው ቁጭ እንዳሉ ተመሳሳይ ጭቅጭቅ ተጀመረ::

«ኧረ ሸንኩርት አልቆብኛል:: ግዛልኝ፤ ካልሆነ ብር ስጠኝና ነገ ልግዛ::»
«የለኝም:: ዛሬም ሥራ አልሰራሁም::» አሉ አቶ ግርማ::
«እንዴ! ታዲያ እንዴት ልንሆን ነው?»
«ቆጥበሽ ተጠቀሚ! የሌለኝን ከየት አመጣለሁ?» ቆጣ አሉ አቶ ግርማ::
«እንዴት የለህም? ጠጅህን እየጠጣህበት ነው እንጂ የለኝም የምትለው:: ወይስ ባለውሽማ ሆንክ እንዴ? አንተ ምን አለብህ? ዝም ብለህ ጠጅና አረቄህን ተጋት እንጂ! . . . » ድንቄ ኃይለኛ ምላሷን መዘዘችው::

አቶ ግርማ እልኸኛና ተናጋሪ እንደሆነች ያውቃሉ:: ተናጋሪነቷን አንዳንድ ቀን ይታገላሉ:: ዛሬ ግን እንዲህ እሳቸውም ሆድ በባሳቸው ሰዓት ስትናገራቸው ብልጭ አለባቸው::

«ዝም በይ! የምን ጠጅና ውሽማ አመጣሽ:: እንዴት እንዲህ ትዪኛለሽ? እኔ ለልጆቼ ሟች እንደሆንኩ አታውቂምና ነው?!» ብለው ጮኹ::

«ድንቄም እቴ! ለልጆችህ ሚች ብትሆንማ ኖሮ ጠጅህን ስትጋት አምሽተህ፣ ባዶ እጅህን አትመጣም ነበር።» አለች ድንቄ ወገቧን ይዛ እየተውረገረገች።

«ሥራ የለም፣ ሥራ አላገኘሁም አልኩሽ። የቀን ሠራተኛ እንደሆንኩ ታውቂ አይደል? ሥራ አንዴ ሲገኝ፣ ሌላ ጊዜ አይገኝም።»

«እሱን እንኳን ተወው! እስከዛሬ ያልጠፋ ሥራ እንዴት እንዲህ በአንዴ ይጠፋል? ሆዳም ሆነህ ነው እንጂ!»

«ዝም በይ አንቺ ለፍላፊ!» አቶ ግርማ ድንገት ከተቀመጡበት ተፈናጥረው ተነስተው በጥፊ አጮሏት።

«ግደለኝ! እዎ ግደለኝ! በረሃብ ከመሞት አንተ ብትገድለኝ ይሻላል! ልጆቼ ሲራቡ ከማይ አንተ ብትገድለኝ ይሻለኛል። ሆዳም ነህ! ግደለኝ!» አለች ድንቄ አንገቷን ወደፊት ሰገግ አድርጋ ፊቷን ለሌላ ጥፊ እያመቻቸችላቸው።

«ዝም በይ!» አቶ ግርማ በዚያ ለዓመታት የጉልበት ሥራ ሲሰሩበት በሻከረው እጃቸው ሌላ ጥፊ ደገሟት።

በለቅሶዋ መሀልም የድንቄ ምላስ ዕረፍት አልነበራትም። ቤት ውስጥ ተኝቶ የነበረው ሚካኤል በጫጫታው ተረብሾ ነቃ። የወላጆቹን ሁኔታ ሲያይ ማልቀስ ጀመረ።

«ሆዳም ነህ!»

«ኧረ አንቺ ሴትዮ ዝም በይ! ዝም በይ'ኮ ነው የምልሽ!» አቶ ግርማ ብስጭታቸው ከልክ አለፈ።

ድንቄ የስድብ ጎተራዋን ስትከፍት፣ ባሏም እጆቻቸውን በድብደባ አደከሟቸው።

ወፍራሟና በቁመት ከአቶ ግርማ ትንሽ ዘለግ የምትለው ድንቄ ራሷን ለመከላከል ሞከረች። አንድ ሁለት ጡጫ ወደባሏ ሰነዘረች። ጉልበት ነበራት። አጭሩና ቀጭኑ አቶ ግርማ ተንገዳግደው ሚዛናቸውን እንደምንም ባይጠብቁ ኖሮ ወደኋላ በወደቁ ነበር። ከአንድ ጥግ የበር መቀርቀሪያ ዱላ አንስተው ጀርባዋና ወገቧ ላይ ደጋግመው መቷት። ድንቄ ቤቱንና ግቢውን በጩኸት አናጋችው። ከሷ ጩኸት ጋር የሚካኤል ለቅሶ ተቀላቅሎ አካባቢውን በጠበጠው። ጎረቤቶቻቸው ተደናግጠው፣ «ምንድነው? ምን ሆናችሁ ነው?» እያሉ መጡ።

አመለዘውድም ከጎረቤቶቻቸው ጋር ነበር ቤት የደረሰችው። እነ እሙሻ ቤት ነበረች። አባቷ ቤት መግባታቸውን አላወቀችም ነበር። የድንቄን ጩኸት ሰምታ ነው የእሙሻ እናት ወ/ሮ የሺና እሙሻ እየተከተሏት ወደ ቤት ስትሮጥ የመጣችው።







ጎረቤቶቻቸው ባልና ሚስቱን ገላገሏቸው። አቶ ግርማ ጎረቤት በመምጣቱና የቤት ገመናቸው በመገለጡ ይበልጥ ተበሳጩ። በዚህ ግርግር ወቅት ተሾመ አስፋልት አካባቢ የቪዲዮ ፊልም ሲያይ አምሽቶ ደረሰ። አባቱ በጣም አናደዱት።

ማታ ራት ሊበሉ የቤተሰቡ አባላት እንደተለመደው በአንድ ማዕድ ዙሪያ ተሰበሰቡ። ተሾመ ግን አንድ ጥግ ዝም ብሎ ተቀመጠ።

«ና እንጂ እንብላ!» አሉት አባት።

«አልበላም» አለ ትከሻውን በእምቢታ ሰቅሎ እያወረደ።

«ለምንድነው ማትበላው?» አባት ግራ ተጋብተው ጠየቁ።

ዝም አለ።

«ምነው አሞሃል እንዴ?»

«አላመመኝም»

«ታዲያ ለምን አትበላም?»

ዝም።

«እ?»

ለአፍታ ዝም ብሎ ቆይቶ፣ «ካንተ'ጋ አልበላም» አለ ተሾመ ፊቱን ወደ አንድ ጎን አዙሮ።

«ለምን ከእኔ ጋር አትበላም?» አሉ አቶ ግርማ እንጀራ መቁረስ የጀመረው እጃቸው ባለበት ደንዝዞ።

«እናቴን ለምን ትመታታለህ?»

«ምን አልክ?»

«አዎ፣ እናቴን ለምን ትመታታለህ። ካንተ ጋር አልበላም።» አለ ተሾመ ተቆጥቶ።

አቶ ግርማ ደነገጡ። ምን ማለት እንዳለባቸው ግራ ገብቷቸው ምንም ቃል አልተናገሩም።

«እንዴ ተሼ መብላትማ አለብህ።» አለችው አመለዘውድ።

«አልበላም!» ብሎ ተነስቶ ከቤት ወጣ።

«ተሼ! . . . ተሸዬ!» እናቱ ጮክ ብላ ተጣራች። «ኧረ ና ብላ!»

ተሾመ ግቢው ውስጥ አንድ ጥግ ተቀምጦ ቆየ።

«ተይው! ጠግቦ ነው! ጥጋበኛ!» አሉ አቶ ግርማ ቆጣ ብለው።

ሌሎቹ በልተው ከተነሱ በኋላ ነበር ተሾመ እናቱ ለብቻው ራት አቅርባለት የበላው።

የአሥራ ሦስት ዓመት ዕድሜ ያለው ተሾመ ለበርካታ ሳምንታት ከአባቱ ጋር በአንድ ማዕድ ዙሪያ ለመቅረብ ፈቃደኛ ሳይሆን ሰነበተ። አባቱ፣ «ይተወው! ጥጋበኛ!» ቢሉም ልጁ በወሰደው እርምጃ ተረበሹ። የሆነ

የጥፋተኝነት ስሜት ቆንጠጥ ስለሚያደርጋቸው፣ አስገድደው አብሯቸው እንዲበላ ሊያደርጉት አልደፈሩም። ተሾመም ምግብ ከአባቱ ጋር በአንድ ማዕድ ላለመመገብ መወሰኑ አባቱን እንደጎዳቸው ተረዳ። የበቀል እርምጃው በመሳካቱ ተደሰተ። . . .

ዳግመኛ አብሮዋቸው መብላት ከጀመረ በኋላ እንደገና አንድ ቀን አባቱ ድንቂን ሲደበድቧት ደረሰ። ተመሳሳይ እርምጃ ወሰደ። ለጥቂት ሳምንታት ከአባቱ ጋር ለመብላት ፈቃደኛ አልነበረም።

አመለዘውድ ሁለቱንም ወላጆቿን በጣም ትወዳለች። አባቷ የዋህ እናቷን ሲደበድቡ ካየች ወይም ከሰማች በአባቷ ትበሳጫለች። ከልጅ አንደበት ይወጣሉ ተብለው በማይገመቱ ቃላት አባቷን ትቆጣቸው ነበር።

«አንተ አሁን አባት ነህ? የቤቱ መሪ፣ መካሪያችን አንተ እኮ ነህ። ካንተ ከአባቴ ይህን አልጠብቅም። የድንቂን ጸባይ አጥተኸው ነው ለምን ተናገረችኝ ብለህ የምትደበድባት? . . . » ሌላም፣ ሌላም . . . ትናገራለች። ንግግሯ ከዕድሜዋ ጋር በጭራሽ የሚነፃፀር አልነበረም። አቶ ግርማ በብስለቷ ይገረማሉ። ቃላቶቹ ከሷ አንደበት መውጣታቸውን ማመን ይከብዳቸዋል።



Sample output to test PDF Combine only



# -9-

*«አባቴ ተምሬ በጣም ጥሩ ደረጃ ላይ እንድደርስለት ይፈልግ ነበር። እኔ ግን ለትምህርቴ ትኩረት አልሰጥም ነበር።»*
*ተሾመ ግርማ*

አቶ ግርማ አመለዘውድም ሆነች ተሾመ በትምህርታቸው እንዲበረቱ አጥብቀው ይመክሯቸዋል። ምክራቸውን አልሰማ ቢልም ለበኩርና ለወንድ ልጃቸው ለተሾመ ይንሰፈሰፉለታል። እንዲያውም የተሻለና ጥራት ያለው ትምህርት እንዲማር ከፍለው የህዝብ ት/ቤት የሚያስተምሩት እሱን ነው። ግን እንደተመኙት በትምህርቱ ሊበረታ አልቻለም። ለትምህርቱ ግድየለሽ ስለሆነ ያዝኑበት ጀምረዋል። ተሾመ በበኩሉ አባቱ እናቱን ስለሚደበድቡበት ይናደዳል፣ ያኮርፋል።

አቶ ግርማ ሴት ልጃቸውን ከቤተሰቡ አባላት አብልጠው እንደሚወዱ ለማንም ግልጽ እየሆነ ነው። አመለዘውድ የኩራታቸው ምንጭ ነበረች። ለቤተሰቧ ዘውድ ሆና እየታየቻቸውና እጅግ እያስደሰተቻቸው ነው። እሷን እንደ ተሾመ የህዝብ ት/ቤት ለማስገባት አቅማቸው ስላልፈቀደ የመንግስት ት/ቤት በነጻ ነው የሚያስተምሯት። በትምህርቷ ጎበዝ፣ አባቷን የምታከብር፣ ወላጆቿን ለማስደሰት የምትጥር፣ ከዕድሜዋ በላይ በአስተሳሰብ የበሰለች ናት። ድንቂን ሲደበድቡባት ደስ ባይላትም፣ እንደ ተሾመ ቂም ይዛ በአባቷ ላይ አታመርም። አባቷ የሚወዷትን ያህል እሷም ትወዳቸዋለች። አባቷ ለእሷ ያላቸው የበዛ ፍቅር ቢያጠፉም ዘወትር ይቅርታ እንድታደርግላቸው ግድ ይላታል።

## -10-

*«አንድ ቀን ፣ 'ለምን አናስታርቃቸውም?' አለችኝ።»*

*ተሾመ ግርማ*

አባታቸው እናታቸውን ከደበደቡና በጎረቤት ገላጋይነት ጠባቸው ከበረደ በኋላ አንድ ቀን አመለዘውድና ተሾመ ግቢያቸው ውስጥ ቁጭ ብለው እያወሩ ነበር።

«ምን ይሻላል ግን?» አለች አመለዘውድ።
«ምኑ?» አላት ተሾመ።
«ለምንድነው ሁለቱ ሁልጊዜ የሚጣሉት?»
«ሁለቱ» ያለቻቸው እናትና አባቷን ነው።
«'ገንዘብ አምጣ' ስትለው፣ 'የለኝም' ስለሚላት ነዋ።»
«ለምን አናስታርቃቸውም?»
ተሾመ ፊት ለፊት እያየ ነበር። በጣም ተገርሞ ሳቅ አለና ዞር ብሎ ታናሽ እህቱን አያት።
«ከምርሽ ነው?»
«እዎ»
«ቀልደኛ ነሽ» አሁንም ሳቅ አለ።
«እንዴ ተሼ! እውነቴን ነው አልኩህ'ኮ።»
«እሺ እንዴት ነው የምናስታርቃቸው?» አላት፤ ድምፁ ውስጥ፣ 'መቼስ የማይረባ ነገር ነው የምታስቢው ቢሆንም እስቲ ልስማሽ' የሚል ዜማ እየተደመጠ።
«በቃ፣ 'እናንተ አትጣሉ እኛ ሰርተን ገንዘብ እናመጣለን' እንበላቸው።»
እህቱን አፍጥጦ አያትና ሳቀ። «ሥራ እንዴት እናገኛለን?»
«ተሳልከን፣ ሰው ቤት አንዳንድ ሥራዎች ሠርተን ገንዘብ ማግኘት እንችላለን። አንተም ዕቃ ምናምን ተሸክመህ ፍራንክ ማግኘት አያቅትህም።»

ተሾመ የእህቱ ሃሳብ ያሳመነው መሠለ።

«እዎ፣ ለእናታችን ሰርቼ ፍራንክ ብሰጣት ደስ ይለኝ ነበር።» አለ ለራሱ የሚናገር በሚያስመስለው ሃሳብ በገባው ሰው ድምፅ።
«ዛሬ ማታ ሃሳባችንን እንንገራቸውና ሁለተኛ እንዳይጣሉ አስምለን እናስታርቃቸው።» አለችው።

ተሾመ የአመለዘውድን ሃሳብ ሙሉ በሙሉ አላመነበትም። ምክንያቱ ባይገባውም አባቱ ድንቄን በማግባታቸው ሁልጊዜ የሚጸጸቱ ነው የሚመስሉት። ለመፈንዳት ቀነ ቀጠሮውን እንደሚጠብቅ እሳተ ገሞራ በየቀኑ



Sample output to test PDF Combine only



አንዳች ብሶት በሆዳቸው እንደሚንተከተክ ይሰማዋል። ያ ብሶት ሲገነፍልና ሲፈነዳ ነው እናቱን በጭካኔ የሚደበድቧት። 'እሱ'ኮ እናቴን ባይደበድብ፣ ደስተኛ እንሆን ነበር።' እያለ ብዙ ጊዜ ያስባል። ለቤተሰቡ ሰላም ማጣት አባቱን ነው መቶ በመቶ ተጠያቂ የሚያደርገው።

«ባክሽ ይስቁብናል።»
«ለምንድነው የሚስቁብን?»
«እሱ አይሰማንም።»
«ለምንድነው የማይሰማን?»
«አይሰማንም። ክፉ ነው።»
«እንደዛ አትበል! አባታችን አንዳንዴ ስለሚጠጣ እንጂ ክፉ አይደለም።»
«ለምን ታዲያ ድንቄን ይደበድባታል?»
«ስለሚጠጣ ነዋ። መጠጥ መጥፎ ነገር ነው።»
«ታዲያ ለምን ይጠጣል?»
«ሱስ ስላለበት ነዋ። ሱስ መጥፎ ነው።»
«እናታችን ገንዘብ እንደሚያስፈልጋት እያወቀ፣ እኛም አንዳንዴ በደንብ ሳንጠግብ እየበላን አሮጌ ልብስ እየለበስን፣ ለምን ይጠጣል?»
«ለማንኛውም ማታ እናስታርቃቸዋለን።»...

ማታ ከራት በኋላ አመለዘውድ ታላቅ ወንድሟን ጠቀሰችው። እጁን በተስፋ መቁረጥ እያወራጨ፣ «ተያቸው ባክሽ!» አላት በምልክት።

አመለዘውድ ልናገር፣ አልናገር ስትል አመንትታ አባቷ ለመተኛት እየተዘጋጁ ስለነበረ ዝም ማለቱን መረጠች።

## -11-

*«ልጅነት ስላለ፣ ለሷ ስሜት ሳንጨነቅ፣ 'ከእኛ'ጋ*
*አበባየሆሽ አትጨፍሪም' ብለናት ነበር።»*
*እመቤት ተፈሪ*

ተሾመ አባቱን የሚጠላው እናቱን ስለሚደበድቡብትና «ትምህርትህን ለምን ጠንክረህ አትማርም?» እያሉ ስለሚጨቀጭቁት ብቻ አይደለም። ከሌሎች የሰፈሩ ልጆች በአለባበስና በኑሮ ሁኔታቸው ዝቅ ብለው ለመገኘ ታቸው ምክንያት አባቱ እንደሆኑም ያስባል።

ዛሬ እንቁጣጣሽ ነው። አዲስ ዓመት! ከጠዋቱ ሦስት ሰዓት ገደማ ሆኗል። ቤተሰቡ በሙሉ ቤት ነበሩ። ተሾመ በማለዳ ወደ ውጪ ወጣ ብሎ ያገኛቸው እኩዮቹ አዳዲስ ልብስ ለብሰው በማየቱ ቅናትና ቁጭት እያንገበገበው ነበር። አባቱን ለብቻው በሆዱ ሲራገምና ሲሳደብ ቆይቶ፣ «ለምንድነው አዲስ ልብስ የማትገዛልን?» ብሎ ጠየቃቸው።

«የለበስከው ልብስ ምን ሆነ?»

ተገርሞ ሳቅ አለ። «እንዴ ይሄ'ማ አሮጌ ልብስ ነው።»

«መች ተቀደደ?» አሉ አባቱ።

አመለዘውድ እናቷ የምትላትን ለመፈጸም ዝግጁ ሆና አጠገቧ ቁጭ ብላለች። ድንቄ ቀደም ብሎ ታርዶ የገነጣጠለውን ዶሮ ሥጋ ስታጥብ እያየቻት ነበር። የተሾመና የአባቷ ቃለምልልስ ስቧት ተሾመ አጠገብ መጥታ እየቆመች፣«የጎረቤት ልጆች በሙሉ'ኮ አዲስ ልብስ ተገዝቶላቸዋል።» አለች።

«እነሱ አባቶቻቸው የወር ደሞዝ የሚከፈላቸው ናቸዋ። እንደእኔ የቀን ሥራ የሚሰሩ ሳይሆኑ፣ የመንግሥት ሠራተኞች ናቸው።»

«ሁሉም አዲስ ልብስ ሲለብሱ፣ እኛ ለምን አሮጌ እንለብሳለን?» ተሾመ ጠየቀ።

«ነገርኳችሁ'ኮ! . . . ይኸው ለበዓሉ ዶሮ ገዝቻለሁ።» አሉ በአገጫቸው ወደ ድንቄ እያመለከቱ። «ለእናንተ ልብስ መግዣ የሚሆን ገንዘብ ግን የለኝም።»

«ሁሉም ቆዳ ጫማ ሲያደርጉ'ኮ እኔ በረባሶ ነው የማደርገው።» አለ ተሾመ።

«እኔም ኮንጎዬ እየተቀደደብኝ ነው። እንደውም ሰፍቼው ነው እንጂ እስካሁንም አላረገውም ነበር» አለች አመለዘውድ ከኋላ እንዲሁም ከፊት አንድ ጎን ላይ በክር የተሰፋውን ኮንጎዋን እያሳየቻቸው።

አቶ ግርማ በረጅሙ ተነፈሱ። «ልጆቼ ገንዘብ ስለሌለኝ እንጂ ቢኖረኝ ለእናንተ እሰስታለሁ?»





«ሹራቤ እዚህ'ጋ ሊቀደድ ነው።» አለ ተሾመ ክርኑ ላይ የሳሳ ሹራቡን ለአባቱ እያሳየ። «ሱሪዬም ቂጡ ላይ የተጣፈ ነው።»

«እኔም ከኔተራዬ አንገቱ ላይ ተቀዳዷል።» አለች አመለዘውድ ወደ ደረቷ እያመለከተች።

አቶ ግርማ የሚያሳዩዋቸውን በእርጋታ ሲያዩ ቆይተው ፊታቸውን ወደ ሌላ አቅጣጫ አዙረው ዝም አሉ።

«የት/ቤት ልጆችም አዲስ ልብስ ይገዛላቸዋል። እኛ ብቻ አሮጌ ለብሰን ልንሄድ ነው።» አለ ተሾመ እንደመነጫነጭ አያለ።

«በቃ ገንዘብ ሳገኝ ሌላ ቀን እገዛላችኋለሁ።» አሉ አቶ ግርማ በረጅሙ ከተነፈሱ በኋላ።

«መቼ?» ተሾመ ፈጥኖ ጠየቀ።

«ሌላ ጊዜ»

«እኮ መቼ?»

«ገንዘብ ሳገኝ አልኩህ አይደል? »

«ለመስቀል? » አመለዘውድ ጠየቀች።

አባቷ ዝም አሉ።

«እሺ ለገና?»

«ገናማ በጣም ሩቅ ነው» አለ ተሾመ።

«አሁን አትጨቅጭቁኝ ገንዘብ ሳገኝ እገዛላችኋለሁ አልኳችሁ!» አቶ ግርማ ድንገት በቁጣ ጮኹ። በልጆቹ ጭቅጨቃ ብቻ ሳይሆን፣ የሚወዷቸውን ልጆቻቸውን በዓመት አንድ ጊዜ ለአዲስ ዓመት ለማልበስ እንኳን እጅ ያጠራቸው ደሃ መሆናቸውን ሲያስቡም አዝነው ነው ቱግ ያሉት።

ሁለቱ ልጆቻቸው ደንገጥ ብለው በዝምታ ባሉበት ለአፍታ ቆዩ። ተሾመ ድንገት ብልጭ አለበት። ሌጭ እንደማለት እጁን አየር ላይ በቁጣ ወርውሮ ከቤት እየተቆናጠረ በፍጥነት ወጣ።

አቶ ግርማ፣ 'ይሄ ልጅ ጎረመሰ' ሲሉ አሰቡ። ምንም ቃል ግን ከአንደበታቸው አልወጣም።

«የት ልትሄድ ነው?» አለችው አመለዘውድ ከቤት ወጥታ ሮጥ ብላ ተሾመ ላይ ደርሳበት እየተከተለችው።

«የእኛ አባት ክፉ ነው» አለ ተሾመ እጁን እያወራጨ።

«እንዴት? ለምን እንደዚህ አልክ?» ግራ ተጋብታ ጠየቀችው።

«ሌሎች አባቶች ለልጆቻቸው ልብስ፣ ጫማ ሌላም ነገር ይገዙላቸዋል። የእኛ አባት ግን ምንም አይገዛልንም። ክፉ ነው!»



Sample output to test PDF Combine only

«እገዛላችኋለሁ ብሏል እኮ»
«አይገዛልንም ውሸቱን ነው:: መቼ? ስንለው ዝም አለን አይደለ?»
«ግን'ኮ አባታችን ይወደናል::» አለች አመለዘውድ::
«ቢወደንማ ልብስ ይገዛልን ነበር::»
«ፍራንክ ስለሌለኝ ነው አለን አይደል
«አለው:: ውሸቱን ነው::»
አመለዘውድ ዝም አለች:: ተሾመ የሚለው አልተዋጠላትም::
«በቃ እኔ ወደ አስፋልት ልሂድ:: እዚህ አዳሜ አዳስ ልብስ ለብሶ፣ እኔ አሮጌ ለብሼ ምን እሰራለሁ? » አላት::
ከግቢው ሲወጣ እየተከተለችው፣ «ተሹ እምሳ ትመጣለህ አይደል?» ብላ ጠየቀችው::
«አልመጣም:: ምን አሰራለሁ?»
«ዶሮ ጣጥ'ኮ ነው»
«ይሁና!»
ቆም ብላ በዓይኖቿ ተከተለችው

ተሾመ ከግቢያቸው ሲወጣ ብምትገኘው፣ አግራና ስቀኝ ስቤቶች በታጠረች ቀጭን መንገድ አልፎ ወደ ዋናው የመንደሩ የጠጠር መንገድ እንደወጣ አዲስ ጂንስ ሱሪና ጃኬት ከለበሰ ከአከያው የሰፈራቸው ልጅ ጋር ተገናኘ:: ድንገት ዷ ብሎ ከፈነዳ ሬኛ አየር በየአቅጣጫው እንደሚበተን፣ የቅናት መንፈስ በመላ ሳውነቱ ከመቅጽበት ተሰራጨ.

«እሺ ተሹ! » አለ ልጁ::
«ታዲያስ!»
ልጁ ባያስተውለውም ፊቱ ላይ ቅናቱ ቁልጭ ብሎ ይታያል::
«አዲስ ልብስህን አትለበስም እንዴ? እንቁጣጣሽ'ኮ ነው?"
«ለመስቀል ነው የሚገዛልኝ» ላብ ስምጥ እያደረገው ዋሽና በፍጥነት አልፎት ሄደ::

«አበባየሆሽ!»
«ለምለም!»
«አበባየሆሽ!»
«ለምለም!» . . .
አመለዘውድ ግቢያቸው ውስጥ እንደቆመች የሰፈሩ ልጃገረዶች ድምጽ ከቅርብ ርቀት ተሰማት:: ቤት ውስጥ እናቷን ለመርዳት ጉድ፣ ጉድ ስትል መዋሏ ልጅነቷን ቀስ በቀስ እየሸራረፈው፣ እንደአዋቂ ለኑሮና ለቤተሰብ ተጨናቂ እያደረጋት ቢሆንም የልጅ ባህሪዋን አለቅልቃ አልደፋችውም:: እናም አበባየሆሽ የመጨፈር ፍላጎት በውስጧ ተንደፋደፈ:: ትንሽ ልቧ



Sample output to test PDF Combine only



በጉጉት ተንጠለጠለች:: እናቷ ግን ዶሮ ስትሰራ እንድታግዛት ትፈልግ ይሆናል:: ሮጣ ወደ ቤት ገባችና::

«ድንቄ አበባየሆሽ ልጨፍር?» ብላ በልመና ዓይነት የእናቷን ፈቃድ ጠየቀች::
«ምን ይሰራልሻል? » አለች ድንቄ ዶሮ ማጠቡ ላይ እንዳተኮረች::
«ደስ ይለኛል:: ልጨፍር ድንቄ!? እ? »
«ትሂድ! » አሉ አቶ ግርማ::
«በይ ሂጂ! ብዙ ግን እንዳትቆዩ! »
«እሺ ድንቄ!»
ወሳኝ ግብ እንዳገባ ስፖርተኛ እየፈነደቀች ከደሳሳ ቤታቸው ሮጣ ወጣች::

የደስታዋ ዕድሜ ግን «አበባየሆሽ» እያሉ የሚያዜሙትን ልጆች እስክታያቸው ድረስ ብቻ ነበር:: አራት ትንንሽ ልጃገረዶች ጎረቤታቸው ወ/ሮ መዓዛ መስፍን ቤት በር ላይ ቆመዋል:: አንዷ ትንሽ ከበሮ ትከሻዋ ላይ አንጠልጥላለች:: ሁሉም አዳዲስ ልብስ ለብሰዋል:: አዲስ ጫማም ተጫምተዋል:: ለአፍታ ረስታው የነበረውን አስታወሰች:: ለካ እሷ አዲስ ልብስ አለበሰችም! ፊቷ ተቀያየረ:: አፈረች፤ ቀናችም:: በመጣችበት ፍጥነት አልተቀላቀለቻቸውም:: በእርጋታ እየተራመደች፣ ሄድ፣ ቆም እያለች መሃላቸው ቆመች::

«እሺ? አበባየሆሽ ልትጨፍሩ ነው?» አለቻቸው::
«አዎ» አለች ዮዲት የምትባለው በዕድሜ ከእሷ ከፍ የምትል ልጃገረድ በንቀት እያየቻት::
«እኔም አብሬያችሁ እጨፍራለሁ» አለች አመለዘውድ ድምጿን ዝቅ አድርጋ:: ተሳቃለች:: አፍራለች::
እመቤት የተባለችው ሌላዋ የሰፈሯ ልጅ ጊዜ ወስዳ በደንብ ገላመጠቻትና፣ «እኛ ብቻ ነን የምንጨፍረው::» አለቻት::

ሁሉም ልጆች በአመለዘውድ መምጣት ደስተኞች አልነበሩም:: አንድ፣ እነርሱን አትመስልም:: ሁለት፣ ከጭፈራ በኋላ የሚያገኙትን ከእነርሱ ጋር በመቀላቀሏ ብዙም ለማትጠቅም ልጅ ማካፈል አልፈለጉም::

«ለምን?» አለች አመለዘውድ በእርጋታ::
«አይሆንም! ከኛ ጋር አትጨፍሪም::» አለቻት ዮዲት በቁጣ::
«እንደኛ አዲስ ልብስ ሳትለብሺ ከኛ ጋር መጨፈር ያምርሻል?!» አለች እመቤትም::

አመለዘውድ ኩምሽሽ ብላ በዝምታ ቆመች::
ዮዲት፣ 'እንዴት ብትደፍረን ነው?!' በሚል ስሜት በንዴት ጦፋለች::

«ስታስጠላ! በቃ አንፈልግሽም! በቃ ኑ እናንተ! እንዳትከተይን! አንፈልግሽም!» ብላ እጆቿን የሁለት ልጆች ትከሻ ላይ አሳርፋ «እንሂድ!» ብላ ወደ ፊት ገፋቻቸው::

አመለዘውድ ድንገት ፍንድት ብላ ማልቀስ ጀመረች:: ገርበብ ብሎ የነበረውን የወ/ሮ መዓዛን ግቢ የብረት በር ከፍታ ገባችና ሃያ እርምጃ ያህል ርቆ ወደሚገኘው ቤት ሮጠች::

«ምነው? ምንድነው አመለዘውድ?» ወ/ሮ መዓዛ እያለቀሰች ተንደርድራ ወደ ቤት ስትገባ ደንግጠው ጠየቋት::

«አበ . . . አበባየሆሽ ከእኛ'ጋ አትጨፍሪም አ አ . . . አሉኝ::» ብሶት በውስጧ እየተንተከተከና እየተንሰቀሰቀች የሆነችውን ነገረቻቸው::

«እነማን ናቸው? የት ነው ያሉት?»

«እዚህ . . . በ. . . በር ላይ ናቸው::»

ወ/ሮ መዓዛ ብድግ ብለው ወጡ:: ልጆቹ ከወ/ሮ መዓዛ ቤት የግቢ በር አምስት እርምጃ ያህል ራቅ ብለው ቆመዋል:: የትኛው ቤት መጨፈር እንዳለባቸው እየተወያዩ ነበር::

«ምንድነው?» አሉ ወ/ሮ መዓዛ ወደ ልጆቹ ቀርበው ተራ በተራ እያዩዋቸው:: ከልጆቹ መሃል አንዷ የራሳቸው ልጅ ፋይል ጉታ ናት::

አመለዘውድ ወ/ሮ መዓዛን ተከትላ መጥታ የወ/ሮ መዓዛ ግቢ በር ላይ ቆማ ዕንባዋን በልብሷ እጅጌ እየጠረገች ሁኔታውን መከታተል ጀምራለች::

«. . . ምን ብላችኋት ነው?» ብለው ጠየቁ ወ/ሮ መዓዛ::

«አንፈልግሽም ስንላት በግድ ከእናንተ ጋር እጨፍራለሁ ትላለች::» አለች ዮዲት::

«ለምንድነው እሷ ከእናንተ ጋር የማትጨፍረው?»

«በቃ እኛ አንፈልጋትም:: ደግሞ አዲስ ልብስ አለበሰችም::» እመቤት መለሰች::

«ታዲያ ባትለብስስ? ሲኖራት እኮ ነው የምትለብሰው:: ከሌላት ያላትን ለብሳ መጨፈር ትችላለች::»

«አሮጌ ልብስ ለብሳ?» ዮዲት ጠየቀች::

«አዎ፤ ከሌላት ከየት ታመጣለች?» አሉና ወ/ሮ መዓዛ ወደ አመለዘውድ ዞር ብለው፣ «ዝም በያቸው አመለዘውድ:: የሌለሽን ከየት ታመጪያለች::»

ወደ ልጆቹ ደግሞ ዞረው፣ «ነውር ነው! እንደዚህ አይባልም:: እሷም እንደ እናንተ ልጅ እኮ ናት:: አበባየሆሽ ማለት፣ መጫወት ትፈልጋለች::»

አራቱ ሕፃናት የወ/ሮ መዓዛን ተግሳጽ በዝምታ ሰሙ::



Sample output to test PDF Combine only



«በሉ አሁን ታረቁ! አብራችሁ ትጨፍር:: . . . ነይ አመለዘውድ!»

አመለዘውድ በእርጋታ ወደ ልጆቹ ቀረበች::

«በሉ እንጂ! ጨብጧት!»

ሁሉም ሳይመስላቸው፣ እጃቸው ላይ ትልቅ ድንጋይ የታሰረ ያህል በግድ እየዘረጉ አመለዘውድን ጨበጧት::

«አዎ እንዲህ ነው!» አሉ መዓዛ ልጆቹ ሲጨባበጡ በፈገግታ እያዩ::

ልጃገረዶቹ እርስ በእርስ እየተያዩ ዝም ብለው ቆሙ::

«በሉ ጨፍሩ! ከዚሁ ከኛ ቤት ጀምሩ::» አሉ ወ/ሮ መዓዛ::

ልጃገረዶቹ ወደ ግቢው የብረት በር ቀረቡ::

«አበባየሆሽ!» አለች ዮዲት::

«ለምለም!» አሉ ሌሎቹ እያጨበጨቡ፣ ባለከበሮዋም ከበሮዋን እየደለቀች::

አመለዘውድ ዓይኖቿ ላይ የተረፈ እንባዋን በእጅጌዋ ጠራረገችና እንደማመንታት እያለች እጆቿን ለጭብጨባ አነሳች::

«አበባየሆሽ!»

«ለምለም!»

«ባልንጀሮቼ፣»

«ለምለም!»

«ቁሙ በተራ::»

«ለምለም!»

«እንጨት ሰብሬ፣»

«ለምለም!»

«ቤት እስክሰራ::»

«ለምለም!» . . .

አመለዘውድ በየቤቱ እየዞሩ ሲጨፍሩ የአራቱን ልጆች ያህል ነፃና ደስተኛ አልነበረችም:: በአሮጌ ልብስና ጫማዋ ምክንያት እሷ የተለየች ሆና ትታይ ነበር:: ሁሉም ሰው እሷን ብቻ ለይቶ የሚያያትና የምታስጠላቸው ይመስላትም ነበር:: መዞር ያለባቸውን ቤት አዳርሰው ጨፈሩ:: በመጨረሻ ያገኙትን ገንዘብ ሲቆጥሩ፣ አራት ብር ከሃምሳ ነበር::

«ስንት ስንት ነው የሚደርሰን ታዲያ?» ሜሮን የምትባለው ልጅ ጠየቀች::

«አምስት ነን አይደል?» አለች ዮዲት ልጆቹን ተራ በተራ እያየች:: ሂሳቡንም እግረ መንገዷን እያሰላች:: አመለዘውድን በንቀት እያየቻት፣ «አንቺ ሳንፈልግሽ ስለሆነ የመጣሽው፣ ሃምሳ ሳንቲም ነው የምንሰጥሽ::» አለቻት::

ከሌሎቹ ያነሰ ማግኘቷ ተገቢ የሆነ ያህል፣ አመለዘውድ ምንም ቃል አልተነፈሰችም:: ሃምሳ ሳንቲሙን ተቀብላ ከባድ የዝቅተኝነት ስሜት እየተሰማት ወደ ቤት ሄደች::

እሷም ሆነ የሷ ቤተሰቦች በእርግጥም ከሰፈሩ ሰዎች ሁሉ የተለዩ እንደሆኑ መረዳት ከጀመረች ሰነባብታለች:: እነሱ ያጡ የነጡ ደሆች ናቸው:: የእነሱ ቤት ሳሎንም፣ መኝታ ቤትም፣ ማዕድ ቤትም ሆና የምታገለግል ባለአንድ ክፍል ደሳሳ ናት:: የሰፈሩ ሰዎች በሙሉ ግን የተለያዩ ክፍሎች ያሏቸው ትልልቅ ቤቶች አሏቸው:: ልጆቻቸው ከነሱ የተሻለ ይለብሳሉ: አባቶቻቸውና እናቶቻቸውም ጥሩ፣ ጥሩ ልብስ ለብሰው ነው የምታያቸው: ብዙዎቹ ልጆቻቸውን ከፍለው የህዝብ ት/ቤት ያስተምራሉ:: ሶፋና ቴሌቪዥንን ሌሎችም ውድ ዕቃዎች አሏቸው:: ልጆቻቸው እንደነሱ መሬት ሳይሆን አልጋ ላይ ነው የሚተኙት::

አዎ፣ ዓለም ለአመለዘውድ በሁለት ዋና ክፍሎች መከፈል ጀምራለች- የእሷ ቤተሰብና ሌሎች::



Sample output to test PDF Combine only



# -12-

*«ባልየው አይወዳትም ነበር:: ራሱን ከፍ አድርጎ ያይ ነበር::*
*ስለወለደችለት ብቻ እንጂ አይፈልጋትም:: . . . ይንቃታል::»*
*ወ/ሮ ሃና መስፍን*
*«ማዘርን ሲመታት ከፍተኛ ተቃውሞ ነበረኝ::እሱም የሆነ*
*ቂስል እንዳለበት ይሰማኛል:: ሳይጠጣም ይደበድባታል::»*
*ተሾመ ግርማ*

በአግዳሚ ወንበሮቹ ላይ በርካታ ጠጪዎች ተደርድረው የሚወዷትን ቢጫ መጠጥ ይጎነጫሉ፤ ጠጂቱን! ብዙዎቹ አጠገባቸው ከተቀመጡ ከሚያውቋቸውም፣ ከማያውቋቸውም ሰዎች ጋር ያወጋሉ:: አንዳንዶቹ እንዲያውም ርቀት አይገድባቸውም፤ ማዶ፣ ለማዶ ተቀምጠውም ወሬያቸውን ይሰልቃሉ:: አስራ ሁለት ሠዓት ገደማ ነው:: በተለይ ከሰዓት በኋላ ጠጪዎች የማይጠፉ ቢሆንም እንዲህ አመሻሽ ላይ ጠጅ ቤቱ በደንበኞች ይጨናነቃል:: ብዙዎቹ የጠጅ ቤቱ ደንበኞች ድራፍት ወይም ቢራ ለመጠጣት እጅ የሚያጥራቸው፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ የቀን ሠራተኞች፣ አትክልተኞች፣ ዘበኞች፣ አናጢዎችና ግንበኞች ናቸው::

አቶ ግርማ አንድ ጥግ ተቀምጠዋል:: ከፊታቸው የተቀመጠውን ብርሌ አንገቱን አንቀው አነሱና ጠጁን ተጎነጩ::

«ሥራ እንዴት ነው?» አጠገባቸው የተቀመጡ ብዙም የማይቀርቧቸው፣ በሩቁ በዓይን የሚያውቋቸው ሰው ጠየቋቸው::

«ምንም አይል:: ጥሩ ነው::»

«ምንድነው የምትሰራው?»

«አንድ ሴትዮ ቤት በአትክልተኝነት እየሰራሁ ነው::»

«ቤተሰብ አለህ አይደል? »

«እንዴ አዎ:: ሦስት ልጆች አሉኝ:: . . . እርስዎስ ቤተሰብ አለዎት? »

«አዎ፣ አምስት ልጆች አሉኝ::»

«ምንድነው የሚሰሩት? »

«የተገኘውን፣ አንዳንዴ ሳልሰራም ውዬ ባዶ እጄን እገባለሁ:: ደግነቱ ባለቤቴ ጎበዝ ነች! እንጀራ እየጋገረች ትሸጣለች:: ቆሎ ቆልታም ልጆቹ ይሸጡታል:: እንደጉልት ነገርም ትሞካክራለች:: እንዴት ዓይነቷ ጎበዝ መሠለችህ! እሷ ባትኖር እኔና ልጆቹ ምን ይውጠን እንደነበረ እንጃ! ሳይደግስ አይጣላም ነው የሚባለው? በዚህ ድህነት፣ በዚህ ሥራ እንደልብ በማይገኝበት ዘመን፣ በኔ ጥረትና ድካም ብቻ ቢሆን ልጆቹን የማሳድገው ኑሮ ከባድ ይሆንብኝ ነበር::»

«አዎ! አዎ!» አቶ ግርማ ራሳቸውን ነቀነቁ።

ስለድንቄ እያሰቡ ቅናት ይለበልባቸው ጀመር። 'አንተ በሽተኛ ሴት አግብተህ። በዚያ ላይ ምላሰኛና ነገረኛ! . . . ወይ ፀባይ የላት፣ ወይ ሥራ ሠርታ ልጆቹን አታሳድግ፣ ሁልጊዜ ባንተ ላይ ተንጠልጥላ. . .' ሲሉ ማሰብ ጀመሩ። ሆድ ባሳቸው። ተበሳጩ።

«ተጫወት እንጂ!» አሉ አጠገባቸው የተቀመጡት ሰውዬ።

«እሺ» ብለው ከፊታቸው የነበረውን ግማሽ ብርሌ ጠጅ የመመንጨቅ ያህል አንስተው በጉሮሯቸው አንቆረቆሩት። ብርሌውን እንደ ጠረጴዛ ከሚያገለግለው አግዳሚ ጋር አጋጭተው ሲያስቀምጡት ውስጡ የቀረው ጭላጭ ነበር። አሁን ከያዙት ጋር ሶስት ብርሌ ጠጅ ጠጥተዋል። ያን ያህል ብቻ ነበር ለመጠጣት ወስነው የመጡት። ብስጭታቸውን ለመርሳት በደንብ መጠጣት እንዳለባቸው አሰቡ።

«ማነህ ና!» በአጠገባቸው የሚያልፈውን አስተናጋጅ ተጣሩ።

ዞር ብሎ አያቸው።

«ቅዳልኝ!» አሉት በቁጣ አዘል ትዕዛዝ ወደ ብርሌው እየጠቆሙ።

☆ ☆ ☆

አቶ ግርማ ቤት ሲደርሱ ሞቅ ብሏቸው ነበር። ድንቄ አንድ ጥግ ቁጭ ብላ ወጥ እያሞቀች ታዜማለች።

«ያገሬ ልጅ ና! ና! የወንዜ ልጅ ና! ና!
ዓይኔ የሚጠግበው አንተን ሲያይ ነውና። . . . »

ባለቤቷ ገብተው ሲቀመጡ ለአፍታ ዞር ብላ አይታቸው፣ «እንደምን ዋልክ?» አለቻቸውና መልሳቸውን ሳትጠብቅ መዝፈኗን ቀጠለች።

«ወጣት ነው ጆግና ነው ኩሩ የተኩራራ
የልጅነት ወዙ ከፊቱ ሚያበራ። . . .»

«ዝም በይ! አታላዝኝብኝ!» አሉ አቶ ግርማ ገና ገብተው ቁጭ ከማለታቸው።

ድንቄ ምንም መልስ ሳትሰጣቸው ልጅነቷን የሚያስታውሳትን ዜማ ማንጎራጎሯን ቀጠለች።

«. . . ቆንጆ ነው፣ ሸጋ ነው የወደድኩት ልጅ፣
ትኩስ ሰውነቱ እንደጣይ ሚፋጅ፣





ከወደቅኩስ ላይቀር ደረቱ ላይ እንጅ። . . .»

«ዝም በይ'ኮ ነው የምልሽ!» አቶ ግርማ ዓይናቸውን አፍጥጠው በንዴት ጮኹ።

ዞር ብላ ገላመጠቻቸውና፣ «ለምንድነው ዝም እምለው?» አለች ድንቄ እሷም ተቆጥታ። «ደግሞ በገዛ ቤቴ ብዘፍን፣ ባቅራራ ማነው የሚያግደኝ?»

«ዝም በይ አልኩሽ፣ ዝም በይ!»

«ዝም ካላልኩ ምን ልታደርገኝ?»

«እገልሻለሁ!»

«እንዴት ባክህ?» ወገቧን ይዛ ትከሻዋን ቀጥ፣ አንገቷን ረዘም፣ ግንባሯን ቋጠር አድርጋ ጠየቀች።

«የሰዉ ሚስት ስንት ነገር ይሰራል። አንቺ እዚህ ሙያ ተገኘና ተጎልተሽ ትዘፍኛለሽ! ወይ ከባለማሲንቆዎቹ ጋር በየጠጅ ቤቱ እየዞርሽ አዝማሪ አልሆንሽና ብር አላመጣሽ። እዚህ እንደ ጉልቻሽ ተጎልተሽ . . .»

«ደግ አረግኩ! እዘፍናለሁ! አበጀሁ! . . . በቤቴ አትተንፍሺ ልትለኝ ነው?»

አቶ ግርማ ምንም ሳይናገሩ ከተቀመጡበት የመፈናጠር ያህል ተነስተው ድንቄን በጥፊ አጮሏት። ደግመው እስኪመቷት እድል አልሰጠቻቸውም። በንስር ፍጥነት ብድግ ብላ ተወርውራ አንገታቸውን አነቀቻቸው። አቶ ግርማ ያልጠበቁት የባለቤታቸው ፈጣን እጸፋ ለአፍታ ቢያስደነግጣቸውም፣ ወደኋላ አንድ ሁለት እርምጃ ተራምደው እጇን በኃይል መትተው ከአንገታቸው አላቀቁ። ያንን የበር መቀርቀሪያ ዱላ በፍጥነት ካለበት አንስተው ያጣድፏት ጀመር።

«ኡ!ኡ!ኡ! ኧረ በሕግ አምላክ! ሊገለኝ ነው።» ድንቄ እንደበቷ የሚፈቅድላትን ያህል ጮኸች።

ከሁለት ከሶስት ደቂቃ በኋላ የድንቄ ጩኸት ያስበረገጋቸው ጎረቤቶች፣ «ምንድነው? ምን ሆናችሁ?» እያሉ ከውስጥ የማይቀረቀረውን የግቢ በር ከፍተው ወደ ቤት ዘለቁ።

«ኧረ ይተዉ አይምቷት!» ጎረቤቶቹ ለመገላገል ባልና ሚስቱ መሃል ገቡ።

በዚሁ ጊዜ ተሾመ ደረሰ። እናቱ አንድ ጥግ ቆማ ታለቅሳለች። ሰውነቱ ከመቅጽበት በቁጣ ጋለ።

«ምነው ምን አደረገችህ?» ብሎ አባቱ ላይ ጮኸባቸው።

አባቱ ከጎረቤት ተግሳጽ ይልቅ የልጃቸው የቁጣ ድምጽ አስደነበራቸው።



Sample output to test PDF Combine only

ተሾመ ብስጭቱ ከልክ ስላለፈ ድንገት አባቱን መደብደብ አሰኘው። አባቱ ፊታቸውን አዙረው በዝምታ ከቤት ባይወጡ ኖሮ፣ ዘሎ በተከመረባቸው ነበር። ንዴቱን መቆጣጠር ስላልቻለ አለቀሰ። ዕንባውን እየጠረገ አባቱን ለራሱ ብቻ በሚሰማ ድምጽ ተራገመ።

እናቱ መሳደብ ጀመረች።

«ተይ በቃ! ተይ!» የጎረቤት ሰዎች ሊያረጋጓት ሞከሩ።

'እሱ ውጪ የፈለገውን አግኝቶ፣ በልቶ ጠጥቶ ተዝናንቶ ይገባል እሷ ግን እዚህ ታፍና ትውላለች። ሲዝናና ቆይቶ መጥቶ ደግሞ ይደበድባታል። ክፉ ነው! ክፉ!' ተሾመ በምሬት አሰበ። አባቱን አምርሮ ጠላቸው።

አቶ ግርማ የበኩር ልጃቸው እንዲያኮርፋቸውና እንዲጠላቸው አይፈልጉም። የአመለዘውድን ያህልም ባይሆን ተሾመን ይወዱታል። እንደሚሎኙት ደብተሮቹና መጽሃፎቹ ላይ ተጣብቆ የሚውል ጎበዝ ተማሪ አልሆነላቸውም። እሳቸው «ዱርዬ» ከሚሏቸው ጎረምሶች ጋር አስፋልት አካባቢ ኳስ ሲጫወትና የቪዲዮ ፊልም ሲያይ እንደሚውል ሰምተዋል። ሲመክሩት አይሰማቸውም። ተሾመ እንደሚመኙት ጥሩ ልጅ ባይሆንላቸውም፣ ለትምህርቱ ግድ የለሽ በመሆኑ ቢተክኑም፣ ይወዱታል፤ እንደ ትልቅ ሰው ያከብሩታልም። ቁጣው ያስፈራቸዋል። ገና ከልጅነቱ ለየት ያለ ባህርይ አለው። ቆራጥ ነው። ኩሩ ነው። አቶ ግርማ ተሾመ እያደገና እየበሰለ ሲመጣ ወደ ህሊናው እንደሚመለስና ለትምህርቱ ትኩረት ሰጥቶ ሰው እንደሚሆን ተስፋ ከማድረግ በዘነው አያውቁም።



Sample output to test PDF Combine only



# -13-

*«ብሩን ብዙ ጊዜ ስመኘው የነበረውን ነገር ነው*
*የበላሁበት። ሌላ ምንም አላደረግሁበትም።»*
*ተሾመ ግርማ*

ተሾመ እንደ ብዙ የደሀ ቤተሰብ ልጆች መንግስት ት/ቤት በነጻ እንዲማር የአባቱ ፈቃድ አልነበረም። የትምህርት ጥራቱ የተሻለ ነው ብለው ስላመኑ፣ መምህራን ኮሌጁ አቅራቢያ በሚገኘው ኪዳነምህረት አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እየከፈሉ ነው የሚያስተምሩት። ኑሮዋቸው ከእጅ ወደ አፍ ቢሆንም፣ «ልጄ ተምሮ ትልቅ ደረጃ ይደርስልኛል» የሚል ጽኑ ተስፋ ስለነበራቸው ነው ጥርሳቸውን ነክሰው ከፍለው የሚያስተምሩት።

አንድ ቀን ጠዋት አቶ ግርማ የአራተኛ ክፍል ወርሃዊ ክፍያ እንዲከፍል 16 ብር ለተሾመ ሰጥተውት ነበር።

«ከፈልክ?» ብለው ጠየቁት ማታ ቤት ሲገቡ። የት/ቤት ክፍያ እንዲከፍል ገንዘብ በሰጡት ዕለት ሁልጊዜ የሚጠይቁት ጥያቄ ነው።

ተሾመ ፊቱን ኩስትርትር አድርጎ፣ «አዎ ከፍያለሁ» አላቸው።

መከሳተሩ እያስገረማቸው፣ «የታል ካርኒው?» ብለው በርጋታ ጠየቁት።

«ከፍያለሁ» አለ እንደተኮሳተረ ዓይኖቹን ከዓይኖቻቸው እያሸሸ።

አቶ ግርማ ተጠራጠሩ። «ምነው? አልከፈልክም እንዴ?»

«ከፍያለሁ አልኩህ'ኮ» አለ ተሾመ በቁጣ።

«ታዲያ ምን ያስቆጣሃል?! የከፈልክበትን ካርኒውን፣ ወረቀቱን እስቲ አሳየኝ!»

ተሾመ ዝም አለ።

ድንቄና አመለዘውድ ቤቱ ውስጥ የተፈጠረው ውጥረት ተሰምቷቸው የሁለቱን ንግግር ማዳመጥ ጀመሩ።

«ተናገር እንጂ! አልከፈልክም እንዴ?!»

«ከፍያለሁ!»

«አልከፈልክም!»

«ከፍያለሁ!»

«ደግ! ከከፈልክ በል ካርኒውን አምጣ!»

«አላመጣም!» አለ ተሾመ በቁጣ።

«ለምንድነው ማታመጣው? ከፈልኩ እያልከኝ አይደል?» አቶ ግርማ በንዴት መጋል ጀመሩ።

«አዎ፣ እንደውም አልከፈልኩም!» አለ ተሾመ 'ምን እንዳታመጣ ነው የምዋሸህ?' በሚል አንባገነናዊ ስሜት።

አቶ ግርማ ከንዴት ይልቅ መገረም እየለባቸው:: ልጃቸው ብሩን አጥፍቶታል ብለው ለማመን ተቸገሩ:: ድፍረቱ እጅግ አስደነቃቸው:: ዝም ብለው አዩት::

«አልከፈልክም!?» ብለው በእርጋታ ጠየቁት::

«አልከፈልኩም!»

አመለዘውድና ድንቄ ደንግጠው እንደ ጠረጴዛ ቴኒስ ተመልካቾች ዓይኖቻቸውን ከግራ ወደ ቀኝ እያንከባለሉ አባትና ልጅ ሲጨቃጨቁ በፀጥታ ይሰማሉ::

«ገንዘቡን ምን አደረግክበት?»

ዝም አለ::

«ምንድነው? ብሩን የት አደረከው ተሸዬ?» አለች ድንቄ::

ዝም አላት::

«ብሩን የት አደረግከው?» አባቱ አፈጠጡበት:: ገና አሁን ነበር ታላቅ ግርምታቸው ወደ ኃያል ቁጣ መቀየር የጀመረው::

«በላሁበት!»

«ምን?!»

«ደስ ያለኝን በላሁበት!» አላቸው ተሾመ በማንአለብኝነት::

«የኛ ጎረምሳ! ለዚህም በቅተሀል?!» ተነስተው ዐይናቸውን ቤቱ ውስጥ ለአፍታ አሽከረከሩና እጃቸው በንዴት እየተንቀጠቀጠ ከአንድ ጥግ የተጠቀለለ ቀጭን ሽቦ አወጡ::

«ምን ልታደርገው ነው?» ድንቄ ፊቷ ላይ መረበሽ እየተነበበ ጠየቀች::

«ዝም በይ! አንቺ ምን አገባሽ? እኔ የማደርገውን አውቃለሁ::» አሉ አቶ ግርማ የተጠቀለለውን ሽቦ እየፈቱ::

ተሾመ አሁን ከንዴቱ መለስ ብሎ አባቱን በጥንቃቄ መመልከት ጀምሯል::

«አምጣ እጅህን!!»

ተሾመ ራሱን ለመከላከል ከመሞከሩ በፊት አባቱ ሁለቱን እጆቹን ለቀም አድርገው ያዙና ቀጭኑን ሽቦ በእጆቹ አንጓ ላይ በፍጥነት መጠምጠም ጀመሩ::

እርር፣ ትክን ብለው፣ «አልፈርድብህም! . . . አልፈርድብህም! አስራ ስድስት ብር ለማግኘት ምን ያህል እንደምደክም ስለማታውቅ እኮ ነው:: ልጄ ተምሮ ጥሩ ደረጃ ይደርስልኛል ብዬ እንጂ'ኮ አስራ ስድስት ብር ትንሽ ብር ሆኖ አይደለም:: ይገባሃል!? . . . በላሁበት!? . . . ደግሞ አፍህን ሞልተህ በላሁበት ትለኛለህ?! ኧከከከከ . . . እንዲህ ትንቀኝ!»

«ልጄን ምን ልታረገው ነው?» ድንቄ ከተቀመጠችበት ተነስታ ወገቧን ይዛ አጠገባቸው ቆመች::





«እንዲያውም ልጁን ያበላሸሽው አንቺ ነሽ::» አቶ ግርማ የልጁን እጅ በሽቦ መጠፍነጋቸውን ለአፍታ ቆም አድርገው ሚስታቸው ላይ በቁጣ አፈጠጡ::

«ምን አድርጌ ነው ያበላሸሁት? ይልቅ አሁን ተወው!»

«ዝም በይ! ከማንም ዱርዬ ጋር ሲውል አትቆጪው፤ አትቆጣጠሪው:: እያሞካሸሽና እያንቆለጳጰስሽ እንዲህ ትዕቢተኛና ጥጋበኛ አደረግሽው::» ብለው ጮሁባት::

«አንተስ አባቱ አይደለህ? ምን እኔን ብቻ. . . »

«እኔማ ሥራ ነው የምውለው:: የት አየዋለሁ? አንቺ እዚህ ተጎልተሽ እየዋልሽ ዱርዬ ሲሆን ዝም ብለሽ ታዪዋለሽ:: ወይኔ ግርማ!» ሽቦውን የልጃቸው እጅ ላይ መጠምጠሙን ቀጠሉ::

«ልጄን ዱርዬ አትበለው::»

«ዝም በይ አንቺ! ዝም በይ!». . .

የአባትና እናት ጭቅጭቅ ተጋጋለ:: አቶ ግርማ በተሾመ እጅግ ቢበሳጩም አልመቱትም:: ከመቆጣትና ከመምከር አልፈው ልጆቻቸውን ገርፈውና ደብድበው አያውቁም:: የዛሬው የተሾመ ጥፋት ከአእምሯቸው በላይ ሆኖባቸው፣ እንዴት ሊቀጡት እንደሚገባ ለማሰብ እንኳን አልቻሉም:: ንዴት ብቻ ሳይሆን ከባድ ሐዘንና ተስፋ መቁረጥ ውስጠታቸውን አማሰሉት:: ከብሩ መጥፋት በላይ እጅግ ያንገበገባቸው የልጃቸው መባለግና ጋጠ ወጥ መሆን ነበር:: ባልና ሚስቱ ሲጨቃጨቁ ቆይተው በመጨረሻ ነገሩ የበረደ መስሉ፣ አቶ ግርማ ግን ውስጣቸው እየተቃጠለ ተኙ::

ተሾመ እጁ እንደታሰረ ነበር የተኛው:: እንቅልፍ ግን አልወሰደውም:: ጥፋቱ ይፀፅተው ጀምሯል:: አባቱ እጅግ እንዳዘኑበት በሚገባ ተረድቷል:: ብስኩት፣ ሳንቡሳ፣ ከረሜላ፣ ጀላቲ፣ ማስቲካ . . . ከዚህ በፊት እንደ ልጅ የሚያጓጉትን ነገሮች በልቶበት አስራ ስድስት ብሩን በአንድ ቀን አውድሞታል:: አባቱ እናቱን በየጊዜው በመደብደባቸው ለእሳቸው ያደረበት ንቀትና ጥላቻ ከጉርምስናው ጋር ተደምረው ልቡን አሳብጠውትና አደድበውት ነው ብሩን ለማጥፋት የተደፋፈረው:: በዚህ ምሽት የአባቱን አስፈሪ ቁጣና ከባድ ሐዘን ካስተዋለ በኋላ ግን ወደ ህሊናው ተመለሰ:: ፀፀት እንደ አገዳ ትል ውስጡን አነኮተው::

ሌሊቱን ከሽቦው ጋር ሲታገል አድሮ እጆቹን እንደምንም ከእስሩ አላቀቀና ጠዋት አስራ ሁለት ሰዓት ገደማ ከቤት ወጥቶ ሄደ::



Sample output to test PDF Combine only

## -14-

*«ብሩን በማጥፋቴ ተጸጸትኩ:: ያጠፋሁትን መክፈል እንዳለብኝ አሰብኩ፤ በመሸከም በምናምን::»*
*ተሾመ ግርማ*

ቀኑን ሙሉ ተሾመ ወደ ቤት አልመጣም:: ሲመሽ እንደሚመጣ አመለዘውድና ድንቁ ተስፋ አድርገው ነበር:: ሲመሽም አልመጣም:: አቶ ግርማ አመሻሽ ላይ ቤት ሲገቡ ቀኑን ሙሉ እንዳልመጣ ተነገራቸው::

«ዱርዬ! ተዉት! ሲርበው ይመጣል!» አሉ::

ሁሉም ተሾመ ማታ እንደሚመጣ ተስፋ አድርገው ነበር:: ሦስት ሰዓት ሲያልፍ እናትና አባቱ እህቱ አመለዘውድም ግራ ገባቸው:: አመለዘውድ ጎረቤት የሚኖረውን ጓደኛውን ደጀኔን እንድታነጋግር ተላከች::

ደጀኔን ግቢያቸው በር ላይ ቆማ አስጠርታው፣ «ዛሬ ተሼን አይተኸዋል?» ብላ ጠየቀችው::

«አላየሁትም:: እስካሁን ወደ ቤት አልመጣም?» አላት ደጀኔ::

«አልመጣም:: የት ሊያመሽ ይችላል? »

«እኔ እንጃ»

አመለዘውድ ተረበሸች::

«ጓደኞቹ እነማን ናቸው?»

«እሉ የሆኑ ልጆች:: አታውቂያቸውም::»

የዕንባ ዘለላዎች ዓይኖቿ ላይ ተንጠልጥለው በፍጥነት ወደ ቤት አመራች::

ቤት እንደደረሰች፣ «ተሼ ዛሬ የሚመጣ አይመስለኝም» አለች::

«ለምንድነው የማይመጣው? የት ነው ያለው?» ድንቁ ጠየቀቻት::

«ደጀኔ፣ 'ከጓደኞቹ'ጋ አስፋልት አካባቢ ሊሆን ይችላል፣ ግን እኔ ዛሬ አላየሁትም' ብሏል::»

«የፈራሁት አልቀረም ዱርዬ እየሆነ ነው ብዬሽ'ኮ ነበር:: ትምህርቱን በስርዓት አይማር፣ ከዱርዬዎች ጋር አስፋልት እየዋለ ተበላሸ::» አሉ አቶ ግርማ::

«ሄደን አናመጣውም?» አመለዘውድ በሐዘን በተሰበረ ድምፅ ጠየቀች::

«የት ብለን ነው የምንሄደው? አስፋልት ስንት ቤት አለ?» አሉ አቶ ግርማ::

«ምን ይሄ ዱርዬ ብሎ፣ ብሎ ደግሞ ውጪ ማደር ጀመረ!? ሆሆይ! » አሰት ድንቁ አፏን ይዛ እየተገረመች::



Sample output to test PDF Combine only



«ደጀኔን ይዘን ለምን አንሄድም? » አለች አመለዘውድ::

«እንደሱ ጎዶነቱን ዱርዬ ለመፈለግማ በጨለማ አልንከራተትም:: 'ምከረው፣ ምከረው አምቦ ካለ መከረ ይምከረው::' አሉ:: እኔ እንግዲህ ትምህርቱን አርፎ እንዲማር ስመክረውኖሬአለሁ:: አልሰማ ካለ ምን ይደረጋል? ቢፈልግ ጅብ ይብላው! ለማንም ዱርዬ ዱር አዳሪ ሌባ ምን አስጨነቀኝ?» በልጃቸው ያመረሩ ቢመስሉም አቶ ግርማ ምሬታቸው ከልባቸው አልነበረም:: ልጃቸው እጅግ ቢያበሳጫቸውና ቢደፍራቸውም ይወዱታል:: እንዲያውም ገና ከሁኑ እየናፈቃቸው ነው::

«ኧረ ግድ የለህም ፈልገን ይዘን እናምጣው?» አመለዘውድ አባቷን ተማፀነች::

«ዝም በይ አንቺ ደግሞ! ይህን ዱርዬ ሰው ነው ብለሽ ነው?! ቆይ ይምጣ ብቻ! የማደርገውን እኔ አውቃለሁ::» አለች ድንቁ:: በጣም ተናዳለች::

«ነገርኩሽ'ኮ አንድ ዱርዬ ፍለጋ በጨለማ እግሬን አላነሳም፣ ደግሞ ጅብስ ቢበላን?» አሏት አቶ ግርማ አመለዘውድን:: ግድየለሽ ለመምሰል ቢሞክሩም፣ ውስጥ ውስጡን ግን እርር፣ ድብን ብለዋል::

ልጆቻቸውን እጅግ ይወዳሉ:: ከሚስታቸው ጋር በሚፈጥሩት አምባጓሮና ጥል ተሾመ ቢቀየማቸውም፣ በአንድ ማዕድ ከእሳቸው ጋር ለመብላት አሻፈረኝ እያለ ቢያኮርፍም፣ በየጊዜው ከት/ቤት እየቀረ እንደሚያውደለድል ቢሰሙም፣. . . ተሾመን ይወዱታል:: ከድንቁ ጋር ዳግመኛ አብረው ለመኖር የወሰኑት ገና ድሮ አራስ ልጅ በነበረበት ጊዜ ወደውት አይደል? የኑሮ አቅጣጫቸውን ያስቀየራቸው የበኩር ልጃቸው እሱ'ኮ ነው:: የተቆጣውን የአስራ አራት ዓመት ልጃቸውን ቀስ በቀስ ሊያባብሉትና፣ ሊያረጋጉት እንደ ሕፃንነቱ ዘመን እንዲወዳቸው፣ የልጅ ፍቅሩን፣ ንፁህ ፍቅሩን ዳግመኛ እንዲሰጣቸው ይመኙ ነበር:: ባለቤታቸው ብታናድዳቸው እንኳ ልጃቸው እንዳያኮርፋቸው ከመማታት የተቆጠቡባቸው ቀናት በርካታ ናቸው::

'ምን ያደርጋል? ዱርዬ ሆነ::' ሲሉ አቶ ግርማ ተስፋ በመቁረጥ አሰቡ:: የመኖር ፍላጎት ሲያጡ ተሰማቸው:: 'ትላንት በጣም ተቆጣሁት ይሆን?' ብለው ተጨንቀው አሰቡ:: ለደቂቃዎች አስበው ካጠፋው ጥፋት ጋር የሚመጣጠን ቅጣት እንዳልቀጡት ግን እርግጠኛ ስለሆኑ ከፀፀት ራሳቸውን አራቁ::

«ተሼ አንድ ነገር ቢሆንስ ግን?» ፊቷ ላይ ፍርሃት እየተነበበ አመለዘውድ ጠየቀች::

አቶ ግርማ ሊላዋን ውድ ልጃቸውን ከንዴታቸው መለስ ብለው አስተዋሏት:: በጣም ተጨንቃለች:: አዘኑላት::

«አይዞሽ ምንም አይሆንም። ነገ ፈልገን እናመጣዋለን። አሁን ግን መሽቷል አራት ሰዓት ሊሆን ነው። . . . » አሏት።

ድንገት የጅብ ድምፅ ጨለማውን አቆራርጦ ተሰማ።

«ይኸው አላልኩሽም ጅቡ እዚህ ቅርብ ነው ያለው።» አሏት።
«እረ ይሄ ጅብ ልጄን እንዳይበላብኝ!» ድንቄ ተጨነቀች።
«ወይኔ ተሼ! ጅቡ እንዳይበላው» አመለዘውድም ተረበሸች።
«አይዞሽ! ምንም አይሆንም።» አሉ አባቷ።
«እረ ጅቡ እንዳይበላው!»
«ምንም አይሆንም አልኩሽ'ኮ» አቶ ግርማ አመለዘውድን ለማፅናናት ሞከሩ።
«እረ እንዲያውም በበላው! አሁን ውጪ ማደርን ምን አመጣው? ጥጋብ'ኮ ነው። ሰሞኑን ምሳ ቤት መብላትም ትቷል። እዛ ከዱርዬ ጓደኞቹ'ጋ ምኑንም፣ ምኑንም እየበላ ነዋ እንዲህ የጠገበው።» አለች ድንቄ ዳግም በንዴት እየጋለች። ዝም ብላ ለአፍታ አሰበችና፣ «ወቸ ጉድ! ውጪ አደረልኝ!» አለች። የልጇን ውጪ ማደር ለማመን የተቸገረች ትመስላለች። የለቅሶ ሳግ ተናነቃትና ዝም ብላ መተከዝ መረጠች።
«ሲርበው ነገ ይመጣል። አሁን እንተኛ!» አሉ አቶ ግርማ። «ሚካኤልም ይተኛበት እየተንጫጫን አንረብሸው።»

ትንሹ ሚካኤል ፍራሹ ላይ በፀጥታ ተኝቷል።

ሦስቱም ከአካላቸው ክፍሎች አንዱ ተቆርጦ ውጪ ያደረ ያህል እየተሰማቸው፣ ነገ ተሾመ አብሯቸው እንደሚያድር ተስፋ እያደረጉ ወደየመኝታቸው ሄዱ።

አቶ ግርማ ለሰዓታት እንቅልፍ አልወሰዳቸውም። ሲያዝኑ፣ ሲናደዱ፣ ሲፀፀቱ ሌሊቱ ተጋመሰ። የበኩር ልጃቸው ተምሮ ከራሱም አልፎ እሳቸውን እንደሚጦራቸው ተስፋ ያደርጉ ነበር። ባለፉት ወራት ጉልበትና ጥንካሬያቸው እየከዳቸው እንደሆነ ቀስ በቀስ መረዳት ጀምረዋል። ወደፊት እንደቀድሞው፣ እንደወጣትነታቸው ተሯሩጠው፣ ላይ፣ ታች ብለው ቤተሰባቸውን ለማስተዳደር እንደማይችሉ አንድ መራር እውነት እየተገለጠላቸው ነው።

'አረጀሁ ማለት ነው?' ይላሉ አንዳንዴ ቀደም ሲል በቀላሉ ሲያከናውኑት የነበረውን ሥራ ዛሬ፣ ዛሬ ሲሰሩት ቶሎ ስለሚደክማቸው። 'ጠጁ ይሆን? ይሄን ጠጅ ልተው መሠለኝ' ብለውም ያስባሉ። ምሽት ላይ ግን ወደ ቤታቸው በጊዜ ለመግባት ብዙ አይጓጉም። ሚስታቸው ሲበዛ ነጭናጫና





ተሳዳቢ ሆናለች። ተሾመ በየጊዜው ያኮርፋቸዋል፣ ጥላቻውንም ከማሳየት ወደኋላ አይልም። ታዲያ በጊዜ ወደ ቤት ለመግባት ለምን ይቸኩላሉ? ተምሮ ራሱን ችሎ ይጦረኛል ብለው በብዙ ድካም ከምትገኝ ትንሽ ገቢያቸው ለት/ቤት እየከፈሉ ቢያስተምሩትም ተሾመ ለትምህርቱ ግድ የለሽ ሆኗል። ጭራሽ የድፍረቱ ድፍረት ለት/ቤት ክፍያ የተሰጠውን ገንዘብ አጥፍቶ ገንዘቡን እንዳጠፋው በይፋ ተናግሯል።

ሁለቱ ትንንሽ ልጆቻቸው አመለዘውድና ሚካኤል አባታቸው ማታ ቤት ሲገቡ ደስ ይላቸዋል። ምንም እንኳ በጉያቸው ለእነርሱ የሚሆን ነገር ሸጎጥ አድርገው የሚገቡት ከስንት አንዴ ቢሆንም፣ ምንም እንኳ እነርሱን ለማቀፍና ለማጫወት ብዙም ፍላጎት ባይኖራቸውም፣ ምንም እንኳ ድንቄ ስታናድዳቸው ቢደበድቧትም . . . ሁለቱ ሕፃናት የልጅነት ፍቅራቸውን ለአባታቸው ከመለገስ ወደኋላ አላሉም።

ስፌ አዳራሽ ውስጥ በክረምት አንድ ጥግ ላይ እሳት ማንደድ አዳራሹን እንደማያሞቀው ሁሉ፣ የሁለቱ ሕፃናት ፍቅር የቀዘቀዘ ልባቸውን አያሞቀውም። እናም ጠጂቱን ይፈልጉታል፣ ያንቆረቁሯታል፤ ከሕይወት አስቀያሚ ገፅታ መሸሸና መደበቂያ ናት፡



Sample output to test PDF Combine only

## -15-

### «ፈለጉኝ። መደበቅ ጀመርኩ።»
### ተሸመ ግርማ

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት አመለዘውድ ተሸመን ፍለጋ ወደ አስፋልት ሄደች። ሌሊት ጥሩ እንቅልፍ አልወሰዳትም። ተሸመን ፈለገችው። የሚያውቀትን ልጆች አይተውት እንደሆነ ጠየቀች። ማንም አየሁት የሚላት ሰው ግን አላገኘችም። ዕንባዋ እንዳይታይባት ከስር ከስር እየጠረገች ወደ ቤቷ እያለቀሰች ተመለሰች። እናቷ ተጨንቃ እየጠበቀቻት ነበር።

«እ? አገኘሽው?»
«የለም። አላገኘሁትም።» አለቻት በለቅሶ ሳግ በታፈነ ድምጽ።

እናትና ልጅ ቤት ገብተው ተላቀሱ።

በዚያ ዕለት ምሽትም ተሸመ አልመጣም።

ሶስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት. . . አስራ አምስት ቀናት አለፉ። ተሸመ ወደ ቤት አልመጣም። አንዳንድ የሰፈሩ ሰዎች እንዳዩት ባይነግሯቸው ኖሮ፣ እጅግ በተረበሹ፣ የሐዘናቸው ክብደት ባቀወሳቸው ነበር። አመለዘውድ በየቀኑ ትፈልገው ነበር። አቶ ግርማና ድንቄም ፈልገውታል፣ አስፈልገውታል። ተሸመን በአካል ሊያገኙት አልቻሉም።

ከሁለት ሳምንት በኋላ ግን አንድ ቀን አመለዘውድ ወንድሟን አገኘችው! በዕድሜ ብዙም ከማይበልጠው ከአንድ ወጣት ጋር ኮተቤ መምህራን ኮሌጅ አካባቢ መንገዱ ዳር ቆሞ ስታየው፣ በህይወቷ ተሰምቷት የማያውቅ ታላቅ ሀሴት ልቧን አጥለቀለቀው። ዳግመኛ የምታየውም አልመሰላት እያለ ነበር። ድንገት እንደጭስ በንኖ እንዳይሰወርባት የሰጋች ይመስል ሮጣ አጠገቡ ደረሰች።

«ተሼ! »
«እሺ አመለዘውድ!» አለ ተሸመ ፈገግ ለማለት እየሞከረ።

ያለፉት ሁለት ሳምንታት ከቤተሰቡ አባላት ሲደበቅ ቆይቷል። ዛሬ እንድታገኘው ሳይፈልግ በድንገት አመለዘውድ ከች ብትልበትም አልከፋውም። ዘላ ተጠመጠመችበት። ከእህቱ ቁጣ እንጂ ፍቅር ስላልጠበቀ ትንሽ ተደናገረ።

«ምነው ተሼ?» አለችው የሚበቃትን ያህል ካቀፈችው በኋላ።
ዝም አላት። በዝምታ ለአፍታ አፈጠጠችበትና ማልቀስ ጀመረች።
«እንዲህ ጨካኝ አትመስለኝም ነበር።»





«ያጠፋሁትን ብር ይዤ ልምጣ ብዬ እኮ ነው።» አላት።
«ዛሬ ቤት አትመጣም?»
«ምን ብዬ ነው የምመጣው?»
«እሱን ፈርተህ ነው?»
«ገንዘቡን ሳልይዝ አልመጣም ብዬ ነው።»
«አይ ዝም ብለህ ብትመጣ ምንም አይልም። እሱ እንዲያውም እንድትመጣ ነው በጣም የሚፈልገው።»

ተሸመ ዝም ብሎ አቀርቅሮ ቆየ። የግንባሩ ደም ስሮች ተወጣጠሩ። «እንዲያውም ልንገርሽ፣ ወደ ቤት ተመልሼ አልመጣም።» አላት በራስ የመተማመን ስሜት በገነነበት ረጋ ባለ ድምፅ።

አመለዘውድ ዝም ብላ ለሰከንዶች ዓይኖቿን አፍጥጣ አየችው። ተሸመ አንዴ ብቻ ዓይኑን ጣል አድርጎባት ዓይኖቿን ለመሸሽ ማዶ፣ ማዶውን ማየት ጀመረ።

አመለዘውድ ብሽቅ አለባት። ዓይኖቿ ዳግመኛ በዕንባ ተሞልተው ነበር። እንባዋን እየጠረገች፣ «ለምን? » አለችው።
«ለምን እንደሆነማ ታውቂያለሽ አይደል?»
«አላውቅም። ምንድነው ምክንያትህ?»
ተሸመ ዝም አለ።
«ንገረኝ!»
«ገንዘብ ስላጠፋሁ ብቻ አይደለም። ለድንቂ ፍራንክ አይሰጣትም። በዛ ላይ ይደበድባታል። ለኛም ልብስና ጫማ አይገዛልንም። . . . ስለዚህ እኔ እየሰራሁ ለድንቂ ገንዘብ እሰጣታለሁ ብዬ ነው።»
«ምንድነው የምትሰራው?»
«እዚህ ታክሲ ተራ ዕቃ እየተሸከምኩ ፍራንክ አገኛለሁ።»
«ትምህርትህንስ ልታቋርጥ ነው?»
«አዎ»
«ለምን? »
«ቀስ ብዬ፣ . . . ወይ የማታ እማራለሁ።» እሷን ደስ ይበላት ብሎ እንጂ የመማር ጉጉት አልነበረውም።
«ኧረ ተሸዬ ግድ የለህም፤ ትምህርት ከምታቋርጥ ቤት ብትመለስ ይሻልሃል። አባታችንም'ኮ ቤት እንድትመጣ ይፈልጋል።» ብላ ተማጸነችው።

በሹፈት ዓይነት ሳቅ አለ። ወዲያው ፊቱ ላይ ንዴት ተነበበ።

«ምን ይፈልጋል? ተይው እሱ ዝም ብሎ ነው! እናታችንን ከመደብደብ በስተቀር ሌላ ምንም የሚያደርገው ነገር የለም።» አለ በብስጭት እጁን እያወናጨፈ።



Sample output to test PDF Combine only

«መቼም እንደሚወድህ ታውቃለህ አይደል? ተሸዬ፣ ተሼ እያለ አይደል የሚጠራህ:: »

ዝም አላት::

«ተው ተሸዬ እንዲህ አትሁን::»

«በቃ ወስኛለሁ:: ካሁን በኋላ ወደ ቤት አልመጣም:: እናቴን ሲደበድባት ከማይ ጎዳና ላይ ብኖር እመርጣለሁ::» አላት ቆራጥነት በሚደመጥበት ድምፅ::

በረጅሙ ተነፈሰች::

«እሺ እናታችንን እንኳ መጥተህ አታያትም?»

«እመጣለሁ»

«መቼ?»

«አንድ ቀን»

ከሰሞኑ አባብላ ወደ ቤት እንደምታስገባው ስላመነች ተረጋጋች::

«እሺ ዛሬ የምትበላው አግኝተሃል? »

«አዎ»

«ሥራ ባይኖርስ? ፍራንክ ብታጣስ? »

«ጓደኞቼ ስላሉ ከእነሱ ጋር ተካፍለን እንበላለን::»

«ጓደኞችህ እነማን ናቸው?»

«ይኸው እሱ አንዱ ነው::» በአገጩ ፊንጠር ብሎ ወደቆመው ጓደኛው አመለከታት:: «ሌሎችም አሉ::»

«የትስ ታድራለህ? ብርድ አይመታህም? »

«በቃ ሂጂ! ላኔ ብዙ አትጨነቂ::» አላት ወደ ታክሲ ተራው ዓይኖቹን እየወረወረ::

«ተው ተሸዬ! ተው ዛሬ ማታ ወደ ቤት ና!»

«በይ ቻው!» ብቻዋን ጥሏት ወደ ጓደኛው ተመለሰ::

አመለዘውድ በቆመችበት ደርቃ ወንድሟን በሃዘኔታ ስታየው ቆየችና ወደቤት አዘገመች:: መንገድ ላይ የወንድሟ ነገር አሳዝኗት አለቀሰች:: ወንድሟን በቅርቡ ወደ ቤት እንደምትመልሰው ግን በልቧ ጽኑ ተስፋ አሳደረች::

አመለዘውድ እንዳሰበችው ተሸመ በቀላሉ ወደ ቤት የሚመለስ አልሆነም:: ሳምንታት አለፉ:: በየቀኑ እየሄደች ትጨቀጭቀዋለች:: ይሰማታል ግን አይቀበላትም::

ወራት አለፉ:: ተሸመ የጎዳና ውሎውንና አዳሩን ለመደው:: ከቤተሰቡ ድህነትና የጓዳ ችግር ራሱን ማግለሉ የተሻለ ሰላምና ነፃነት ሰጠው:: አመለዘውድ አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ቢያንስ በቀን አንዴ ሳታገኘው



Sample output to test PDF Combine only



አትውልም:: ወደ ቤት እንዲመለስ ከመወትወትም ተቆጥባ አታውቅም:: ጥረትና ድካሟ ሁሉ ግን በጭንጫ ላይ ያረፈ ዘር ሆነ::

ከበርካታ ወራት በኋላ ነበር አቶ ግርማ ተሸመን ኮተቤ ኮሌጅ ፊት ለፊት አንድ ቀን ያገኙት::

«ምነው ልጄ? ምን ክፉ ነገር ባንተ ላይ አደረግኩ? ለምን ከቤት ጠፍተህ ቀረህ?» አሉት:: ፈገግ ሊሉ ቢሞክሩም አልቻሉበትም::

«ያጠፋሁትን ብር ልመልስልህ ብዬ ነበር::» አላቸው::

«እሱማ እንዴ ጠፍቷል፤ ተወው:: እኔ መልስልኝ አልኩህ?»

ዝም አላቸው::

«ለምንድነው ወደ ቤት የማትመጣው?»

«እዚህ ስለሚመቸኝ ነው::»

«እኔ ምን አደረግኩህ? ለመሆኑ መትቼህስ አውቃለሁ?»

«ለምን እናቴን ትመታታለህ?»

«ልጄ ነህ፤ ያውም የበኩር ልጄ:: ከቤት ወጥተህ እንድትቀር፣ ባለቤት እንደሌለው ውሻ ጎዳና ላይ እንድትንከራተት አልፈልግም:: እንድትማር ጥሩ ደረጃ ላይ እንድትደርስ ነው የምፈልገው::»

«እናቴን የምትመታት ከሆነ፣ ካንተ ጋር መኖር አልፈልግም::»

ሊያባብሉት ሞከሩ:: ተሸመ ፍንክች የሚል አልሆነም::

ታስፋ ቆረጡ፤ አዘኑም::

«በል የሚያዋጣህን አንተ ታውቃለህ:: ወደ ቤት መምጣት ከፈለግክ ግን እኔ አልከለክልህም::» ብለውት ሄዱ::

ከእናቱ ጋር ደግሞ ሌላ ቀን ተገናኙ::

የገብርኤል ዓመታዊ ክብረ በዓል ስለነበር እሱና የጎዳና ተዳዳሪ ጓደኞቹ ከቤተሰቦቹ ቤት በቅርብ ርቀት ወደሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሄደው ነበር:: ቤተክርስቲያን ቆይተው ወደ አስፋልት አቋራጭ በሆነው በነተሸመ ሰፈር ውስጥ ሲያልፉ፣ ከጎረቤታቸው ከወ/ሮ ሻሼ ሱቅ አጠገብ እናቱ ተቀምጣ አያት:: ሊደበቃት አልሞከረም:: ቀጥታ ወደ እሷ ሄዶ፣ «ድንቄ!» ብሎ ጠራት::

ዞር ብላ አየችው:: ዓይኖቿን ማመን አልቻለችም::

«አንተ?! . . . ተሼ ነህ እንዴ?!» ከተቀመጠችበት አንዳች ነገር ያስደነገጣት ያህል ተስፈንጥራ ተነሳች:: ለአፍታ ፍዝዝ ብላ አየችው::

ተሸመ እንዳያቅፋትና እንዳይስማት ሁኔታዋ ግራ አጋብቶት፣ ባለበት እንደቆመ፣ «ደህና ነሽ?» አላት ፈገግ ብሎ::

ድንቂ ድንገት በጥፊ አጮለችው:: ትከሻውን በጡጫ መታችው፤ ጀርባውን ደለቀችው::

የዱላ መዓት አወረደችበት፤ «አንተ ነህ እንዴ?!? . . . አንተ ዱርዬ! . . . ተሼ ነህ?. . .» ትላለች ቁና ቁና እተነፈሰች::

ተሾመ ባልጠበቀው የእናቱ ቁጣና ድብደባ ከበላዩ የድንጋይ ናዳ የሚወርድበት ጋራ ሥር ያለ ሰው ሊሰማው የሚችለው ዓይነት ድንጋጤ ተሰማው:: በጥፊና በጡጫ ስታጣድፈው ራሱን ለመከላከል ከመሞከር በስተቀር አንድም ቃል ለመናገር እንኳን ዕድል አላገኘም:: ድንቂ እየመታችው ማልቀስ ጀመረች:: ድንገት የምትንሰፈሰፍለትን ልጇን መደብደብ አቁማ ጎትታ ደረቷ ላይ ለጥፋ አቀፈችውና ጸጉሩን፣ ግንባሩን፣ ጉንጩን እየሳመች ተንሰቀሰቀች::

«አንተ ዱርዬ! አንተ ጨካኝ! . . . ደህና ነህ ግን ተሼዬ? . . .» ትለዋለች አልፎ፣ አልፎ ከእቅፏ አውጥታ ትከሻዎቹን ይዛ እያየችው:: ጎተት አድርጋ ደግሞ ደጋግማ ትጨመጭመዋለች::

ለበርካታ ደቂቃዎች በዚህ ሁኔታ ቆዩ::

«በል ና እንሂድ!» አለችው የእናትነት ፍቅሯንና ናፍቆቷን ጭምጭም አድርጋው ካሰከነች በኋላ::

«የት?» ብሎ ጠየቀ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ የዱላና የፍቅር ዶፍ የዘነበበት ተሾመ ተገርሞና ግራ ተጋብቶ::

«ወደ ቤት ነዋ! ኋላ የት ልትሄድ ነው?» አሁን ደግሞ የመገረሙ ተራ የድንቂ ሆነ::

«ሌላ ቀን እመጣለሁ ድንቂ::» አላት::

«ምን? . . . ምን አልክ? . . . ተመልሰህ ልትሄድ ነበር እንዴ የመጣኸው?!» በቁጣ ዓይኖቿን አፈጠጠችበት::

«ዛሬ ከጓደኞቼ ጋር ጉብርኤል ስመጣ ነው ያገኘሁሽ::» አላት አገጮቻቸው በግርምት ሳልተው ጥቂት እርምጃዎች ርቀው ወደሚያዩዋቸው ጓደኞቹ እያየ::

ድንቂ ለመጀመሪያ ጊዜ ጓደኞቹን አስተዋለቻቸውና «እናንተ! የት ታውቁታላችሁ?!» ብላ እነርሱም ላይ አፈጠጠች:: «ልጄ ነው! . . . የኔ ልጅ ነው:: ሂዱ ከዚህ! ጥፉ ከዚህ! . . . ቀጥሉ!. . . ዱርዬ ሁላ! ከነዚህ'ጋ ገጥመህ አይደል እኔን የተውከኝ?»

«ሂዱ! እደርስባችኋለሁ::» አላቸው ተሾመ በእናቱ ሁኔታ እየሳቀ:: ጓደኞቹ ግን ፈገግ እንኳን አላሉም:: የእናትነት ፍቅሯ ያስደነቃቸውን ያህል ቁጣዋም አስፈርቷቸዋል::





«የት ነው የምትደርስባቸው? ቀጥል አንተም ወደ ቤት!» ወደ ጓደኞቹ ዞራ፣«ሂዱ'ኮ ነው ምለው! ቀጥሉ!» አለቻቸው በአመልካች ጣቷ ወደ አስፋልት ወደሚወስደው መንገድ እያመለከተቻቸው::

ጓደኞቹ ተንቀሳቀሱ::

«ሌላ ቀን እመጣለሁ አልኩሽ'ኮ ድንቂ» አለ ተሾመ ፊቱን በፈገግታ ሞልቶ::

«ዝም በል! አታፍርም እንዲህ ስትል? ከስንት ጊዜ በኋላ መጥተህ ሌላ ቀን እመጣለሁ ትላለህ!?» ጭንቅላቱ ላይ በጥፊ መታችውና ወደ ቤታቸው አቅጣጫ ጎተተችው::

እናትና ልጅ መሃል መንገድ ላይ መጓተት ጀመሩ::

«ነገም ቢሆን እመጣለሁ ድንቂ::»

«ስፈልግህ ኖሬ ዛሬ እንዲህ አግኝቼህማ አለቅህም!»

ተሾመ ብዙ ታግሎ ራሱን አስለቀቀና ሮጦ አመለጣት:: ወደ አስፋልት ሲሄድ እንባው በጉንጮቹ እየወረደ ነበር:: ለራሱ ሳይሆን ለእናቱ አዘነላት::

ከዚያች ዕለት በኋላ ተሾመ በየጊዜው እየሄደ እናቱን ይጠይቅ ጀመር:: ታዲያ ከሄደም አባቱ ቤት የሌሉበትን ሰዓት አስልቶ ነበር የሚሄደው::

እናቱን፣ «ድንቂ ይኸው ለቡና ይህችን ፍራንክ'ኮ ልሰጥሽ ነው የመጣሁት::» ብሎ ጥቂት ብሮች ሲያሳያት ብሩን እየተቀበለችው የምሬት ሳይሆን የልማድ ንጭንጯን ትጀምራለች::

«አንተ ዱርዬ'ኮ ነህ! እዚህ ቤት ማስገባትም አልነበረብኝም::»

«አይ ድንቂ!» እያለ ተሾመ ይስቃል::

«ዝም በል! የአባትህን ብር አጥፍተህ ትስቃለህ?!»

ገንዘብ የሌለው ቀን መጥቶ ደግሞ፣ «ድንቂ ርቦኛል:: ባክሽ ምሳ ካለ ስጪኝ!» ሲላት አትጨክንበትም:: ያለውን ታቀርብለታለች::

ተሾመ አልፎ፣ አልፎ ለእናቱ ትንሽ ገንዘብ መስጠቱ ከጎረቤት ወይም ከሌሎች ሰዎች ዘወትር ለሚቀርብለት፣ «ቤት ለምን አትገባም?» የሚል ጥያቄ መልስ ለመስጠት ረዳው::

«ሠርቼ ለእናቴ የቡና መግዣ እሰጣታለሁ» ይላል::

ድንቂ የቡና ሱሰኛ ናት:: ከቤት ከመውጣቱ በፊት እናቱ ቡና ካላገኘች በጣም ስለምትነጫነጭ፣ ተሾመ ይናደድባት ነበር:: አንድ ጊዜ እንዲያውም ቡና መጠጣት እንድታቆም፣ ሳታየው ጀበናና ስኒዎች ሰብሮባት ነበር:: ለጀበናና ስኒ መግዣ ተጨማሪ ወጪ ከመውጣቱ በስተቀር ግን ይህ ሙከራው ድንቂን ቡና ከመጠጣት አላገዳትም::



Sample output to test PDF Combine only

## -16-

*«አባትየው ሳንባ ያማቸዋል። ይተኛሉ፤ ይነሳሉ።»*
*ወ/ሮ የሺ ካሰው*

በቅርቡ አቶ ግርማ ወ/ሮ አሰገደች የተባሉ ሴት ቤት በአትክልተኝነት ተቀጥረው እየሰሩ ነው። በወር መቶ ሃምሣ ብር ይከፈላቸዋል።

ድንቄ አራተኛ ልጅ አርግዛለች። . . .

አቶ ግርማ ሰሞኑን እያሳላቸው ነው።

«ኃይለኛ ጉንፋን ሊይዘኝ ነው መሰል› ይላሉ አፋቸውን በመዳፋቸው ሸፍነው እየሳሉ።

ሌሊትም ሳል ይቀሰቅሳቸዋል። ማታ፣ ማታ በዝንጅብል የተፈላ ሻይ መጠጣት አዘወተሩ። ነጭ ሽንኩርትም በሉበት። አልተሻላቸውም። ለጥቂት ሳምንታት ሳሉ ቀጠሉ። ፊታቸው መክሳትና መገርጣት ጀመረ።

«መጠጥ ይሆን ያባሰብኝ?» ብለው ጠጅ መጠጣት አቆሙ።

ጉንፋን የመሰላቸው ሳል እየባሰባቸው እንጂ እየተሻላቸው አልሄደም። ብርድ ብርድም ይላቸው ጀመር።

«ይሄ ነገር ሳምባ እንዳይሆን እስቲ ለማንኛውም ተመርመር!» የሚሏቸው ሰዎች በዙ።

ወ/ሮ አሰገደች ሊያሳክሟቸው ፈቃደኛ ነበሩ። አንድ ቀን ሐኪም ቤት ሄዱ። በሽታቸው የሳምባ ነቀርሳ (ቲቢ) እንደሆነ ተነገራቸው። መርፌና ኪኒን ታዘዘላቸው። መርፌውን ለአንድ ወር ተወግተው ጨረሱ። ኪኒኑንም መውሰድ አላቋረጡም፣ ግን ሰውነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመነመነ ሄደ። በቂ ምግብ አያገኙም። ቢያገኙም በሽታውን ለመቋቋም የሚያስችላቸው ገንቢ ምግብ አልነበረም። ወ/ሮ አሰገደች ላሞች አሏቸው። አንድ ሊትር ወተት በየቀኑ በነጻ እንዲወስዱ ፈቀዱላቸው። አቶ ግርማ ግን አሁንም በበሽታው መዳከማቸውን ቀጠሉ።

ያሉት የቤተሰቡ አባላት ጠግበው ሳያድሩ፣ኑሯቸው ፈቀቅ ሳይል፣ . . . አንድ ቀን ታደለ የተባለ አራተኛ ሕፃን ቤተሰቡን ተቀላቀለ።

አቶ ግርማ በበሽታቸው ምክንያት አቅም እያነሳቸው ነው። ወደ ሥራ ሲሄዱ ቁልቁለቱ እንኳ፣ ያደክማቸው ጀምሯል። ሲመለሱማ ወደሰፈራቸው በሚወስደው ዳገታማ መንገድ መጓዝ ቀጥ ያለ ገደል የመውጣት ያህል ጭንቅ ሆነባቸው። እንደ ኤሊ እያዘገሙ አሁንም፣ አሁንም መንገድ ዳር ለማረፍ ይቀመጣሉ። ይዘውት የሚመጡት አንድ ሊትር ወተት በየደቂቃው ክብደት እየጨመረ ኩንታል የተሸከሙ ያህል ይከብዳቸዋል።



Sample output to test PDF Combine only



ለበርካታ ደቂቃዎች መንገድ ዳር ቁጭ ብለው ያርፋሉ። ትንሽ ትንፋሻቸው መለስ ሲል ደግሞ ሸቅብ የኤሊ ጉዟቸውን ይቀጥላሉ። ብዙም ሳይራመዱ ሰውነታቸው ይዝላል። ወገባቸውን ይዘው ቆም ይሉና ትንፋሽ ለመሰብሰብ ይሞክራሉ። ለመቀመጫ የሚሆን ድንጋይ ካዩም አረፍ ይላሉ። በፊት በአስርና በአስራ አምስት ደቂቃ የሚወጡት ዳገት፣ አሁን ሰላሳና አርባ ደቂቃ ይፈጅባቸው ጀመር።

አንድ ቀን አመሻሽ ላይ እግሮቻቸውን እየጎተቱ ወደ ቤት ገቡና ከተሰጣበት ገመድ ንፋስ አውርዶ እንደጣለው እርጥብ ልብስ የሚተኙበት ፍራሽ ላይ እንዘጭ ብለው ተቀመጡ። ሲያቃስቱና በረጅሙ ደጋግመው ሲተነፍሱ ቆዩ።

«ምነው? አሞሃል እንዴ?» አመለዘውድ ቆም ብላ ጠየቀቻቸው።

«አመለ አልቻልኩም! እህ! . . . መንገድ ላይ በጣም ስለሚደክመኝ፣ ከነገ ጀምሮ አንቺ ብትሸኚኝ ይሻላል።» አሏት።

«እም፣ ትሸኝህ!» ድንቄ አዲሱን ልጃቸውን ታደለን አቅፋ እንደ ወንበር በሚገለገሉበት የዛፍ ጉቶ ቅርጽ ባለው ድንጋይ ላይ ተቀምጣለች።

ህጻኑ ታደለ ከወ/ሮ አሰገደች ቤት የሚመጣውን ወተት ከአባቱ ጋር እየተጋራ ስለሚጠጣ ሰውነቱ ፋፍቷል።

«እሺ! ምን ችግር አለ? እሸኝሃለሁ።» አለች አመለዘውድ አንድ ጥግ የተጣደ ብረት ምጣድ ላይ ለራት ወደጠፈጠፈችው ቂጣ እተራመደች። «. . . ኧረ ማታም ስትመለስ አስፋልት ጠብቄህ ደግፌህ እመጣለሁ።»

«እም ታምጣህ!» አለች ድንቄ ዞር ብላ ለአፍታ አቶ ግርማን እያየች።

«ጎሽ የኔ ልጅ! ያላንቺ ማን አለኝ። ያ ዱርዬማ እንዲህ ታምሜና ከስቼ፣ እንኳን ሊያስታምመኝ፣ 'አባቴ እንዴት ነህ?' ሊል እንኳ አልመጣ።»

«እሱም አንድ ቀን ወደ ቤት ይመጣል። ሁላችንም አንድ ላይ አብረን እንኖራለን።» አለች አመለዘውድ።

«አዬ! ትምህርት አይወድ። ባይመለስ ይሻላል። ይሄኔ ጫትና ሲጋራ ለምዶ ይሆናል። እህ! . . . ብቻ ሌባ ሆኖ አንዱ እጅ ከፍንጅ ይዞ እንዳይገድለው።»

«ኧረ! እንደዛማ አይሆንም።» አለች አመለዘውድ ድንጋጤና መረበሽ በሚደመጥበት ጎላ ያለ ድምፅ። የምትሰራውን ሥራ ቆም አድርጋ አባቷን አየቻቸው።

«ሌባ መሆኑማ የት ይቀራል?! የዱርዬ መጨረሻ አያምርም።» አለች ድንቄ።

«እሱን ተዪው! ይልቅ እኔ የጤናዬ ነገር ነው ሚያስጨንቀኝ። አህ! . . . እህ!» አሉ አቶ ግርማ እያቃሰቱ።

«አይዞህ! በቃ ከነገ ጀምሮ እኔ እሸኝሃለሁ።» አለች አመለዘውድ።

ጫማቸውን ለማውለቅ እየሞከሩ፣ «እሺ አመለ! . . . እሺ የኔ ልጅ! እህ! . . . ኡህ!. . . እሺ የኔ አመለዘውድ!» አሉ አባቷ ድምጻቸው ውስጥ ለአመለዘውድ ያላቸው ጥልቅ ፍቅር በጉልህ እየተደመጠ።

አመለዘውድ የጫማቸውን ክር ለመፍታት እንዳጎነበሱ ቁና፣ ቁና ሲተነፍሱና ሲያቃስቱ አስተዋለች።

«ቆይ እኔ ልፍታልህ!» አለችና ፈጠን ብላ ከፊት ለፊታቸው ተቀመጠችና የጫማቸውን ክር ፈትታ አወለቀችላቸው።

አቶ ግርማ እያቃሰቱ የመነመኑ እግሮቻቸውን ፍራሹ ላይ ሰቀሉ።

«እንዲያው የእንጀራ ነገር ሆኖብኝ እንጂ ሥራ አቁሜ፣ ቤት ተኝቼ መዋል ነበረብኝ።» እያጉተመተሙ ተጋደሙ።

አመለዘውድ አባቷን ቆም ብላ ቁልቁል አየቻቸው። በጣም ከስተዋል። በሱሪያቸው ውስጥ ጭን ለማለት የሚከብድ አጥንት ነው የሚታየው። የፊታቸው አጥንቶች ወጣ፣ ወጣ ብለው መታየት ጀምረዋል። አንድ አይነት ፍርሃት ልቧን አቋርጦ አለፈ። ግን ከነገ ጀምሮ ወደ ሥራ ሲሄዱና ሲመለሱ አብራቸው እንደምትሆን ስታስብ፣ የሷ እርዳታና ድጋፍ የጤናቸውን ሁኔታ እንደሚያሻሽለው ተስፋ አደረገች።

«አይዞህ!» አለች።

አቶ ግርማ በጭስ በጠቆረው የቆርቆሮ ጣሪያ ላይ የተከሉትን ዓይናቸውን ሳይነቅሉ፣«ይሻለኛል ልጄ!» አሏት ማሰብና መተከዟን አስተውለው።

እንደእውነቱ ከሆነ ግን እንደሚሻላቸውና የድሮ ጤናቸው እንደሚመለስላቸው ተስፋ ማድረግ ጉም ለማቀፍ የመሞከር ያህል የማይታሰብና የማይታለም እየሆነባቸው ነው።



Sample output to test PDF Combine only



# -17-

*«ኡ! እሷ'ንማ ብጣም ነው የሚወዳት! ስለማይችል ትሸኘዋለች፤ ሥራው በታ ታደርሰዋለች። ማታ አስፋልት ዳር ጠብቃ ይዛው ወደ ቤት ትሄዳለች።»*
*ወ/ሮ አበበች ገመቹ*

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት አቶ ግርማ ወደ ሥራ ሲሄዱ ከአልጋቸው ለመነሳት ሲሞክሩ ሰውነታቸው ተሳሰረባቸው።

«ዛሬስ ባልሄድ ይሻላል» ከብርድ ልብሳቸው ውስጥ አጥንትና ቆዳ ብቻ የሆነ እግራቸውን አውጥተው በጭንቀት ተውጠው አጉተመተሙ።

ድንቁና ታደለ በፍራሹ ሌላ ጥግ ተኝተዋል። አመለዘውድ ጭራሮና ቅጠል ይዛ ከውጭ ገባች።

«አመለ! ዛሬስ ከሥራ ልቅር» አሉ አቶ ግርማ። ልክ ቀጣሪያቸውን ፍቃድ የሚጠይቁ ይመስሉ ነበር።

«ለምን? እኔ'ኮ እሸኝሃለሁ» አለቻቸው ጭራሮና ቅጠሉቹን እንደያዘች ፊት ለፊታቸው ቆማ።

«ልሂድ ብለሽ ነው? . . . አሞኛል»

«ምነው? ምን ሆንክ?»

«አሞኛል። ዛሬ ባርፍ ጥሩ ነው።» አሉ ጭንቀት ከፊታቸው እየተነበበ።

«በቃ ወተቱን አሙቄ ልስጥህ»

ጭራሮና ቅጠሉን ምድጃው አጠገብ ጣለችና እሳት ለማቀጣጠል ቁጭ አለች።

ድንቁ ከተኛችበት ቀና ብላ ፊታቸው ላይ ህመምና መረበሽ የሚስተዋልበትን ባለቤቷን አቶ ግርማን አየቻቸው። ከአመለዘውድ ጋር የተነጋገሩትን ሰምታለች።

«ካመመህ ቅራ! ምን ያስጨንቅሃል? አንተ ደህና ከሆንክ ሥራው ነገ ከነገ ወዲያ ይሰራል።» አለቻቸው።

አቶ ግርማ እንዲህ መባል ነበር የሚፈልጉት። ዝም ብለው ሲያስቡ ቆዩና ብርድ ልብሱን ተከናነቡት።

አቶ ግርማ ከሁለት ቀናት በኋላ ሻል ያላቸው ሲመስላቸው፣ ወደ ሥራ ለመሄድ ተነሱ። ከአመለዘውድ ጋር ሆነው መንገድ ጀመሩ። ቀስ እያሉ ነበር የሚያዘግሙት። አመለዘውድ አንዳንዴ ሳታስበው ቀድማቸው ትራመድና፣

ፍጥነቷን ከአባቷ እኩል ለማድረግ ራሷን ገታ አድርጋ ቆም ብላ ትጠብቃቸዋለች።

አቶ ግርማ አስፋልት እስኪደርሱ ሦስት ጊዜ መንገድ ዳር ቁጭ ብለው አረፉ። የሚያውቋቸው የሰፈር ሰዎች በመንገድ ሲያልፉ ሰላምታ ይሰጡዋቸው። አንዳንዶቹም ቆም ብለው ያናግሯቸዋል። መንገዱ ላይ ምንም ሰው ባይኖር ይመኛሉ። ማውራት ራሱ ያደክማቸዋል። እንዲህ ደክመውና ከስተው በመታየታቸው ሀፍረት ይሰማቸዋል። የዝቅተኝነት መንፈስ በአዕምሯቸው ይንሰራፋል።

በፊት ሰዎች፣ «ዋናው ነገር ጤና። ከጤና በላይ ምን አለ?!» ሲሉ እንደተራ አባባል ነበር የሚሰሙት። አሁን አራት፣ አምስት እርምጃ ለመራመድ ጭንቅ ሲሆንባቸው፣ ጤና ከሁሉም፣ ከምንም ነገር በላይ መሆኑ በደንብ ገብቷቸዋል። ጤነኝነትን እጅግ ይናፍቃሉ። ጤነኛ ሆነው በፍጥነት ተራምደው የሥራ ቦታቸው መድረስ፣ የሚቆፈረውን መቆፈር፣ የሚታጨደውን ማጨድ፣ የሚታረመውን ማረም፣ የታዘዙትንና መስራት ያለባቸውን ሁሉ በትጋትና በቅልጥፍና ማከናወን ከሁሉም የላቀ የፈጣሪ ፀጋ መሆኑ ይሰማቸዋል። በመታመማቸው እጅግ ያዝናሉ። ቅስማቸው ሰብር፣ ሞራላቸው ድቅቅ ብሏል።

አርፈው ሲነሱ አመለዘውድ ወገባቸውን በቀጫጭን እጆቿ ደግፋ ታነሳቸዋለች። ደጋግማ፣ «አይዞህ!» እያለች ከአባቷ አጠገብ ቆም ብላ አባቷን ለማበረታታት ትሞክራለች።

ከአስፋልቱ በኋላም የሚቀራቸው መንገድ ረጅም ነው። አብዛኛው መንገድ በታክሲ አርባ አምስት ሳንቲም ተከፍሎ መሄድ ቢቻልም፣ አቶ ግርማ የታክሲ ለመክፈል አቅም የላቸውም። ያላቸው ምርጫ በእግር መሄድ ነውና የሴት ልጃቸውን ቀጭን ትከሻ ደገፍ እያሉ ጥርሳቸውን ነክሰው አዘገሙ።

የአስፋልት መስመሩን ይዘው ሲያዘግሙም በተጨማሪ አራት ጊዜ ያህል መንገድ ዳር ቁጭ ብለው ማረፍ ነበረባቸው። ትንፋሽ ለመሰብሰብ ጥቂት ተራምደው ቆም ለማለትም ይገደዱ ነበር።

«ግን እንደዚህ ሆነህ እንዴት ልትሰራ ነው?» አመለዘውድ ወደ ወ/ሮ አሰገደች ቤት ሲቃረቡ ሃሳብ ገብቷት ጠየቀቻቸው።

«አይ ቢያንስ ውሃ ማጠጣት አያቅተኝም።» አሏት። «ሴትየዋ ቢያዩኝ ደግሞ ጥሩ ነው። ዝም ብዬ መቅረቴ ደግም አይደል።»

ግቢው በር ላይ ሲደርሱ፣ «በይ ሂጂ!» አሏት።





የያዘችውን ባዶ የወተት ማምጫ ዕቃ እየሰጠቻቸው፣ «በኋላ ስንት ሰዓት መጥቼ ልውሰድህ?» ብላ ጠየቀቻቸው። አቶ ግርማ ምሳ ብቻ ሳይሆን ቁርስም ወ/ሮ አሰገደች ቤት በነጻ ስለሚመገቡ ምሳ አይዙም።

«እሥራ አንድ ሰዓት ተኩል ሲሆን አስፋልቱ ዳር ጠጅ ቤቱ አጠገብ ጠብቂኝ።»

«እማማ ልኬ ጠጅ ቤት?»

«አዎ»

«ኧረ እዚህ ድረስ እመጣለሁ።»

«አይሆንም! አይሆንም! እዚያው ጠብቂኝ። እኔ ቀስ እያልኩ እዚያ መድረስ አያቅተኝም።»

«ተው! ግድ የለም! እኔ'ኮ አይደክመኝም።»

«አይሆንም አልኩሽ!» ቆጣ እንደማለት አሉ።

አመለዘውድ ቆማ ታያቸዋለች።

ሆር ብለው አይተዋት፣ «በይ ሂጂ!» አሉ በሩን እያንኳኩ።



Sample output to test PDF Combine only

## -18-

*«በጣም ትመክረኝ ነበር፡፡ በህይወቴ አላማ እንዲኖረኝ፣የጫት፣ የመጠጥ፣ የሲጋራ ሱስ እንዳይዘኝ ትመክረኝ ነበር፡፡ እኔም በእህቴ ምክንያት ጫት፣ መጠጥ፣ ሲጋራ ሳልቀምስ ነው የኖርኩት፡፡»*

*ተሾመ ግርማ*

አመለዘውድ ወደ ቤት ስትመለስ አስፋልት አካባቢ ተሾመን በዓይኗ ፈለገችው፡፡ ያውና! ከአንድ በዕድሜ ብዙም ከማይበልጠው ልጅ ጋር የአንድ ቡና ቤት ግድግዳ ተደግፎ ቆሟል፡፡ ሁልጊዜ ወንድሟን ስታየው ለወራት ተለይታው የቆየች ያህል በጣም ደስ ይላታል፡፡ ወደ እሱ ስትቀርብ አያት፡፡ ከጓደኛው ተነጥሎ ወደ እሷ መጣ፡፡

«ተሼ እንደምን አደርክ?»

ተጨባበጠ፡፡

«ደህና፡፡ ምነው ዛሬ በጠዋት መጣሽ?»

«አባታችንን ወደ ሥራ ቦታ ልሸኘው ብዬ ነው፡፡ ሰሞኑን አሞታል፡፡»

ምንም ሳይል አቀርቅሮ ለአፍታ ዝም አለ፡፡

«ተሺ፣ አባክህ አንተም ብርድ እንዳይመታህ ተጠንቀቅ!» አለችው ፊቷ ላይ ጭንቀት እየተነበበ፡፡ ተሾመም እንዳባቷ ሲሰቃይ ለአፍታ አስባ ነበር የተረበሸችው፡፡

«እኔ ምንም አልሆንም፡፡» አላት ፈገግ ብሎ፡፡ እሷ እናት እሱ ልጅ የሆኑ ያህል ተሰማው፡፡

«ለምንድነው ግን አባታችንን መጥተህ የማትጠይቀው?»

«ብጠይቀውስ ምን አደርግለታለሁ? ተሸክሜ ለዛሬ የምትሆነኝን የማገኝ ኩሊ ነኝ፡፡»

«እንደዚያ አትበል፡፡ አባትህ አይደል እንዴ?! ልጁ ስለሆንክ ይወድሃል፡፡»

«ይወደኛል ብለሽ ነው?» 'ተሳስተሻል አይወደኝም' የሚል መልስ ያዘለ ጥያቄ ነበር፡፡

«አዎ፣ በጣም ይወድሃል፡፡ 'እንዴት ነህ? ተሻለህ ወይ? እግዜር ይማርህ፡፡' እንድትለው ይፈልጋል?»

ተሾመ አቀርቅሮ ዝም አለ፡፡ ፈገግ ያለ ይመስላል፡፡ ፈገግታው የትካዜው መሸፈኛ እንዲሆን ፊልጎ አልተሳካለትም፤ ሙት ፈገግታ ነበር፡፡

«ደግሞ አሁንኮ መጠጣት ትቷል፡፡ ድንቄንም አይደበድባትም፡፡ አሁን እንደ ድሮው ቤታችን አይረበሽም፡፡ አሁን ቤት ተመልሰህ ብትገባ ጥሩ ነው፡፡»

«ስለታመመ ተገዶ ነዋ መጠጣትም፣ እሷንም መደብደቡ ያቆመው፡፡ ሲሻለው እንደገና መጠጣት መጀመሩ ይቀራል?»



Sample output to test PDF Combine only



«እንደዚህ ታሞ ከተሻለው እንኳ ተመልሶ ጠጪ የሚሆን አይመስለኝም፡፡»

«አይመስልሽም?»

«አይመስለኝም!»

«እሺ ታዩያለሽ!»

ይህን ክርክራቸውን ወደደችው፡፡ አባቷ እንደሚሻላቸው እርግጠኛ ሆነው ወይም መስለው ነበር የሚከራከሩት፡፡ ሰሞኑን የአባቷ በጠና መታመም የፈጠረባትን ከበላዩዋ ያለማቋረጥ የሚያንዣብብ የፍርሃት ደመና የሚበታትን ክርክር ሆነላት፡፡

«ተሼ አንተ ግን ሱስ እንዳይዝህ፡፡ መጠጥ፣ ሲጋራ፣ ጫት ንክች እንዳታደርግ! አደራ ተሸዬ!» ጭንቀት ፊቷ ላይ እየተነበበ ክንዱን ይዛ ተማፀነችው፡፡

«ኧረ እኔ ጠጥቼም፣ አጭሼም አላውቅም»

«ጫትስ ትቅማለህ?» ደንግጣ ጠየቀችው፡፡

«ቅሜም አላውቅም፡፡ ከዚህ በፊትስ ነግሬሽ አይደል?!» አላት እየሳቀ፡፡

«ተሼ፣ የመጠጥም ሆነ የሌላ ነገር ሱስ ለማንም አይጠቅምም፡፡ ጓደኞችህ የሚገፋፉህ እንኳ ቢሆን እምቢ በላቸው፡፡ እሺ?»

«ብዙ ጊዜ ነገርኩሽ'ኮ እኔ ምንም ዓይነት ሱስ የለብኝም፡፡»

«እዎ ተሼ፣ መጠጥ፣ ሲጋራ፣ ጫት ንክች እንዳታደርግ!»

«አይዞሽ፤ አላደርግም፡፡»

ሳቅ አለና ፊቱ ላይ ደስ የሚል ፈገግታ እየተነበበ ታናሽ እህቱን በፍቅር አያት፡፡ በእህቱ ሁልጊዜ ደስተኛ ነው፡፡ ይወዳታል፡፡ አልዋሻትም፡፡ መጠጥ፣ ሲጃራና ጫት አምረውት፣ አጓጉተውት ወይም ፈልጓቸው አያውቅም፡፡

አመለዘውድ ፈገግታውን አስተዋለችው፡፡ በጣም አልፎ፣ አልፎ የሚያሳያት ዓይነት ደስ የሚል ልባዊ ፈገግታ ነበር፡፡ በሐዘንና ጭንቀት የተኮማተረውን ልቧን በደስታ ሞልቶ የሚያፍታታ ፈገግታ ሆነላት፡፡ ደስ አላት፡፡ ትንሽ ሲያወሩ ቆይተው ተሰናብታው ወደ ቤት መንገድ ጀመረች፡፡

ባለበት እንደቆመ ከኋላዋ በዓይኖቹ ሸኛት፡፡ በአድናቆትና በአክብሮት ነበር የሚያያት፡፡ ይህቺ ቀጭን እህቱ የቤተሰቡን መከራና ስቃይ ተሸክማለች፡፡ እንደእሱ አልሸሸችም፡፡

እህቱ ሁልጊዜ ትገርመዋለች፡፡ ዓለም ሁሉ ለእሱ ደንታ ቢስ እንደሆነ ሲሰማው፣ ስለአመለዘውድ ማሰብ ያስደስተዋል፡፡ እህቱ ለእሱ ያላት ጥልቅ ፍቅር ወቅቶችና ሁኔታዎች የሚቀይሩትና የሚያላሉት አይደለም፡፡ ሳታየው አታድርም፡፡ ሁልጊዜ ፍቅሯን በተለያየ መልኩ ትገልፅለታለች፡፡

እሱ ለማንም ሳይጨነቅና ሳያስብ ለራሱ የራሱን ሕይወት ብቻ ሲኖር ነበር የሚያስበው:: ታናሽ እህቱ ግን አሁንም በሕይወቱ ውስጥ መመላለሷን ቀጥላለች:: ለቤተሰቡ ግድ የለሽ እንደሆነ ቢያስብም፣ ቢያንስ፣ ቢያንስ በዓለም ላይ አንድ እሱን አጥብቃ የምትወድ፣ በየቀኑ የምትፈልገው እህት ያለችው መሆኑን ሲያስብ ደስ ይለዋል:: አመለዘውድን ይወዳታል፣ እጅግም ያከብራታል::

ብዙ ጊዜ ሲያገኛት ቀዝቀዝ ብሎና ግድ የለሽ ሆኖ ቢቀርባትም፣ አንዳንድ ቀን ቀኑን ሙሉ ሳያያት ከዋለ ስለእሷ ያለማቋረጥ ያስባል:: ፈገግታዋ፣ ፍቅሯ፣ ምክሯ፣ ንግግሯ፣ . . . ሁሉ ነገሯ ይናፍቀዋል:: በዚህ ሕይወቱ ውስጥ ትንሽ ለቤተሰቡና ለራሱም ደህንነት እንዲያስብ፣ ትንሽ ፍቅ እንዲኖረው የምታስገድደው፣ ከልብ የመፈቀርና የመፈለግ ሰዋዊ ጥመ የምታረክለት፣ ከቤተሰቡ ጋር ሙሉ በሙሉ እንዳይቆራረጥ ድልድ፤ የሆነችው አመለዘውድ ናት::

ለማወዳት እናቱ አንድ ወይም ሁለት ብር ሊሰጣት፣ አንድ አፍታም ሊያያት አልፎ አልፎ ቤት ይሄዳል:: ግን እናቱ የጎዳና ህይወቱን በመጨረሻ የተቀበለችው ይመስላል:: እንደ አመለዘውድ ወደ ቤት እንዲመለስ አትወተውተውም:: ልታባብለው አትሞክርም:: እንዲያውም በአልባሌ ምክንያቶች ልትቆጣውና ልትጮህበት ትፈልጋለች:: የዋህ እናቱን መውደዱን ይወደዋል እንጂ ለምን እንደ አመለዘውድ አልተጨነቀችልኝም ብሎ ቅንጣት አይከፋባትም:: ብትጮህበትም እንደምትወደው አሳምሮ ያውቃል::



Sample output to test PDF Combine only



## -19-

*«ያመዋል:: ደካማ ነበር፣ ለመስራት ብዙም አቅም አልነበረውም::*
*ብዙ ጊዜ፣ 'ባለቤቴን አሟታል' እያለ ከሥራ ይቀር ነበር::»*
*ወ/ሮ አስገደች ሉቃስ*

አስራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ነው:: አመለዘውድ አባቷን ለማምጣት ወደ ሥራ ቦታቸው እየተጣደፈች ነው:: አስፋልት መንገዱ ላይ ወደ ቤት ሲመጡ አየቻቸው:: ደክሟቸው፣ ጥውልግልግ ብለው የምታገኛቸው መስሏት ነበር:: ነገር ግን ፣ እርምጃቸውን ቆጥበው ቀስ ብለው ከመራመዳቸው በስተቀር ደህና ናቸው:: ሮጣ አጠገባቸው ደረሰችና ይዘውት የነበረውን ወተት ተቀበለቻቸው::

«እንዴት ነህ?»
«ሰላም ነኝ ልጄ:: ምንም አልልም::»
«ሥራ ሰራህ?»
«የሚሽከረከር ውሃ ማጠጫ አለ እሱን ከቦታ ቦታ እያንቀሳቀስኩ ውሃ ሳጠጣ ዋልኩ:: ሴትየዋ ትንሽ እረፍት እንዳደርግ ፈቅደውልኛል:: መቼም የተባረኩ ናቸው::» አሉ:: 'ሴትየዋ' ያሉት አሰሪያቸውን ወ/ሮ አስገደችን ነው:: ዛሬ እንዲህ የጠነከሩትና ሻል ያላቸው የመሰሉት፣ የወ/ሮ አስገደች ደግነት ብርታትና ኃይል ሰጥቷቸው ነው::

ወገባቸው ላይ አቅፋ ደገፍ እንደማድረግ ስታደርጋቸው፣ «ምንም አልልም:: አቀበቷ ስንደርስ ትደግፊኛለሽ:: ካሁን በኋላ መታጠፊያው ላይ አስፋልቱ ዳር ከጠበቅሽኝ ይበቃል:: እዚህ ድረስ መምጣት አልነበረብሽም::» አሏት::

«እሺ አሁን ልደግፍህ!»
«ግድ የለም ልጄ! አሁን ድጋፍ አያስፈልገኝም::» ጭራሮ እጇን ከወገባቸው አላቀቁ::

አባትና ልጅ ቀስ እያሉ አዝግመው፣ ከዋናው አስፋልት ተገንጥለው ወደ ቤታቸው የሚወስደውን የገረጋንቲ መንገድ እንደጀመሩ፣ አቶ ግርማ ድካም ተሰማቸው::

«ትንሽ ልረፍ» አሉና መንገዱ ዳር ድንጋይ ላይ ተቀመጡ::

ዳገቱን ገና ሲያስቡት ይደክማቸዋል:: ደሳሳ ቤታቸው ከብዙ ድካምና ጥረት በኋላ የምትገኝ፣ የምትታይ፣ የምትጨበጥ ዓይነት መንግስተ ሰማያት ትሆንባቸዋለች:: እጅግ የደከመ የማራቶን ሯጭ የውድድሩን የመጨረሻ መስመር እንደሚናፍቅ፣ ቤታቸው ትናፍቃቸዋለች::

ተነስተው መንገድ ሲጀምሩ አስፋልት ዳር ያየችባቸው ጥንካሬ እንደሸሻቸው አመለዘውድም አስተዋለች። በእርግጥ ዳገቱ ይረብሻቸዋል። ህመም ብቻ ሳይሆን ፣ 'እንዴት ነው ይህን አቀበት የምወጣው? . . . በቃ ሊያመኝ ነው።' የሚል ፍርሃትም ያደክማቸዋል።

«አይዞህ!» አለች አመለዘውድ እንደ ቅድሙ ወገባቸውን እየያዘች።

አባትና ልጅ ቀስ እያሉ ተጓዙ። አንድ፣ ሦስቴ ማረፍ ነበረባቸው። አጠገባቸው ቆማ ወይም ተቀምጣ በትዕግስት ትጠብቃቸዋለች። አቶ ግርማ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዛሬ የልጃቸው መኖር የሰጣቸው በራስ መተማመን ነበር። የሷ መኖር አረጋጋቸው፣ አበረታታቸው። የዛሬው ፍርሃታቸው እንደ ሌሎች ቀናት ከባድ አልነበረም። ቀጭኗ ሴት ልጃቸው እሳቸውን ለመደገፍ ብዙም አቅም ባይኖራትም፣ 'ደክሞኝ ወይም አዙሮኝ እወድቅ ይሆን? ስወድቅስ ማን ያነሳኛል?' ከሚል ስጋትና ጭንቀት ገላገለቻቸው። አቅም አንሷቸው ቢወድቁ፣ ሮጣ ሰው መጥራት አያቅታትም። አመለዘውድም የምትወዳቸውን አባቷን በማጀቧ የዕርካታ ስሜት ተሰምቷታል።

ቤት ሲደርሱ ድንግዝግዝ ብሎ ነበር።

አቶ ግርማ ሲያማቸው ከሥራ እየቀሩ፣ ሲሻላቸው እየሄዱ ጥቂት ወራትን አሳለፉ። ሥራው ከእሁድ እስከ እሁድ ያለዕረፍት የሚሠራ መሆኑ በየጊዜው ለሚታመሙት ለአቶ ግርማ እጅግ ፈታኝ ሆኖባቸዋል። ሁልጊዜ «አመመኝ» የሚል ምክንያት ሰጥተው መቅረት ስለሚከብዳቸው አንዳንዴ፣ «ባለቤቴ የሚጥል በሽታዋ ተነስቶባት ነው የቀረሁት» ብለው በሚስታቸው ያሳብባሉ።

ወ/ሮ አሰገደችም አይጨክኑባቸውም። ድንቄ ግን ከስንት ጊዜ አንዴ አልፎ አልፎ ነው የሚጥላት።

«ሳይደግስ አይጣላም» እንዲሉ፣ አቶ ግርማ ወ/ሮ አሰገደች ቤት በ150 ብር የወር ደመወዝ አትክልተኛ ሆነው ባይቀጠሩ ኖሮ፣ ኑሮ ለእሳቸውና ለቤተሰባቸው እጅግ ከባድ በሆነ ነበር። የቀን ሥራ ዛሬ ተገኝቶ ነገ በማይኖርበት ሁኔታ፣ በዚያ ላይ እንዲህ በሽታ ሥጋቸውን በቁማቸው ጨርሶት በአጥንታቸው አስቀርቷቸው፣ ጉልበታቸው ከድቷቸው ከሥራ እየቀሩ ቤት በሚውሉበት ሁኔታ ቤተሰቡ ሲራብ ሁሉ ይችል ነበር።

አቶ ግርማ ወደ ሐኪም መሄድ ባስፈለጋቸው ጊዜ ወ/ሮ አሰገደች ከደመወዛቸው በተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ ያደርጉላቸው ነበር። ሕክምናው ግን ጤናቸውን አልመለሰላቸውም። መድኃኒት ቢወስዱም በቂ ገንቢ ምግብ ስለማያገኙ ሰውነታቸው መመንመኑን ቀጥሏል።





## -20-

*«ስመጣ መጥቶ ጠየቀኝ። . . .ተጎሳቁሏል። ልብሱ ሁሉ አጉል ነው።»*
*ወ/ሮ ማርታ ገብረ ጻድቅ*

አቶ ግርማ ወ/ሮ አሰገደች ቤት በአትክልተኝነት ሲሰሩ፣ ጎረቤት ወደሚገኘው የእነወ/ሮ ማርታ ቤት በየጊዜው ጎራ ይላሉ። አቶ ተክሉ አሁንም እዚያው ነው የሚሠሩት። የወ/ሮ ማርታ አባት አቶ ገብረጻድቅ ከሞቱ ዓመታት ተቆጥረዋል።

አንድ ቀን አቶ ተክሉ ወ/ሮ ማርታ ከሰሞኑ ከአሜሪካ እንደሚመጡ ለአቶ ግርማ ነገሯቸው። ወ/ሮ ማርታና አቶ ደመቀ ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ አንድ፣ ሁለቴ መጥተው ሄደዋል። በደርግ ተወርሶ የነበረው ትልቁ ቤታቸውም ተመልሶላቸዋል። አቶ ግርማ የሚሰሩት ሌላ አካባቢ ስለነበር ከወ/ሮ ማርታ ጋር ለመገናኘት አልቻሉም።

ይመጣሉ በተባሉ ሰሞን አቶ ግርማ አንድ ቀን አቶ ተክሉን ለመጠየቅ ሲሄዱ ወ/ሮ ማርታ እንደመጡ ተነገራቸው። ከኢትዮጵያ ሲወጡ ዕድሜያቸው በአርባዎቹ መጀመሪያ ላይ የነበረው ወ/ሮ ማርታ፣ ከሃያ ዓመታት በኋላ ከአቶ ግርማ ጋር ሲገናኙ፣ ስድሳዎቹን ያጋመሱ አዛውንት ነበሩ።

ወ/ሮ ማርታ አቶ ግርማን ሲያዩዋቸው ደስ አላቸው። ያ ድሮ ትሁት የነበረው ወጣቱ ግርማ አሁንም ከነትህትናው ነበር የጠበቃቸው። እንደ ድሮ ሥራን ጥሩ ምግብ የመብላት ያህል ተሻምቶ የሚሰራው ትጉሁ፣ በቀላሉ የማይደክመው ታታሪ ወጣት ሆኖ ግን አላገኙትም። ያ በሕይወት የተሞላ ወጣት፣ ዛሬ በደካማ፣ ሰውነቱ በበሽታ በተሸረሸረና በተጎሳቆለ፣ የሌሎች ሰዎች ዕርዳታና ድጋፍ በእጅጉ በሚያስፈልገው፣ ነፍሱ በመቃብር አፍ ላይ በምትንገዳገድ ሽማግሌ ተተክቷል።

ወ/ሮ ማርታ ለአዛውንቱ አቶ ግርማ አዘኑላቸው።

«አገባህ እንዴ?» ብለው ጠየቋቸው።
«አዎ፣ አግብቻለሁ። ልጆችም አሉኝ።» አሉ አቶ ግርማ።
«ኑሮ እንዴት ነው?»
አቶ ግርማ አቀረቀሩ፣ «እግዚአብሔር ይመስገን። ምንም አይልም። እዚህ ጎረቤት ነው የምሰራው። ያው ባለቤቴ ያማታል እንጂ . . . »
«ምነው?»
«ይጥላታል።»



Sample output to test PDF Combine only

«የሚጥል በሽታ አለባት!?»

«አዎ፣ እንደሰዉ ሚስት ተሯሩጣ መስራት አትችልም። ያው እኔ በደካማ አቅሜ ሠርቼ በማገኛት ነው ልጆቹን የምናሳድገው።»

«ያሳዝናል» አሉ ወ/ሮ ማርታ።

ወ/ሮ ማርታና ባለቤታቸው አቶ ደመቀ በአሜሪካ እ.ኤ.አ. በ1977 ዓ.ም. ያቋቋሙትን «ፕሮጀክት መርሲ» የተባለ መንግሥታዊ ያልሆነ የዕርዳታ ድርጅት በኢትዮጵያ ሥራ ለማስጀመር ነበር ዋና አመጣጣቸው። ፕሮጀክት መርሲ በተለያዩ ደሀ አገሮች የሚንቀሳቀስ ድርጅት ነው። ለድርጅቱ ሥራ እንቅስቃሴ መሠረት ጥለው ወደ ልጆቻቸውና ወደ ሁለተኛ አገራቸው ወደ አሜሪካ እስኪመለሱ ድረስ አቶ ግርማ በየጊዜው ጎራ እያሉ ይጠይቋቸው ነበር።



Sample output to test PDF Combine only



# -21-

*«አክስቴ ናት ሌሊት ቀስቅሳን አባቴ እንደሞተ የነገረችን።»*
*ሚካኤል ግርማ*

ከጥቂት ወራት በኋላ አቶ ግርማ በአመለዘውድ ድጋፍ እንኳን ወደ ሥራ መሄድ የማይችሉበት ጊዜ መጣ። የአልጋ ቁራኛ ሆኑ።

አንድ ሌሊት ቤተሰቡ በሙሉ ተኝተው ነበር። አዲስ አበባ የምትኖረው የአቶ ግርማ እህት ያን ሰሞን በጣም ስለተዳከሙ ልታስታምማቸው መጥታለች። ሌሊት፣ ሌሊት ውሃ ይጠይቁ ስለነበር እህታቸው ድንገት ነቅታ ያለወትሯቸው ዝም ሲሉ ውሃ ልትሰጣቸው ስትጠራቸው መልስ ነፈጓት።

«ግርማ! . . .ግርማ! . . . ግርማ!»

ብትነቀንቃቸውም አይሰሙም። እንደሞቱ አረጋገጠችና ድንቄንና አመለዘውድን ቀስቅሳ የአቶ ግርማን ሞት እያለቀሰች አረዳቻቸው።

አቶ ግርማ መጠን የለሽ ጉልበት አፍስሰውባት፣ ብዙ ላብ አንጠፍጥፈውባት፣ ትንሽ የሰጠቻቸውን፣ ይህቺን የጨከነችባቸውና የጠመመችባቸውን፣. . . ዓለም ተሰናበቱ። ተምሮ ሰው እንዲሆን ይመኙለት የነበረው የበኩር ልጃቸው ባልጠበቁት ሁኔታ የጎዳና ተዳዳሪ ሆኖባቸው፣ የሚሳሱላትን ሴት ልጃቸውን አስተምረው ወግ ማዕረጓን ሳያዩ፣ በልጅ አቅሟ የዋለችላቸውን ውለታ ሳይመልሱ፣ ትንንሾቹ ልጆቻቸው ገና ትምህርት ቤት መሄድ እንኳን ሳይጀምሩ . . . ብዙ ማድረግ እንዳለባቸው እያሰቡ፣ ምንም ያደረጉ ሳይመስላቸው፣ በኑሯቸው ሳይረኩ፣ በህይወታቸው የመጨረሻ ምዕራፍ በዚህች ዓለም መኖራቸው ሌሎች አራት ነፍሶችን ወደ ስቃይ ለማምጣት እንደሆነ እያሰቡ የጥፋተኝነት ስሜት ልባቸውን እንደቆፋፈረው፣ ለቤተሰባቸው ከደሳሳ ቤታቸውና ከግቢው በስተቀር ምንም ቅርስና የገቢ ምንጭ ሳይተዉ . . . ሞቱ።

አመለዘውድ ሞታቸውን ለመቀበል የሚያስገድድ ስቃይና ህመማቸውን፣ አጥንትና ቆዳቸው ብቻ ለአፈር እስኪቀር መመንመናቸውን በቅርብ ሆና አይታለችና አባቷ ሊሞቱ እንደሚችሉ አስቀድማ ተረድታለች። ያም ሆኖ ግን ሐዘኗ መሪር ነበር። ቀደም ሲል በአባቷ ስቃይና ህመም ታዝን ነበር። አሁን ደግሞ ለዘለዓለም ስለተለዩዋት እጅግ አዘነች። ደሳሳ ቤታቸው ብቻ ሳይሆን ሰፊ ግቢያቸውንም ሞልቶና አጨናንቆ የሚታያት የአባቷ ግርማ ዳግመኛ እንደማይታያት ስታስብ ዕንባዋን አፈሰሰች። የአባቷን ድምጽ ዳግመኛ ላትሰማ፣ የአባቷን ፍቅር ዳግመኛ ላታጣጥም፣ የአባቷ ቁጣ ዳግመኛ ከጥፋቷ ላይመልሳት፣ የአባቷ አይዞሽ ባይነት ዳግመኛ ላያበረታታት፣ በአባቷ ምክር

ዳግመኛ ላትጠቀም. . . ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለተለዩዋት አምርራ አለቀሰች። ህመምና ስቃያቸውን እያስታወሰች አነባች።

አቶ ግርማ የዕድር አባል ስለነበሩ በዕድሩ የበላይ ተቆጣጣሪነት ድንኳን ተጥሎ፣ ወንበር፣ የመመገቢያና የመጠጫ ዕቃዎች ቀርበው የሐዘኑ ተካፋዮች በጥሩ ሁኔታ ተስተናገዱ። ቀብራቸው ከቤታቸው አቅራቢያ ባለው ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ሲፈጸም፣ ከቤተሰባቸው፣ ከእህታቸው፣ ከወዳጅና ጎረቤት፣ በሩቅ ከሚያውቋቸው ግለሰቦች በተጨማሪ የዕድሩ አባላትም የተገኙበት ስለነበር ከማንም የማያንስ በርካታ ሰዎች የታደሙበት ቀብር ነበር። ዕድሩ የማይሸፍናቸውን ወጪዎች ወ/ሮ አሰገደች ከ300 ብር በላይ አውጥተው በመሸፈናቸው ደንብና ባህሉ የሚፈቅድው የቀብር ሥነስርዓት በተሟላ ሁኔታ ተደረገ።

የአቶ ግርማ ደመወዝ ትንሽም ብትሆን የቤተሰቡ ብቸኛ ገቢ ነበረችና ከባለቤቷ ሞት በኋላ ድንቄ በአስጨናቂ ሁኔታ ውስጥ ራሷን አገኘችው። ልጆቹ ከአቶ ግርማ እህት በስተቀር ዘመድ የላቸውም። አክስታቸውም የራሷ ቤተሰብ ያላት፣ ከራሷ አልፋ ለሌላ ሰው የማትተርፍ ነች። ለተወሰኑ ቀናት እየተመላለሰች ጠየቀቻቸው። ድንቄ በሷ መምጣት ደስተኛ አልነበረችም። አንዳንድ ሰዎች፣ «ጠጋ፣ ጠጋ የምትልሽ መሬትሽን ልትነጥቅሽ ነው።» ብለው ስለመካከሯት፣ አቶ ግርማ ትተውት የሄዱትን ትልቅ ንብረት፣ ደሳሳዋ ቤት ያረፈችበትን ቦታ የምትቀራመታቸው ስለመሰላት ፊት ነሳቻት። በዚህ ምክንያት የአቶ ግርማ እህት ቤታቸው መምጣት አቆመች። ጠፋች፣ ጠፋች።

ወ/ሮ አሰገደች ቤተሰቡ ምንም ገቢ እንደሌለው ሲሰሙ ድንቄን፣ «አይዞሽ! እኔ እረዳችኋለሁ።» ብለው አጽናኗት።

እንዳሉትም በየወሩ ለቤተሰቡ የጤፍ ዱቄት፣ ሽሮ፣ በርበሬ . . . በመኪና ይልኩላቸው ጀመር።

አባቱ ሲሞቱ «ወፌ ቆመች!» ይባልለት ለነበረው ለሕፃኑ ታደለ፣ ወ/ሮ አሰገደች ወተት እንዲሰጠው ፈቀዱ። አመለዘውድ በየቀኑ ወ/ሮ አሰገደች ቤት እየተመላለሰች ወተት ታመጣለች።



Sample output to test PDF Combine only



## -22-

*«ወ/ሮ አሰገደች ለአምስት ወር ያህል ረድታቸዋለች።»*
*አቶ መሃመድ ሳኒ (የአቶ ግርማ የሥራ ባልደረባ)*

ወ/ሮ አሰገደች ለአምስት ወር ያህል ቃል በገቡት መሰረት ለቤተሰቡ አስፈላጊ የሆነውን ምግብ ሲያቀርቡ ቆዩ። ድንቄ ከባሏ ሞት በኋላ ራሷን ጣል፣ ጣል ማድረግ ጀምራለች። ንጽህናዋን አትጠብቅም። ያደፈ ልብስ ለብሳ ወ/ሮ አሰገደች ቤት ስትሄድ፣ «ልብስሽን እዚሁ እጠቢ። ገላሽንም ታጠቢ!» ብለው ንጽህናዋን እንድትጠብቅ ይመክሯታል።

ወ/ሮ አሰገደች የሚያደርጉላትን ዕርዳታ ድንቄ እንደ ውለታ ቆጥራ ሌሎች የባህርይ ለውጦች እንድታሳይ፣ ቢቻል እንደ እሳቸው የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ እንድትሆን ይመኙ ነበር። ድንቄ ብዙም ምክራቸውን የምትሰማ አልሆነችም። ጭራሽ አንድ ቀን ወይዘሮዋን ኃይለ ቃል ተናገረቻቸውና ተበሳጩባት። «ባጎረስኩ እጄን ተነከስኩ» እንደሚባለው፣ ለጽድቅ ስራቸው ምስጋና-ቢስ እንደሆነች ያሰቡት ወ/ሮ አሰገደች ወርሃዊ እርዳታቸውን አቋረጡ።

ባልታሰበና ባልተጠበቀ ጊዜ ቤተሰቡ ከባድ ችግር ውስጥ ወደቀ። ገንዘብ ለማግኘት መስራት የግድ ሆነ።

.ኮተቤ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ከፍተኛ የውሃ ዕጥረት አለ። በተለይ ቤተ-ሠሪዎች ውሃ በብዛት ስለሚያስፈልጋቸው ውሃ የሚያመላልስላቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል። ሌላ ሥራ ማግኘት ያልቻሉ ደሆች ይህን አድካሚና አሰልቺ ሥራ ለመስራት ይገደዳሉ። ድንቄም ውሃ ማመላለስ ጀመረች። ልብስም ለጎረቤት ሰዎች እየተከፈላት ታጥባለች። አልፎ አልፎም ከሰፈሩ ማዶ ከሚገኝ ጫካ እንጨት እያመጣች ትሸጣለች። ያም ሆኖ ጤፍ ለመግዛት አቅም ጠፋ። የእንጀራ ምጣዳቸው ግድግዳ ተደግፎ፣ በአቧራ ተሸፍኖ መዋል ጀመረ። ምድጃና ማሰሻ ናፈቁት።

ድንቄ ውሃ አመላልሳ፣ እንጨት ሸጣና ልብስ አጥባ በምታገኘው ብር በአብዛኛው ባቄላ ትገዛለች። ባቄላውን በብረት ምጣድ ቆልታ ትቀቅለዋለች። የልጆቿ ዋነኛና የዘወትር ምግብ አሹቅ ሆነ። ያገኘች ዕለት ሰፈር ውስጥ የሚጋገር ሸልጦ ትገዛለች። አንዳንዴ ሁኔታዎች ከተመቻቹ ወጥ ሠርተው ዳቦውን በወጥ ይበሉታል።

ድንቄ ውጪ ስትሰራ ስለምትውል፣ ግማሽ ቀን እየተማረች፣ በግማሹ ቀን ደግሞ የቤቱን ስራ የመስራትና ታደለን የመንከባከብ ኃላፊነት የአመለዘውድ ሆነ። ድንቄ የምታመጣው በቂ ስላልሆነ፣ ብዙ ጊዜ ይራባሉ። በቀን አንዴ ለመብላትም የማይችሉባቸው ቀናት ነበሩ። የእናቷ ጥረት ቤተሰቡን ለማስተዳደር በቂ ሊሆን እንዳልቻለ አመለዘውድ ተረዳች። አሁን

ሥራ ለመስራት እናቷን ማስፈቀድ አላስፈለጋትም፡፡ ችግር ዓይኑን አፍጥጦ መጥቷል፡፡

አስፋልት አካባቢ ከሚገኝ እሷ «ቡርቴ» ከምትላት ሴት ቤት ግማሽ ቀን መስራት ጀመረች፡፡ ቡርቴ አንድ የወንዶች ፀጉር ማስተካከያ ቤት ከፍታ ከወጣት ሴት ልጇ ጋር ፀጉር ያስተካክላሉ፡፡ አመለዘውድ ለቡርቴ ቤተሰብ ዕቃና ልብስ ታጥባለች፣ በቅርብ ከሚገኝ ቦኖ ውሃ ታመጣለች፣ ትላላካለች፣ ፀጉር ቤቱን ታጸዳለች፡፡ ቤት ለምሳ ብቅ ከማለቷና ምሽት ላይ ለአዳሯ ከመምጣቷ በስተቀር፣ ከት/ቤት ውጪ ውሎዋ ቡርቴ'ጋ ሆነ፡፡

ማታ ቡርቴ የምትሰጣትን ምግብ ይዛ ወደ ቤት ትገባለች፡፡ ምግቡ በአብዛኛው ከቡርቴ ቤተሰብ የተራረፈ፣ የተቆራረሰና ወጥ የነካካው እንጀራ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ከሳሙና መግዣነት የማያልፍ አንድ ወይም ሁለት ብር ይሰጣታል፡፡

አመለዘውድ የአስር ዓመት ልጅ ናት፡፡ የሷ ድካምና ጥረት ቤተሰቧ እንዳይራቡ ከማድረግ ያለፈ በኑሯቸው ላይ ያመጣው ለውጥ አልነበረም፡፡ ከአቶ ግርማ ሞት በኋላ፣ በተለይ ደግሞ የወ/ሮ አሰገደች ድጋፍ ከተቋረጠ ወዲህ፣ ወደ ባሰ የድህነት አዘቅት እየተምዘገዘጉ ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግቢው ውስጥ ካሉት ባህር ዛፎች መካከል አንድ ወይም ሁለት አስቆርጠው ከሸጡ ብቻ ነበር ቤታቸው እንጀራ የሚጋገረው፡፡

የኤሌትሪክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ነበሩ፡፡ የአንድ አምፖል የኤሌትሪክ አገልግሎት ክፍያ በወር አራትና አምስት ብር መክፈል እንኳን አቅቷቸው መስመሩ ተቆረጠ፡፡ ለኩራዝ ተዳረጉ፡፡ ወርሃዊ የዕድር ክፍያም መክፈል ስላልቻሉ ዕድሩ ከአባልነት ሰረዛቸው፡፡

ለልጆች ልብስና ጫማ መግዛት የሚታሰብ አልነበረም፡፡ ሚካኤልና ታደለ በባዶ እግራቸው ነበር የሚሄዱት፡፡ በኮተቤ አካባቢ ድህነታቸው የተመሰከረ ምስኪን ቤተሰቦችን የሚደግፍ ብርሃነ ሕይወት የተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት ልብስና ጫማ በዓመት አንድ ጊዜ ባይሰጣት ኖሮ አመለዘውድም በታረዘች ነበር፡፡ ድርጅቱ ካለው ከፍተኛ የተረጂ ቁጥር አንጻር፣ ከቤተሰቡ ልጆች እሷን ብቻ ነበር የሚያለብሳት፡፡

የኑሯቸው ቀዳዳዎች መብዛት ሳያንስ፣ በክረምት የቤታቸው ጣሪያ ማፍሰስ ጀምሯል፡፡ ድንቄ ላስቲክ ከላይ አንጥፋ ድንጋይ ብትጭንበትም በየጊዜው ያንጠባጥባል፡፡ ድንቄ ላስቲኩን እያስተካከለች ተጨማሪ ድንጋይ ትጭንበታለች፡፡





## -23-

*«ህጻኑ ከስር ነበር፡፡ ድንቄ እንጨቱ ፊቷ ላይ ሆና ህጻኑን ላይ ወድቃበታለች፡፡»*
*ወ/ሮ አለምአገኝ ካሳሁን*

አንድ ቀን ጥቂት የነድንቄ ሰፈር ሴቶች ወደ ቤት ሲመጡ ሰፈራቸው አቅራቢያ ካለው አቧራማ መንገድ ዳር ጥቂት ልጆች የሆነ ነገር ከበው ሲመለከቱ አስተዋሉ፡፡ ምርር ብሎ የሚያለቅስ ሕፃን ለቅሶም ተሰማቸው፡፡ ሴቶቹ ልጆቹ አጠገብ ሲደርሱ፣ ቦይ ውስጥ አንዲት ሴት ወድቃ አዩ፡፡ የወደቀችው ሴት ሕፃን ማዘሏን ሲያስተውሉ ደነገጡ፡፡ ጭራሽ ድንቄ መሆኗንና ያዘለችው ሕፃን ደግሞ የመጨረሻ ልጇ ታደለ መሆኑን ሲረዱ ተሸበሩ፡፡

«ውይ ድንቄ ናት እንዴ?! . . . እሷ ናት እንዴ?!» ሴቶቹ ተንጫጩ፡፡

ድንቄ በጀርባዋ ስለወደቀች ታደለ ላይ ተኝታበታለች፡፡ በጭንቅላቷ ተሸክማው የነበረ እንጨት ፊቷ ላይ በከፊል አርፏል፡፡ ሴቶቹ እንጨቱን ከላዩዋ ላይ አንስተው ህጻኑን ከስሯ አወጡት፡፡

እናቱ የሚጥል በሽታዋ ተነስቶባት ስለወደቀችበት ታደለ ተጎድቷል፡፡ ራቁት የህጻን ባቶቹ ተጫጭረዋል፡፡ እናቱና የተሸከመችው እንጨት ተጭነውት ከመሬቱ ጋር አጣብቀውት ነበር፡፡ በሴቶቹ እቅፍ ውስጥ ከገባም በኋላ ታደለ ህመሙን በእሪታው መግለጹን አላቆመም፡፡

«አይዞህ! አይዞህ! በቃ! በቃ! ተርፈሃል!» እያሉ አባበሉት፡፡
«እንደው እኮ እግዚአብሔር ነው ያወጣው! ተጨፍልቆስ ቢሞት?!»

ሴቶቹ ለጥቂት ደቂቃዎች ህጻኑን እያባበሉ ድንቄን ጠበቋት፡፡

ድንቄ ወደ አንድ አቅጣጫ ሽርተት፣ ሽርተት እያለች በዝግታ ትንቀሳቀሳለች፡፡ ዓይኖቿ መክፈት የሚችሉትን ያህል ተከፍተው ወደ ሰማይ ፈጠዋል፡፡ ቶሎ የምትነቃ አልነበረችም፡፡ ሴቶቹ የሚያለቅሰውን ህጻን እያባበሉ ወደ ቤት ወሰዱት፡፡

የከበቧት ሰዎች፣ «ምንድን ነው የሚያነቃት? . . . ክብሪት እንፈልግ እንዴ? . . . ውሃ ብንረጫት ይሻላል?» ሲባባሉ ድንቄ ድንገት ዓይኖቿ በትክክል ማየት ጀመሩ፡፡ ዙሪያዋን የቆሙትን ሰዎች ግራ ተጋብታ አስተዋለቻቸው፡፡

«ነቃች! . . . ነቃች!»
«የት እንዳለች አላወቀችም፡፡ ምስኪን!»
«አይዞሽ ድንቄ!»



Sample output to test PDF Combine only

ፊቷ ላይ ድካም ይነበባል:: ለመነሳት ሞከረች፤ ግን አቅም ስላነሳት ተመልሳ ወደ ኋላ ዘንፈል አለች::

ሁለት ሰዎች ደጋግፈው አነሷትና ቆመች::
«አረፍ ትበል!» አሉ::
ዞር ስትል በልጥ የታሰረውን እንጨት ከጎኗ ወድቆ አየች:: ልጇን አዝላ እንደነበር ትዝ አላት::

ድንጋጤና ፍርሃቷን በሚገልጽ ድክም ባለ ድምጽ፣ «ልጄስ?» ብላ ጠየቀች::



Sample output to test PDF Combine only



## -24-

*«ስንፈጠርም ተበድለን እንደተፈጠርን አመንክ::»*
*ተሾመ ግርማ*

አመለዘውድ ከሥራ ጋር ትምህርቷን ቀጥላለች:: ድንቄ ለበርካታ ወራት ውሃ ማመላለሱን እየሠራች ቆየች:: አንድ ጊዜ ግን ውሃ በጄሪካን የምትሸከምበት ጀርባዋ አልማዝ ባለጭራ በሚባል በሽታ ስለቆሰለ ውሃ የማመላለሱን ሥራ ለማቆም ተገደደች::

ታማ በሰነበተችባቸው ሳምንታት እሷን የማስታመምና ታናናሽ ወንድሞቿን የመንከባከብ ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ በአመለዘውድ ትከሻ ላይ አረፈ:: አመለዘውድ ከዕድሜ ዕኩዮቿ ያነሰ ደቃቃ ሰውነት ቢኖራትም፣ ችግርና ተፈጥሮ ስላበሰሏት፣ ኃላፊነቱን በጠባብ የልጅ ትከሻዋ ተሸከመችው:: ቤተሰቡ ቢያንስ በቀን አንዴ እንዲመገብ ትሯሯጣለች:: ከቡርቴ ጋር የምታመጣው ምግብ ብዙ ጊዜ ለቤተሰቡ አይበቃም:: እንደዚህ ባሉ ቀናት ተሾመን ፍለጋ ትሄዳለች:: ተሾመ ካለው እነሱን ከመርዳት ወደኋላ አይልም:: ለቤተሰቡ የሚያደርገው መልካም ነገር ያረካዋል፣ በጣም ያስደስተዋል::

በኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ካፍቴሪያ ከተማሪዎች የተረፈ ምግብ አስር ሳንቲም በሚሸጥ ስስ ፌስታል ተሞልቶ አንድ፣ አንድ ብር ይሸጣል:: ተሾመ ኮሌጁ ውስጥ ገብቶ አንድ ወይም ሁለት ፌስታል ምግብ ገዝቶ ለአመለዘውድ ይሰጣታል:: ብዙ ጊዜ ትርፍራፊ ምግቡ የሚሸጠው ተማሪዎቹ ራት ከበሉ በኋላ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ገደማ ነው:: አመለዘውድ ያንን ምግብ ከወንድሟ ተቀብላ ወደ ቤት ትገሰግሳለች:: ጨለማው ስለሚያስፈራት ተሾመ ከግማሽ መንገድ በላይ ሄዶ ይሸኛታል:: እናቷ ሻል ካላት በኋላ ደግሞ ከእናቷ ጋር እስከ አስፋልት ይመጡና ድንቄ አንድ ጥግ አስፋልት መንገዱ ዳር ትጠብቃታለች:: ከተሾመ ምግቡን ከተቀበለች በኋላ እናትና ልጅ አብረው ወደ ቤት ያዘግማሉ:: ከትርፍራፊ ምግቡ ወጥ የነካካውን እና ጸዳ፣ ጸዳ ያለውን በልተው፣ ደረቁንና ለዓይን ብዙም ደስ የማይለውን በማግስቱ ፀሐይ ላይ ያስጡታል:: ድርቆሽ ያደርጉትና ቤት ውስጥ ምግብ በሌለ ቀን ፈትፍተው ይበሉታል::

ተሾመ አዘውትሮ ይህን ምግብ ይገዛላቸው ጀመር:: ሰሞኑን ጥሩ ገቢ እያገኘ ነው:: እዚያው ኮተቤ አካባቢ በማኅበር የተደራጁ ሰዎች ለሚሰሯቸው ቤቶች ግንባታ ሲሚንቶና ብሎኬት ከመኪና እያወረደ በሳምንት እስከ ሰማኒያ ብር ያገኛል:: ከጓደኞቹ ጋር ቤት ተከራይቶ መኖርም ጀምሯል:: አባቱ ከሞቱ በኋላ ወደ ቤት እንዲገባ አመለዘውድ ብትወተውተውም ፈቃደኛ አልሆነም::

አንድ ምሽት ተሾመ ከኮተቤ መምህራን ኮሌጅ ሁለት ፌስታል ምግብ ገዛ:: አመለዘውድ ብቻዋን ነበረች:: እሷን መሸኘት ስለነበረበት ምግቡን ይዞ እያወሩ የቤታቸውን መንገድ ተያያዙት::

«አንተና ጓደኞችህ ቤት ከመከራየታችሁ በፊት በቃ ደጅ ነበር የምታድሩት?» አመለዘውድ ጠየቀችው::

«አዎ፣ ነግሬሽ አይደል?»

«ብርዱን እንዴት ትችሉታላችሁ?»

ፈገግ አለ:: «የማይለመድ ነገር የለም::»

«እንዲያው አንድ ቀን ምርር ብሎህ፣ 'አሁንስ በቃኝ ወደ ቤት ልመለስ' ያልክበት ጊዜ የለም?»

«አለ:: ለምን አይኖርም?»

«እንዲህ የተማረርክበትን ቀን እስቲ ንገረኝ!» በጉጉት ቀና ብላ አየችው::

«ምን ያደርግልሻል?»

«ንገረኝ በናትህ!»

ተሾመ በረጅሙ ተንፍሶ ዝም አለ::

«ንገረኝ!»

«አንድ ጊዜ» ብሎ ጀመረ:: «ሌሊት ሰውነቴን የሆነ ነገር ሲነቀንቀኝ ተሰማኝና ከእንቅልፌ ነቃሁ:: ለካ ጎርፍ ላይ እየተንሳፈፍኩ ነበር::»

«የምን ጎርፍ? የት ተኝተህ ነው?» አለች አመለዘውድ ግራ ተጋብታ::

«ዶፍ ዝናብ እየዘነበ ነበር:: ባስ ፌርማታ ውስጥ ከጓደኞቼ ጋር ተኝቼ ነበር:: እነሱ ምኑንም፣ ምኑንም ወሳስደው እንደ ሬሳ ተጋድመዋል:: መነሳት ብፈልግም ከበደኝ:: ጎርፉ ውስጥ የተኛሁበት ጎኔ በብርድ ደንዝዞ ነበር::»

«ወይኔ ተሼ!» አለች አመለዘውድ ቆም ብላ በአንድ እጇ ራሷን ይዛ::

«ከጎርፉ ውስጥ እንደምንም ተነሳሁ:: በጣም በረደኝ:: 'ምነው ከቤት ባልወጣሁ ኖሮ' ብዬ አለቀስኩ:: ተጸጸትኩ:: 'እዚህ ከምሞት የማልታወቅበት አገር ሄጄ ብሞት ይሻላል' ብዬ አሰብኩ:: በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ከዚህ አካባቢ መጥፋት እንዳለብኝ ወስኜ በሃምሳ ሰባት ቁጥር አውቶቢስ ተሳፍሬ ለገሃር ሄድኩ::»

«የት ልትሄድ?»

«በቃ አንዱ አገር በባቡር ልሄድ አስቤ ነው::»

«እሺ ከዚያስ?»

«በባቡር ተንጠልጥዬ ጉዞ ጀመርኩ:: ሌሎች እንደ እኔ ባቡሩ ላይ ተንጠልጥለው የሚሄዱ ልጆችም ነበሩ:: መንገድ ላይ አንድ ልጅ የያዘው ብረት በድንገት አሚልጮት ባቡሩ ስር ገባ:: ባቡሩ ሲበላው አየሁ:: በጣም ዘገነነኝ::»

«እንዴት? በቃ ጨፈለቀው?» አመለዘውድ የሰማችውን ማመን አልቻለችም::



Sample output to test PDF Combine only



«አዎ፣ . . . ከታተፈው ብልሽ ይሻላል::» አለ ተሾመ ሐዘን በሚደመጥበት ድክም ያለ ድምጽ::

«ውይ እንዴት ያሰቅቃል!» አለች አመለዘውድ በሁለት እጆቿ ራሷን ይዛ::

«አዎ በጣም! . . . በጣም ነበር የዘገነነኝ!»

«እሺ ከዚያስ?»

«ወደ ሌላ ቦታ የመሄዱን ሃሳብ ተውኩት:: ባቡሩ የሆነ ከተማ ላይ ሲደርስ ወርጄ በሌላ ባቡር ተንጠላጥዬ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ::»

«ምነው ግን ተሼ ይህን ሁሉ መከራ ከምታይ ከቤት ባልወጣህ ኖሮ::»

«አዎ፣ ከቤት ውጪ ስትኖሪ ብዙ ከባድ ችግሮች ያጋጥሙሻል::»

«ሌሎቹ ልጆች ግን ለምንድነው ከቤት የሚወጡት?»

«ብዙ ምክንያት አለ:: ወይ እናትና አባታቸው ሞተዋል:: ወይም ቤተሰቦቻቸው በጣም ደሃ ስለሆኑና ስለሚርባቸው ሠርተውም ሆነ ለምነው ለመኖር ይሆናል የሚወጡት:: አንዳንዶቹ ደግሞ እንደኔ አባትና እናቶቻቸው በየቀኑ ሲጨቃጨቁና ሲጣሉ ማየት የሰለቻቸው ናቸው::» ለአፍታ ዝም አለ:: « . . . ሌላም መአት ሺ ምክንያት ሊኖር ይችላል::»

አመለዘውድ አቀርቅራ ስትተክዝ ቆየችና፣ «እኔ ግን ምን እንደምመኝ ታውቃለህ?» አለችው::

ዞር ብሎ አያት::

«ወደፊት ተምሬ ትልቅ ስሆን ድርጅት አቋቁሜ እናትና አባት የሞቱባቸውን ህጻናት ሰብስቤ ማሳደግ እፈልጋለሁ::»

በጨረቃ ብርሃን ፊቷን በደንብ አየው:: ድምጿ ውስጥ የሰማውን እርግጠኝነት ፊቷ ላይም አነበበው:: ልቧ ትልቅ መሆኑ እጅግ በጣም አስገረመው:: ደስ አለችው::

ሳያስቡት ሰፈር ደረሱ::

«እንዴ ቤት ድረስ መጣሁ አይደል?!» አለ ተሾመ እየተደነቀ::

«እዚህ ደርሰህማ አትመለስም:: ዛሬ ከኛ ጋር ታድራለህ::» አለችው አመለዘውድ::

ተሾመ ጥቂት አመንትቶ እዚያው ለማደር ወሰነ:: እህቱን ተከትሎ ወደ ግቢያቸው ዘለቀ:: ድንቄ ልጇ በመምጣቱ በጣም ተደሰተች:: ሚካኤልም ታላቅ ወንድሙን ሲያይ ደስ አለው:: ትንሹ ወንድማቸው ታደለ ተኝቷል::

ቡና ተፈልቶ ሲጫወቱ አመሹ:: ጨዋታና ወጋቸው ሲደራ ቤቷም ሞቅ፣ ሞቅ አለች:: ተሾመ በህይወቱ እጅግ ከተደሰተባቸው ጥቂት ምሽቶች

የዛሬው አንዱ ነበር። ይህን የቤተሰብ ፍቅርና መተሳሰብ አጥቶ መኖሩ ቆጨው። አመለዘውድም በወንድሟ ቤት መምጣት በጣም ተደስታለች። ከመተኛታቸው በፊት፣ ከዚህ በፊት አይታው የማታውቅ ያህል፣ ተሾመን ደጋግማ በስስትና በፍቅር ታየው ነበር።

ተሾመ ከቤት ከወጣ ጀምሮ እንዲህ እንደ ዛሬው ሌሊት ጥሩ እንቅልፍ ወስዶት አያውቅም። . . .

ሌሊት የሆነ ጓጓታ ሰምቶ ከእንቅልፉ ነቃ። እናቱ የሚጥል በሽታዋ ተነስቶባታል! ደነገጠ። ሁልጊዜ የሚጥል በሽታዋ ሲነሳባት እንደ አዲስ ይረበሻል። ድንቁ ፍራሹ ላይ ጋደም እንዳለች ሰውነቷ በመጠኑ ይወራጫል።

«አመለዘውድ! . . . አመለዘውድ!» ተሾመ እህቱን ተጣራ።

በሩ መከፈቱን አስተዋለ። ገርበብ ብሎ በተከፈተው በር በሚገባው የጨረቃ ብርሃን እናቱ ግንባሯ ላይ መድማቷን አየ። ፊቷን ወደ ግራ እንዲሁም ወደ ቀኝ ዞር፣ ዞር ስታደርገው የሆነ ነገር እንደገጫት ተረዳ። ከድንቁ አጠገብ በግድግዳው በኩል ትራስ ተቀምጧል። እህቱ ቤት ውስጥ የለችም! ተነስቶ ከቤት ሲወጣ፣ አመለዘውድ ግቢያቸው ውስጥ ያደገው ሳር ላይ ተቀምጣለች።

«ምነው ለምን ወጣሽ?»

«አጠገቧ ሆኜ መተኛት አልችልም። ወይ ይገፋ ለማቆም አቅም የለኝ። ፍራሽ ላይ ስለሆነች ምንም አትሆንም ብዬ ነው እስኪሻላት የወጣሁት። በግድግዳው በኩል ትራስ አድርጌላታለሁ። ዛሬ አንተ ስላለህ እንጂ ሌላ ጊዜ ቤት ውስጥ ሆኜ ነው የምጠብቃት። ድንገት ተነስታ ልሂድ ስትል፣ በሩን እይዝባታለሁ።»

«ብዙ ጊዜ ያማታል እንዴ?» አጠገቧ እየተቀመጠ ጠየቃት።

«ኧረ አልፎ አልፎ ነው የሚጥላት።»

ዝም ብለው ለበርካታ ሰከንዶች ቆዩ።

«እኛ ስንፈጠርም ተበድለን ነው የተፈጠርነው።» አለ ተሾመ በምሬት።

አመለዘውድ ዞር ብላ አየችውና፣ «እንደዚህማ አትበል ተሼ!» አለችው።

«ሃብት የለን፣ ዘመድ የለን። ደሃም ሆነን ተረጋግተን መኖር አልቻልን። ይህ ኑሮ ይባላል?!»

«ታያለህ! እኛም አንድ ቀን ያልፍልናል። እኔ ተምሬ፣ ስራ ይዤ ሁላችንም አንድ ቤት ውስጥ በሰላምና በደስታ እንኖራለን።» በንግግሯ ውስጥ ፍጹም እርግጠኝነት ይደመጥ ነበር።

ተሾመ ዞር ብሎ በመገረም አያት። ጥንካሬዋና በተስፋ የተሞላች መሆኗ እጅግ አስደነቀው።





እናታቸው እስኪሻላት ብለው ከቤት የወጡት እህትና ወንድም ረዘም ላለ ጊዜ ስለብዙ ነገሮች ሲያወሩ ቆዩ። ድምጽ ሰምተው ወደ ቤቱ አቅጣጫ ሲዞሩ ድንገት ድንቁ ከቤት ስትወጣ አዩዋት።

«ተነስ ተሼ! ልትሄድ ነው። ተነስ!»

ከብረት ጎጆው ድንገት ያመለጠ አንበሳን ወደ ነበረበት ለመመለስ እንደሚሯሯጡ የቤተአራዊት ሠራተኞች፣ ሁለቱም ከተቀመጡበት በጥድፊያ ተነስተው ሮጥ ብለው ቀረቧትና እናታቸውን ከግራና ከቀኝ ይዘው አቆሟት። ካልሄድኩ ብላ ታገለቻቸው። ጉልበተኛ ነበረች። ራሷን አታውቅም። እንደምንም እየጎተቱ ወደ ቤት አስገብተው በሩን ዘጉባት።

ድንቁ ከጣላት በኋላ ስትነሳ፣ ወይ ቶሎ ወደ አእምሮዋ ትመለሳለች፣ ካልሆንም ራሷን ሳታውቅ ተነስታ እግሯ ወደወሰዳት ልሂድ ትላለች። አመለዘውድ በዚህ ሌሊት ትልቁ ወንድሟ ስላለ እንጂ ወደ ውጪ የወጣችው ሌላ ጊዜ በሩ መቀርቀሩን አረጋግጣ ነው ቤት ውስጥ ቁጭ ብላ እስክትነቃ በትዕግስት የምትጠብቃት። ሚካኤል ቢረዳትም በሁለቱ ጉልበት እናታቸውን ሊያቆሟት አይችሉም። ድንቁ ጉልበተኛም ብትሆን ራሷን በማታውቅበት ሁኔታ ውስጥ የተቀረቀረ በር መክፈት የሚያስችል የአእምሮ ብቃት ስለሌላት በመጨረሻ እንደምንም ያስተኟታል።

የእሳት ራት በብርሃኑ ተስቦ ባለማወቅ ራሱን እሳት ውስጥ እንደሚዶል፣ ተሾመ በዚህ ምሽት በቤተሰቡ ፍቅር ተታሎ ወደቤት ተመልሶ መምጣቱና ከእነርሱ ጋር ለመኖር መመኘቱ ስህተት እንደሆነ አመነ። ከቤት ውጪ፣ ከቤተሰቡ ተለይቶ ሲኖር አንዳንድ ችግሮች ቢያጋጥሙትም፣ ከዚህ ሰቆቃ ትንሽ ራቅ ብሎ በተሻለ ነጻነት የራሱን ኑሮ መኖሩ እንደሚሻል አሰበ። እናም በሚቀጥለው ቀን ቤት አላደረም። አመለዘውድ ከወንድሟ ናፍቆትና የአካሏ ክፍል ውጪ ተቆርጦ የቀረ ያህል ከሚሰማት ቅሬታ ጋር ከእናቷና ከታናናሽ ወንድሞቿ ጋር ኑሮዋን ከመቀጠል ውጪ ምርጫ አልነበራትም።



Sample output to test PDF Combine only

## -25-

*«ቤት መጥታ፣ 'ድንቄ የቡና መግዣ ብላሻለች' ትለኛለች::»*
*ወ/ሮ መዓዛ መስፍን*

ቤት ውስጥ ምግብ ካለ ቡና አይኖርም:: ቡና ከሌለ የድንቁ ንጭንጭና ጭቅጭቅ ቤተሰቡን ያስጨንቃል፤ ቤቷን በአንድ እግር ያቆማታል::

አንድ ቀን፣ «አመለዘውድ፣ ቡና! ቡና አማረኝ:: . . . ቡና መጠጣት እፈልጋለሁ::» አለቻት እናቷ::
«ምንም ፍራንክ የለኝም»
«ምን ይሻለኛል? ቡና ሳልጠጣ እንዴት ነው የምውለው?»
«ድንቄ፣ ቢኖረኝ አሁኑኑ እገዛና አፈላልሽ ነበር::»
«ከጎረቤትም ቢሆን ለምኚ እንጂ ቡና ሳልጠጣማ መዋል አልችልም::»
«ምን ብዬ ነው የምለምነው?»
«እንዲያው የተቆላ ቡና የሚያሸተኝ እንኳ ባገኝ!»
አመለዘውድ ሲጨንቃት ከቤት ወጣች::
'የት ቤት ልሂድ?' ብላ አሰበች::

ወ/ሮ መዓዛ ቤት ለመሄድ ወሰነች:: ወ/ሮ መዓዛ ደግ ሴት እንደሆኑ ታስባለች:: ከሁለት ደቂቃ በኋላ የወ/ሮ መዓዛን ቤት የውጪ በር እያንኳኳች ነበር:: ከትልቁ በር ጋር ተያይዞ የተሰራ ትንሽ በር በወ/ሮ መዓዛ ሴት ልጅ በፋይል ተከፈተ::

«እትዬ ማዕዛ አሉ?» ብላ ጠየቀቻት:: ወ/ሮ መዓዛን «እትዬ ማዕዛ» ነው የምትላቸው::
«አዎ» አለቻት ፋይል ወደ ውስጥ እንድትገባ በሩን ሰፋ አድርጋ እየከፈተችላት::

ወ/ሮ መዓዛን ማዕድ ቤት ወጥ እየሰሩ አገኘቻቸው::

«እንደምን ዋልሽ አመለዘውድ?» የወ/ሮ መዓዛ ከልብ የመነጨ ፈገግታ ፊታቸውን አደመቀው:: ድምፃቸው ውስጥ ሁልጊዜ ቅንነትና ለሰው ያላቸው ፍቅር ይደመጣል::

«ደህና ነኝ፣ ድንቄዬን አመመብኝ እንጂ»
'አነጋገሯ ልክ እንደ አዋቂ እኮ ነው' ሲሉ ወ/ሮ መዓዛ በመገረም አሰቡና፣ «አልተሻላትም እንዴ?» ብለው ጠየቁ::
«እዎ ያማታል::» አለች አመለዘውድ እያቀረቀረች::
«አይዞሽ! ይሻላታል::»





«ቡና እንደምትወድ ያውቁ አይደል?»
«አዎ፤ አዎ አውቃለሁ»
«ቡና ካላፈላሽልኝ አለችኝ:: የቡና መግዣ ሃያ አምስት ሳንቲም ማዕዛን ጠይቂያቸው ብላኝ ነው የመጣሁት::»
ወ/ሮ መዓዛ ከልብ አዝነው ከንፈራቸውን መጠጡ::
«አይ የደሀ ነገር!»

ተነስተው ወደ መኝታ ክፍላቸው ሄዱ:: የእሳቸውም ባለቤት አቶ ግርማን ከአንድ ዓመት በኋላ ተከትለው ነው ያረፉት:: የባላቸውን ጡረታ ስለሚያገኙ ግን ኑሮ እንደድንቄ በከባድና ውስብስብ ዕለታዊ የህልውና ጥያቄዎች አያስጨንቃቸውም::

አንድ ብር ይዘው ተመልሰው መጡ::
«እንቺ! በዚህ ቡና ግዢላት::»

የአመለዘውድ ፊት በሚያምር ፈገግታ ፈካ:: «እሺ! እሺ እትዬ ማዕዛ!»

ከታላቅ የክብር እንግዳ ሽልማት እንደሚቀበል ተሸላሚ፣ ጎንበስ ብላ ብሩን በሁለት እጆቿ ተቀበለቻቸው::

ከዚህች ቀን በኋላ አመለዘውድ ትንሽ የልመና ድፍረት ስላገኘች ገንዘብ ከእጇ ሲጠፋ ሰፈሩን ማዳረስ ጀመረች:: ወ/ሮ መዓዛን ጨምሮ፣ የተሻለ አቅም ካላቸው ጎረቤቶቻቸው ከወ/ሮ ሄና፣ ከወ/ሮ አለምአገኝ፣ ከወ/ሮ ሀገሬ፣ ከወ/ሮ ሻሼ ትለምን ነበር::

ወ/ሮ መዓዛ ለልመና ወደ እሳቸው ደጋግማ በመምጣቷ ተሰላቹ::

«ለመሆኑ አመለዘውድን የቡና መግዣ ገንዘብ ጠይቂያት እያልሽ በየጊዜው የምትልኪያት አንቺ ነሽ?» ብለው አንድ ጊዜ ድንቄን ጠየቋት::
«ኧረ እኔ እቴ! ራሷ ትሆናለች እንጂ እኔ ሰው እንድታስቸግር አልፈልግም::» ብላ መለሰች ድንቄ::
«ልጅሽ ባልጋለች:: በየጊዜው እየመጣች፣ 'ድንቄ ቡና መግዣ ብላሻለች' ትለኛለች:: እየተበላሸች ነው:: ተቆጪት!»
«የታባቷ! ጠይቂ ሳልላት ምን አድርጊ ነው የምትልሽ?» ብላ ድንቄም መቆጣት አማራት::
«ምከሪያት እንዳትበላሽብሽ::» አሉ ወ/ሮ መዓዛ::

ድንቄ ከጎረቤት ለምኚም ባትል፣ በየቀኑ ቡና፣ ቡና ማለቷ ልጇ ላይ ሊፈጥር የሚችለውን ጫናና ውጥረት ግን አላስተዋለችውም:: «ቡና አማረኝ» ስትል ቤት ውስጥ ብዙ ጊዜ ገንዘብ ስለማይኖር አመለዘውድ የምትወስደው



Sample output to test PDF Combine only

አማራጭ የጎረቤት በር ማንኳኳት ነው፡፡ የልጅ አዋቂ በመሆኗ አብዛኛው ባህርይዋ ከሕፃናት የተለየ ቢሆንም፣ ልጅነቷ ግን ለመለመን ድፍረት ሰጥቷታል፡፡ በእርግጥ የጎረቤት ሴቶች በሙሉ እንደሕፃን አይተዋት አያውቁም፡፡ የአነጋገር ለዛዋ፣ ቃላት አመራረጧ፣ ብስለቷና ባህሪዋ የአዋቂ በመሆኑ እሷን እንደሌሎች ሕፃናት አያዩዋትም፡፡ በእርግጥ ዕድሜዋ አሁን አሥራ አንድ ቢሆንም፣ አመለዘውድ እንደ ልጅ አልነበረችም፡፡

ዛሬ ራት ተበልቶ ለነገ ቤት ውስጥ ምንም ምግብ የማይተርፍበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡ ቁርስ ብዙ ጊዜ ቅንጦት ነው፡፡ ቁርስ የማይበላባቸው ቀናት በርካታ ናቸው፡፡ ምሳም አልፎ፣ አልፎ ላይገኝ ይችላል፡፡

የሁለቱ ሕፃናት ወንድሞቿና የእናቷ ጦም መዋል እጅግ የሚያስጨንቃት ያችው አመለዘውድ ናት፡፡ ምግብ ቤት ውስጥ በሌላቸው ቀናት እሷ ገንዘብም ሆነ ምግብ ሠርታ ልታገኝ የምትችልበት ምንም አማራጭ ከሌለ፣ ተሾመም ሊረዳቸው የማይችል ከሆነ በባዶ አንጀቷ ታደለን አዝላ ከጎረቤቶቻቸው አንዳቸው'ጋ ትሄዳለች፡፡ በተለይ ሰሞኑን ደግሞ ተሾመ ጠፍቷል፡፡ አስፋልት አካባቢ ብትፈልገውም አላገኘችውም፡፡

«ዛሬ'ኮ ምንም የምንበላው የለንም፡፡» ትላለች፡፡ ብዙዎቹ ጎረቤቶቻቸው ያዝናሉ፡፡ ካላቸው ምግብ ከመስጠት ወደኋላ አይሉም፡፡

ዕድሜ ለአመለዘውድ ቤተሰቡ እህል ሳይቀምስ አያድርም፡፡ የሰው ፊት ገርፏት፣ የራሷንና የቤተሰቧን ድህነት በይፋ አምና፣ ለምና የምታገኛትን ይዛ ወደ ቤት ትገባለች፡፡ ተፍ፣ ተፍ ብላም ያዘጋጀችውን ምግብ ለሚካኤልና ለታደለ እንዲሁም ለእናቷ ታቀርባለች፡፡ እሷ ብዙም የምግብ ፍላጎት የላትም፡፡ አመለዘውድ ከምንም በላይ የሚያጠግባት የወንድሞቿና የእናቷ የሚበቃቸውን ያህል መመገብ ነው፡፡

ባለፉት ጥቂት ወራት በቂ ገንዘብ ስለሚያገኝ ምግብ ፍለጋ ብሎ ጎራ ባይልም፣ አንዳንድ ቀን ተሾመ ቤት ይመጣና፣ «ዛሬ ባክሽ ቺስታ ወገረኝ፡፡ ምንም ሳንቲም ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ርቦኛል፡፡» ይላታል፡፡

ቤት ውስጥ ምግብ ካለ በደስታ ታቀርብለታለች፡፡ አጠገቡ ተቀምጣ ሲበላ ማየት ከምንም በላይ ያስደስታታል፡፡

«አንቺ አትበዪም?» ሲላት፣
«እበላለሁ፡፡ ብላ አንተ ተሼ!» ትለዋለች፡፡

በጣም ከራበው ለሷ ብዙም ሳይጨነቅ ያቀረበችለትን ጥርግ አድርጎ በልቶ ወደ አስፋልት ለመሄድ ይነሳል፡፡ አንዳንድ ቀን ግን እሷ አብራው ካልበላች



Sample output to test PDF Combine only



እንደማይበላ አስረግጦ ይነግራትና አብረው ሲበሉ ይቀመጣሉ፡፡ ለነገሩ እሷ ብዙ አትበላም፤ አንጀቷ መብላት የለመደው በትንሹ ነው፡፡

«ተሼ በኋላም ና! ለራትም አስቀምጬልሃለሁ፡፡» ትለዋለች፣ ጥልቅ ፍቅሯን የምትገልፅበት ፈገግታ ወዝ በሌለው ፊቷ ላይ እያብረቀረቀ፡፡ ወንድሚ ጠግቦ ሲሄድ ጥግብ ትላለች፡፡

«እሺ» ብሏት ሲሄድ ደስ ይላታል፡፡ ግን ማታ እሷ ተዘጋጅታ ብትጠብቀውም ተመልሶ አይመጣም፡፡

ድንቁ የሐበሻ መድኃኒት ተጠቅማ አልማዝ ባለጭራው ከሰመላት፡፡ ውሃ ማመላለሷን ቀጠለች፡፡

አንድ ቀን ደግሞ አልማዝ ባለጭራው አመለዘውድ ጀርባ ላይ ወጣ፡፡ እናቷን ያዳናትን የሐበሻ መድኃኒት መጠቀም ጀመረች፡፡ ሶስት ቀን ብቻ ነበር የተኛችው፡፡ ስለተሻላት ሳይሆን መሥራትና ቤተሰቦቿን መመገብ ስላለባት፣ በአራተኛው ቀን ከተኛችበት ተነሳች፡፡ ቁስሉ ገና ሳይጠግ፣ ጀርባዋን እየሸመቀቃት ጥርሷን ነክሳ ወደ ሥራ፣ ቡርቴ'ጋ ሄደች፡፡

## -26-

*«እጁን ይዛ አለቀቀችም። ፖሊሱ በመጨረሻ መንጭቆ አስለቅቃት።*
*ጉልበቱ ላይ ወደቀች።»*
*ተሾመ ግርማ*

ከዛሬ ነገ እንደምታገኘው ተስፋ ብታደርግም ባለፉት ሁለት ረጃጅም ሳምንታት አመለዘውድ ተሾመን አላየችውም። አንዳንድ የሚያውቁትን ልጆች ጠየቀች። የት እንዳለ እንደማያውቁ ነገሯት። ሌላም ረጅም ሳምንት ተደገመ። ግራ ገባት።

'ምናለበት እዚህ ቦታ ሄጃለሁ ብሎኝ ቢሄድ?' ስትል አስባ አዘነችበት፤ ተናደደችበትም።

ባዶነት ተሰማት። የሄደበትን አለመናገሩ፣ ሃሳብ የለሽነቱ አበሳጫት። ወንድሟ እጅግ ናፈቃት። «ወጥና ወንድም ማስፈራሪያ ነው» እንዲሉ፣ ባይረዳቸውም ተሾመ በቅርብ እንዲኖርና በየቀኑ ልታየው ተመኘለች።

. . . አንድ ወር አለፈ። ወንድሟ የት እንዳለ የሚነግራት ሰው አላገኘችም። አንድ ጊዜ ስለጎዳና ህይወት ጠይቃው ባቡር ጨፍልቆት ወደሚሄድበት ሳይደርስ፣ ወደተነሳበትም ሳይመለስ ስለቀረው ልጅ የነገራትን አዘውትራ ታስብና ሰውነቷ በፍርሃት ይንዘፈዘፋል። በቁሟ እየቃዠች ትባንናለች። ምናልባት ያ በመንገድ የቀረ ልጅ እንደ ተሾመ የሚወዱት እናት፣ የምትወደው እህት ይኖሩት ይሆናል። ምናልባትም የዚያ ልጅ ዘመዶችና ቤተሰቦች ከዛሬ ነገ ይመጣል እያሉ እስከዛሬ በተስፋና በናፍቆት እየጠበቁት ይሆናል።

አንድ ቀን የተሾመን ጓደኛ ሳሙኤልን አስፋልት አካባቢ አየችው። እሱም ሰሞኑን ጠፍቶ ነበር። ወንድሟን ያገኘች ያህል ተደሰተች። ተንደርድራ አጠገቡ ሄዳ ሞቅ ያለ ሰላምታ አቀረበችለትና፣ «የት ጠፍተህ ነው?» ብላ ጠየቀችው።

«ክፍለ ሃገር ሥራ አግኝቼ ሄጄ ነበር።» አላት።

«ተሾመን አይተኸዋል?» ብላ በጉጉት ጠየቀችው።

«አላየሁትም» አላት ሳሙኤል ፈጠን ብሎ።

«የት ጠፋ ታዲያ?»

«እኔ እንጃ። ምናልባት ሥራ አግኝቶ ሌላ ቦታ ሄዶ ሊሆን ይችላል።»

«የት?»

«እኔ እንጃ»

«ታዲያ ለኛ ሳይነግረን ነው የሚሄደው? የኛስ ይቅር እሺ ላንተ እንኳን አይነግርህም?» ዓይኖቿ በእንባ ተሞሉ።



Sample output to test PDF Combine only



«አልነገረኝም» አላት። ላይ ላዩን ለሷ ግድ የለሽ እንደሆነ ለመምሰል ቢጥርም እያዘነላት ነበር። ወንድሟን በጣም እንደምትወደው አሳምሮ ያውቃል።

አመለዘውድ ፊቷን አዙራ አንገቷን ደፍታ መንገድ ስትጀምር ከጀርባዋ ሲያያት ይበልጥ አሳዘነችው።

«አመለዘውድ!» ብሎ ጠራት።

በእርጋታ ዞረች። እንባ ጉንጮቿ ላይ ተከልብሷል።

«ነይ እንዴ!»

አጠገቡ ስትደርስ፣ «ወንድምሽ ታስሯል።» አላት በእርጋታ።

«ምን?» አለች ድንግጥ ብላ።

«ታስሯል።»

«ምን አድርጎ?»

«ከመኪና ዕቃ ለማውረድ ከሆኑ ልጆች ጋር ተጨቃጨቅንና ተደባደብን። ሁላችንንም አሰሩን። እኔን በዋስ ዘመዶቼ በቀደም አስፈትተውኝ ነው።»

«የት ነው የታሰረው?» አለች ለመሮጥ እያቆበቆበች። የተሳከረ ስሜት ውስጥ ገባች፤ በህይወት መኖሩን ማወቋ ሲያስደስታት፣ መታሰሩን መስማቷ ደግሞ ሸብር ለቀቀባት።

«ተረጋጊ!» አላት ግርምት ያየለበት፣ ሐዘን የተቀላቀለበት ፈገግታ እየፈገገ።

«በናትህ ንገረኝ! የት ነው ያለው?»

«እዚህ ሾላ አካባቢ፣ ወረዳ 28 ጽህፈት ቤት ውስጥ ያለው ፖሊስ ጣቢያ ነው የታሰረው።»

«እሺ፣ በቃ ቻው አመሰግናለሁ!» አለችው በጥድፊያ።

ፊቷን አዙራ አንድ ሁለት እርምጃ እንደተራመደች፣ «ነይ ቆይ!» አላት ሳሙኤል።

ቆም ብላ ዞረችና፣ «እ? ምነው?» አለችው።

«እኔ እንደነገርኩሽ እንዳትነግሪው። አትንገሯት ብሎ አስጠንቅቆናል። እንድትጨነቂ ስላልፈለገ ነው። የነገርኩሽ ስላሳዘንሽኝ ነው።»

«እሺ፣ አልነግረውም» ብላው በፍጥነት ወደ ሰፈር ሄደች።

አንድ ሰሃን ምግብ ማዘጋጀት ቀላል አልነበረም። ዳቦ መግዛት ብቻ ነበር የቻለችው። ዳቦውን ለወንድሟ ይዛ ታስሮበታል ወደተባለበት ቦታ ከነፈች።

ተሾመ ስምንት ሳምንታት በእስር ቤት አሳልፏል። ከሱ ጋር የታሰሩት ጓደኞቹ ቤተሰብና ዘመድ የ350 ብር ዋስ እየገቡ አስፈትተዋቸዋል። እሱ ዋስ ሊሆነው የሚችል አቅም ያለው ቤተሰብ ወይም ዘመድ ስለሌለው የነበረው

ብቸኛ አማራጭ በእስር መማቀቅ ነበር። እናቱና እህቱ መታሰሩን ሰምተው እንዲጨነቁ አልፈለገም። የሚፈታ መሐረብና መቀነት፣ ብር የሚመዘዝበት የገንዘብ ቦርሳ ሳይኖራቸው የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት የሚማስኑት ምስኪን ሴቶች ዋስ ላይሆኑት ለምን በከንቱ ስለሱ ይጨነቃሉ? በዚህ ምክንያት ነበር የተፈቱት ጓደኞቹ መታሰሩን ለእህቱ እንዳይነግሯት አጥብቆ ያስጠነቀቃቸው።

ሰው እንደሚፈልገው ተነግሮት ከውጪ በፍርግርግ ብረት ወደታጠረው የእንግዳ ማናገሪያ መስኮት ቀርቦ እህቱን ሲያያት መጀመሪያ ተገረመ፤ ከዚያ ደስ አለው።

«ማን ነግሮሽ መጣሽ?» አላት ፈገግ ብሎ።
«ተሼ ደህና ነህ?» ስታየው በጣም ደስ አላት።
«እንዴት ነሽ?» እጁን በመስኮቱ ፍርግርግ ብረቶች መሃል አሾልኮ ወደ እሷ ዘረጋ። እጁን ጨብጣ ይዛ ወደ አፏ አስጠግታ ደጋግማ ሳመችው። በህይወት መኖሩን ይበልጥ ማረጋገጥ የፈለገች ይመስል፣ እጁን አንድ ጊዜ ወደ አንገቷ፣ ሌላ ጊዜ ወደ ደረቷ እያስጠጋች ተንሰቅስቃ አለቀሰች።
«ተሼ! ተሸዬ! ደህና ነህ አይደል?»
«ደህና ነኝ።»
«ታስረህ ነው ለካ? እኔ'ኮ አላወቅኩም። . . . ተሸዬ! ደህና ነህ አይደል?» . . .

«ደህና ነኝ አልኩሽ'ኮ። . . . በቃ ዝም በይ! አታልቅሺ!» ብሎ ሊያባብላት ሞከረ።
ማልቀሷን አላቆመችም። እጁን ለአፍታ አልለቀቀችም።
«መቼ ነው የሚፈቱህ?»
«እኔ እንጃ» አላት።

ለበርካታ ደቂቃዎች የተሾመን እጅ ይዛ ስታለቅስና በለቅሶዋ መሃል ስለደህንነቱ ደጋግማ ስትጠይቀው ቆየች።

አንድ ፖሊስ መጣና፣ «ብቃችሁ ሰዓት ደርሷል።» አለ።
ሁለቱም ያልሰሙት መሰሉ።
«በቃ! በቃሽ!» አላት ፖሊሱ ለጥቂት ሰከንዶች አጠገባቸው ቆሞ ጠብቋቸው።

ጭራሽ አመለዘውድ የወንድሟን እጅ በሁለት እጆቿ አጥብቃ ያዘች። ፖሊሱ አጠገቧ ቆሞ ይታዘባታል። ለቅሶዋ ባሰ። ሁለት ወር እሷ ሳታውቅ እንዳልታሰረ ሁሉ ዛሬ ወንድሟን እስር ቤት «ብቻውን» ትቶ መሄድ ከበዳት።


Sample output to test PDF Combine only



ለወንድሟ ያላት ጥልቅ ፍቅር የማመዛዘን አቅሟን ቀንሶባት ትታው መሄድ ጥፋት እንደሆነ ተሰማት።

«በቃሽ አልኩሽ'ኮ!»

ፖሊሱ ተቆጥቶ እጇን ከተሾመ እጅ በግድ መንጭቆ አላቀቀው። አመለዘውድ እየተንሰቀሰቀች በፖሊሱ ጉልበት ላይ ወደቀች። በጭንቀት ልታብድ ደርሳ ነበር።

«ምንድነው?» አለ ፖሊሱ ተገርሞ።
«በናትህ ወንድሜ'ኮ ነው።»
«እና ቢሆንስ? አንቺ ብቻ ነሽ ወንድም ያለሽ?» ፖሊሱ ተቆጣ።
«አባታችን ሞቷል። ደሃ ነን። ያለን እሱ ብቻ ነው።»
«ምን አይነቷ ናት ባካችሁ!?» አለ ፖሊሱ በመገረም ቁልቁል እያያት።

ትንሰቀሰቃለች። አሳዘነችው።

በረጋ አንደበት፣ «በይ አሁን ተነሽ! ከሶስት ወይም ከአራት ቀን በኋላ ይፈታል።» አላት።
አመለዘውድ ከተደፋችበት ቀና ብላ ለቅሶ ባቀላቸውና ዕንባ በሚያጎርፉ ዓይኖቿ አየችው። «እውነትህን ነው? . . . ይፈታል?»
«እዎ፣ ተነሽ!» አላት።

የፊቱ ገጽታ፣ እንዲሁም የድምጹ እርጋታ እንድታምነው የሚያስገድድ ነበር። ከተደፋችበት ተነሳች።

የመፈታቱ ዜና ለተሾመም አዲስ ነበር። ፖሊሱ አመለዘውድን ለማጽናናት ዋሽቶ ሊሆን እንደሚችል በመጠኑ ቢጠራጠርም እሱም ፖሊሱን ማመን መረጠ።

አመለዘውድ እንባዋን እየጠራረገች፣ «ተሼ፣ ደህና ሁን። እመጣለሁ።» አለችው።

ስትሄድ ከዓይኑ እስክትሰወር ከኋላዋ አያት። በብቸኝነት ውርጭ የደነዘዘ አእምሮውን በጋለ የእህትነት ፍቅሯ ስላፍታታችለት በመምጣቷ በጣም ተደስቷል።

ፖሊሱ እንዳለው ተሾመ በሶስተኛው ቀን ከእስር ተፈታ። ከእስር ቤት ወጥቶ ወደሰፈሩ ሲሄድ፣ መንገድ ላይ እህቱ እሱን ለሁለተኛ ጊዜ ልትጠይቀው እየተጣደፈች ስትመጣ አገኛት። አመለዘውድ ከፍርግርግ ብረት ጀርባ ያየችው ወንድሟ ነጻ ሆኖ ስታገኘው ደስታዋ ወሰን አልነበረውም።

## -27-

*«እናቷ እሳት ላይ ትወድቃለች። ልጅቷ ከቤት ወጥታ ለመሄድ ትሳቀቅ ነበር። 'እባካችሁ ድንቄን እያያችሁልኝ! አደራ!' ብላን ነበር የምትሄድ።»*
*ወ/ሮ የሺ ካሠው*

ድንቁ የሚጥል በሽታዋ አቶ ግርማ በህይወት እያሉ ብዙም አይጥላትም ነበር። ባሏ ሞተው ከባድ የኑሮ ሸክምና የቤተሰብ ኃላፊነት በጫንቃዋ ከተጫነ በኋላ ግን በየጊዜው ይጥላት ጀምሯል። አመለዘውድ ብዙ ጊዜ እናቷ በሚጥል በሽታ ወድቃ ብታይም፣ አንድ ቀን የሆነችውን ግን በጭራሽ አትረሳም።

እሷ ከቤታቸው ጥቂት እርምጃዎች ፈቀቅ ብላ ትንሽ ድንጋይ ላይ ተቀምጣ ግቢው ውስጥ ዕቃ ስታጣጥብ እናቷ ቤት ውስጥ ቡና እየቆላች ነበር። ድንገት ብረት ምጣዱ ከሆነ ነገር ጋር ሲጋጭና ሲንኳኳ ሰማች። ብረት ምጣዱ ላይ የሚመላለሰው መቁያ የሚያሰማው ድምፅ ፀጥ ማለቱን ከጥቂት ሰከንዶች በኋላ አስተዋለች። እናቷ ቡና ቆልታ እንደጨረሰች አሰበችና ዕቃ ማጠቧን ቀጠለች።

አፍታም ሳይቆይ የድስት መንኳኳትና ከወለሉ ጋር የሆነ ነገር ሲጋጭ ሰማች። እናቷ የሚጥል በሽታዋ ተነስቶባት ሊሆን እንደሚችል ለመጀመሪያ ጊዜ አሰበችና በፍጥነት ብድግ ብላ በሩጫ ወደ ቤት ገባች።

አልተሳሳተችም። እናቷ የአፈር ወለሉ ላይ ተጋድማ ትወራጫለች። ብረት ምጣዱ ከነቡናው ከምድጃው ላይ ወርዶ ወለሉ ላይ ተገልብጧል። ቡናው ወለሉ ላይ ተበትኗል።

«ድንቄ!» ብላ ጮኸች። የእናቷ መውደቅ ሁልጊዜ እንደ አዲስ ያስደነግጣታል።

እናቷን ይዛ ከመንሸራተቷ ልታቆማት አቅሟ አይፈቅድላትም። ማድረግ የምትችለው በዙሪያዋ ያሉትንና ብትገጫቸው ወይም ከስሯ ቢገቡ ሊጎዷት የሚችሉ ዕቃዎችን ማራቅ ነው። በራስጌዋ በኩል የሚታየው ቡና የሚወቀጥበት ትንሽ ሙቀጫ አነሳች። የሆነ ለየት ያለ፣ የሚቃጠል ነገር ሸተታት። ለካስ የድንቄ ቀሚስ ጫፍ እየነደደ ባለው እሳት ላይ አርፏል። አመለዘውድ ጭስና እሳት ድንገት አስተውላ ዓይኖቿን ወደ ድንቄ እግሮች ስትወረውር፣ የእናቷ ቀሚስ ቢጫ፣ ብርቱካንማና ሰማያዊ ምላሶቹን ወጣ፣ ገባ በሚያደርግ ነበልባል ሲቃጠል አየች።

«ወይኔ ድንቄ! » እጆቿን በደመነፍስ ወደ ነበልባሉ ዘረጋች። አቃጠላትና እጆቿን በፍጥነት ሰበሰበች። በነበልባሉ ላይ ዘላ ወደ ውጪ ወጣች።


Sample output to test PDF Combine only



ሳፋ ውስጥ ዕቃ ስታጥብበት የነበረውን ውሃ አንስታ ወደ ቤት ስትንደረደር ተቀምጣበት የነበረው ድንጋይ አደናቀፋት። በደረቷ ወደቀች። ሳፋው ከእጇ አምልጦ ወደፊት ተወርውሮ እንደመንሸራተት ብሎ ቆመ። ከወደቀችበት እንደምንም ተነስታ ወደ ሳፋው በጉጉት አየች። የተወሰነው ተንቦራጭቆ ከሳፋው ውጪ ቢረጭም የቀረ ውሃ ነበር። አንስታው ወደ ቤት እየተንገዳገደች ገባች።

የእናቷ ቀሚስ እየነደደ ነበር። ሳፋው ውስጥ የቀረውን ውሃ ነበልባሉ ላይ ቸለሰችው። ውሃው እናቷ ቀሚስ ላይ ሲያርፍ ከሰከንዶች በፊት ጉልበተኛ የነበረው የእሳት ነበልባል፣ አስፈሪ ምላሶቹን ሰብስቦ አቅመ ቢስ ጭስ ሆነ። ውሃው ያልደረሰበት አንድ ጫፍ ላይ ትንሽ የእሳት ነበልባል አስተዋለች። በፍጥነት በርከክ ብላ «እፍ! እፍ!» ብላ በትንፋሽዋም በእጇም አጠፋችው። እናቷ በእሳት ከመቃጠል መትረፏን ካረጋገጠች በኋላ፣ ውጪ በጀሪካን የነበረ ውሃ አምጥታ የምድጃውን እሳት ላይ አርከፈከፈችው።

ድንቄ አንድ እግሯ በእሳቱ ከመለብለቡ በስተቀር ከባድ ጉዳት አልደረሰባትም። አመለዘውድ ትንሽ ብትዘገይ ወይም ቤት ባትኖር ኖሮ፣ እናቷን በአሰቃቂ ሁኔታ ልታጣት ትችል እንደነበር አስባ ዝግንን አላት።

ከዚያች ቀን በኋላ በተቻለ አቅም እሷ ቤት ውስጥ ከሌለች እናቷ እሳት እንድታነድና ምግብ እንድታበስል አትፈልግም።

ወደ ት/ቤት ወይም ወደ አስፋልት ለሥራ ስትሄድ፣ ጎረቤታቸውን የእሙሽን እናት ወ/ሮ የሺ ካሣውን፣ «እባክሽ እናቴን ብቅ እያልሽ እዩያት። አደራ!» ብላ ነበር የምትሄደው።

## -28-

*«ብዙ ጊዜ ረፍዶባት እየሮጠች ስትመጣ፣ እኛ ትምህርት ቤቱ በር አካባቢ እየተጫወትን እናያት ነበር።»*
*እመቤት ተፈሪ*
*«እናቴን ስለምወድና ስለምጠብቅ ትምህርት ቤት ቀሪ 30 ቀን ሞልቶ ወጣሁ።»*
*አመለዘውድ*

እነሆ አቶ ግርማ ከሞቱ ሁለት ዓመታት አለፉ። አመለዘውድ ከሁለት ወደ ሶስት፣ ከሶስት ወደ አራት አልፋ የአራተኛ ክፍል ተማሪ ሆናለች። ድንቁ በሽታዋ በተደጋጋሚ ይጥላታል። አመለዘውድ የምትማረው ግማሽ ቀን ቢሆንም፣ እናቷንና ወንድሞቿን በመንከባከብ፣ ሌሎች የቤት ውስጥ ሥራዎችን በማከናወን ትባትላለች። ከቤት ውጪ ደግሞ ቡርቴ ጋር እየሰራች ለመኖር የሚያስፈልጋቸውን ለሟሟላት ትጥራለች። ኃላፊነቶቿ ስለበዙና ስለከበዱ ገና የአራተኛ ክፍልን በጀመረችባቸው የመጀመሪያ ቀናት ት/ቤት አርፍዳ መድረስ አዘወተረች። ረፍዶባት ወደ ት/ቤት ስትሮጥ፣ ቀደም ብለው የደረሱት የሰፈሯ ልጆች ት/ቤቱ በር አካባቢ ሲጫወቱ ያዩዋታል።

«ይቺ አመለዘውድ ደግሞ ሁልጊዜ ነው እንዴ የምታረፍደው?» እያሉ ይጠቋቆሙባታል።

አርፍዳ መድረስም እያቃታት መጣ። ለመሄድ ብትጓጓም የት/ቤት ሰዓት ይረፍድና ትቀራለች። እናቷንና ወንድሞቿን ስትንከባከብ ት/ቤት ለመሄድ ጊዜ አጥታ፣ የቀረችበት ጊዜ በቀናት ሳይሆን በሳምንታት ተቆጠረ።

ትምህርት በሕይወቷ ውስጥ ቅድሚያ የማትሰጠው፣ ለነገ የምትቀጥረው፣ አስፈላጊ ግን አንገብጋቢ ያልሆነ ነገር ሆነ። አንገብጋቢውና ጊዜ የማይሰጠው የእናቷ ደህንነትና የወንድሞቿ በልቶ ማደር ነው። እሷና ቤተሰቦቿ ዛሬን በልተው ማደር ሳይችሉ ት/ቤት ምን ብላ ትሂድ? በባዶ ሆድስ ትምህርት ይገባታል?

ከሳምንታት በኋላ አንድ ቀን «ተመቻትና» እጅግ ወደ ናፈቃት ት/ቤት ሄደች። ነገ ተመልሳ እንደምትመጣ እርግጠኛ አልነበረችም። ክፍሏ ገብታ ተማሪዎቹን በተዘበራረቀ ስሜት ውስጥ ሆና አየቻቸው። ናፍቆት፣ ሃዘንና ቅናት ተፈራረቁባት። ተለይታቸው ለሳምንታት ስለቆየች ናፍቀዋታል። እንደ እነሱ በተረጋጋ መንፈስ መማር አለመቻሏ አሳዘናት። እነሱ በሰላም የመማር እድል ስላገኙ ደግሞ ቀናችባቸው። የክፍል ኃላፊ መምህሯ ክፍል ውስጥ ተቀምጣ ሲያያት ደስ አለው።

«እንደምነሽ አመለዘውድ? የት ጠፍተሽ ነው?» ብሎ ፊቱን በፈገግታ አድምቆ ጠየቃት።

«አልተመቸኝም። ስላልተመቸኝ ነው የቀረሁት።» አለች እያቀረቀረች።



Sample output to test PDF Combine only



አስተማሪዋ ፊቱን ድንገት ጭልም አድርጎ፣ «በኋላ በዕረፍት ሰዓት የምንነጋገረው ነገር አለ። ቢሮ ነይ!» አላት።

«እሺ»

ሌሎች መምህራንም ሲገቡ፣ ለምን እንደጠፋች ጠየቋት። ክፍል ውስጥ በንቃት ስለምትሳተፍ ሁሉም በደንብ ያውቋታል፣ ይወዷትማል።

በዕረፍት ሰዓት የክፍል ኃላፊ መምህሯ'ጋ ሄደች።

«አመለዘውድ በዚህ ሴሚስተር ከሠላሣ ቀን በላይ ቀርተሻል። ከሠላሣ ቀን በላይ ቀሪ የሆነ ተማሪ ደግሞ ትምህርት መቀጠል አይችልም።» አላት ረጋ ብሎ።

ደነገጠች።

«እና በቃ ትምህርት ማቋረጥ አለብኝ ማለት ነው?»

«እዎ፤ ልረዳሽ አልችልም።»

«እባክዎ ቲቸር ትምህርት ማቋረጥ አልፈልግም።» አለች ዕንባ እየተናነቃት። «ያመለጠኝን እገለብጥና እጠናለሁ።»

«አዝናለሁ። ምንም ማድረግ አልችልም አመለዘውድ።» አላት መምህሯ።

ከት/ቤቱ ግቢ ስትወጣ ልቧ በሀዘን ስብር ብሎ ነበር።

«ወይኔ አባቴ! አንተ ብትኖርልኝ ኖሮ'ኮ . . . »

አባቷ ጤነኛ ሆነው በህይወት ቢኖሩ ኖሮ፣ ያለ ብዙ ሃሳብና ጭንቀት ትምህርቷን መማር ትችል እንደነበር አሰበች። አባቷ ናፈቋት።

ዕንባዋ ወደ ጉንጮቿ በእርጋታ ሲወርድ ተሰማት። ጠረገችው።

'ግድ የለም እናቴ ደህና ትሁንልኝ እንጂ እማራለሁ።' ራሷን አጽናናች።

አንድ ቀን ወደ ት/ቤት እንደምትመለስ እርግጠኛ ነበረች፣ «መቼ?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ራሷን ባታስጨንቀውም።

## -29-

*«መንገድ ላይ አገኙኝና፣ 'ልብስህን ይዘህ ና!' አሉኝ::»*
*ሚካኤል ግርማ*
*«እህቱ እየመጣች ታባብለዋለች:: አንድ ቀን ይዛው ሄደች:: በዚህ ምክንያት ጠላኋት፣ ሰደብኳት፣ 'እኛ'ጋ ሁለተኛ እንዳትመጪ!' አልኳት::»*
*ወ/ሮ አበበች ገመቹ*

አንድ ቀን ወ/ሮ ልኬ ጉደታ ሚካኤልን መንገድ ላይ አገኙት::

«ና አንተ!» አሉት::

ሚካኤል ወደእሳቸው ሄዶ ሽቅብ እያያቸው አጠገባቸው ቆመ::

«የግርማ ልጅ አይደለህ?»
ራሱን በአዎንታ ነቀነቀ::

አዛውንቷ ትንሹን ልጅ ይወዱታል:: ሚካኤል እንደአባቱ ቀላ ያለ ድንቡሼ ልጅ ነው:: ከአቶ ግርማ ልጆች መልኩ የበለጠ የሚያምር የእሱ ነው:: አሮጌ ልብስ ለብሷል:: አመለዘውድ ልብሶቹን በተቻላት አቅም በየጊዜው ስለምታጥብለት ብዙም አልቆሸሸም:: ጫማ የሚናፍቁ እግሮቹ ግን አቧራ ለብሰዋል::

ወ/ሮ ልኬ በሃዘኔታና በፍቅር ለአፍታ አዩትና ሚካኤልን ሊያሳድጉት ወሰኑ::

«ሂድ ልብስህን ይዘህ ና! ከእኔ'ጋ ትኖራለህ:: እኔ አሳድግሃለው::» አሉት::

ሚካኤል ቤት ሄዶ ለእናቱ ወ/ሮ ልኬ ያሉትን ሲነግራት መሄዱን አጥብቃ ባትቃወምም፣ «ባትሄድ ይሻላል:: እዚሁ እኛ እንደሆነው ትሆናለህ::» አለችው፣ ልጁ ራሱ እንዲወስን ሙሉ መብት እየሰጠችው::

ሚካኤል መሄድ ፈለገ:: እናቱ እንኳንስ ልታስተምረው በቀን ሶስቴ ልትመግበው እንኳ አልቻለችም:: ሚካኤል ያሉትን ጥቂት አሮጌ ልብሶች ይዞ ወደ ወ/ሮ ልኬ ቤት ሄደ::

በዚያው ሰሞን ሲገናኙ፣ «ይሄን ልጅሽን እኔ ላሳድግልሽ ብዬ እኮ ነው፤ ትምህርቱንም በደንብ ይማራል::» አሏት ወ/ሮ ልኬ ድንቄን::
«እሺ እማማ:: መማሩ ጥሩ ነው::» አለች ድንቄም::

በሚካኤል መሄድ ግን አመለዘውድ ደስተኛ አልሆነችም:: ቤቱ ጭር አለባት:: በተለይ ማታ ሁለቱን ወንድሞቿንና እናቷን ቤት ውስጥ ስታገኛ


Sample output to test PDF Combine only



ቸው ደስ ይላት ነበር:: እንደሌሎች የቤተሰቦቿ አባሎች ሁሉ ሚካኤልን በጣም ትወደዋለች::

የምትሰራበት የቡርቴ ቤት ከወ/ሮ ልኬ መኖሪያ ቤት በቅርብ ስለሚገኝ ሚካኤልን ጎራ ብላ ሳታየው አታድርም::

«እንዴት ነህ?»
«ደህና ነኝ»
«ምግብ በደንብ ታገኛለህ?»
«አዎ፤ ቁርስ፣ ምሳ፣ ራትም እበላለሁ::»
«እኔም ስለምሰራ እኛም ቤት የምንበላው ነገር'ኮ አይጠፋም:: ለምን ወደ ቤት አትመለስም?»
«እማማ እዚህ እንድኖር ይፈልጋሉ::»
«እኔም'ኮ ቤት እንድትመጣና አብረን እንድንኖር እፈልጋለሁ:: እህትህ አይደለሁ?»
እሺም፣ እምቢም ማለት ስለሚከብደው ዝም ይላታል::

ሚካኤልን ባገኘችው አጋጣሚ ሁሉ ወደ ቤት እንዲመለስ ልታግባባው ትጥራለች:: በሷ ድክመት ወንድሟን የወሰዱባት ይመስላታል::

ሚካኤል የአመለዘውድ ፍቅር አሸነፈው:: ወ/ሮ ልኬ ቤት ጥቂት ሳምንታት እንኳን ሳይቆይ አንድ ቀን ከእህቱ ጋር ወደ ቤት ተመለሰ:: . . .

ወ/ሮ ልኬና ልጃቸው ወ/ሮ አበበች ገመቹ በአመለዘውድ በጣም ተናደዱባት::

«እስኪ አሁን እነሱ ቤት ምን አለ ብላ ነው ልጁን የወሰደችው?» አሉ ወ/ሮ አበበች::
«አይገርምሽም!? በየቀኑ እየመጣች፣ ምን እንደምትለው ባልሰማም፣ ስታናግረው ቆይታ ትሄድ ነበር::» አሉ ወ/ሮ ልኬ::
«በጣም ችግረኞች እንደሆኑ እናውቃለን! ምን አብልታ ልታሳድገው ነው የወሰደችው?!» ወ/ሮ አበበች አፋቸውን በግርምት በእጃቸው ከደኑ::
«እኔም እኮ ግራ ነው የገባኝ::»

ወ/ሮ አበበች አመለዘውድን በዚያው ሰሞን መንገድ ላይ ሲያገኟት ጠሯት::

«ምን ነካሽና ነው አንቺ ልጁን የወሰድሽው?» በቁጣ ጠየቋት::
«ማንን?»
«አሁን ማንን እንዳልኩ ጠፍቶሽ ነው?!»
«ሚካኤልን ነው የሚሉኝ? ራሱ መምጣት ፈልጎ ነው::»

«ሂጅ! ቀጣፊ! ራስሽ አይደል የወሰድሽው::»
«አዎ፣ ግን ከኛ ጋር መኖር ፈልጎ ነው::»
«ምናለ እኛ'ጋ እየኖረ ቢማር? እናንተ'ጋ ምን ያገኛል?» ወ/ሮ አበበች በጣም ተቆጡ:: «ሁለተኛ እናቴ ቤት ድርሽ እንዳትይ!»

እመለዘውድ አቀርቅራ ዝም አለች::



Sample output to test PDF Combine only



## -30-

### *«'መሬቱማ የልጆቼ ሀብት ነው:: እሱንማ አልሸጠውም::' ትል ነበር»*
### *ተሾመ ግርማ*

ድንቁ ምንም ኑሮ እጅግ ቢፈታተናት፣ ምንም የዋሀ ብትሆን፣ ምንም አንዳንድ ሰዎች፣ «ለምን ቤቱንና መሬቱን አትሸጪውም?» እያሉ ሊፈታተኗት፣ ሊያባብሏትና ሊያታልሏት ቢሞክሩም፣ «መሬቱማ የልጆቼ ሀብት ነው:: እሱንማ አልሸጠውም::» ትላለች::

ትንሿ ደሳሳ ቤት ብቻ አንድ ጥግ ላይ መገኘቷ የግቢውን ስፋት አጉልቶታል:: ከቤቷ በስተቀኝ ያደጉት ባህር ዛፎች ባይኖሩ ደግሞ ግቢው የበለጠ ባዶ መስሎ በታየ ነበር:: እነዚህ ባህር ዛፎች ናቸው አልፎ አልፎ ተሸጠው እንጀራ ቤት ውስጥ የሚበላው:: ቤተሰቡም አቶ ግርማ በህይወት የነበሩበትን ዘመነ እንኮዬ የሚያስታውሰው፣ ግድግዳ ተደግፎ የሚውለውም የሸክላ ምጣድ በእሳት የጋለ ገጹ በቀጭን የጤፍ ሊጥ የሚሸፈነውና ሊጡን በግለቱ ነዳድሎ በጥቃቅን ዓይኖች የመሙላትና የማብሰል ወግ የሚደርሰው ያኔ ነው:: ከሰፈራቸው ትንሽ ርቆ ከሚገኘው የመንግስት የባህር ዛፍ ደን ከሚያመጡት እንጨት በተጨማሪ፣ የግቢውን ባህር ዛፎች ጭራሮና ቅጠሎች ለምግብ ማብሰያም ይጠቀማሉ::

· ከቤቷ በስተግራ ጥቂት እርምጃዎች ርቆ ያለው አጥር ከአንድ ሜትር ብዙም የማበይልጥ አጭር ሆኖ በሲሚንቶ ባልተያያዙ ትንንሽ ድንጋዮች ክምር የተሰራ ነው:: ከቤቷ በስተጀርባ እንደ አጥር የሚያገለግለው ደግሞ ከትንሿ ቤታቸው አጠገብ ሲታይ ሰማይ ጠቀስ የሚመስለው የጎረቤቶቻቸው ሰርቪስ ክፍሎች ግንብ ነው:: ከቤቷ ፊት ለፊት በግራ በኩል ፈንጠር ብሎ የሚታየው በጭቃ የተሰራ የጎረቤት ቤትም እንደ አጥር ያገለግላል:: ከቤቷ በስተቀኝ ያለውን የሌላ ቤት አጥር ታክኮ የተሰራው የግቢው በር የሆነ ጠንካራ ጥርስ ያለው አውሬ ያላመጠው በሚመስል ጨርማታ ስስ ቆርቆሮ የተሠራ ነው:: ቆርቆሮው የተመታበት እንጨት ምስማሮች ስለላሉ በሩ ሲከፈትና ሲዘጋ እንደ አራስ ልጅ አንገት ልምጥ፣ ልምጥ እያለ ዘጊና ከፋቹን፣ «መገንጠሌ ነው» በሚል ዛቻ ያሳቅቃል::

ሰዎች ከሚመላለሱበት ሳሩ ከተመለጠ ቀጭን የእግር መንገድና የባህር ዛፎቹ ቅርንጫፎች ጥላ ካረፈበትና ቅጠሎቻቸው ከሚረግፉበት ጥግ በስተቀር ግቢው በሳር የተሸፈነ ነው::

## -31-

### «መንገዱ ዳር ቁጭ ብላ ስትስል አገኘኋት::»
### ወ/ሮ አለምአገኝ ካሳሁን

ድንቄ ሰሞኑን ሳል ያጣድፋታል:: ሐኪም ቤት ለመሄድ ገንዘብ ያስፈልጋል:: ገንዘብ የላትም:: በእርግጥ ድንቄ ሐኪም ቤት የመሄድ ጥቅምም አይገባትም:: ሆስፒታል ወይም ጤና ጣቢያ ከመሄድ ባህላዊ መድኃኒቶችን መውሰድ ትመርጣለች:: እያመማትም የዕለት ጉርሣቸውን ለማግኘት ውሃ የማመላለሱን ሥራ ጠንክር ያለች ቀን መስራት ነበረባት::

አንድ ቀን ውሃ ከአስፋልት አካባቢ በጀሪካን ቀድታ ተሸክማ ወደ ሰፈር እያዘገመች ነበር:: ዳገቱን ሽቅብ ስትወጣ አቅም አነሳት:: ያስላት ጀመር:: ወደ ላይ ሊያስመልሳት ሲተናነቃት፣ በጨርቅ ያዘለችውን ጀሪካን መንገድ ዳር አስቀመጠችው:: ደረቷን ደግፋ ቁጢጥ ብላ ተቀመጠች:: ትንፋሽ እስኪያጥራት አሳላት:: ሳሏ ጋብ ያለ መሰለና ድንገት ቋቅ አላት:: ራት አልበላ ብሷት ትንሽ ነው የበላችው:: ቁርስ የሚባል ነገር ዛሬ ብቻ ሳይሆን ባለፉት በርካታ ቀናት አልቀመሰችም:: ከሆዷ የሚወጣ ምግብ ስላልነበረ ለሀጭ መሰል ነገር ከአፏ እየተዝለገለገ በዝግታ ወጣ:: በዚያው ሁኔታ ውስጥ እንደሆነች እንደገና በኃይል አሳላት::

ጎረቤቷ ወ/ሮ አለምአገኝ በዚያ መንገድ ሲመጡ አገኟት::

«ምነው ድንቄ? ምን ሆንሽ?» አሏት ወደ እሷ ቀረብ ብለው::
ድንቄ ደረቷን ይዛ እንዳቀረቀረች፣ «ያመኛል» አለች::

ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ያህል ያለማቋረጥ አሳላት::
ጉሮሮዋ ላይ ሳሉን ተከትሎ የመጣውን ፈሳሽ ተፋችው:: ደም ነበር::

ወ/ሮ አለምአገኝ ደነገጡ::

«እንደዚህ እያመመሽ ምነው ውሃ ማመላለሱ ቢቀርብሽ?» አሏት ፊታቸው ላይ እና ድምፃቸው ውስጥ ጥልቅ ሀዘን እየታየና እየተደመጠ::
«ምን ላርግ? ምን እንብላ? ልጆቼ በረሀብ ከሚያልቁ ብዬ'ኮ ነው::»
ወ/ሮ አለምአገኝ ለአፍታ የሚመልሱት አልነበራቸውም:: «እንዴ! ቢሆንም እንዲህ ታመሽ ውሃ ማመላለስ የለብሽም::»

ድንቄ ምንም ማለት አልቻለችም::
«ለምን ግን ሐኪም ቤት አትሄጅም?»



Sample output to test PDF Combine only



«እሄዳለሁ:: ለነገሩ ሐኪም ለግርማስ ምን ፈየደ? አሳዳነውም እንጂ ስንቱን መድኃኒት ነበር የሚውጠው::»
«ቢሆንም የአንቺና የእሱ በሽታ አንድ ላይሆን ይችላል::»
«እሱስ እዎ:: . . . ሌሎች ሰዎችም ጠበል ሂጂ ብለውኛል:: እስቲ አንዱ'ጋ እሄዳለሁ::»

ወ/ሮ አለምአገኝ ለጥቂት ደቂቃዎች አጠገቧ ቆመው፣ ሲተካከዙና ከንፈራቸውን ሲመጡ ቆዩ:: ድንቄ ጀሪካኑን ዞር ብላ አየችው:: ገና የሚጠብቃትን ዳገት ስታስብ ሐሞቷ ፍስስ አለ:: ቤት አመለዘውድ ታደለን እየተንከባከበች ሽሮ ለመስራት ተፍ፣ ተፍ እያለች ነው:: ውሃውን እንደምንም አድርሳ በምታገኘው ገንዘብ ማባያውን ካልገዛች ወጡን በምን ይበሉታል? ጉልበቶቿን በእጆቿ ተደግፋ በዝግታ ተነሳች:: መገጣጠሚያዎቿ እንደ አሮጌና የዛጉ የበር ማጠፊያዎች የላሉ እስኪመስላት ህመም ተሰማት::

«ቆይ ላሸክምሽ» ብለው ወ/ሮ አለምአገኝ ሃያ ሊትር ውሃ የሚይዘውን ጀሪካን አንስተው ጀርባዋ ላይ አስቀመጡት:: ድንቄ ጀሪካኑ ጀርባዋ ላይ ሲያርፍ፣ 'በደረትሽ ሂ ብለሽ መሬት ላይ ተነጠፊና ለዘለዓለም አትነሺ!' የሚል ተፈታታኝ ስሜት ወጠራት::

ጎረቤቷ ልክ ጀሪካኑን ከሲታ ጀርባዋ ላይ ሲያሳርፉት ያወጣችው ትንፋሽ ድካሟን ነግሯቸዋል:: አዘኑላት፤ ግን ሊረዷት ሁኔታዎች አልፈቀዱላቸውም:: እሳቸው ወደ አስፋልት እየወረዱ ነበር:: ጀሪካኑን በደንብ እንድታዝለው ረድተዋት ቁልቁል ወረዱ::

ድንቄ የጀሪካኑ ክብደት በብዙ እጥፍ የጨመረ መሰላት:: ውሃውን ደፍታ ግማሽ ጀሪካን ውሃ የመውሰድ ሃሳብ ለአፍታ አእምሮዋን አቋርጦ አለፈ:: ውሃውን የምትወስድላቸው ሰዎች ለግማሽ ጀሪካን ውሃ ሊከፍሏት ፈቃደኛ አይሆኑም:: በዚያ ላይ ግማሽ መንገድ ያህል መጥታለች:: ይሄን ውሃ ካላደረሰች ደግሞ ልጆቿ ሊራቡ ነው:: ወጡን አይጠጡት ነገር::

ጥርሷን ነክሳ፣ እግሮቿን እየጎተተች ሽቅብ እንደቀንድ አውጣ ተሳበች:: በህይወቷ እጅግ የተፈተነችበት ቀን ነበር:: ውሃውን ተሸክማ ሰፈር ለመድረስ በየቦታው አሁንም፣ አሁንም ማረፍ ነበረባት:: ወደ ሰፈር ስትቃረብ እሙሻ አገኘቻት::

«ድንቄ ምነው?»
«አልቻልኩም እያመመኝ ነው:: እስቲ አግዢኝ!»

እሙሻ በዕድሜ ከአመለዘውድ ብዙም ባትበልጥም ሰውነቷ ገዘፍ ያለ ነው:: የውሃውን ጀሪካን ተሸክማ ጎረቤት ቤት አደረሰችላት::

ድንቄ ቤት ስትገባ አመለዘውድ ታደለን ፍራሽ ላይ አስተኝታ ወጥ እያማሰለች ነበር:: ፊቷ ላይ ትልልቅ ኪንታሮቶች እዚህም፣ እዚያም ይታያሉ:: ሰዎች ጥፍር ቀለም ያጠፋዋል ስላሏት፣ ከቡርቴ ጥፍር ቀለም ለምና ቀብታዋለች::

«ምነው ቆየሽ?» አመለዘውድ እናቷን ጠየቀች::

«ደክመኝ:: ኡህ! አህ! . . . አሞኛል:: . . . በጣም አሞኛል:: . . . ውይ! ውይ! ውይ! ኡ! . . . » ድንቄ እጅና እግሯ ተገነጣጥሎ እንዳይወድቅ የሠጋች ይመስል ቀስ ብላ የሳር ፍራሹን በእጇ ተደግፋ ቁጭ አለች:: መገጣጠሚያዎቿ ላይ ህመም ይሰማታል:: ጋደም ብላ ሰውነቷ ሙሉ በሙሉ ፍራሹ ላይ ሲያርፍ በረጅሙ ተነፈሰች:: ዝለቷና ድካሟ ከመጠን ያለፈ ነበር::

«አንቺ በዚህ ሽልጦ ግገር!» በእጇ ጨብጣው የነበረውን በትግል የተገኘ ሃምሳ ሳንቲም ወለሉ ላይ ጣል አደረገችው:: ሳንቲሙ የአፈር ወለሉ ላይ በጠርዙ አንድ ስንዝር ያህል ተንከባሎ በገጹ ጋደም አለ::

አመለዘውድ ወጥ ማማሰሏን ትታ እናቷን አትኩራ እያየች ነበር:: ህመምና ድካሟ ከባድ እንደሆነ ተረዳች:: ለአፍታ 'ትሞትብኝ ይሆን?' ስትል አሰበችና ፈራች::

«በቃ ድንቄ ሁለተኛ ውሃ አታምጪ:: በጣም እያመመሽ እኮ ነው:: እኔ እሰራለሁ:: . . . መቼም የምንበላው ነገር አናጣም::» አለች የመጨረሻውን ዓረፍተ ነገር ስትናገር ዕንባ እየተናነቃት::

ድንቄ ለሷ መልስ የምትሰጥበት ጉልበትና ንቃት አልነበራትም:: ኩርምት ብላ ተኛታለች:: የልጇን ድምፅ ሩቅ ከሚገኝ ጋራ ላይ ነጥሮ የመጣ የገደል ማሚቶ ይመስል በሰመመን ውስጥ ሆና ነው የሰማችው::

አመለዘውድም ባለፉት ወራት ጤና አልነበራትም:: እግሮቿ ይተሳሰሩባታል፣ ይደክማታል፣ ያስላታል፣ አሁን ሰሞኑን ደግሞ ፊቷን ትልልቅ ኪንታሮቶች ወረውታል:: ሳሉ ስለበረታባት በቅርቡ ጤና ጣቢያ ሄዳ ተመርምራ ነበር:: የሳንባ ነቀርሳ በሽታ እንዳለባት ተነግሯት መርፌ እየተወጋች ነው:: ደግነቱ ህክምና በነጻ ነው ያገኘችው:: የምትታከምበት የወረዳ 28 ጤና ጣቢያ የሚገኘው አባቷ ይሰሩበት ከነበረበት የወ/ሮ አሰገደች ቤት አካባቢ ስለሆነ ግን በየቀኑ እየተመላለሰች መርፌ መወጋቱ አድካሚና አሰልቺ ሆኖባታል:: የተሰጡዋትን በመቶዎች የሚቆጠሩ ኪኒኖች አስታውሳ መዋጥም ማለቂያ የለሽ ሥራ የመስራት ያህል ይታክታታል::





ውጪ ሠርታ ገንዘብና ምግብ ማምጣት፣ የቤት ውስጥ ሥራዎችን መሥራት፣ ወንድሞቿን መንከባከብ፣ እናቷን ማስታመም . . . የእሷ ኃላፊነቶች ቢሆኑም እምብዛም ምግብ አትበላም:: የሷ ጥጋብ የትንንሽ ወንድሞቿና የእናቷ ጥጋብ ነው:: የእሷ ደስታ የእነሱ ደስታ ነው:: ለራሷ ሆድ ቅንጣት አትጨነቅም:: ብትታመምም መተኛት አትችልም:: ስንትና ስንት ኃላፊነት ተቆልሎባት እንዴት ልቧ አርፎ ትተኛለች?!

ሽሮ ወጡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ደረሰ:: ወጡን አውጥታ እሳቱን አጠፋች:: እናቷ ወለሉ ላይ የጣለችውን ሃምሳ ሳንቲም አንስታ አምባሻ ልትገዛ ወጣች::

አምባሻውን ገዝታ ወደ ግቢያቸው እንደገባች፣ ትንሹ ወንድሟ ታደለ አምርሮ ሲያለቅስ ሰማች:: ጤናዋ በፈቀደላት ፍጥነት ሮጣ ቤት ስትገባ እናቷ የሚጥል በሽታዋ ተነስቶባት ከፍራሹ ተንሸራትታ ወርዳ ወለሉ ላይ አገኘቻት:: ታደለ ከእንቅልፉ ነቅቶ፣ ፍራሹ ላይ ተቀምጦ እናቱን ልክ እንደማያውቃት ሰው ቁልቁል እያየ በፍርሃት ዓይኖቹ ፈጠው ያለቅሳል:: የአመለዘውድ መምጣት ለእሱ ትልቅ እፎይታ ነበር፣ ማልቀሱን ባያቆምም::

አመለዘውድ በእናቷ ዙሪያ ከግድግዳው ሌላ ቢገጫት ሊጎዳት የሚችል ነገር እንደሌለ ለማረጋገጥ እየሞከረች በነበረበት ቅፅበት የወጡን ድስት ከግርጌዋ አየችው:: ፈጥና ወደ ድስቱ ተራመደች:: በዚሁ አፍታ እናቷ ድንገት ተወራጨችና ድስቱን በእግሯ መታችው:: ድስቱ ተንሸራቶ አንድ ስንዝር ያህል እንኳ ከማይርቀው ከቤቱ የጭቃ ግድግዳ ጋር ተጋጨ:: ክዳኑ ተንኳክቶ ወደ አንድ ጥግ ተፈናጠረ:: ድስቱ በአፍጢሙ ሊገለበጥ ያለ መሰላትና አመለዘውድ በፍጥነት ደርሳ አነሳችው:: ትኩሱ ወጥ እጇ ላይ ተረጭቶ ስላቃጠላት ወዲያው ቁጭ አደረገችው:: ሁለት እጆቿን አየሩ ላይ አርገብግባ ለማቀዝቀዝ ሞከረችና እንደገና ድስቱን ከነበረበት አነሳችው:: ትንሽ ወጥ ወለሉ ላይ ቢደፋም፣ ለምሳቸው የሚበቃ ያህል ተርፎ ነበር:: ድስቱን እናቷ የማትደርስበት ቦታ አስቀመጠችው:: እናቷ እግር ላይ ወጡ ተፈናጥቆባታል:: ከአንድ ጥግ አሮጌ ጨርቅ መዝዛ ትኩሱን ወጥ ከእናቷ እግር ላይ ጠረገችላት::

ታደለ ጠባቧን ቤት በለቅሶ አጨናንቋታል:: የድስቱ መንኳኳት፣ የአመለዘውድ ድንጋጤና መሯሯጥ ሽብር ለቆበታል:: አመለዘውድ ወደ እሱ መለስ ብላ አቀፈችው::

«አይዞህ! . . . አይዞህ በቃ! . . . በቃ ዝም በል ታዱ!» እናቷን ቁልቁል በጭንቀት እያየች ትንሽ ወንድሟን አባበለችው::



Sample output to test PDF Combine only

## -32-

*«በእውነት ነው የምልህ ድምጹን አልሰማሁትም እንጂ እግዚአብሔር አዘኛል፡፡*
*መኝታ ቤቴ ከገባሁ በኋላ 'እንዴት አልጠየቅሽም እሷን ሰው?' የሚል ተሰማኝ፡፡*
*. . . አመለዘውድ አንድ የእግዚአብሔር ፀጋ በላዩዋ ላይ ነበር፣*
*የሰው ፍቅር የሚሠጣት፡፡ ለምን እንደጠደድኳት ላስረዳህ አልችልም፡፡»*
*ወ/ሮ ማርታ ገብረጻድቅ*

ወ/ሮ ማርታ ገብረ ጻድቅ አሜሪካ ሁለት ዓመት ያህል ቆይተው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው መጡ፡፡ እ.ኤ.አ. በ1977 ዓ.ም. በአሜሪካ ያቋቋሙት «ፕሮጀክት መርሲ» የሚባለውን መንግሥታዊ ያልሆነ የዕርዳታ ድርጅት በኢትዮጵያ ሥራ ስለጀመረ ስራውን ለመምራት ነው ከባለቤታቸው ከአቶ ደመቀ ጋር የመጡት፡፡

ከዘመዶቻቸውና አቶ ተክሉን ከመሳሰሉ አንጋፋ ሠራተኞች ጋር ሲገናኙ፣ ባለፈው የመጡ ጊዜ አዘውትረው ይጠይቋቸው የነበሩት አቶ ግርማ ግን «እንኳን ደህና መጣሽ!» ሊሉ አልመጡም፡፡

«ግርማ ደህና ነው?» ብለው ጠየቁ፡፡
የአቶ ግርማ ሞት ሲነገራቸው ደነገጡ፣ አዘኑም፡፡

«አዎ፣ ባለፈው ጊዜ በጣም ከስቶ ነበር፡፡ ያመው ነበር ማለት ነው?»
«አዎ፣ የሳንባ በሽታ ነበረበት፡፡»

ወ/ሮ ማርታና አቶ ደመቀ በድርጅታቸው ፕሮጀክት መርሲ ስር ከቡታጅራ ከተማ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ወጣ ብሎ በሚገኝ ቦታ የሕፃናት ማሳደጊያ፣ ት/ቤትና ሆስፒታል አቋቁመዋል፡፡ በድርቅ ለተጎዱ ሰዎች የምግብ ዕርዳታም ያከፋፍሉ ነበር፡፡ የጀመሯቸውን ግብረ ሰናይ እንቅስቃሴዎች ውጤታማ ለማድረግ ላይ፣ታች ሲሉ ሥራ በዝቶባቸው ከራረሙ፡፡

ወ/ሮ ማርታ አንድ ምሽት ሊተኙ ወደ መኝታ ክፍላቸው እንደገቡ ድንገት ስለአቶ ግርማ አሰቡ፡፡

'ግርማስ ሞተ፡፡ «ሚስት አለኝ፡፡ ልጆች አሉኝ፡፡» ብሎኝ ነበር፡፡ . . . ሚስቱ የሚጥል በሽታ እንዳለባትም ነግሮኛል፡፡ ሚስቱና ልጆቹ እንዴት ሆነው ይሆን? . . . እንዴት እንደሆኑ እንኳን እስካሁን ሳልጠይቅ?! . . .' ወዲያው ጊዜ ሳያባክኑ ከመኝታ ክፍላቸው ወጥተው ሠራተኞቻቸውን ጠሯት፡፡

«ተክሉ ነገ እንደመጣ፣ የግርማን ቤተሰብ አምጣልኝ ብላሃለች ብለሽ ንገሪልኝ» አሏትና ተመልሰው መኝታ ክፍላቸው ገቡ፡፡

በሚቀጥለው ቀን ጠዋትም የግርማን ቤተሰብ አስታወሱ፡፡





«ለተክሉ ነገራችሁት?» ብለው ሲጠይቁ እንዳልተነገራቸው ተነገራቸው፡፡ «ጥሩልኝ እስቲ!» አሉ፡፡

አቶ ተክሉ ተጠርተው መጡ፡፡

«ተክሉ ለመሆኑ የግርማ ቤተሰቦች ደህና ናቸው? እሱ ከሞተ በኋላ አግኝተሃቸው ታውቃለህ?»
«ኧረ አግኝቻቸውም አላውቅ፡፡»
«ቤታቸውን ታውቀዋለህ?»
«አዎ፡፡ ሲሞት ቀብር ሄጀ ነበር፡፡ እዚህ ገብርኤል ቤተክርስቲያን አካባቢ ነው፡፡»
«በል እባክህ ሚስቱንና ልጆቹን ዛሬውኑ ሄደህ ይዘህልኝ ና፡፡» አሉ ወ/ሮ ማርታ ከሌሎች ሥራዎቻቸው ሁሉ ዛሬ ለአቶ ግርማ ቤተሰብ ቅድሚያ ሰጥተው፡፡

አቶ ተክሉ ወ/ሮ ማርታ ላይ ያዩት ጥድፊያ አስደንቋቸዋል፡፡

'እነዚያን ደሆች ዛሬ ማስታወሷ ይገርማል! . . . እግዚአብሔር ይስጣት!' ብለው እያሰቡ በዚያው ቀን ወደ ድሮ የሥራ ባልደረባቸው ቤት አዘገሙ፡፡

ወ/ሮ ድንቄና ልጆቿ ወ/ሮ ማርታን በአካል አያውቋቸውም፡፡ አቶ ግርማ ስለእሳቸው ሲያወሩ ግን ሰምተዋል፡፡ ኑሮ ጥቋቁር ማድያት ፊታቸው ላይ እዚህም፣ እዚያም ያተመባቸው፣ ጥቁር ፀጉሮች የሸሹት ነጭ ሉጫ ፀጉር ያላቸው፣ ጠይሙና አጭሩ እዛውንት አቶ ተክሉ ቤታቸው ደርሰው ወ/ሮ ማርታ ሊያገኟቸው እንደሚፈልጉ ሲነግሯቸው፣ ድንቄና አመለዘውድ ከሰማይ እንደተላከ መልዓክ ቆጠሯቸው፡፡

አቶ ተክሉ የድንቄን ከፍተኛ ለውጥ አስተውለው እጅግ አዘኑ፡፡ ከአቶ ግርማ ሞት በኋላ አላዩዋትም፡፡ ባለፉት አራት ዓመታት ያየችው መከራና የኖረችው ጎስቋላ ሕይወት ሁለመናዋ ላይ ይንፀባረቃል፡፡ ከስታለች፣ ጠቁራለች፡፡ ህመሟ ያስከተለው ድካምና በማጣት የተሞላ ኑሮ የፈጠረባት መታከት ፊቷ ላይ በግልጽ ይነበባል፡፡ የለበሰችው ልብስ አሮጌ ነው፡፡ ትልቋ ልጇ አመለዘውድም ቀጭንና፣ ክሳሳ ናት፡፡ ለሳንባ ነቀርሳ በሽታዋ የታዘዘላትን መርፌ ሳትጨርሰው አቋርጣዋለች፡፡ ኪኒኑንም ለሁለት ወር ያህል ወስዳ ሻል ያላት ስለመሰላት መዋጡን ትታዋለች፡፡ ሁለቱ ወንዶች ልጆች ብቻ ናቸው ፊቶቻቸው ወዝ ባይኖራቸውም፣ ጉንጮቻቸው ሞላ፣ ሞላ ብለው የሚታዩት፡፡

ወ/ሮ ማርታ ቤት ደርሰው ግቢው ውስጥ ሲገቡ፣ አመለዘውድ በሕይወቷ አይታ በማታውቀው በአትክልቶች በተጌጠ ሰፊ ግቢ ውብት



Sample output to test PDF Combine only

ፈዘዘች፡፡ የውጪውን አቧራ፣ ግርግርና ድህነት ባለአበባ ሃረጎች የተንጠላጠሉበት ረጅሙ የግቢው የግንብ አጥር በብቃት ጋርዶታል፡፡ ይህ የሰከነ፣ ንፁህና ውብ ዓለም ነው፤ የተለየ ዓለም፡፡ ከቅጥር ግቢው ውስጥ መሆንና ውጪ መሆን ሰማያዊ ገነትና ምድራዊ ዓለም ያላቸውን ልዩነት የሚያሳስብ አስገዳጅ ስሜት ውስጥ ይከታል፡፡ እንደዚህ ለማሰብ ደግሞ ረጅም ግድግዳ ብቻ መብቃቱ ያስገርማል፡፡ አቶ ግርማ ጉልበትና ጤና በነበራቸው ጊዜ ላባቸውን ያንጠፈጠፉበት ግዙፍ መኖሪያ ቤት ከግቢው ዋና በር ፊት ለፊት ይታያል፡፡

«ቆይ አንድ ጊዜ እዚህ ቆዩኝ!» ብለው አቶ ተክሉ ወደ ወ/ሮ ማርታ ቢሮ ሄዱ፡፡

አመለዘውድ የግቢውን ውበት አድንቃ ሳትጠግብ አቶ ተክሉ ተመልሰው መጡ፡፡

«ኑ!»

አዛውንቱን ተከትለው በመዳዳ ከተሰሩት ሰፋፊ ሰርቪስ ክፍሎች አንዱ ውስጥ ገቡ፡፡ የወ/ሮ ማርታና የአቶ ደመቀ ቢሮ ነው፡፡ ባልና ሚስቱ ግቢውን እንደ መስሪያ ቤትም እንደ መኖሪያም ነው የሚገለገሉበት፡፡ የወ/ሮ ማርታ ቢሮ ሁለት ጠረጴዛዎችና ወንበሮች፣ ሌሎችም የቢሮ ዕቃዎች አሉበት፡፡ የቢሮ ዕቃዎቹ መኖር ግን ስፋቱን አልደበቀውም፡፡

እነአመለዘውድ ሲገቡ ለበሩ ቅርብ ከሆነው ጠረጴዛ በስተጀርባ ወ/ሮ ማርታ ተቀምጠዋል፡፡ ወ/ሮ ማርታ ከመቀመጫቸው ተነስተው ተቀበሏቸው፡፡ ከራሳቸው ጎንበስ ብለው ድንቄን ጨበጧት፡፡

«እንደምነሽ?»
«ደህና ነኝ»
ልጆቹንም እየጨበጡ፣«ደህና ናችሁ ልጆች? እንደምናችሁ?» አሏቸው ረጋ ባለና ፍቅር በሚደመጥበት አንደበት፡፡
«ደህና ነን፡፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡» አለች አመለዘውድ፡፡ ገና ካሁኑ ትልቋን ሴትዮ ወደደቻቸው፡፡ ትህትናቸውና ሥነሥርዓታቸው ማረካት፡፡

«ቁጭ በሉ! . . . ቁጭ በሉ!»

ድንቄና አመለዘውድ ከጠረጴዛው ግራና ቀኝ በሚገኙ ወንበሮች ላይ ተቀመጡ፡፡ ድንቄ ታደለን ጭኗ ላይ ስታስቀምጠው፣ አመለዘውድ ደግሞ ለሚካኤል ተጠጋችለትና ወንበሩን ለሁለት ተጋሩ፡፡

«ልጆችሽ እነዚህ ብቻ ናቸው?» ወ/ሮ ማርታ ድንቄን ጠየቁ፡፡





«ሌላ አንድ ወንድ ልጅም አለኝ፡፡ ግን እሱ ከኛ ጋር አይኖርም፡፡ ብዙም አይጠጋኝም፡፡» አለቻቸው፡፡
«የት ነው የሚኖረው?» ወ/ሮ ማርታ በመገረም ጠየቁ፡፡
«የትም ነው የሚውለውና የሚያድረው፡፡ እኔ ምን አውቃለሁ?»
«የለም እንደዛማ አይሆንም፡፡ እሱም አብሯችሁ መኖር አለበት፡፡»
«አቅቶኝ'ኮ ነው፡፡ እኔም አባቱም ወደ ቤት ተመለስ ብለን ተቆጥተነዋል፡፡ ልጁ የሚሰማ አይደለም፡፡»
«ቢሆንም፣ አባብለሽም ቢሆን ወደ ቤቱ መግባት አለበት፡፡»

ለአፍታ ፀጥታ ሰፈነ፡፡

ወ/ሮ ማርታ ጎስቋላዋን ሴት በሃዘኔታ እያዩዋት፣ 'ሰው አትመስልም፣ እንዴት ከስታለች!' ብለው አሰቡ፡፡
«ለመሆኑ እንዴት ነው የምትኖሩት? . . . ማለቴ ምን ትሰሪያለሽ?» ብለው ጠየቋት፡፡
«ምን አገኛለሁ ብለው ነው፡፡ የዕለት ጉርሳችንን ለማግኘት ውሃ አመላልሳለሁ፡፡»
«ውሃ?»
«አዎ»
«ለማን?»
«እኛ ሰፈር ውሃ የለም፡፡ ቤት ለሚሰሩ ሰዎችና ለመጠጥም የሚሆን እየከፈሉኝ ከአስፋልት ውሃ እወስድላቸዋለሁ፡፡ ግን አሁን፣ አሁን እያመመኝ፣ አቅምም እያነሰኝ እሱንም መስራት እያቃተኝ ነው፡፡»

አመለዘውድ የእናቷንና የወ/ሮ ማርታን ውይይት በንቃት ትከታተላለች፡፡ ወ/ሮ ማርታ ቀይ፣ ረጅም፣ ቆንጆ ሴት ናቸው፡፡ ዕድሜያቸው ስድሳዎቹን እያጋመሰ ቢሆንም፣ እርጅና የልጅነት ውበታቸውን መደበቅ ተስኖታል፡፡ የአነጋገር ለዛቸው፣ ሲያወሩ የእጃቸው እንቅስቃሴ ረጋ ማለት እንዲሁም ሰላምታ ሲያቀርቡ ከራሳቸው ዘንበል ብለው የሚያሳዩት ትህትና፣ ከቁመናና ውበታቸው በተጨማሪ ግርማ ሞገስ አጎናፅፏቸዋል፡፡

«አሁን ጤናሽንስ እንዴት ነሽ?» ወ/ሮ ማርታ ጠየቁ፡፡
«ያመኛል» አለች ድንቄ አቀርቅራ፡፡
ዝም አሉ ወ/ሮ ማርታ፡፡
«. . . ያመኛል» አለች ድንቄ ደግማ፡፡
«የሚጥል በሽታ እንዳለብሽ፣ ነፍሱን ይማረውና ግርማ ነግሮኝ ነበር፡፡»
«አዎ፣ ይጥለኛል፡፡»
«የሚጥል በሽታን'ኮ በህክምና ማዳን ባይቻልም መከላከል ግን ይቻላል፡፡»
«ይቻላል ብለው ነው?»



Sample output to test PDF Combine only

«አዎ፣ እንዳልኩሽ ሙሉ በሙሉ ባይድንም መውደቁን በመድኃኒት ማስቀረት ይቻላል:: እኛ እናሳክምሻለን:: ዛሬ ማታ ወደ ውጪ እሄዳለሁ:: ስመለስ አንድ ቀን ትመጪና ሃኪም'ጋ እንወስድሻለን::»

«እሺ፣ እግዜር ይስጥልኝ::» አለች ድንቄ ከተቀመጠችበት እንደመነሳት እያለች::

«ዛሬ የጠራኋችሁ ትናንት በአጋጣሚ፣ እንዲያው እንደድንገት አስቤያችሁ ነው:: ያው ብዙም ገንዘብ ባይሆን በየወሩ ትንሽ እርዳታ እናደርግላችኋለን::»

«እሺ! እግዜር ይስጥልኝ የኔ እመቤት!» አለች ድንቄ ከመቀመጫዋ እንደመነሳት ብላ እጅ እየነሳች::

የአመለዘውድ ጠይም ፊት በውብ ፈገግታ ደመቀ::

ቡታጅራ አቅራቢያ በሚገኘው የሕፃናት ማሳደጊያ በፕሮጀክት መርሲ ለሚረዱት ሕፃናት ከተዘጋጁ ልብሶች ለነአመለዘውድ ልብስ እንዲያመጡላቸው ወ/ሮ ማርታ ባዘዙት መሠረት ልብስ በልካቸው ተመርጦ መጣላቸው::

መጀመሪያ ለአመለዘውድ ነበር የሰጧት:: ልብሱን ከተቀበለች በኋላ አንድ ያልጠበቁት ባህሪ አስተዋሉባት:: ልብሱን አገላብጣ ለማየት ቅንጣት ጉጉት አልነበራትም:: የራሷን ልብስ ተቀብላ አንዴ ሁለቱን ወንድሞቿን፣ ሌላ ጊዜ ወ/ሮ ማርታን ማየት ጀመረች:: ደስ ያላትም አትመስልም:: ወ/ሮ ማርታ ሁኔታዋ አስገረማቸው:: ለሁለቱ ወንድሞቿ ልብስ ከሰጡዋቸው በኋላ ነበር አመለዘውድ የራሷን አገላብጣ ማየት የጀመረችው::

«እግዜር ይስጥልን እማማ! በጣም እናመሰግናለን!» አለቻቸው የሚያምረውን ልባዊ ፈገግታዋን እየፈገገች::

ወ/ሮ ማርታ አንድ ለየት ያለ ነገር በድምጿ ውስጥ አደመጡ:: አነጋገሯ እንደአዋቂዎች አነጋገር የሆነ ጥንካሬና ክብደት ነበረው:: በእሷ ዕድሜ ያሉ ልጆች በራሳቸው ደስታ ስለሚዋጡ ለማመስገን አይጨነቁም:: ቢያመሰግኑም ልክ እንደአመለዘውድ በሙሉ የራስ መተማመንና ግልፅ በሆኑ ቃላት ማመስገን ይሳናቸዋል::

'ለየት ያለች ልጅ ናት::' ሲሉ አሰቡ::

☆ ☆ ☆

በሚቀጥለው ወር ከወ/ሮ ማርታ የተቆረጠላቸውን ገንዘብ ለመውሰድ አመለዘውድ ብቻዋን መጣች:: ወ/ሮ ማርታ ከሄዱበት ውጭ አገር ተመልሰው ነበር::





«እንደምን ነዎት እማማ? ደህና ነዎት?» በትህትና ጎንበስ ብላ ወ/ሮ ማርታን ጨበጠቻቸው::

«እንዴት ነሽ?» አሏት ወ/ሮ ማርታ የአዋቂ በሚመስል ሰላምታ አሰጣጧ እየተደነቁ::

«ስምሽን ማን ነበር ያልሽኝ?»

«አመለዘውድ»

«የአለምዘውድ?»

«አይ» ሳቅ አለች:: «አመለዘውድ»

«አመለዘውድ? . . . እሺ ያለምዘውድ»

አመለዘውድ ወ/ሮ ማርታ ደግመው ስሟን ሲጠሩ በመሳሳታቸው ሳቅ አለች:: ወ/ሮ ማርታ ገባቸው::

«አመለዘውድ ነው ያልሽኝ?» አሉ ፈገግ ብለው:: «እናትሽ እንዴት ናት?»

«ዛሬ ትንሽ ስላመማት ነው እኔ ብቻዬን የመጣሁት::»

«ምነው? ምን ሆነች?»

«አንዳንድ ጊዜ ያማታል::» አመለዘውድ እንደመተከዝ ብላ ዝም አለች::

«እናሳክማታለን:: በቀደም ዕለት ስትመጡም ነግሬአት ነበር ::»

«አዎ»

«በቃ በሚቀጥለው ጊዜ ስትመጪ ይዘሻት ነይና እናሳክማታለን ::»

«እሺ እማማ» ደስ አላት ::

«ትትንሾቹ ወንድሞችሽስ?»

«እነሱ ደህና ናቸው::» ፈገግ አለች::

ወ/ሮ ማርታ ልጅቷን እየወደዷት ነው:: ሥነስርዓቷ፣ ለሳቸው የምታሳየው አክብሮትና ፊቷ ላይ የሚነበበው ፍቅር አስደስቷቸዋል::

«ትምህርትሽን እየተማርሽ ነው አይደል?»

«አይ በዚህ ዓመት ትምህርት አቋርጫለሁ:: እናቴን ስለሚያማት ቤት ውስጥ ሥራ እሰራለሁ:: ውጪም እየሰራሁ እናቴን እረዳታለሁ:: ትንሹን ወንድሜንም ማሳደግ ስላለብኝ ለመማር አልተመቸኝም ነበር::»

«እና አትማሪማ?» ወ/ሮ ማርታ አዝነውና ተገርመው::

«መማር በጣም እፈልጋለሁ:: ትምህርት እወዳለሁ:: አሁን እርስዎ ስለሚረዱን በሚቀጥለው ዓመት ትምህርት ለመጀመር አስቤአለሁ::»

«አዎ፣ ትምህርትሽንማ መቀጠል አለብሽ::»

«እሺ እማማ፣ እማራለሁ::»

'እንዲህ ብለውኝ ነው? ትምህርት ምን ያህል እንደምወድ ቢያውቁ!' ስትል አሰበች::



Sample output to test PDF Combine only

ወ/ሮ ማርታ በወር ሊሠጧቸው ያሰቡትን ገንዘብ ሰጥተው ሸኟት። የወ/ሮ ማርታ ዕርዳታ በጣም ስለሚያስፈልጋቸው አመለዘውድ ወር እስኪሞላ መጠበቅ አልቻለችም። በየጊዜው እየመጣች ችግሮቻቸውን ታስረዳለች። ብዙ ጊዜም ቀና ምላሽ ታገኛለች። ብትመጣ እንደሚያሳክሟት ወ/ሮ ማርታ ቢናገሩም፣ ድንቄ ችላ ስለምትል ይዛት ለመምጣት ‘ቆይ ዛሬ፣ . . . ቆይ በሚቀጥለው ስሄድ . . .’ ስትል አልሆነላትም ።



Sample output to test PDF Combine only



# -33-

*«እኔ ሞት ምን እንደሆነ ስለማላውቅ፣ አልገባኝም።»*
*ብዙነሽ መሃመድ (እሙሽ)*
*«‘ድንቄ ምን ሆና ነው? ኑ እስቲ እዩዋት’ አለችን።»*
*ወ/ሮ አለምአገኝ ካሳሁን*

ጥቂት ወራት አለፉ። ድንቄ ብዙ ጊዜ ትታመማለች። ሰሞኑን ደግሞ ህመሟን ለመርሳት እንደመፍትሄ ያደረገችው አረቂ አዘውትራ መጠጣት ነው። አልኮል ህመሟን ለሰዓታትም ቢሆን ያስረሳታል። ሠርታም ይሁን ለምናና አስለምና ገንዘብ ስታገኝ ጎረቤት ወዳሉት አሮጊት አረቂ ሻጭ ቤት ለመሄድ ትጣደፋለች።

አንድ ቀን ድንቄ ትንሹ ታደለን፣ «ዛሬ አረቂ መጠጣት አለብኝ! ታዴ፣ እስቲ ሂድና ለድንቄ የቡና መግዣ ብለህ ከጎረቤት ፍራንክ ለምን!» ብላ ላከችው።

ታደለ የተባለው ተምታታበትና፣ «ድንቄ እንዳለች፣ ‘ያረቂ መግዣ ፍራንክ ስጡኝ!’» ብሎ በጣፋጭ የልጅ አንደበቱ ሲለምን ተለማኙ ጎረቤት እጅግ ተገርመው ከት ብለው ሳቁ። ይህ የታደለ ስህተት አንድ ሰሞን የሰፈሩ መነጋገሪያና መሳቂያ ርዕስ ሆኖ ነበር።

ድንቄ አልፎ አልፎ ደግሞ ሻል ሲላት መሥራት የምትችለውን ስራ ለመስራት ቀና፣ ደፋ ትላለች። ልብስ ታጥባለች፣ እንጀራ ትጋግራለች። አንድም፣ ሁለትም ብር ቢሰጧት፣ ዝም ብላ ተቀብላ ትሄዳለች፤ አነሰኝ ብላ አትከራከርም። ሠርታም ይሁን ለምና ወይም ትንሹ ታደለን ለቡና ብላ አስለምና ሳንቲምና ብር ካገኘች፣ ህመሟን ለመርሳት አረቄዋን ትጠጣለች።

የሚጥል በሽታዋ ቶሎ፣ ቶሎ ይጥላታል። አረቂ መጠጣት የሚጥል በሽታዋን እንደሚቀሰቅስባት አመለዘውድ ተረድታለች ። እንዳትጠጣ ብትመክራትና ብትለምናትም ድንቄ አትሰማም። ወ/ሮ ልኬ ቤት እያለች በዓመት፣ በሁለት ዓመት አንዴ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ደግሞ በወር፣ በሁለት ወር ነበር የሚጥላት። አሁን ግን ከዚህ በፊት ባልተለመደ ሁኔታ በሁለትና በሶስት ቀን ልዩነት ሆነ የምትወድቀው። ወድቃ አጠገቧ ካለ ነገር ጋር ስትጋጭ የተወሰኑት የፊት ጥርሶቿ ወለቁ። ሁኔታዋ ለአመለዘውዷ የሚያስቅቅና የሚያሳዝን ነበር። የሚጥል በሽታን ፈጽሞ ማዳን ባይቻልም፣ ራስን የመሳቱና የመውደቁን ሁኔታ ግን በሐኪም የሚታዘዝ መድኃኒት ያለማቋረጥ በመውሰድ መከላከል ይቻላል። አቶ ግርማም ሆነ ሌሎች የሚያውቋት ሰዎች መታከም እንደምትችል ስለማያውቁ፣ ድንቄ አንድም ቀን ሐኪም ቤት ሄዳ አታውቅም።

ሐኪሞች እንቅልፍ፣ በመተኛትና በመንቃት መሃል ያለው የሰመመን ጊዜ፣ ድካም፣ ህመም፣ ሆድ ድርቀት፣ የወር አበባ፣ ጭንቀት እና አልኮል መጠጣት የሚጥል በሽታን እንደሚቀሰቅሱ ይናገራሉ። ከአንድ ከሁለቱ በስተቀር፣ ድንቄ ለእነዚህ የበሽታው ቀስቃሾች በሙሉ የተጋለጠች ነበረች።

ወ/ሮ ልኬ ሚካኤልን አስፋልት አካባቢ አግኝተው ደግመው ወስደውት፣ እሳቸው ቤት ማደርና መዋል ከጀመረ ጥቂት ወራት ተቆጥረዋል። አመለዘውድ በሚካኤል መሄድ አሁንም ደስተኛ አይደለችም። የተሻመ አንሶ ደግሞ ታናሽ ወንድሟ ከአጠገቧ እንዲርቅ አትፈልግም። ሚካኤል ግን ጥሩ ምግብ በተገቢው ሰዓት ስለሚያገኝ ወ/ሮ ልኬ'ጋ ሳይራብ መኖሩን አልጠላውም። ቄስ ትምህርት ቤት አስገብተውት ፊደል መማርም ጀምሯል ።

ድንቄ ከፍተኛ እንክብካቤ ስለሚያስፈልጋት አመለዘውድ ከቤት አካባቢ አትጠፋም። ሚካኤልን ለመጎብኘት ብዙም ጊዜ አልነበራትም። ራሱ ሚካኤል ግን አንዳንድ ጊዜ፣ ከት/ቤት እየቀረም ቢሆን፣ ወደ ቤት ጎራ ብሎ እናቱን፣ እህቱንና ታናሽ ወንድሙን ይጠይቃል።

አንድ ቀን አመለዘውድ እነእሙሽ ቤት ሄዳ ከእሙሽ ጋር ቁጭ ብለው እያወሩ ነበር። ድንገት በጨዋታቸው መሃል እንደ መተከዝ ብላ፣ «ሰሞኑን ድንቅዬ አሟታል» አለች አመለዘውድ።

«አዎ፣ ክስትስት ብላለች።» አለች እሙሽ።

«አዎ፣ ከስታለች አይደል?» ብላ አመለዘውድ ዝም አለች። ሃሳብ ገባት።

«. . . ዛሬ እንዴት ናት?»

«ያው ናት። ተኝታ ነው ያረፈደችው።» ትንሽ ተካከዘችና፣ «. . . እስቲ ሄጄ ምሳ ልስጣት» ብላ አመለዘውድ ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ቤታቸው ሄደች።

ቤት ስትገባ ድንቄ የሳር ፍራሹ ላይ ተኝታ ነበር። ቀና ብላ አመለዘውድን አየቻትና፣ «ልጄ ስንቄን ስጪኝ!» አለቻት።

«ምን አልሽ ድንቄ?»

«ስንቄን ስጪኝ!»

«የምን ስንቅ?»

«እንጀራ ስጪኝ!»

«ምሳ ስጪኝ ነው እንዴ የምትይኝ?»

«አዎ» አለች እናቷ።

ባለፉት ጥቂት ወራት ድንቄ የምግብ ፍላጎቷ በጣም ቀንሷል። አመለዘውድ ብትጨቀጭቃትም በደንብ አትበላም። ዛሬ ያለወትሮዋ ምሳ ማለቷ አመለዘውድን አስደነቃት።



Sample output to test PDF Combine only



ምሳ አዘገጃጀታ፣ ታደሰን ከጎረቤት ጠርታ፣ ምግቡን አብረው በሉ። ድንቄ ትንሽ በላች።

«ምነው? አትበይም?»

«በቃኝ»

ታደሰ ተመልሶ ወደ ጎረቤት ቤት ሊጫወት ሄደ። አመለዘውድ ለድንቄ ቡና አፈላችላት። ዕድሜ ለወ/ሮ ማርታ! አመለዘውድ አሁንም ለተጨማሪ ገቢ መስራት ቢኖርባትም፣ እሳቸው ቤተሰቡን በገንዘብ መደጎም ከጀመሩ በኋላ ለልመና ጎረቤት ቤት ከመንከራተት ድናለች።

ድንቄ የምትወደውን ቡና ጠጣች።

እናቷ ቶሎ መተኛት እንደምትፈልግ አመለዘውድ ተረድታለች። ቡና ከጠጣች በኋላ ድንቄ ተመልሳ ፍራሹ ላይ ጋደም አለች። ባለፉት ጥቂት ወራት የሰውነቷ ክብደት በፍጥነት ቀንሷል። ጉስቁልቁል ብላለች። ስለሚደክማትና አቅም ስለሚያንሳት በተለይ ከሁለት ሳምንታት ወዲህ ጭራሽ ከምትተኛበት ፍራሽ አልተነሳችም።

«አይዟችሁ! ምንም አትሆኑም። እግዚአብሔር አለላችሁ።» አለች ድንቄ።

አመለዘውድ ስኒዎቹን አጣጥባ ሳታነሳ እዚያው ተቀምጣ ነበር። ግራ ገባት። እናቷ ጋደም ብላ ዓይኖቿን ታቁለጭልጭ ጀመር። ዓይኖቿ ድንገት መቁለጭለጫቸውን አቁመው ፈጠጡ።

«ድንቄ!» አመለዘውድ እናቷን ተጣራች።

እናቷ እንደ ወትሮዋ «አቤት» አላለቻትም። ዓይኗ እንደፈጠጠ ድርቅ ብላለች።

«ድንቄ!»

ዝም።

ነቅነቅ አደረገቻት። አሁንም ዝም አለቻት። እጇን በአንገቷ ሥር አሾልካ አቀፈቻትና ደጋግማ ጠራቻት።

«ድንቄ! . . . ድንቄ! . . .»

ድንቄ ዓይኖቿ እንደፈጠጡ በዝምታዋ ገፋችበት። አመለዘውድ ዓይኖቿ አስፈሯት። በጣቶቿ ዳብሳ ከደነቻቸው።

«ድንቄ! . . . ድንቄ!»

ድንቂ መልስ አልሰጠቻትም::

ግራ ገባት:: እናቷ በየጊዜው ትታመማለች፣ ሻል ሲላት ትነሳለች:: ደግማ ትታመማለች . . . :: ይህን ሁኔታዋን ስለለመደችው ዛሬ የተለየ ነገር ይፈጠራል የሚል ሥጋት የላትም::

እንደገና ፍራሹ ላይ አስተኛቻት::

«ድንቂ!»

እናቷ ፀ . . . ጥ ብላ መተኛቷን ቀጠለች:: አመለዘውድ እጇን ትከሻዋ ላይ አሳርፋ ደጋግማ ነቀነቀቻት:: ድንቂ አልነቃችም:: ከግማሽ ሰዓት በፊት ምሳ ስትበላና ቡና ስትጠጣ የነበረችው እናቷ አሁን ብትነቀነቅ የማትሰማው ምን ሆና ነው? ምን ዓይነት ከባድ እንቅልፍ ነው?!

«ድንቂ! . . . ድንቂ!»

የእናቷ ሰውነት ዝልፍልፍ አለባት:: የዛሉ እጆቿ ከያሉበት ተንሸራተው ፍራሹ ላይ አርፈዋል::

«እንዴ! ድንቂ! ምነው? ምን ሆንሽብኝ?» አለች አመለዘውድ:: ተሸበረች:: ልቧ ድም፣ ድም፣ ዱጭ፣ ዱጭ አለባት::

'ምን ሆና ነው?' አመለዘውድ በርከክ ካለችበት ተነሳችና እናቷን በፍርሃት ለአጭር ጊዜ ስታያት ቆየች::

'እነእሙሻን ሄጄ ልጠይቃቸው እስቲ' እናቷ የለበሰችውን ጋቢ አስተካክላ አለበሰቻትና ወደ እነእሙሻ ቤት በጥድፊያ ሄደች::

ገና ቤት ለመግባት ጥቂት እርምጃዎች እየቀሯት፣ «እሙሻ! . . . እሙሻ!» ብላ እየተጣራች ወደ እነእሙሻ ቤት በፍጥነት ዘለቀች::

እሙሻ አመለዘውድ ፊት ላይ ፍርሃትና ግራ መጋባት አነበበች::

«ምነው አመለዘውድ?»

«ድንቂ፣ ድንቂ ስቀሰቅሳት አትሰማም:: አትናገርም:: ነይ እስቲ አንዴ!»

እነአመለዘውድ ቤት ሁለቱ ልጆች ተከታትለው ሲገቡ ድንቂ አመለዘውድ ትታት እንደሄደችው ነበረች::

«ድንቂ! . . . ድንቂ! . . . ድንቂ! . . .» እያለች እሙሻ ደጋግማ ጠራቻት::





አመለዘውድ በቆመችበት ሰውነቷ በፍርሃት እየራደ ካሁን፣ አሁን ድንቂ ትነቃለች በሚል ተስፋ ጠበቀች:: 'እናቴ ሞታለች' ብላ ለማሰብና ለመገመት በጣም ከበዳት::

'ብዙ ጊዜ ታማ ተኝታለች፤ ዛሬ ለምን ትሞታለች? ምሳ አብረን በልተን አይደል? ለምን ትሞታለች? እንዴት ትሞታለች? ሞት እንደዚህ ነው እንዴ?' በጭንቀት የተወጠረ ጭንቅላቷን በየደቂቃው በጥያቄዎች ትሞላዋለች::

እሙሻ የድንቂን እጅ ይዛ ሳብ፣ ጎተት ስታደርጋት ድንቂ ከፍራሹ ላይ ገልበጥ ብላ ወለሉ ላይ በደረቷ አረፈች:: እሙሻ ዞር ስትል አመለዘውድ በፍጥነት ከቤት ስትወጣ አየቻት::

አመለዘውድ እናቷ የሆነችውን ሌሎች ሰዎች እንዲያረጋግጡላት ፈልጋለች:: ግቢያቸውን አቋርጣ በቤቶች ከግራና ከቀኝ የታጠረውን ቀጭን መንገድ አልፋ ሰፊው መንገድ ላይ ወጣች::

ወ/ሮ አለምአገኘንና ዮናስ የተባለ ወጣት የሰፈሩን ነዋሪ መንገዱ ላይ አገኘቻቸው::

«ድንቂ! ድንቂ! ምን እንደሆነች እንጃ! . . . ወይኔ ድንቂ!» አለች አመለዘውድ ትንፋሿ ቁርጥ፣ ቁርጥ እያለ::

«ምነው? ድንቂ ምን ሆና ነው?» ወ/ሮ አለምአገኘና ዮናስ ግራ ተጋቡ::

«እኔ እንጃ! እስቲ እዩዋት! . . . ወይኔ ድንቂ! አትናገርም፤ ዓይኗም ተከድኗል::»

ዮናስና ወ/ሮ አለምአገኘ እየተጣደፉ ወደ እነአመለዘውድ ቤት አመሩ::

እሙሻ ድንቂ የሆነችው አልገባትም:: አመለዘውድ ጮክ ብላ ስትናገር ከሩቅ ይሰማታል:: ድንግርግር አላት:: ነጠላ ትከሻዋ ላይ ጣል አድርጋ ነበር:: በደመነፍስ ነጠላዋን አውርዳ ድንቂን አለበሰቻትና ከቤት ፈጥና ወጣች:: ዮናስና ወ/ሮ አለምአገኘ ወደ ግቢው ሲገቡ አየቻቸው::

ሁለቱ አዋቂዎች ቤቱ ውስጥ ሲገቡ ድንቂ በደረቷ ወለሉ ላይ ፀጥ ብላ ተኝታለች:: ወ/ሮ አለምአገኘ መጠጋት ፈርተው በሩ አካባቢ ቆሙ:: ዮናስ ጠጋ ብሎ ድንቂን ብብቶቿ ውስጥ እጆቹን አስገብቶ ከወደቀችበት ሲያነሳት፣ ሰውነቷ ዝልፍልፍ አለበት:: ክብደቷ ቀላል ስለነበር፣ የሌላ ሰው ዕርዳታ ሳያስፈልገው አንስቶ ፍራሹ ላይ አሳረፋት:: ለአፍታ በጥንቃቄ አስተዋላት:: ሰውነቷንም ነቅነቅ አደረገው:: ህይወት አልባ እንደሆነች በታላቅ ድንጋጤ ተረዳ:: ቀና ብሎ ወ/ሮ አለምአገኘን አያቸው:: ተያዩ::

«ሞታለች» አላቸው::

ወ/ሮ አለምአገኘ፣ «ውይ!» ብለው ራሳቸውን ያዙና ማልቀስ ጀመሩ::

አመለዘውድ ሌሎች ሰዎችን አስከትላ ወደ ቤቱ ውስጥ ገባች::



Sample output to test PDF Combine only

«ድንቂ ምን ሆና ነው? . . . እናቴ ምን ሆና ነው?»

«አይዞሽ አመለዘውድ! አይዞሽ በቃ!» አላት ዮናስ፣ እናቷን አመቻችቶ አስተኝቶ ከተቀመጠበት እየተነሳ።

«ምነው ሞታለች?» ብላ ዮናስን ጠየቀችው።

ለአፍታ ዓይኖቹን ወደ ዓይኖቿ ወርውሮ ረጋ ባለ ድምጽ፣ «አዎ» አላትና፣ «. . . አይዞሽ በቃ!» የሚል የማጽናኛ ቃል አከለበት።

«ኡ! ወይኔ ድንቂ! ወይኔ እናቴ! ድንቅዬ፣ እኔ ልሙትልሽ! ወይኔ! . . .» አመለዘውድ ራሷን ይዛ ጮክ ብላ ማልቀስ ጀመረች።

እናቷ በየጊዜው ብትታመምም ሁልጊዜ ትድናለች የሚል ተስፋ ነበራት። የድንቂ ሞት ለእሷ እጅግ ያልተጠበቀ ነበር።

«ወይኔ እናቴ! ድንቂ! የኔ ድንቅ እናት! ድንቅዬ! ኡ! . . .»

ከቀኑ ሰባት ሰዓት ገደማ ሆኖ ነበር። የጎረቤት ሰዎች ተጠራርተው ተሰባሰቡ። ከአንድ ሰዓት በኋላ የድንቂ ሬሳ በሰሌን ተጠቅልሎ ለቀብር ተዘጋጀ።

አመለዘውድ ሐዘኗ ከባድ ነበር። እናቷ መሞቷን ለማመን ቸግሯታል። የእናቷን ሬሳ በሰሌን ተጠቅልሎ ስታይ ነበር ከእናቷ ጋር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የመለያየታቸው ነገር ቁልጭ ብሎ የተገለጸላት።

'እናታችን እንዴት እኛን ትታን ሞተች? እንዴት ዛሬ ሞተች? እሷ ሳትኖር እንዴት ነው ብቻችንን የምንኖረው?' ስትል እያሰበች በግራ መጋባት ውስጥ ሆና አነባች። ቤቱ ያለእናቷ ባ . . .ዶ ሲሆን ታያት። ሲሞት፣ ቅዝቅዝ ሲል ተሰማት። እንደዚያ ዓይነት ቤት ውስጥ እሷና ወንድሞቿ እንዴት ሆነው ነው የሚኖሩት?! የሚያስፈራና የሚያስጠላ ህይወት ሲመሩ ታያት። እሷ ለራሷ ቅንጣት አልተጨነቀችም። መኖር ካለባት የምትኖረው ለወንድሞቿ ስትል ብቻ እንደሆነ አሰበች። ያማታል፤ እንደ ድንቂ እሷም በቅርብ ቀን በድንገት ልትሞት እንደምትችል አመነች። ለመኖር ምንም ጉጉት አልነበራትም። ትንንሽ ወንድሞቿ ግን ይኖራሉ፤ መኖር አለባቸው። የእነርሱ ነገር እጅግ አስጨነቃት።

'እሺ አሁን ወንድሞቼ ምን ሊውጣቸው ነው? የሚረዳን ዘመድ የለ። ማን አለን? ማን ያሣድገናል? የት እናድራለን? እቤታችን ብናድር አንፈራም?'

«ወይኔ ድንቂ ምነው? ምነው? ብቻችንን ጥለሽን? ምነው ድንቂ?» እየጮኸች ራሷን ይዛ አለቀሰች።





# -34-

*«'እናቴን ወስደው ሊቀብሯት ነው። እናንተ ሳትደርሱ እንዲቀብሯት አልፈልግምና ኑ ከእኔ'ጋ' አለችኝ።»*
*ወ/ሮ ማርታ ገብረጻድቅ*

ወ/ሮ ማርታ ገብረጻድቅ ከባለቤታቸው ከአቶ ደመቀ ጋር ቢሮዋቸው ሆነው ጫጫታና ለቅሶ ሰሙ።

«የምን ለቅሶ ነው? እዚህ ቤት ነው ወይስ ከግቢ ውጪ?» አሉ ወ/ሮ ማርታ። «ግቢ ውስጥ ይመስላል» አሉ አቶ ደመቀ።

ባልና ሚስቱ ከቢሮዋቸው ወጡ። ማዕድ ቤቱ አካባቢ የግቢው ሠራተኞች አንድ ቦታ ተሰብስበዋል።

ወደ ሰዎቹ እየተጠጉ፣ «ምንድነው?» ብለው ወ/ሮ ማርታ ሲጠይቁ አመለዘውድ በሰዎቹ ተከባ ስታለቅስ አዩ።

«ምንድነው? . . . የግርማ ልጅ! አንቺ ነሽ እንዴ? ምነው? ምን ሆንሽ?» አሏት።

«እናቴን ወስደው ሊቀብሯት ነው። እናንተ ሳትደርሱ እንዲቀብሯት አልፈልግም። እባካችሁ ኑ ከኔ'ጋ!» አለች አመለዘውድ እያለቀሰች።

«አረፈች?!» ወ/ሮ ማርታ ክው ብለው ደነገጡ።

«አዎ! አሁን ከምሳ በኋላ ሞተችብኝ።» አለች አመለዘውድ «ሊቀብሯት ነው። እባካችሁ ኑ ከኔ'ጋ!»

«መቼ ነው የሚቀብሯት?» ብለው ጠየቋት ወ/ሮ ማርታ።

«አሁን ሊቀብሯት ነው። በሰሌን ጠቅልለዋታል።»

«ምን? በሳጥን አላደረጓትም?!»

«በሰሌን ነው የጠቀለሏት» አለች አመለዘውድ ያለማቋረጥ የሚወርደውን ዕንባዋን በእጇ እየጠረገች።

ወ/ሮ ማርታ አንዱን ሹፌር ጠርተው ሳጥን በአስቸኳይ ገዝቶ እንዲመጣ ላኩት። ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ከባለቤታቸው ጋር አመለዘውድን ይዘው በመኪና ወደ እነአመለዘውድ ሰፈር እየተጓዙ ነበር። ቤት ሲደርሱ የሰፈሩ ነዋሪዎች ግቢው ውስጥ ተሰብስበዋል። ድንቂን ለመቅበር የአመለዘውድን መምጣት ብቻ ነበር የሚጠብቁት።

ወ/ሮ ማርታ ለጎረቤት ሰዎች ሳጥን እንዲገዛ ሰው መላካቸውን አሳወቁ። ለቅሶ ደራሾቹ ሳጥኑ እስኪመጣ መጠበቅ ጀመሩ። ቤቷ ጠባብ ስለሆነች ወ/ሮ ማርታና ባለቤታቸው፣ ሌሎችም ለቅሶ ደራሾች ውጪ ነበር የተቀመጡት። ተሾመና ሚካኤልም ከያሉበት ተጠርተው መጥተው ነበር። ተሾመ በጣም



Sample output to test PDF Combine only

ደንግጧል። እሱም እንደ እህቱ እናቱ ብትታመምም፣ ትሞታለች ብሎ አስቦ አያውቅም ነበር። ደህና እንደሆነች ነበር የሚያስበው። ሚካኤል ልጅ ስለሆነና ሞት ምን ማለት እንደሆነ በደንብ ስላልገባው ግራ ተጋብቷል።

ከወ/ሮ ማርታ ቀደም ብለው በሌላ መኪና የመጡት የወ/ሮ ማርታ ዘመድ፣ ወ/ሮ ወርቅነሽና ሌላ አንዲት ሴት ገዝተው ያመጡትን ስንዴና ሽንብራ መልቀም ጀምረዋል፣ ንፍሮ ሊያዘጋጁ። ወጥ ለመስራትና ቡናም ለማፍላት የጎረቤት ሴቶች እያገዟቸው ጉድ፣ ጉድ እያሉ ነው።

ሳጥኑን የያዘው መኪና ትንሽ ቆይቶ ደረሰ። ሬሳው ሳጥን ውስጥ ገብቶ የቀብር ዝግጅት ሲጠናቀቅ ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ሆኖ ነበር።

«አሁን አስራ አንድ ሰዓት ሆኗል። መሸ። ለምን አሳድረን ነገ አንቀብራትም?» ብለው ጠየቁ ወ/ሮ ማርታ።

«በፍፁም! ዛሬ ነው መቀበር ያለባት። መሬቱ ተቆፍሯል። ሁሉም ነገር ተዘጋጅቷል።» አሉ ከጎረቤቶቹ አንዷ።

ድንቋ ቅርብ በሚገኘው ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ልጆቿ፣ ጥቂት ጎረቤቶቿና እነወ/ሮ ማርታ በተገኙበት በዚያው ዕለት ተቀረበች። ቀብሩ ላይ ወ/ሮ ማርታ ልጆቹን በኃላፊነት ስሜት የሚንከባከብ፣ በአጠቃላይ ቀብሩንም በኃላፊነት የሚያስተባብር ሰው አለመኖሩን ታዝበው እጅግ ተገረሙ። በጣምም አዘኑም።

«በሉ ቀባሪው ሁሉ እንዳይበተን! ቤት እንሂድና ቡና ቁርስ ቀምሰን እንለያያለን።» አሉ ወ/ሮ ማርታ ቢቸግራቸው።

«እሺ»

ጎረቤቶቹ ሰብሰብ ብለው መወያየት ጀመሩ።

«እነዚህን ልጆች ለአንድ ወይም ለሁለት ሳምንት እንረዳቸው ይሆናል። ከዚያ በኋላ ግን ዞርም ብለን ላናያቸው እንችላለን። ልንረዳቸውም ብንፈልግ አቅሙ የለንም።» አሉ አንዷ ሴትዮ።

«ኧረ ከሰልስቱ በኋላም ዞር ብለን አናያቸው። እኛስ መች ሞላልንና የሰው ልጅ እናሳድጋለን?»

«እና ምን ይሻላል?»

«እኚህ ሴትዮ ዛሬውኑ እንዲወስዷቸው ማድረግ አለብን።»

«ዛሬውኑ?!»

«አዎ፣ እስከ ሰልስቱም ለመቆየት ዕድር፣ ቤተዘመድ ሲኖር እኮ ነው። እነሱ ከኛ ሌላ ማን አላቸው? እኛ ደግሞ ለቅሶውን ደርሰናል፣ ቀብረናል። ዛሬ፣ አሁኑኑ ቁርጡን ነግረናቸው ይውሰዷቸው።»



Sample output to test PDF Combine only



«ለነገሩ አሁንም ቀብሩንም መልክ ያሲያዙት እኮ ሴትየዋ ናቸው። እኛ በሰሌን ልንቀብራት አልነበር?»

«ስላላቸው ነዋ። እኛስ ቢኖረን ያን ማድረግ ጠልተን ነው?»

«ልክ ነሽ! ልጆቹ እዚህ መቆየታቸው ለማንም አይጠቅምም። እኛም ልጆቹም ከምንሳቀቅ፣ ዛሬውኑ ቢሄዱ ይሻላል።»

«ነገርኳችሁ! ዛሬውኑ ካልሸኘናቸው በኋላ ልጆቹም፣ እኛም ስንሳቀቅ እንኖራለን።»

«አይ እኔ እንኳን እስከ ሰልስቱ ቢቆዩ ብዬ ነበር። በሉ እስቲ እንዳላችሁ ይሁን።»

ከውይይታቸው በኋላ ወደ ወ/ሮ ማርታ ቀርበው፣ «ከእርስዎ ጋር መነጋገር እንፈልጋለን።» አሏቸው።

«ምንድነው የምታነጋግሩን?» ብለው ጠየቁ ወ/ሮ ማርታ ተገርመው።

«ልጆቹ ዛሬ እዚያ ቤት ማደር አይችሉም።»

«ለምን?»

«ቤቱ ግድግዳው ፈርሷል። ጅብም ሊበላቸው ይችላል። ማን ይጠብቃቸዋል?»

«ይሄን ያህል ጊዜ እዚህ ሲኖሩ ጎረቤት፣ አበልጆች፣ ዘመድ፣ እንዴት ነው ለአንድ ቀን፣ ኧረ እስከ ሰልስቱስ ድረስ አብረዋቸው የማይቆዩት?» ብለው ጠየቁ ወ/ሮ ማርታ እጅግ ተገርመው።

«ማናችንም እንደዚያ ለማድረግ አንችልም። አቅማችን አይፈቅድም።» አሏቸው ጎረቤቶቹ።

ወ/ሮ ማርታ ልጆቹ በዚህች ዓለም አይዟችሁ፣ አለሁላችሁ የሚላቸው ዘመድ እንኳ የሌላቸው ደሆች መሆናቸውን አስበው በጣም አዘኑላቸው።

«ይገርማል!» ብለው፣ «እሺ በቃ ልጆቹንስ እኛ እንወስዳቸዋለን፣ ቤቱንስ ማን ሊጠብቀው ነው?» ብለው ጠየቁ።

«ትልቁ ወንድማቸው አለ። እሱ ሊጠብቀው ይችላል። ትንንሾቹን ግን እናንተ ዛሬውኑ ብትወስዷቸው ነው የሚሻለው።» አሉ ጎረቤቶቹ።

«እሺ፣ እንዳላችሁት እናደርጋለን። አሁን ወደ ቤት እንሂድ!» አሉ ወ/ሮ ማርታ።

ቤት ተመልሰው እነወ/ሮ ወርቅነሽ ያዘጋጁትን ንፍሮና ቡና እንዲሁም እንጀራ በወጥ ቀባሪው ቀማመሰ። ምናልባትም እነወ/ሮ ማርታ ባይኖሩ የሚበላውም ነገር ባልተዘጋጀ ነበር።

ወ/ሮ ማርታ አመለዘውድንና ሁለቱን ትንንሽ ወንድሞቿን ታደለንና ሚካኤልን በዚያው ዕለት ምሽት ወደ ቤታቸው ወሰዱዋቸው።

ይድረስ በጣም ለምወድሽ እናቴ ገንዬ*[1]፣ ለጤንነትሽ አንቺ እንደምን አለሽልኝ? እኔ ኢየሱስ ይመስገን በጣም ደህና ነኝ:: ገንዬ ከዚህ በፊት በጣም ቢያመኝም አሁን ግን እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ:: ገንዬ፣ አንቺ ለኔ በጣም ደግ ነሽ ትጨነቂልኛለሽ:: ገንዬ፣ በጣም ነው የምትወጂኝ:: እኔም ግን በጣም ነበር የምወድሽ:: ለነገሩ እኔም የአሁኑን አያድርገውና በጣም እድለኛ ነበርኩ:: ለአባትና ለናቴ አንድ (ሴት ልጅ) በመሆኔ ያልኩት ይገዛልኝ ነበር:: ይሁን እንጂ የአባቴን ሣቅና ጨዋታ ሣልጠግብ አባቴ የ2ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ተለየኝ:: ከዛም እናቴ ቀኑ ጨለማ ሆነባት:: ምክንያቱም እሷ የሚጥል በሽታ አለባት:: በሚነሣባት ጊዜ ኤሌክትሪክ፣ እሳት አትልም፣ ዘላ ትገባለች:: ታላቅ ወንድሜ የአባታችንን ሞት ሲያይ ከቤት ጠፍቶ ውሎ ማታ ለመኝታ መምጣት ጀመረ::*[2]

በዚህ ሁኔታ በሽታዋ በሚነሣባት ጊዜ የምይዛትና በቅርብ ያለሁት እኔ ስለሆንኩ፣ ስለማልችላት ስትጋጭ ጥርሷን ጨረሠች:: ከዛን በኋላ እኔም የሚያስተምረኝ አጣሁ:: እናቴ ምንም ሥራ አትሠራም:: አባቴ በነበረ ጊዜ ለልጆቼ ብሎ ያስቀመጠው ገንዘብ ነበር ለምግባችን የሚሆነው::*[3] በመጨረሻ ላይ የሚወዱኝ አስተማሪዎች መማሪያ እኛ እንገዛልሻለን ብለው አስገቡኝ:: እናቴን ስለምወድና ስለምጠብቅ ትምህርት ቤት ቀሪ 30 ቀን ሞልቶ ወጣሁ:: እናቴ በጣም እየወደቀች ስለነበረ ለመማት:: በኋላ 1 ወር ከታመመች በኋላ አንድ ቀን ቡና አፈላሁላትና ምሣ በልታ (ብላ) የማታውቀውን «መጠጊያዬ! ልጄ! ስንቄን ስጭኝ!» አለችኝ:: እኔ ግን አልገባኝም ነበር:: እሷ ለካ ምሣ ስጪኝ ማለቷ ነበር::

«እንጀራ ስጪኝ» አለችኝና አብረን ሁላችንም በላን:: ትንሽ ቀምሣ በቃኝ አለችኝ:: ቡና አፍልቼ፣ አጣጥቤ፣ ስኒ ሣላነሣ ቆየሁ:: እሷም ዝም አለችኝ:: ትንሽ ቆይቼ ስጠራት፣ «አይዞአችሁ! ምንም አትሆኑም:: እግዚአብሔር አለላችሁ::» አለችኝና ተኝታ አይኗን ማቁለጭለጭ ጀመረች:: ወዲያው ፊጠጠች:: «እማዬ!» ብዬ ስጠራት አትሰማም:: ብጠራት፣ ባቅፋት፣ ቀዘቀዘች:: አይኗን ስነካት ተዘጋ:: ተመልሶ አልተከፈተም:: ከዚህ በኋላ ተረጋግቼ ጋቢ አለበስኳትና ጐረቤት ሄጄ፣ «እማዬ አትናገርም:: አይኗ ተዘግቷል::» አልኩ ቶሎ መተው ሲያዩ አለቀሱ:: መሞቷ ስለገባኝ የመጨረሻ ሆድ ባሠኝ:: የመማር ፍላጐት እያለኝ ባለመማሬ ይከፋኝ ነበር:: ይሁን እንጂ በእናቴ ደስ ስለሚለኝ፣ ምንም አይመስለኝም ነበር:: እሷን ሣጣ የሚሠማኝን አንቺ መገመት ትችያለሽ:: ገንዬ፣ አባቴ እያለ ሠላም



Sample output to test PDF Combine only



ነው ቤታችን:: አባታችን ከሥራ ሲመጣ ከበር፣ «ልጆቼ! ተሾመ! አመለ!» ይል ነበር:: እኛም ሮጠን ተቀብለነው ነበር፤ የምንኖረው በጥሩ ነገር ነበር:: አባታችን በጣም ይወደን ነበር:: በዓል ሆኖ ደሞዝ ተቀብሎ ለኛ አንድ ነገር ሣይገዛልን አይገባም ነበር:: ይሁንና እሷም በመሞቷ ከፍተኛ ሐዘን ተሰማኝ:: «እሺ አሁን ማን ያሣድገናል? የት እንበላለን? የት እናድራለን? እቤታችን ብናድር አንፈራም?» ብዬ አለቀስኩ:: ይሁን እንጂ ጌታ አልጣለንም:: እዚህ አስቀምጦናል:: ገንዬ፣ ይህን ሁሉ የፃፍኩልሽ ስለምወድሽ ቤተሰቤን ላስተዋውቅሽ ብዬ ነው:: አባቴ ግርማ ይመር ይባላል:: እናቴ ድንቋ ዳምጠው ትባለለች::

ጌታ ይባርክሽ!

*[1] ይህ ደብዳቤ የወላጆቿን ሞት በተመለከተ አመለዘውድ ለወ/ሮ ገነት ገብረጻድቅ የጻፈችው ነው:: ወ/ሮ ገነትን በመጽሃፉ የመጨረሻ ክፍል ባሉ ምዕራፎች እናውቃታለን::

*[2]/*[3] አመለዘውድ የወንድሟና የአባቷ ስም እንዳይጎድፍ ይመስላል በህይወቷ ከተከሰቱ ሁኔታዎች የተለዩ ነገሮች በዚህ ደብዳቤ ጽፋለች:: የመጀመሪያው አንቀጽ የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር ወንድሟን ዱርዬ እንዳይባል ሰግታ የጻፈችው ይመስላል:: የሁለተኛውን አንቀጽ ሶስተኛ ዓረፍተ ነገር ደግሞ አባቷ ልጆቻቸውን በትነው የሞቱ ሃሳብ የለሽ፣ እንዳይባሉ ለመከላከል ሊሆን ይችላል የጻፈችው::

## -35-

*«እንጀራ እየቆረሰች ወደ ሁለቱ ፊት ታዞራለች። . . . እዚህ ቤት በነበሩበት ጊዜ በቂ እየተሰጣቸው፣ እያወቀች በቂ መኖሩን፣ ውስጧ አይችልም። ሁልጊዜ ትትንሾቹ በልተው እስኪጠግቡ ትጠብቃቸዋለች።»*

*ወ/ሮ ማርታ ገብረ ጻድቅ*

ከእናታቸው ቀብር መልስ ወ/ሮ ማርታ ቤት ደርሰው ብዙም ሳይቆዩ ለአመለዘውድና ለሁለቱ ወንድሞቿ በአንድ ማዕድ ራት ቀረበላቸው። አመለዘውድ እጅግ አዝና ነበር።

ወ/ሮ ማርታ ልጆቹን ብቅ ብለው ሲያዩዋቸው አመለዘውድ አትበላም።
«ብዪ እንጂ!» አሏት።
«እሺ» አለቻቸው።

እንጀራ ቆረሰች፣ ግን አልጎረሰችውም። ከወንድሞቿ ፊት አስቀመጠችው።

«ብዪ! . . . ኧረ ብዪ!» አሉ ወ/ሮ ማርታ።
«እሺ» አለች።

አሁንም እንጀራ ቆረሰች። አሁንም ከወንድሞቿ ፊት አኖረችው እንጂ ወጥ አላጠቀሰችም።

ወ/ሮ ማርታ፣ 'ሐዘኑ ስለጎዳት ይሆናል ቀስ ብላ ትብላ' ሲሉ አስበው ትተዋቸው ሄዱ። ትንሽ ቆይተው ሲመለሱ አሁንም አመለዘውድ አትበላም።

«ምነው አትበይም እንዴ የአለምዘውድ?» ስሟን አመለዘውድ ብለው መጥራት አልሆነላቸውም። የአለምዘውድ ነው የሚሏት።

«እበላለሁ።» አለች እንዳቀረቀረች።

ወንድሞቿ በልተው እስኪጠግቡ ለራሷ አንድም ጉርሻ አልጎረሰችም። እነሱ ሲበቃቸው፣ ትንሽ በልታ ተነሳች።

ወ/ሮ ማርታ ይህ ባህርይዋ እናቷ በሞተች ዕለት ብቻ ሊኖር የሚችል ነው ብለው አሰቡ። ከዚያም ቀን በኋላ ግን ለበርካታ ሳምንታት ልጆቹ በቤታቸው በቆዩበት ጊዜ፣ አመለዘውድ ወንድሞቿ እስኪጠግቡ አንድም ጉርሻ ለራሷ አትጎርስም ነበር። ያለመታከት እንጀራ እየቆረሰች ከፊታቸው ታስቀምጣለች። ወ/ሮ ማርታ ከወንድሞቿ እኩል እንድትበላ ሊያግባቧት ደጋግመው ሞክረው አልተሳካላቸውም። ወንድሞቿ መጥገባቸውን ካላረጋገጠች በጭራሽ አትበላም።



Sample output to test PDF Combine only



«ቤቷ እያለች ምናልባት በቂ ምግብ ስለማይኖር፣ ከወንድሞቿ ጋር ተሻምታ ከበላች፣ እነሱ ይራባሉ ብላ ታስብ ይሆናል። እዚህ በቂ ምግብ እንዳለ እያወቀች ለእነሱ ይህን ያህል ማሰቧና መጨነቋ ምን ይባላል? ማንም በሷ ዕድሜ ያለ ልጅ ምግብ ቀርቦለት ሲበላ እንጂ እንደሷ ሲሆን አይቼ አላውቅም።» ይላሉ ወ/ሮ ማርታ እጅግ እየተገረሙ።

አመለዘውድ እናቷን በታህሳስ ወር 1995 ዓ.ም. በሞት ስትነጠቅ ዕድሜዋ አስራ አራት ቢሆንም ሰውነቷ በምግብ ዕጥረት፣ በሃሳብና ጭንቀት፣ በበሽታ እንዲሁም በሥራ ጫና የተጎዳ ስለነበረ የዘጠኝ ወይም የአስር ዓመት ልጅ ነበር የምትመስለው።

ለዓመታት የለመደችውን የሰቆቃ ሕይወት በጥቂት ቀናት ውስጥ ልትረሳው አልቻለችም። አሁን ደግሞ እሷና ወንድሞቿ ሁለቱንም ወላጆቻቸውን አጥተዋል። አሁን ለታናናሽ ወንድሞቿ ያለቻቸው እሷ ብቻ ነች። ጫንቃዋ ላይ ወንድሞቿን የመንከባከብ ኃላፊነት እንዳለባት የሚያስታውስ ቀንበር ሲጫናት፣ ሲቆረቁራትና ሲከረክራት ሁልጊዜ ይሰማታል። መኖር ካለባት፣ የምትኖረው ለወንድሞቿ ስትል ብቻ እንደሆነ ዘወትር ታስባለች። እንደዚህ በማሰቧ ደግሞ ወ/ሮ ማርታ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ቢያቀርቡላቸውም፣ የቀረበላትን እንደፈለገች ከመብላት ይልቅ፣ ወንድሞቿን እስኪጠግቡ ስታበላ በመቆየት፣ 'ኃላፊነቴን ተወጥቻለሁ' ከሚል እሳቤ የምታገኘው ዕርካታ እጅግ የላቀ ነበር። ለነገሩ ሆዷም ቁጠባ ለምዶ ቶሎ ትጠግባለች። ለምግብ ያላት ፍላጎት በፊትም፣ አሁንም እምብዛም ነው።

# ክፍል ሁለት

*«ጌታ እንደሚያድነን ተስፋ አለኝ።»*
*አመለዘውድ*

Sample output to test PDF Combine only

## -36-

*«የጻፈችውን የሐዘን እንጉርጉሮ 'ነይ ላንብልሽ' ብላ ታነብልኝ ነበር።»*
*ወ/ሮ ወርቂ ቤተ*
*«መፅሐፍ ቅዱስ ሳነብ የምንድን ነው የሚመስለኝ።»*
*አመለዘውድ*

አመለዘውድና ወንድሞቿ እነወ/ሮ ማርታ ቤት ሲኖሩ ወርቂ ቤተ ከተባለች የወጥ ቤት ሠራተኛ'ጋ በአንድ የኮንቴይነር ቤት ውስጥ ነበር የሚያድሩት። አመለዘውድ እትዬ ወርቂ ትላታለች። በኋላም እየተግባቡና እየተቀራረቡ ሲመጡ፣ ፍቅር በተሞላ አንደበት፣ 'አብዬ' ብላ ትጠራት ነበር።

እትዬ ወርቂ አስተዋይ፣ ረጋ ያለች፣ ቀይ፣ አጭር ሴት ናት። ፕሮጀክት መርሲ ቡታጅራ ከተማ አቅራቢያ ባሰራው ት/ቤት የምትማር ብርሃኔ የምትባል ልጅ አለቻት። እናት እንደመሆኗ ልጆቹ ወላጆቻቸውን በማጣታቸው ታዝንላቸዋለች። በተቻላት አቅምም ትንከባከባቸው ነበር።

አመለዘውድ እናታቸው ያረፈች ዕለት ስለመጡ ሐዘኗን በለቅሶ ቤት ሳይሆን አዲሱን ሕይወት እየኖረች ከማዘን ሌላ ምርጫ አልነበራትም። ብቻዋን ታለቅሳለች። የሐዘን እንጉርጉሮም ትጽፍ ነበር። የምትጽፈውን የሐዘን እንጉርጉሮ ለእትዬ ወርቂ ማንበብ ያስደስታታል። በረጅሙ የምትጽፈውን ግጥም አንብባ ስትጨርስ፣ የእንባ ሳግ ይተናነቃታል። እትዬ ወርቂም ዓይኖቿ እንባ ያጢዛሉ። በግጥሞቹ እናቷ ልጆቿ እንዳይራቡ ብላ ውሃና እንጨት በማመላለስ መድከሟን፣ እንጨት ተሸክማ እንደወደቀች፣ ደግና የዋህ እንደነበረች . . . ታብራራ ነበር። ተመስጣና እናቷን እያሰበች ስለሆነ የምታነበው፣ እትዬ ወርቂ የማየት አቅማቸው የደከሙትን ታማሚ ዓይኖቿን በእንባ ከመሞላት ማገድ ያቅታታል። ለራሷ ብቻ የምትጽፋቸውን የሐዘን እንጉርጉሮዎች ለእትዬ ወርቂ የምታነብላት አዛኝነቷን ስለተረዳችና ስለወደደቻት ነው።

አንድ ቀን ወ/ሮ ማርታ አመለዘውድን፣ «ለምን እዚህ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት እየሄዳችሁ አትማሩም?» አሏት።

መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ከወ/ሮ ማርታ ቤት ፊት ለፊት ያለውን አቧራማ መንገድ ተሻግረው የሚገኝ ነው። አመለዘውድ በመጀመሪያው ቀን ወደ ቤተክርስቲያኑ ሄዳ ያየችውና የሰማችው ለሷ የተለየ ዓለም ነበር። ከዚያም በኋላ በተከታታይ በሰንበት ወደ ቤተክርስቲያኑ ስትሄድ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን መዳንና መንግስተ ሰማያትን መውረስ እንደሚቻል፣ ከሞት በኋላ ሌላ ሕይወት፣ ያውም ዘላለማዊ ሕይወት እንዳለ ሲነገር አዳመጠች። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች፡ሲያነቡ ሰማች። በሰማቻቸው ኢየሱስ ክርስቶስ

አዳኝ መሆኑን በሚያሳስቡ መዝሙሮች ተመሰጠች:: የወ/ሮ ማርታ አስታዋሽነት ሳያስፈልጋት እሁድ፣ እሁድ መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን በሙሉ ፍላጎት የምትመላለስም ሆነች::

አንድ ቀን ወ/ሮ ማርታ፣ «እንዴት ነው ቤተክርስቲያን መሄዱን ወደድሽው?» ብለው ጠየቋት::

ዓይኖቿ በስፋት ተከፈቱና ብርሃን ፈነጠቁ:: ፊቷም በፈገግታ ፏ! ብሎ በራ:: «አዎ እማማ! በጣም ወድጄዋለሁ!» አለች ፍፁም እውነት በሚደመጥበት ድምፅ::

«ምኑን ነው የወደድሽው?»

«መጽሐፍ ቅዱሱ፣ የሚያነቡት፣ በጣም ደስ ይለኛል::»

«መጽሐፍ ቅዱስ ቢኖርሽ ደስ ይልሽ ነበር?»

«አዎ፣ እማማ በጣም ደስ ይለኝ ነበር::» የራሷ መጽሐፍ ቅዱስ ሊኖራት እንደሚችል ማሰብ በራሱ አስደሰታት::

«እዚህ ቤት መጽሐፍ ቅዱስ አለ፤ እሰጥሻለሁ::» አሏት ወ/ሮ ማርታ::

«እሺ እማማ!» አለች አመለዘውድ ከልቧ ተደስታ:: ውብ ፈገግታዋ ፊቷን ይበልጥ አደመቀው::

ወ/ሮ ማርታ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ሰጧት:: ከዚያች ዕለት ጀምሮ አመለዘውድ መጽሐፍ ቅዱስ ከእጇ የማይለይ ውድ ንብረቷ ሆነ:: ይዛው መዞር ብቻ ሳይሆን በየቀኑ ለበርካታ ሰዓታት ተደፍታበት ታነበው ጀመር::

እነወ/ሮ ማርታ ቤት ብዙም ሳይቆዩ አመለዘውድ ዳግመኛ በአልማዝ ባለ ጭራ ተጠቃች:: እትዬ ወርቄ በቅርብ ወደሚገኘው የወረዳ 28 ጤና ጣቢያ እያመላለሰቻት አስፈላጊው ህክምና ተደረገላት::

አንድ ቀን ወ/ሮ ማርታ ስለጤንነቷ ሲጠይቋት ቆይተው፣ «አይዞሽ! እግዚአብሔር ያድንሻል!» አሏት::

«አዎ፣ እግዚአብሔር ይፈውሰኛል!» አለቻቸው ቃላቶቹን እየረጋገጠች ጠንካራ እምነት በሚደመጥበት ድምፅ::

ወ/ሮ ማርታ ለአፍታ በአነጋገሯ እንደመገረም ብለው ቆም ብለው አዩዋት::

ህክምናው ረድቷት በቀጣዮቹ ሳምንታት ተሻላት::

አመለዘውድ ስለሃይማኖት የምታስብበት ጊዜ በሕይወት ዘመኗ ኖሯት አያውቅም ነበር:: እናትና አባቷ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ነበሩ:: እሷም፣ ወላጆቿም እንደ ሁኔታው በሰንበት ቤተክርስቲያን ተሳልሞ ከመምጣትና ዓመታዊ የቅዱስ ገብርኤል ክብረ በዓል ሲከበር ታቦት


Sample output to test PDF Combine only



ከማንገስ በስተቀር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ለመስማት ብዙም ዕድልና አጋጣሚው አልነበራቸውም:: በየትኛው ጊዜያቸው!? ኑሮ ሲጋልባቸው፣ ሲያሯሩጣቸው ይነጋል፣ ይመሻል:: ከአባቷ ሞት በኋላ አልፎ አልፎ አመለዘውድ ከእሙሽ ጋር አመሻሽ ላይ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን ጎራ ትል ነበር:: የሚሰጠውን ትምህርት ለመከታተልና ለመረዳት ግን ጊዜውም የአእምሮ መረጋጋቱም አልነበራትም::

ወ/ሮ ማርታ ቤት ሲኖሩ እሷና ታናናሽ ወንድሞቿ ምንም የጎደለባቸው ነገር የለም:: አመለዘውድ ያጣችው አንድ ትልቅ ነገር ቢኖር ውድ ወንድሟን ተሾመን ብቻ ነበር:: ተሾመ እጅግ ይናፍቃት ጀመር:: አንድ ቀን እሱን ፍለጋ ወደ አስፋልት ሄደች:: አፈላልጋ አገኘችው::

ሲያያት ደስ አለው::

«እንዴት ነህ?»

«ደህና ነኝ::» . . .

ወደ አንድ ካፌ ወሰዳት::

«ኑሮ እንዴት ነው?»

«ጥሩ ነው:: እኛ ካንተ ሃሳብና ናፍቆት በስተቀር በጣም ደህና ነን::»

«ስለኔ አታስቢ» አላት፤ «እስከዛሬ ከቤተሰብ ተለይቼ ብቻዬን ኖሬአለሁ አይደል?»

«አብረን እንድንኖር እፈልጋለሁ:: ወ/ሮ ማርታን መጥተህ ብታናግራቸው ደስ ይለኛል::»

«እናንተን ካሳደጋችሁ ራሱ ጥሩ ነው::»

«አይሆንም ተሺ፤ ከእኛ እንድትለይ አልፈልግም::»

«ቤቱን እኔ እጠብቃለሁ:: እኔ ከሌለሁ ማን ይጠብቀዋል?»

«እኛ ሥራ እስክንይዝና ራሳችንን እስክንችል ጎረቤቶቻችን ይጠብቁታል::» . . .

ለደቂቃዎች አወሩ፤ ግን ተሾመ ወ/ሮ ማርታ ቢፈቅዱ እንኳን፣ በእሳቸው ድጋፍ ለመኖር ጉጉት አልነበረውም::

## -37-

*«ምሳ የቦለቄ ሾርባ ነበር:: እኔ አልወደውም ነበር::»*
*ሚካኤል ግርማ*

የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ትምህርት ሲጀመር ሦስቱ ልጆች ወደ መደበኛ ት/ቤት እንዲገቡ ተወሰነ:: ከአዲስ አበባ በደቡብ ምዕራብ አቅጣጫ 130 ኪ.ሜ. ርቃ ከምትገኘው ቡታጅራ ከተማ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ርቆ ወደሚገኘው የፕሮጀክት መርሲ መድኃኒዓለም ት/ቤት ተወሰዱ:: አመለዘውድ ወደ አራተኛ ክፍል ብትዘዋወርም አራተኛ ክፍልን ለጥቂት ቀናት ብቻ ነበር የተማረችው:: መድኃኔዓለም ት/ቤት የደረሱት የዓመቱ አጋማሽ ላይ ስለነበር ግማሹን ዓመት ስላልተማረች አራተኛ ክፍል መግባት አልቻለችም:: መማር ስላለባት ተብሎ ግን የሦስተኛ ክፍል የሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ትምህርቷን ጀመረች:: ት/ቤቱ ውብ በሆነ ገጠራማ ቀበሌ የሚገኝ፣ በወቅቱ ከአርባ የማይበልጡ አዳሪና በመቶዎች የሚቆጠሩ ተመላላሽ የአካባቢው ልጆች በነፃ የሚማሩበት ነው::

በ1991 ዓ.ም. አካባቢው በድርቅ ተጠቅቶ ነበር:: ከክረምት እረፍት በኋላ ት/ቤት ሲከፈት ብዙዎቹ ተማሪዎች በምግብ ዕጥረት ተጎድተው ነበር የመጡት:: በዚህም ምክንያት ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ ተመላላሽ ተማሪዎችም ምግብ እንዲሰጣቸው ተወሰነ:: ቁርስና ምሳ ተማሪዎቹ በሙሉ እዚያው በት/ቤቱ ካፍቴሪያ ውስጥ በነጻ ይመገባሉ:: ቁርስ ላይ አጥሚት ይጠጣሉ:: ምሳ ብዙ ጊዜ የቦለቄ ሾርባ ነው የሚቀርብላቸው:: ቡታጅራ አካባቢ ያሉ ገበሬዎች በብዛት የሚያመርቱት በቆሎና እንሰት ነው:: የዘወትር ምግብ የሆነው ከእንሰት ሥር የሚገኘው ቆጮ በውስጡ ካርቦሃይድሬት እንጂ ፕሮቲን ስለሌለው የአካባቢው ህጻናት ለፕሮቲን እጥረት የተጋለጡ ናቸው:: ቦለቄ በፕሮቲን የበለጸገ ስለሆነ ተማሪዎቹ የቦለቄ ሾርባ አዘውትረው እንዲመገቡ የሚደረገው ተመጣጣኝ ምግብ እንዲያገኙ ሆን ተብሎ ታስቦና ታቅዶ ነው::

ከሞገደኛና ማዕበላማ ባህር ወደ ሰላማዊ የውሃ አካል ድንገት በነፈሰ ንፋስ ተገፍታ እንደገባች መርከብ ከእናቷ ሞት በኋላ ሕይወት ለአመለዘውድ እጅግ የተለየ አቅጣጫ ይዛለች:: ቤተሰቦቿን ለመመገብ እናቷንና ወንድሞቿን ለመንከባከብ ከጠዋት እስከ ማታ መሯሯጥ ግዴታዋ እንዳልነበር፣ ወ/ሮ ማርታ ቤትና እዚህ ቡታጅራ ሰዎች ምግብ አዘጋጅተው የሚያቀርቡላት ሆናለች::

እነዚያ ቢደክሙም እንዲያርፉ የማትፈቅድላቸው ከቤት እስከ አስፋልት ያለውን ቁልቁለት የምትንደረደርባቸው፣ ከአስፋልት እስከ ቤት ያለውን ዳገት


Sample output to test PDF Combine only



በቀን ሁለት፣ ሶስት ጊዜ የምትወጣበቸው ቀጫጭን እግሮቿ ለዓመታት ያጡትን ዕረፍት አግኝተዋል:: አእምሮዋም ከአባቷ ሞት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ በትምህርቷ ላይ ብቻ የማተኮር ዕድል አገኘ:: እናቴን በሽታዋ ይጥላት ይሆን? ዛሬ ተኝታ ልትውል ነው? እናቴና ወንድሞቼን ዛሬ ምን ላበላቸው ነው? ከሚል የዕለት ተዕለት ሃሳብና ጭንቀት ተገላገለች::

ቤታቸው ለቀው ከወጡ በኋላ የሷ ዋና ሃሳብና ጭንቀት አንድ ብቻ ነው፤ ተሾመ:: ተሾመ ይናፍቃታል:: በየቀኑ እሱን ሳታይ ማደር አይሆንላትም ነበር:: አሁን እዚህ ቡታጅራ ከተማ አቅራቢያ መኖር ከጀመሩ በኋላ ደግሞ የበለጠ ተራርቀዋል:: እሱን ማግኘት አትችልም:: ብቸኛ መሆኑን እያሰበች ብዙ ጊዜ ትቆዝማለች:: አንዳንድ ጊዜ ሰው ዕንባዋን ሳያይባት ተደብቃ ታለቅሳለች:: ራሷን ከሌሎች ልጆች የማግለልና ብቸኝነትን የመምረጥ ፀባይም ይስተዋልባት ጀምሯል:: ብቻዋን ስትሆን በተለይ ስለእናቷና ስለተሾመ እያሰበች ትተክዛለች፣ ታዝናለች:: ጆሮዋ አጥርቶ ስለማይሰማ የዕድሜ እኩዮቿ በሌላ ነገር እንኳ ከሳቁ፣ በሷ የሳቁ ስለሚመስላት ትናደድባቸዋለች::

ሚካኤልና ታደለም ትምህርት ጀምረዋል:: ቡታጅራ ከመጡ ጀምሮ ሶስቱ በአንድ ገበታ ዙሪያ ቀርበው አያውቁም:: ሁሉም ተማሪ ለራሱ አንድ ሰሀን ይዞ ነው የሚመገበው:: አመለዘውድ እንደወትሮዋ እዚህም ብዙ አትበላም:: ጥሩ የምግብ ፍላጎት ያላት እንኳን ቢመስላት፣ ምግቡ ፊት ስትቀርብ ከጥቂት ጉርሻዎች ያለፈ አትደፍርም:: አሁን ማድረግ የምትችለው ወንድሞቿ በደንብ መብላታቸውን ወደ ሰሀናቸው አስር ጊዜ እየተገላመጠች ማረጋገጥና ካልበሉ መቆጣት ነው:: ታደለ ጥርግ አድርጎ ይበላል:: ሚካኤል ግን ለምሳ የሚቀርበውን የቦለቄ ሾርባ ብዙም አይወደውም::

«ለምንድነው የማትበላው!» እያለች ትጨቀጭቀዋለች:: በሌሎችም ጉዳዮች ወንድሞቿ እሷ ጥሩ ልጆች ናቸው እንደምትላቸው እንዲሆኑ ስለምትፈልግ ትመክራቸዋለች፣ ትቆጣቸዋለች:: አለባበሳቸውን፣ ንፅህናቸውን፣ ከሌሎች ልጆች ጋር በሰላም መኖር መቻላቸውን፣ ለትምህርታቸው ትኩረት መስጠታቸውን . . . በምታገኘው አጋጣሚ ሁሉ በቅርበት ትከታተላለች:: ሚካኤል ምክርና ቁጣዋን ስለማይቀበላት፣ ብዙ ጊዜ ይጋጫሉ::

«ሱሪህን ለምን አቆሸሽከው? አቧራ ላይ አትጫወት አላልኩህም? . . .. የቤት ሥራ ሠርተሃል? . . . ለመሆኑ ታጠናለህ? . . . ማጥናት አለብህ! ካላጠናህ ፈተና ማለፍ አትችልም:: . . . ለምንድነው ያቺን ልጅ የመታሃት? . . . » እያለች ቁጥጥርና ክትትል ስለምታበዛበት ሚካኤል ታናድደዋለች::

«እንደፈለግኩ ብሆን አያገባሽም!» ይላታል ብዙ ጊዜ ምክሯ ጭቅጨቃ እየሆነበት::

«ለምን አያገባኝም? እህትህ እኮ ነኝ::»

«በቃ አያገባሽም! አትጨቅጭቂኝ!» . . .

እሷም በትምህርቷ በፊት እንደነበረችው ጎበዝ ተማሪ መሆን አልቻለችም:: የመስማት አቅሟ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ በትምህርት አቀባበሏ ላይ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው:: አስተማሪዎቹ የሚሉት እንዲሰማት ከፊት ባለ ዴስክ ላይ ነው የምትቀመጠው:: በጆሮዋ ችግር ምክንያት ከሌሎቹ ተማሪዎች ስለምትለይ የዝቅተኝነት ስሜት ይሰማታል:: በዚህም ምክንያት ብቸኝነትን የመምረጥ አባዜ ተጸናውቷታል:: ከክፍል ውጪ ከጨዋታ ይልቅ የሚቀናት ማንበብ ነው:: ደብተሮቿንና መጽሃፍቷን የማታጠና ከሆነ ደግሞ ወ/ሮ ማርታ የሰጧትን መጽሐፍ ቅዱስ፣ ጋዜጦች ወይም ሊነበብ የሚችል ማንኛውም እጇ የገባ መጽሐፍ ታነባለች:: በተለይ የታሪክ መጽሃፍት ማንበብ ያስደስታት ነበር:: አልፎ አልፎ እነወ/ሮ ማርታ ቤት ግቢ ውስጥ ሲኖሩ ለቀረበቻቸው አንዳንድ ሰዎች ደብዳቤ ጽፋ ከአዲስ አበባ በሚመጡ ሹፌሮች ትልካለች::



Sample output to test PDF Combine only



## -38-

*«ዓይኗን መግለጥ ስላልቻለች እንዳያውቁ፣ እንዳትሳቀቅ፣*
*ዓይን ሐኪም'ጋ ወሰድናት::»*
*ወ/ሮ ማርታ ገብረ ጻድቅ*

አመለዘውድ በአዳሪ ት/ቤቱ ጥቂት ሳምንታት እንደቆየች ያስላት ጀመር:: ተመርምራ ሳምባ ነቀርሳ መሆኑ ታወቀ:: ከዚህ በፊትም በሳምባ ነቀርሳ ተይዛ ህክምና ጀምራ ማቋረጧ ተገቢ እንዳልነበር ስለተረዳች ተጸጸተች:: ስድሳ መርፌ ለሁለት ወር መወጋት ግዴታዋ ሆነ:: ብዙ ኪኒኖችም ትውጥ ጀመር::

«በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለች ደግሞ፣ ቀደም ሲል ከእናቷ ጋር ስትኖር የወጡባት ዓይነት ኪንታሮቶች ፊቷ ላይ ዳግመኛ መታየት ጀመሩ:: አባትና እናቷ እንደሞቱ ስለሚታወቅ፣ ህመሟ ምናልባት ኤድስ ሊሆን እንደሚችል ተጠረጠረ:: ወደ አዲስ አበባ ሄዳ እንድትመረመርም ተወሰነ:: ሚካኤልም ቀዳው ነጭና አመዳም ነገር ይሆናል:: እግሮቹም ላይ ቁስል ነገር አይጠፋም:: ታደለ ብቻ ነበር የተሟላ ጤንነት የነበረው:: ለማንኛውም ተብሎ ሶስቱም ልጆች፣ እንዲሁም ሌሎች ወላጆቻቸውን በኤድስ ያጡ ሁለት እህትማማቾችም ለምርመራ ወደ አዲስ አበባ እንዲሄዱ ተደረገ::

በምርመራው አመለዘውድና ሚካኤል ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲብ መሆናቸው ሲረጋገጥ ታደለና ሁለቱ እህትማማቾች ከቫይረሱ ነፃ እንደሆኑ ታወቀ:: የሁለቱ ልጆች ፖዘቲብ መሆን ለወ/ሮ ማርታና ለባለቤታቸው አስደንጋጭ መርዶ ነበር:: ልጆቹ ወደ ቡታጅራ ተመለሱ:: ለሁሉም ለኤች.አይ.ቪ. ሳይሆን እንዲሁ ለአጠቃላይ የጤና ምርመራ ደማቸውን እንደተመረመሩ ነበር የተነገራቸው::

እነወ/ሮ ማርታ ገና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ሳይወስኑ፣ ድንገት ኪንታሮቱ ተባብሶ የአመለዘውድን ፊት ወረረው:: አተር የሚያካክሉ ትልልቅ ኪንታሮቶች በተለይ የዐይኖቿ ሽፋሎች ላይ በብዛት ወጡባት:: የኪንታሮቶቹ ክብደት የዓይኖቿን ሽፋሎች ቁልቁል መዝነው ከደኗቸው:: እናም ጤነኛ ዓይኖች እያሏት፣ ዓይኖቿን ገልጣ ማየት ተሳናት:: ሁኔታዋ ለእሷም፣ አብረዋት ለሚኖሩ ሕፃናትና ለፕሮጀክት መርሲ ሠራተኞችም አስደንጋጭ ነበር::

አምስቱ ልጆች ማለትም አመለዘውድና ሁለቱ ወንድሞቿ እንዲሁም ሁለቱ ወላጆቻቸውን በኤድስ ያጡ እህትማማቾች ለሁለተኛ ጊዜ የኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ እንዲደረግላቸው ተወስኖ ወደ አዲስ አበባ መጡ።

አመለዘውድና ሚካኤል አሁንም ከኤች.አይ.ቪ. ጋር እንደሚኖሩ በደም ምርመራው ተረጋገጠ። ታደለ ለሁለተኛ ጊዜም በተደረገለት ምርመራ በደሙ ውስጥ ኤድስ አምጪው ቫይረስ አልተገኘም። ሁለቱ አብረዋቸው የተመረመሩት እህትማማቾችም ኤች.አይ.ቪ. ኔጌቲቭ ሆኑ። አሁንም የተደረገላቸው የኤች.አይ.ቪ. የደም ምርመራ መሆኑ አልተነገራቸውም። ከምርመራው በኋላ ሁሉም ልጆች ወደ ወ/ሮ ማርታ ቤት ተወሰዱ። ከጥቂት ቀናት በኋላ ሁለቱ ሴቶች ልጆች ወደ ቡታጅራ ሲመለሱ አመለዘውድና ወንድሞቿ ግን እዚያው እንዲቆዩ ተደረገ። ሁለቱ እህትማማቾች፣ «ወደ ቡታጅራ ልትወሰዱ ነው» ሲባሉ፣ በጣም ደስ አላቸው፤ ፈነጠዙ። በዚያው መጠን ደግሞ አመለዘውድና ወንድሞቿ ከፋቸው።

«እኛስ ለምን ወደ ቡታጅራ አንመለስም?» ብላ አመለዘውድ ጠይቃ ነበር።

«አንቺ ሲሻልሽ ትሄዳላችሁ።» የሚል መልስ ተሰጣት።

እነወ/ሮ ማርታ እንዳይረበሹ በማለት ልጆቹ ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ መሆናቸውን በይፋ ሊነግሯቸው አልደፈሩም። አመለዘውድ ዓይኖቿን መግለጥ የተሳናት በኤች.አይ.ቪ. ምክንያት በተከሰተባት ኪንታሮት ምክንያት እንደሆነ አሳምረው ቢያውቁም፣ የዓይን በሽታ ነው ብላ እንድታስብና እንድትረጋጋ የዓይን ሐኪም'ጋ ወሰዷት። የዓይን ሐኪሙ አመለዘውድ የኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ተጠቂ መሆኗን ገና ሲያያት ጠረጠረ። እሷ ሳትሰማ ለምን እንዳመጧት እነወ/ሮ ማርታ በግልፅ ነገሩት።

የዓይን ሐኪሙ ጤነኛ ዓይኖችን ሊጎዳ የማይችል ጠብታ አዘዘላት።

«አይዞሽ የአለምዘውድ! በቃ አሁን መድኃኒት ታዞልሻል ትድኛለሽ።» አሏት ወ/ሮ ማርታ።

«እሺ እማማ» አለቻቸው ፈገግ እያለች።

እናቷ በሕይወት እያለችም ያማት ስለነበረ፣ ከእናቷ ሞት በኋላ እሷም እንደምትከተላት ታስብ ነበር። በፕሮጀክት መርሲ አዳሪ ት/ቤት ቆይታዋ ግን የመኖር፣ በትምህርቷም ስኬታማ የመሆን ተስፋ በውስጧ ጭል፣ ጭል ማለት ጀምሮ ነበር፤ ሳምባ ነቀርሳ፣ የጆሮዋ ህመም፣ ኪንታሮቶቹ ተደራርበውባት ጤናና ሰላም ነሷት እንጂ።

«የዓይን ጠብታውን ትጠቀሚና አሁን ይሻልሻል።» አሏት ወ/ሮ ማርታ።



Sample output to test PDF Combine only



በወ/ሮ ማርታ ድምፅ ውስጥ የምታደምጠው ከባድ ሐዘን ነበር። እንደከዚህ በፊቱ ነፃ ሆነው የሚነጋገሩ ለማስመሰል ቢጥሩም፣ የሆነ የተለየ ነገር እንዳለ ደመነፍሷ ነግሯታል። ህልውናዋን አደጋ ላይ የሚጥል አንድ ውስብስብ ችግር ውስጥ እንዳለች ቢሰማትም፣ ለመኖር ያላት ጉጉት የእነወ/ሮ ማርታን ቅዱስ ውሸት እውነት አድርጋ እንድትቀበል ረዳት። ራሷን ለማረጋጋት ትሞክራለች። ተሽሏት ቡታጅራ አቅራቢያ ወደሚገኘው መድኃኒዓለም ት/ቤት ስለመመለስና ትምህርቷን ስለመቀጠል ታልማለች።

ዐይኖቿን ለመግለጥ በመቸገሯ፣ ወንድሞቿን ለመንከባከብና ለማንበብ ባለመቻሏ ትበሳጫለች። ግን በሚያም ትዕግስት እስኪሻላት ከመጠበቅ ውጪ ሌላ አማራጭ አልነበራትም።

## -39-

*«(ፖዘቲቭ መሆናቸውን) የምታውቅ ይመስለኛል። እሷ ጆሮዋ በደንብ ባይሰማም፣ ሚካኤል እንዲህ አሉን፣ እንዲህ አደረጉን እያለ ይነግራት ነበር።»*

*ወ/ሮ ወርቁ ቤተ*

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ ትልልቆቹ ኪንታሮቶች ከአመለዘውድ ፊት ላይ እየፈነዱና እንደ መቁሰል እያሉ ቀስ በቀስ መጥፋት ጀመሩ። የዓይኖቿን ሽፋሎች የከደኑት ኪንታሮቾችም ከሰሙ። አመለዘውድ ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ካለማየት ወደ ማየት ተሸጋገረች። የምትሳሳላቸውን ወንድሞቿን ዳግመኛ ማየት ቻለች። ደህና ናቸው። ሚካኤል ቆዳው ላይ ለክፉ የማይሰጥ ሽፍታ ነገር ይታይበታል። ስታነበው የምትድን ስለሚመስላት የምትወደውን መጽሐፍ ቅዱስም ዳግመኛ ለማንበብ በቃች።

አመለዘውድ ዓይኖቿን መግለጥ ከቻለችም በኋላ ብዙም ደስተኛ አልነበረችም። እነወ/ሮ ማርታ ጥብቅ ምስጢር አድርገው ቢይዙትም፣ «እነዚህ ልጆች ምን ሆነው ነው በሰላም ከሚማሩበት ከቡታጅራ መጥተው እዚህ የተቀመጡት?» ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት አሳ የጎረጎሩ ግቢው ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ፣ ዘንዶውን እውነት አግኝተውታል።

አመለዘውድ ከባድ ችግር ውስጥ እንዳለች ያወቁ አንዳንድ ሰዎችን በሁኔታቸውና በአነጋገራቸው መለየት ጀመረች። ብዙ ጊዜ ሐዘን፣ አንዳንዴም ፍርሃት የፈጠረው ቅዝቃዜ ይስተዋልባቸዋል። አንዳንዶቹ ጮክ፣ ፈጠን ብለው በፈገግታ በመናገር ድምፃቸውን ሊያሞቁት እንኳ ቢጥሩም፣ ጥረታቸውና ድካማቸው የተሳካ እንኳ ቢመስልም፣ በፊት ከሚሰጧት ፍቅር ላቅ ያለ ስለሚሆንባት ግራ ይገባታል። በግድ ለይስሙላ ባሞቁት ድምፅ ውስጥ ኃይለኛ ቅዝቃዜ ይሰማታል። ነፍሷን ይበርደዋል። ጥቂቶች ደግሞ በሩቁ ሰላም ለማለት እንኳ ይጸየፋሉ። በአጠገቧ እያለፉ ልክ የሌለች ያህል ይዘጓታል።

ሚካኤልም የሚሰማቸውና የሚያያቸው ነገሮች ነበሩ። ግቢው ውስጥ ከሚውሉና ከሚያድሩ ሠራኞች አንዷ ደረጀ የሚባል ከሚካኤል ትንሽ የሚያንስ ልጅ ነበራት። አመለዘውድና ሚካኤል ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ጋር እንደሚኖሩ ከሰማች በኋላ ልጇ እንዲጠነቀቅ ትመክረው ነበር።

«እነሱ የማይድን በሽታ ይዟቸዋል። አብረሃቸው እንዳትጫወት! እንዳትጠጋቸው!» ብላ ታስጠነቅቀዋለች።

የደረጀ እናት ስለበሽታው በቂ ግንዛቤ ስለሌላት ህጻን ልጇን ለመከላከል እንደ እናትነቷ እየጣረች ቢሆንም ደረጀ ከሚካኤል'ጋ አልፎ አልፎ መጫወቱን አላቆመም።



Sample output to test PDF Combine only



ደረጀ አንድ ቀን ለሚካኤል፣ «እናንተ የማይድን በሽታ ይዟችኋል።» አለው።

አባባሉ ለሚካኤል ከማስደንገጥ ይልቅ የማይገባ ነገር ሆነበት።

«ማ?»
«አንተ፣ እህትህና ወንድምህ»
«እንዴት አወቅክ?»
«እናቴ ነገረችኝ»
«ውሸቷን ነው። እኔ አላመመኝም።» አለው ሚካኤል ዘና ብሎ።
«ግን እናቴ፣ 'የማይድን በሽታ ስለያዛቸው ከእነሱ ጋር አትጫወት' ብላኛለች።»
«ታደለን ልጥራውና አኩኩሉ እንጫወት?» አለ ሚካኤል ስለሌላ ነገር ሲያወሩ የቆዩ ይመስል።
«እሺ» አለው ደረጀ ተደስቶ። . . .

ከጥቂት ቀናት በኋላ ሚካኤል ለአመለዘውድ ደረጀ ያላትን ነገራት።

«የማይድን በሽታ ይዟቸዋል አለህ?»
«አዎ፣ እናቱ ናት የነገረችው»
«ምን የሚሉት በሽታ?»
«እኔ እንጃ»
«ውሸቱን ነው። ምንም አልሆንም» አለችው።
«እኔም፣ 'ውሸትህን ነው' አልኩት።»

ሚካኤል ዛሬ ምሳ ምን እንደበላ ያወራላት ያህል ቅንጣት ሳይጨነቅ ነበር የሚናገረው። አመለዘውድ ግን ወንድሟ የነገራትን ከዚያ በኋላ ባሉት ቀናት ደጋግማ አሰበችው፤ አላመጠችው፤ አመነዠገችው። የምትጠረጥረውንና የምትገምተውን ስለሰማች በጣም አልተደነቀችም። «ምን ሆነን ነው?» ብላ ለመጠየቅ አልፈለገችም። እውነቱን መስማት ስለፈራች ወይም ብዙም ከማትግባባትና ከማትቀርባት ሴት የመጣ መረጃ ስለሆነ ሆን ብላ ላለማመን ስለፈለገች ሊሆን ይችላል። ለእሷም ግልጽ አይደለም። ግን ማንንም፣ «ምን ሆነን ነው?» ብላ ለመጠየቅ አልደፈረችም።

ከወ/ሮ ማርታ፣ ከአቶ ደመቀና ከእትዬ ወርቂ እንዲሁም ከሌሎች በጣት ከሚቆጠሩ ጥቂት ሰዎች በስተቀር በሌሎቹ ሠራኞች ላይ የምታስተውለው ፍርሃትና የማግለል ሁኔታ ነበር። ሚካኤል የነገራትን እውነታ ትክክል እንደሆነ ብታምንበትም እሷ የምትወዳቸውና የምታከብራቸው ሰዎች

እስካላገለሏት ድረስ ሌሎቹን ንቃ ልትተዋቸው ወሰነች። መጨነቋና አንዳንድ ቀን በሚያጋጥማት ዓይን ያወጣ የማግለል ሁኔታ መጎዳቷ ግን አልቀረም።

ታደለ ከኤች.አይ.ቪ. ነጻ እንደሆነ ሁሉም ሠራተኞች ቢሰሙም «ከነ-ግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ» እንደሚባለው፣ እንደ ታላላቆቹ ያገሉት ነበር። አንድ ቀን ከግቢው የጥበቃ ሠራተኞች አንዱ ደረጀን ክፍላቸው ውስጥ ይዘው ገብተው ያቅፉታል፣ ጉንጮቹን ይደባብሱታል፣ እየሳሙ ያንቀለጳጽሱታል። ታደለ ከደረጀ'ጋ ሊጫወት ፈልጎ ወደ ጥበቃ ሠራተኛው ወደ አቶ አሸብር ክፍል ገባ። ሰውየው ታደለን ሲያዩ ከመቅፅበት ፊታቸው ተለዋወጠ። ታደለ ክፍሉ ውስጥ ሲገባ እመለዘውድ ከበሩ ፊት ለፊት በቅርብ ርቀት ሆና በዓይኗ ተከትላዋለች።

አቶ አሸብር፣ «ውጣ!» ብለው ጮኹበት።

ታደለ ልጅ ነውና ቁጣቸው በደንብ ስላልገባው ክፍሉ ውስጥ ያለውን አልጋ ደገፍ ብሎ ቆመ።

«አልጋዬን አትንካ! . . . ውጣ እኮ ነው የምልህ! . . . ውጣ!» በቁጣ አንባረቁበት።

ታደለ አሁን ነበር የሰውየውን መናደድ ያስተዋለው። ደንግጦ ከክፍሉ በፍጥነት ወጣ።

የሚሆነውን ሁሉ ትከታተል የነበረችው እመለዘውድ ተንደርድራ ታደለ አጠገብ ደረሰችና የወንድሟን እጅ ይዛ፣ «ምነው? ምን አደረገ?» ብላ ሰውየውን በቁጣ ጠየቀቻቸው።

«እዚህ ክፍል እንዳይገባ! አልጋዬንም እንዳይነካ!»

«ምን ስላደረገ?»

«በቃ እንዳይገባ ብያለሁ፣ እንዳይገባ!» አሉ ሰውየው በቁጣ።

እመለዘውድ የእንባ ሳግ ጉሮሮዋን ስለደፈነው ምንም መናገር አልቻለችም። ማድረግ የቻለችው አቶ አሸብርን መገላመጥ ነበር። አቶ አሸብር፣ በጭኖቻቸው መሀል ወደ ያዙት ወደ ደረጀ ትኩረታቸውን ስለመለሱ፣ በግልምጫዋ ልታስተላልፈው የፈለገችው የቁጣ መልዕክት አልደረሳቸውም።

ታደለን እቅፍ አድርጋ ግቢው ውስጥ አንድ ጥግ ላይ ተቀመጠች።

«አይዞህ ታደለ! . . . አይዞህ ታዱ! . . . ዝም በላቸው!»



Sample output to test PDF Combine only



ታደለ ዓይኖቹን እያቁለጨለጨ ዝም ብሎ ያያታል። እፅናኝና አባባይ የሚያስፈልጋት እመለዘውድ እንጂ ታደለ አልነበረም። ዘበኛው አቶ አሸብር ታደለን ባዩበት ዓይን እሷንና ሚካኤልንም እንደሚያዩ እርግጠኛ ስለሆነች የመገለልና የመገፋት ስሜት ተሰማት። ተከፋች፤ አዘነችም።

ምንም የማያውቅ ሕፃን ወንድሟን እንደተለየ ፍጡር ማየታቸው አበሳጫት። እናቷ፣ እሷና ወንድሞቿ በራሳቸው ዓለም የሚኖሩ፣ የሚገፉ፣ የሚጠቁ ደሆች እንደሆኑ ስታስብ የኖረችውን ሕይወት አሁን ዳግመኛ የበለጠ እንድታስበው ተገደደች።

ደሀ በመሆኗ ከእኩዮቿ እኩል መልበስ፣ በነጻነት ትምህርት መማር፣ የተሻለ ኑሮ ከሚኖሩ ጎረቤቶቻቸው ልጆች ጋር መጫወት፣ አበባየሆሽ መጨፈር አልቻለችም። ይህ ደግሞ ራሷንና ቤተሰቧን የተለዩ እንደሆኑ እንድታስብ አድርጓታል። ቡታጅራ የተለየ ዓለም አይታ ነበር፤ እሷም ወንድሞቿም ከሌሎች ልጆች እኩል እንደሆኑ እንዲሰማት የሚያደፋፍር ሁኔታ። ጆሮዋ በደንብ ስለማይሰማ፣ በአጠቃላይ የጤንነቷ ሁኔታም ጥሩ ስላልነበር የዝቅተኝነት ስሜት የሚሰማትና አንዳንድ ጊዜ ራሷን የማግለል ችግር የነበረባት ቢሆንም የመድኃኒዓለም ት/ቤት ቆይታዋ ከሞላ ጎደል ጥሩ ነበር። አሁን ወደ ኋለኛው አስተሳሰቧ ተሸቀንጥራ ለመመለስ አፍታም አልፈጀባት። አዎ፣ ዛሬም እንደድሮው ዓለም በእመለዘውድ ዓይን ለሁለት ትከፈላለች፤ እሷና ወንድሞቿ እንዲሁም ሌሎች።

እስተቃቀፏ ምቾት እስኪነሳው ድረስ ወንድሟን ጥብቅ አድርጋ አቅፋ፣ «አይዞህ! . . . አይዞህ ታዱ!» አለችው።

ለእትዬ ወርቂ ከሁለት ዓመታት በኋላ በጻፈችው ደብዳቤ ለጥበቃ ሠራተኛው ለአቶ አሸብር ሰላምታ አቅርባ እንደታዘበቻቸው ግን ገልጻለች።

*ይድረስ በጣም ለምወድሽ እናቴ እትዬ ወርቂ፣ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ አንቺን መለየት ሳልፈልግ በግድ ተለያየን። አብዬ፣ እኛ በጣም ደህና ነን። አታስቢ። ግን አብዬ ፀልይልን። ዓይንሽን አሁን ይሻልሻል ወይ? እኔ ከዚህ ሆኜ እጠይቃለሁ። ግን ምን ያደርጋል አብዬ?! እኔኮ በጣም እወድሻለሁ! በተረፈ ለብርሀኔ ደብዳቤ ፅፌ ለጳውሎስ ሰጥቸዋለሁ። ጋሽ አሸብርን፣ ሐብቴን፣ ግርማን ንጉሴን እትዬ ወርቅነሽን ሠላም በይልኝ። በጣም እወዳችኋለሁ፤ ግን ጋሽ አሸብር አስቀይመውናል። ለምን? ታደለን «አልጋዬን እንዳትነካ!» ብለው ደረጀን ያቅፉት ነበር። ግን እግዚአብሔር ይህን አይቶ አልጠላንም። ሁሌ እንደጠበቀን ነው። አምንም አያውቅም። ሁላችንም ትምህርት ቤት ገብተናል። እኔ 4ተኛ*

*ክፍል እገባለሁ፣ ለሚቀጥለው:: አሁን ሦስተኛ ክፍል ነኝ:: 5ኛ ወጥቻለሁ:: 3ተኛ ከወጣሁ ከአንቺ ሽልማት አለኝ አብዬ? ያኔ ለብርሃኔ ፎቶ ተነስተሽ ስትሰጪያት፣ «ለኔም» ስልሽ፣ «አሳጥቤ እሠጥሻለሁ» ብለሽኝ ነበር:: አብዬ! እኔም እኮ የአንቺ ልጅ ነኝ:: ትናፍቂኛለሽ:: አሁን ከተለያየን 2 ዓመት ከምናምን ነው:: ታዲያ አልናፈቅንሽም? ፎቶውን በፖስታ አድርገሽ፣ ደብዳቤ ፅፈሽ ላኪልኝ:: አንቺ ካልተመቸሽ ግርማ ወይም ንጉሴ ይፃፉልሽ:: በተረፈ ለዘላለም እወድሻለሁ::*

*ቻው*
*ቻው*





## -40-

*«እህቴና ወንድሜ ኤች.አይ.ቪ. እንደያዛቸው ነገሩኝ:: ቅስሜ ሰብር አለ፤ ሁሉ ነገር ጨለመብኝ:: ሸክም ተሸክሜ ፊቴ ላይ ድቅን ይሉብኛል::»*
*ተሾመ ግርማ*

*«እንዲያው በቃ ቁጡ ሆነች:: አሁን ደህና ስትጫወት የነበረችው ልጅ ድንገት ስትቆጣ ታያታለህ::»*
*ወ/ሮ ወርቅነሽ ወልደየስ*

አመለዘውድ ለወራት የናፈቀችውን ውድ ወንድሟን ተሾመን ማየት ፈለገችና አንድ ቀን ወ/ሮ ማርታ'ጋ ሄደች::

«እማማ ታላቅ ወንድሜ በጣም ናፈቀኝ:: ሄጄ ልጠይቀው እችላለሁ?» ብላ ጠየቀቻቸው::

«ወንድምሽ? ወደ ቤት የገባው እኮ እናንተን ይዘናችሁ ስንመጣ ነው:: አሁንም እዛው ቤት ይሆን እንዴ?»

«እዚህ ኮሌጅ አካባቢ አይጠፋም:: ፈልጌ ባገኘውና አይቼው ብመጣ ደስ ይለኛል::»

«አንቺማ አምሻል:: ከቤት መውጣት የለብሽም:: እናስጠራዋለን::» አሏት:: «እንዲያውም የቤታችሁን የመሬት ግብር ለመክፈል፣ እኔም ላናግረው እፈልጋለሁ::»

አመለዘውድ ስታመነታ ቆይታ፣«ወንድሜ ብቻውን መሆኑን ሳስበው ያሳዝነኛል:: እኛስ እናንተ አላችሁልን:: እሱ ግን ማንም የሚረዳው የለም::» አለቻቸው:: እሱንም እርዱት ለማለት ዳር፣ ዳር ማለቷ ነበር::

«ምንድነው የሚሰራው ግን?» ብለው ጠየቁ ወ/ሮ ማርታ::

«ዕቃ መሸከም ምናምን ይመስለኛል:: አንዳንድ ጊዜ ሥራ ስለማያገኝ ይርበዋል::» አቀርቅራ እንደ መተከዝ አለች::

«እስቲ ለሁሉም ይምጣና አነጋግረዋለሁ»

«እሺ እማማ!» አለች ፍላጎቷን እንደተረዱላት ተስፋ እያደረገች::

ተሾመ በሚቀጥለው ቀን ተጠርቶ መጣ:: አመለዘውድን ግቢው ውስጥ ሲገባ በሩ ፊት ለፊት አያት:: ተያዩ::

«ተሼ!»

ሮጣ ሄዳ አቀፈችው:: ቶሎ አልለቀቀችውም:: ለወራት በናፍቆቱ ስትሰቃይ ኖራለች:: ውስጧ የሚተራመሰው ፍቅርና ናፍቆት ሰቀቀን ሆኖባት ነበር::

ግሩም ፈገግታዋ ፊቷን እንደሞላው፣«እንደምን ነህ?» አለችው::

«ደህና ነኝ» አላት:: «እናንተ ደህና ናችሁ?» ተሾመ እህቱን በማግኘቱ ተደስቶ ፊቱ በስስ ፈገግታ ፈክቷል::



Sample output to test PDF Combine only

«ደህና ነን። በጣም ደህና ነን! እነእማማ በጣም ጥሩ ሰዎች ናቸው። ሁሉ ነገር ተሟልቶልናል። መኝታ ቤታችን ፎቁ ላይ ነው። ምግብ በደንብ በሥነ ሥርዓት ይቀርብልናል። ልብስ ይሰጠናል። አንተ ደህና ነህ? እኔ አንተ ብቻህን መሆንህን ሳስብ ነው የምጨነቀው። እኛስ አብረን ነን። »

«አይ እኔ ደህና ነኝ። ስለእኔ አታስቢ።»

«እኛም ደህና ነን። ስለኛ ምንም አታስብ። ለመሆኑ አሁን የት ነው የምታድረው?»

«ያው አስፋልት አካባቢ ስሰራ ውዬ ማታ ቤት ገብቼ አድራለሁ። ብዙ ጊዜ ጓደኞቼ አብረውኝ ያድራሉ።»

«እማማ ሲጠሩህ ትገባና ታነጋግራቸዋለህ። እና ተሼ አደራ! የሚሉህን እሺ በል!» አለችው ዓይን ዓይኑን በልምምጥ እያየች።

ዝም አላት። ድንገት ጉልበቱ ላይ ወደቀች።

«እንዴ! ምን ነካሽ?» አለ ተሾመ ደንግጦ ጎንበስ ብሎ ትከሻዎቿን እየያዘ።

«ተሼዬ! እባክህ የሚሉህን እሺ በላቸው። አደራ!»

«እሺ በቃ ተነሽ!» አላት።

«እሺ ትላቸዋለህ?»

«አዎ አልኩሽኮ! ተነሽ!» አለ ተሾመ ሊያነሳት እየሞከረ።

ደስ ብሏት ከተንበረከከችበት ተነሳች።

«ነግሬሃለው አደራ! እዚህ ቆይ፤ መምጣትህን ልንገራቸው። በኋላ እናወራለን።» ብላው ወደ ወ/ሮ ማርታ ሄደች።

ወ/ሮ ማርታ በዕለቱ በርከት ያሉ እንግዶች ስለጋበዙ ወጥ ቤት ምግብ እያዘጋጁ ነበር።

«ወንድማችን መጥቷል እማማ።» አለቻቸው አመለዘውድ ወጥ ቤት እንደገባች።

«መጣ? ቆይ አነጋግረዋለሁ።» አሉ የሚከትፉት ቲማቲም ላይ እንዳተኮሩ።

«ምን ልስራ እማማ?» አለቻቸው።

«እነሱን ሰሃኖች እጠቢ!» አሏት።

አንድ ቦታ የተቆለሉትን ሰሃኖች ማጠብ ጀመረች። እጇ ይንቀሳቀስ እንጂ፣ አእምሮዋን ሙሉ በሙሉ የተቆጣጠረው የወንድሟ ጉዳይ ነበር። 'ምን ይሉት ይሆን? እሱስ ምን ይላቸዋል? . . . አቤት ከእኛ ጋር እንዲኖር ቢፈቅዱለት እንዴት ደስ ይለኝ ነበር! ጌታ ሆይ እርዳኝ!' እያለች ያለማቋረጥ ታስባለች።

«እስቲ ያንን ልጅ ጥሪው» አሏት ወ/ሮ ማርታ እትዬ ወርቁ ወደ ወጥ ቤቱ ስትገባ። የጀመሩትን የቲማቲም ከተፋ እያጠናቀቁ ነበር።





ተሾመ ተጠርቶ መጣ።

«እንደምን ነህ?» አሉት ወ/ሮ ማርታ እጃቸውን እየዘረጉለት።

«ደህና» አለ እየጨበጣቸው።

«ቁጭ በል እስ'ጋ» አሉት ወደ አንድ ወንበር እያመለከቱት፤ እሳቸውም ወንበር ስበው ተቀመጡ።

አመለዘውድ ሰሃኖቹን እያጠበች ሰረቅ እያደረገች ወንድሟን ታየው ነበር። ወ/ሮ ማርታ እሷን እያዩ፣ «እንዴት ነው ኑሮ?» አሉት ስለሆነ ነገር እያሰቡ እንደሆነ በሚጠቁም ጎተት ባለ ድምጽ።

«ጥሩ ነው።»

አመለዘውድ ሰረቅ አድርጋ ስታያቸው ከወ/ሮ ማርታ ጋር ዓይን ለዓይን ተገጣጠሙ። ፊታቸውን አንብባ ብቻውን ሊያናግሩት እንደሚፈልጉ ተረዳች። ወዲያው የምትሰራውን ሥራ አቋርጣ ከወጥ ቤቱ ወጥታ ሄደች።

«ታያታለህ እህትህን!? ትልቅ ሰው እኮ ናት! ውጪልን ሳልላት ወጥታ ሄደች።» አሉት።

ተሾመ ወ/ሮ ማርታ ለእህቱ ያላቸው አድናቆት ከልብ የመነጨ መሆኑን ፊታቸውን አይቶ ተረዳ።

«ቤቱን እየጠበቅክ ነው አይደል? »

«አዎ»

«ምንድነው አሁን የምትሰራው?»

«የተገኘውን»

«የተገኘውን ስትል?»

«ያው ታክሲ ተራ አካባቢ፣ እሸከማለሁ . . . ሌሎችም ስራዎች ካሉ እሰራለሁ።»

«የግንባታ ሥራ እዚህ እኛ'ጋ ብናገኝልህ ትሠራለህ?»

«አዎ» አላቸው። «የማላስቸግራችሁ ከሆነ»

«ሥራ እንፈልግልሃለን። እህትህ ብቻውን ነው እያለች ትጨነቃለች።» አሉና ወ/ሮ ማርታ ለአፍታ ዝም አሉ።

ከጥቂት ሰከንዶች ፀጥታ በኋላ፣ «. . . ሌላ እንድታውቀው የምፈልገው ነገር አለ።» ብለው በረጅሙ ተነፈሱ።

«ምንድነው?» ብሎ እንዲጠይቃቸው ቢጠብቁም ተሾመ በዝምታ የሚናገሩትን ለመስማት ይጠባበቅ ነበር።

«አመለዘውድና ሚካኤል ኤድስ የሚባለው በሽታ ይዟቸዋል።» አሉት።

በደንብ ያልሰማቸው መሰለው።

«ምን አሉኝ?»



Sample output to test PDF Combine only

«ሁለት ጊዜ ደማቸውን አስመርምረናቸው። ሁለት ጊዜም ፖዘቲቭ ሆነዋል። ትንሹ ግን ደኅና ነው።» ቀጠሉ ወ/ሮ ማርታ። «አባታችሁና እናታችሁም በዚሁ በሽታ ምክንያት የሞቱ ይመስለኛል።»

'ምን?' ክው ብሎ ደነገጠ። ልቡ በኃይል ትመታ ጀመር። ዓይኖቹን ሰብሮ ድርቅ ብሎ ከመቀመጥ በስተቀር ምንም ቃል መተንፈስ አልቻለም። 'ኤድስ?! . . . እንዴት ያዛቸው?!' እያለ ያስብ ነበር። በድንጋጤ አንደበቱ ተለጎሞ ፍዝዝ ብሎ ተቀመጠ።

«እህትህን ነው እንጂ የሚያማት ወንድምህ እስካሁን ደህና ነው። . . . አንተም ራስህን ጠብቅ! እንደ አባትህ ጠጅና አረቄ አትጠጣም አይደል?»

«እ?»

«መጠጣት የለብህም። መጠጥ ነው ይህን ሁሉ ችግር ያመጣባችሁ።»

«ኧረ እኔ አልጠጣም» አላቸው።

«አዎ፤ መጠጥ መጥፎ ነው።»

የመጠጥ ሱሰኛ አድርገው እንዳሰቡት ገመተ። የግንባሩ ደም ስሮች ተወጣጠሩ። ከምንም ዓይነት ሱስ ነፃ መሆኑን ባለማወቃቸው ተናደደባቸው። ወ/ሮ ማርታ የፊቱን መለዋወጥ ሳያስተውሉ ማውራት ቀጠሉ።

«እኛ እህትህንና ወንድሞችህን በደንብ እንከባከባለን። . . . » ዝም አሉ። «. . . የቤታችሁ የቦታ ግብር የሁለት ዓመት እንዳልተከፈለ ሰምቻለሁ እሱን እኛ እንከፍላለን። . . . » አሉት።

ተሾመ አቀርቅሮ ዝም ከማለት ውጪ ምንም አልተናገረም።

«ምነው ዝም አልክ?»

«እሺ! ጥሩ ነው።»

«በል ያልኩህን የግንባታ ሥራ ከሰሞኑ መጥተህ መጀመር ትችላለህ። . . . ደግሞ አንተም ብትመረመር ጥሩ ይመስለኛል። ለማንኛውም፣ ጥንቃቄ እንድታረግ መመርመሩ ጥሩ ነው።»

«እሺ» አላቸው ቀዝቃዛ ላብ እያላበው።

ከወጥ ቤቱ ሲወጣ፣ ውጪ አመለዘውድ ሚካኤልንና ታደለን ይዛ እየጠበቀችው ነበር። የጨለመ ፊቱን እንደምንም በፈገግታ አፈካውና ወንድሞቹን እየጨበጠ ጉንጮቻቸውን ሳመ።

«እ? ምን አሉህ?» አለችው አመለዘውድ የተባለውን ለመስማት በጣም ጓጉታ።

«ሥራ አለ እንቅጠርህ አሉኝ።»

«አሉህ?»

«አዎ»



Sample output to test PDF Combine only



በደስታ እየተፍነከነከች፣ «አላልኩህም?! ጥሩ ሰው ናቸው። እና አንተ ምን አልካቸው?»

ዓይኖቹን ከዓይኖቿ እያሸሸ፣ «እሺ ብያቸዋለሁ» አላት።

አመለዘውድ ደስታዋ ወሰን አልነበረውም። ትከሻውን አቅፋው ጎኑ ላይ ተለጠፈችና፣ «ጎሽ ተሸዬ! በቃ አብረን ልንኖር ነዋ!? ሊረዱህ ነዋ?!» አለችው።

ፈገግ ብሎ ዝም አላት። አሳዘነችው።

«ቆይ መጣሁ። ምሳ አብረን በልተን ትሄዳለህ።» ብላው ከሁለቱ ወንድሞቹ ጋር ትታው ሄደች።

«ደህና ናችሁ?» ተሾመ ሚካኤልን ጠየቀው።

«ደህና ነን» አለ ሚካኤል።

ተሾመ ምን እንደሚል ሲያስብ ቆየና፣ «አያማችሁም አይደል?» ብሎ ጠየቀው።

«አያመንም» አለና ሚካኤል ትንሽ አሰቦ፣ «አመለዘውድ ኪንታሮት ፊቷ ላይ ወጥቶባት ነበር።» ሲል አከለ።

ዝም ብለው ለአፍታ ቆዩ።

«እዚህ አንድ ትንሽ ልጅ አለ። 'እናንተ የማይድን በሽታ ይዟችኋል' አለኝ።» አለ ሚካኤል ትንሽ ሲያስብ ቆይቶ።

«ምን?»

«'የማይድን በሽታ ይዟችኋል' አለኝ።»

ተሾመ፣ 'ያውቃሉ ማለት ነው?' ሲል አሰበና ዝም አለ።

ተሾመ አዘነ። 'እንዴት ግን እኛ ቤት ውስጥ ኤድስ ሊገባ ቻለ?' ሊመልሰው ያልቻለውን ጥያቄ ደጋግሞ ራሱን ጠየቀ።

አመለዘውድ ተመልሳ መጣች። ልክ ሁልጊዜ እሱን ስታገኘው እንደምትሆነው ደስተኛ ነበረች። በህይወቷ ምንም ፈተና አጋጥሟት የማታውቅ፣ ከበሽታ፣ ከሥጋት፣ ከሀዘን፣ ከሰቀቀን ፍፁም ነፃ የሆነች መስላ ነበር የምታናግረው።

አራቱ የአቶ ግርማና የወ/ሮ ድንቄ ልጆች፣ ከብዙ ወራት በኋላ ምሳ በአንድ ትሪ ዙሪያ ተቀምጠው ተመገቡ። አመለዘውድ፣ ሚካኤልና ታደለ ከቡታጅራ መጥተው እዚህ መኖር ከጀመሩ በኋላ ለየብቻ ነበር ምግብ የሚሰጣቸው። በተለይ አመለዘውድና ሚካኤል ብዙም የምግብ ፍላጎት ስለሌላቸው እትዬ ወርቂ ሲያስተርፉ ለመከታተልና ለመቆጣት እንዲመቻት ነበር ቡታጅራ የለመዱትን እዚህም እንዲቀጥሉበት ያደረገችው።

እነሆ ዛሬ አመለዘውድ ሁሉም ወንድሞቿ በአንድ ማዕድ ዙሪያ ተሰብስበው ማየቷ እጅግ በጣም አስደሰታት፡፡ ይጎራረሱ ጀመር፡፡ አመለዘውድ ተሾመን፣ ተሾመ ደግሞ ሁሉንም አጎረሳቸው፡፡ ተሾመ ወ/ሮ ማርታ የነገሩትን ለጊዜውም ቢሆን ለመርሳት ሞክሮ ተሳካለት፡፡ ደስተኛ መስሎ ይታይ ነበር፡፡ ፈገግታ ከፊቱ አልጠፋም፡፡ ግን አልፎ አልፎ ጥልቅ ሐዘን ፊቱ ላይ ይነበብና ይተክዝ ነበር፡፡ አመለዘውድ በደስታ ስለተዋጠች ማዘኑን አላስተዋለችም፡፡

ከምሳ በኋላ ተሾመን ከቡታጅራ ከመጡ የፕሮጀክት መርሲ ሠራተኞችና እዚያው ግቢው ውስጥ ከሚሰሩ ሰዎች ጋር አስተዋወቀችው፡፡

«ወንድሜ ነው፤ ተዋወቁት!» ስትል በከፍተኛ ኩራትና ደስታ ተሞልታ ነበር፡፡

ከሰዎቹ ጋር ካስተዋወቀችው በኋላ በትንንሾቹ ወንድሞቻቸው ታጅበው ተቀመጡ፡፡ ልትነግረው ስትመኘው የነበረውን ነገር አሁን ልትነግረው ወሰነች፡፡

«ተሼ፣ ከዚህ ግቢ ፊት ለፊት ያለው መካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን መሄድ ጀምሬአለሁ፡፡»

ቀና ብሎ አያት፡፡

ስሜቱን ለማጥናት ለአፍታ ዝም ብላ ቆየችና ዝም ሲላት መናገር ቀጠለች፡፡ «ብታይ የሚያስተምሩት በጣም ደስ ይላል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሁላችንንም ለማዳን እንደሞተ ተምሬአለሁ፡፡ ኢየሱስ አንተንም፣ እኛንም፣ ሁላችንንም ይወደናል፡፡ የሞትልንም እኛ ለዘላለም እንድንኖር ነው፡፡ . . .» የምታውቀውን የተረዳችውን ልታስረዳው ጣረች፡፡

አቀርቅሮ ዝም ብሎ ቆየና፣ «ጴንጤ አደረጓችሁ?!» አለ፡፡

«እነሱ ሁኑ ስላሉን አይደለም፡፡ እኔ ራሴ አይቼ ስለወደድኩት ነው፡፡ ተሼ! በእውነት! በጣም ደስ ይላል! . . .» የተረዳችውን ነገር ልታብራራለት ሞከረች፡፡

ተሾመ እህቱ ሃይማኖትን በተመለከተ አንድ እሱ ያልገባው ነገር እንደገባት ተረድቷል፡፡ በተጽዕኖ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይ እንደሆነች በበኩሉ ቢያምንም፣ አሁን በምታወራው ነገር ፍጹም እንደምታምንበትም ተገንዝቧል፡፡ እሷ የተረዳችውንና ያመነችበትን እሱም እንዲያውቅና እንዲያምንበት ያላትን ከፍተኛ ጉጉት ከፊቷ አንብቧል፡፡ ጉጉቷ ለሱ ካላት ፍቅር የመነጨ እንደሆነም አውቋል፡፡ እስካሁን በድብቅ ሲያዝን ዕንባውን ወደ ውስጥ ሲያፈስ የነበረው ተሾመ ማልቀስ ጀመረ፡፡ አመለዘውድ ደነገጠች፡፡





«ምነው? ለምን ታለቅሳለህ?»

ተሾመ መልስ ሳይሰጣት ዕንባውን አፈሰሰ፡፡ ሚካኤልና ታደለ በመገረም ወንድማቸውን አዩት፡፡ ወ/ሮ ማርታ ስለነገሩት ምስጢር የሚያውቁት ነገር የለምና ፕሮቴስታንት ስለሆኑ ብቻ አዝኖ ያለቀሰ መሰላቸው፡፡

«ነገርኩህ'ኮ ተሼ፤ ራሴ ፈልጌ እንጂ ሳላምንበት አይደለም፡፡»

ተሾመ ለጥቂት ደቂቃዎች አለቀሰ፡፡ ጥቂት ቆይቶም ለመሄድ ተነሳ፡፡

ከግቢው ሲወጣ አመለዘውድ ተከትላው ከግቢ እየወጣች፣ «ትመጣለህ አይደል ተሼ?»

«አዎ»

«መቼ ትመጣለህ?»

ትንሽ አሰበ፣ «የሚቀጥለው ሳምንት»

«ለምን ነገ አትመጣም?»

«ነገ አይመቸኝም፡፡»

«ለምን?»

«በቃ የሚቀጥለው ሳምንት እመጣለሁ አልኩሽ'ኮ» አላት እንደ መሰላቸት ብሎ፡፡

«እሺ» አለችው ፈጠን ብላ፡፡ «እንዳትቀር እሺ!»

«አልቀርም»

«ማልልኝ»

«እመጣለሁ አልኩሽ'ኮ»

«አይሆንም ማልልኝ! . . .ግርማ ይሙት በል!»

«ግርማ ይሙት!»

«እንዳትቀር! ነግሬሃለሁ!»

ተጨባብጠው ተለያዩ፡፡

ተሾመ ከሄደም በኋላ አመለዘውድ ብቻዋን ፈነጠዘች፡፡ ወንድሟ ከእነሱ ጋር ሊኖር ነው፡፡

አንድ ሳምንት አለፈ፡፡ ከዚያ በኋላ ባሉት ቀናት አመለዘውድ የግቢው በር ሲከፈት በሰማች ወይ ባየች ቁጥር የልቧ ምት ይጨምራል፡፡ ወንድሟን ለማየት ትጓጓለች፡፡ ልቧ ስቅል ብሎ በተስፋ ብትጠብቀውም እመጣለሁ ባለበት ሳምንት አልመጣም፡፡ በሚቀጥለውም ሳምንት ከዛሬ ነገ ይመጣል ብላ በተስፋ ጠበቀችው፡፡ ተሾመ ዳግመኛ ወደ ወ/ሮ ማርታ ቤት ሳይመጣ ቀረ፡፡ አመለዘውድ እዝን፣ ትክዝ አለች፡፡

«ወንድምሽ ምነው ቀረ?» አሏት ወ/ሮ ማርታ አንድ ቀን፡፡

«እኔ እንጃ፤ 'እመጣለሁ፣ አልቀርም' ብሎኝ ነበር፡፡» አለች በሃፍረት ራሷን ደፍታ፡፡



Sample output to test PDF Combine only

'እሳቸው ሊረዱት ሲያስቡ እሱ ይጠፋል እንዴ?!' ብላ በወንድሟ አፈረችበት፤ ተናደደችበት፤ አዘነችበትም።

አንድ ቀን እነወ/ሮ ማርታ ከሚረዷት፣ ግቢው ውስጥ ከምትኖር እታፈራሁ ከምትባል በዕድሜ በጥቂት ዓመታት ከምትበልጣት ልጅ'ጋ ተሸመን ፍለጋ ወደ ቤት ሄደች። ቤቱ ውስጥ የጫት ገራባና የሲጋራ ትርኳሽ አይታ ደነገጠች።

«በቃ ይሄ ልጅ ተበላሸ ማለት ነው።» ብላ አዘነች።

አመለዘውድ ከዚያ በኋላ እነወ/ሮ ማርታ ቤት በነበራት ቆይታ ቁጡና ኃይለኛ ሆነች። አንዳንድ ጊዜ ቡታጅራ መመለስና እንደሷና እንደወንድሞቿ ካሉ ወላጆቻቸውን ካጡ ልጆች ጋር እኩል ሆኖ መኖር ያምራታል። ግን መጀመሪያ ለምን መጡ? ችግር ስላለባቸው አይደል? ከነዚያ ወላጆቻቸውን ካጡ ልጆች ጋር እንኳን እኩል አይደሉም። ይህን ማሰብ ያበሽቃታል። በዚያ ላይ ወንድሟ ተሾመ እመጣለሁ ብሎ ዋሽቷት፣ ምሎላት ቅልጥ ብሎ ቀርቶ አብግኗታል፣ አሳርሯታል። ህይወትን እየጠላች ነው። እናቷ ከመሞቷ በፊት ምንም ዓይነት ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ብትገባ እንኳ መኖር አስጠልቷት አያውቅም ነበር። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ አሁን በሰዎች መፈቀር በእጅጉ ትሻለች። ሊያገኟት ያሰቡ የመሰላትን ንዴትና ቁጣዋን በግልጽ ታሳያቸዋለች። ብሶት ስላለባት ብስጭቷን ለመደበቅ ምንም ሙከራ አታደርግም።

አንድ ቀን በቆሎ መጥበስ ፈልጋ ከግቢው ነዋሪዎች አንዷ ወ/ሮ ወርቅነሽ እንዳትጠብስ ከለከሏት። ተናደደች።

«ለምንድነው የማልጠብሰው?»

«በቃ አይሆንም አልኩሽ። የምልሽን ስሚ።» አሉ አዛውንቷ። ልጅቷ ታማሚ ስለሆነች አርፋ ብትቀመጥ ይሻላል ብለው አስበውላት ነበር የከለከሏት።

«እኮ ለምን?»

«አይሆንም። ሌላ ሰው ጠብሶ ይሰጥሻል።»

«እኔ የማልጠብስበት ምክንያት ምንድነው? ያስረዱኛ!»

«ሌላ አዋቂ ሰው ጠብሶ ይሰጥሻል።»

«እኔ በቆሎ መጥበስ አያቅተኝም።»

«በቃ አይሆንም ብያለሁ፣ አይሆንም!»

«ለምን? . . . ለምን?» ጮኸችባቸው።

«አርፈሽ ተቀመጭ!»

ንዴቷ ሊያቀውሳት የደረሰ መሰለ። ዞር፣ ዞር ብላ ክፍሉን ቃኘች። በቅርብ ከተቀመጡ የሚያማምሩ የሸክላ ሰሃኖች አንዱን ድንገት ብድግ አድርጋ በሁለት እጆቿ ከራሷ በላይ ከፍ አድርጋ ይዛ የሲሚንቶው ወለል



Sample output to test PDF Combine only



ላይ ፈጠፈጠችው። ሰሃኑ ኃይለኛ ድምጽ አሰምቶ ተሰባበረ። ስብርባሪዎቹ ወለሉን አዥጎረጎሩት።

እትዬ ወርቅነሽ የልጅ ልጃቸው ከምትሆን ትንሽ ልጅ እንዲህ ዓይነት ቁጣ ስላልጠበቁ በመጀመሪያ ክው ብለው ደንግጠው ያዩትን ለማመን ተቸገሩ። ከድንጋጤያቸው መለስ ሲሉ ግን ተናደዱ፣ «እንዴ! እንዴ! እንዴ! . . . ሰበርሽው!? . . . በይ የሰበርሽትን ወስደሽ አሳዩ! ትሰሚኛለሽ?!» ብለው አፈጠጡባት።

ሲቆጧት እንደ ማንኛውም ልጅ ትፈራለች ብለው ገምተው ነበር። ግን ሌላ ከግምታቸው ውጪ የሆነ ሁኔታ ተከተለ።

አመለዘውድ፣ «አሳያለሁ!» ብላ በፍጥነት የተወሰኑ የሸክላ ሰሃኑን ስብርባሪዎች ለቅማ ከክፍሉ እየተጣደፈች ወጣች። እትዬ ወርቅነሽ ከክፍሉ ስትወጣ እያዩዋት በልጅቷ ኃያል ቁጣ እጅግ ተደንቀው ፈዘዙ።

አመለዘውድ ቀጥታ ወ/ሮ ማርታ ወዳሉበት ነበር ያመራችው።

«እማማ!» አለች አመለዘውድ ወ/ሮ ማርታ ፊት ቆማ።

«አቤት»

«እኚህ እትዬ ወርቅነሽ አናደውኝ ይህን ሰሃን ሰበርኩት።»

«የቱን?»

«ይኸው! ይህንን!»

ወ/ሮ ማርታ ለአፍታ ፀጥ ብለው አሰቡ። «ይሰበር! የታባቱ! አንቺና እኔን ሊያጣሉን ነው አይደል? ተይው! ይሰበር!» አሏትና ወደ ደረታቸው ሳብ አድርገው አቀፏት።

አመለዘውድ በወ/ሮ ማርታ እቅፍ ውስጥ እንደገባች ንዴቷ በፍጥነት ሰከነ።

ከሰዎች ጋር ከመሆን እነወ/ሮ ማርታ ከሚያሳድጉት ዳንቴ ከሚባል ውሻ ጋር መጫወት ትመርጣለች። በግቢው ውስጥ ባደገው የተከረከመ ሳር ላይ ድንኩን ቀይ ውሻ አቅፋው ትተኛለች። ትደባብሰዋለች። ታቆላምጠዋለች። እሱም ጭራውን እየነሰነሰ፣ እየላሳት፣ እየተቁነጠነጠ ፍቅሩን በራሱ ቋንቋ ይገልፅላታል። ዳንቴ አያገላትም። ከሰው ልታገኘው የምትፈልገውን ፍቅር ያለስስት፣ ያለፍርሃት፣ ያለመሳቀቅ ይሰጣታል። ዳንቴ ከክፋትና ከጥላቻ የጸዳ ነው። ንጹህ ነው።

ወ/ሮ ማርታና ባለቤታቸው አቶ ደመቀ ሥራ ስለሚበዛባቸው ከልጆቹ ጋር ብዙ ጊዜ ማሳለፍ አይችሉም። ወ/ሮ ማርታ ጊዜ ኖሯቸው ከልጆቹ ጋር ሲገናኙ ግን በአመለዘውድ ዘውትር ይደነቁባት ነበር። ብስለቷ፣ አነጋገሯ፣

ለወንድሞቿ ያላት ፍቅር ያስደምማቸዋል። የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል ለማወቅ ያላት ጥረትና ጉጉት ይማርካቸዋል። በአጭር ጊዜ ውስጥ ያዳበረችው ጠንካራ እምነት ያስገርማቸዋል።

«ይህቺ ልጅ የሆነ የእግዚአብሔር ፀጋ አላት። ተባርካ የተፈጠረች ናት።» ይላሉ ለባለቤታቸውና ለሌሎች ሰዎች። ፍቱን መድኃኒት ባልተገኘለት የኤድስ በሽታ መሰቃየቷን ሲያስቡ እጅግ ያዝኑላታል። «እግዚአብሔር ይምራታል!» ይሉም ነበር፣ ሙሉ እምነት በሚደመጥበት ድምፅ። 'ገና ልጅ ናት። በለጋ ዕድሜዋ እንዲህ መሠቃየቷ ያሳዝናል። ወንድሟም ሕፃን ነው።' ብለው እሷንና ሚካኤልን ለማሰብ ጊዜ ባገኙ ቁጥር ይተክዛሉ።

የወ/ሮ ማርታ ባለቤት አቶ ደመቀም ሁልጊዜ ፊታቸውን በፈገግታ አድምቀው ነው ልጆቹን የሚቀርቧቸው። ድምፃቸውም፣ ፈገግታቸውም አይቀየርም። ዘወትር አንድ ዓይነት ነው። ፊታቸውን ያለበሰው ጺም እንዲሁም ፀጉራቸው ከጥቁር ይልቅ ነጭ ፀጉር ይበዛበታል። ሽበታቸው ከጠይም ፊታቸው ጋር እየተጣቀሰ ግርማ ሞገስ አጎናፅፋዋቸዋል። መነፅር ያደርጋሉ። አዘውትረው የሚለብሱት ሙሉ ልብስ ከከረቫት ጋር ነው።

አመለዘውድን ሲያዩዋት ጣፋጭ የአዛውንት ፈገግታ ፊታቸውን ይሞላዋል። ንግግራቸው ቁጥብ ያለ፣ ቃላቶቻቸው የተመረጡ ናቸው። አመለዘውድ ሁልጊዜ አንድ አይነት ፈገግታ፣ አንድ ዓይነት ፀባይ ስለምታይባቸው ትወዳቸዋለች።

ተሾመ ወ/ሮ ማርታ እንዳይጠጣ ስለመከሩትና ከጠጪዎች እንደአንዱ ስለቆጠሩት ተናደባቸዋል። ይህ ግን ተራ ሰበብና ምክንያት ነው። ከሁሉም በላይ እህቱና ወንድሙ ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ መሆናቸውን በመስማቱ ስለተሸበረ፣ የሚረብሸውን አስቀያሚ እውነታ ለመሸሽ ሲል ነው ወ/ሮ ማርታ ቤት ድርሽ ላለማለት የወሰነው።

ትዝታ ያሰቃየዋል። ስለቤተሰቦቹ ማሰብ ያመዋል። በተቻለ አቅም በዛሬው ሕይወቱ መጠመድና ትናንትን መርሳት ይፈልጋል። አመለዘውድንና ወንድሞቹን ቢወዳቸውም ሊረሳቸው ይፈልጋል። በተለይ አመለዘውድን ሊረሳት ባይችልም፣ ቢያንስ በየጊዜው ሊያስባት አይፈልግም።

ወ/ሮ ማርታ የአቶ ግርማን ቤት የዚያን ዓመትና የሁለት ዓመት ውዝፍ የመሬት ግብር ከፈሉ።



Sample output to test PDF Combine only



## -41-

*«ወደ (ህጻናት ማሳደጊያው) ሄድን። አልተስማማንም። በጣም ሚያስፈሩ ሰዎች አሉ። . . . ማታ ማታ ይጨፍራሉ። ከዛ አለቀስንና እንፈልግም ብለን ወደዚህ መጣን።»*

*ሚካኤል ግርማ*

ወ/ሮ ማርታና አቶ ደመቀ ሦስቱ ሕፃናት እነሱ ቤት ከብዙ ነገሮች አኳያ ሊቆዩ እንደማይችሉ ተገንዝበዋል። ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ሕፃናት እንደሌሎች ሕፃናት አይደሉም። የተለየ ትኩረት ያስፈልጋቸዋል። ስለበሽታውና ስለቫይረሱ በቂ ግንዛቤ ባላቸው ሰዎች እንክብካቤ ሊያገኙ ይገባል።

ግቢው ውስጥ ያሉ ሠራተኞች ብዙዎቹ፣ ልጆቹ ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ጋር እንደሚኖሩ እንደሚያውቁ ወ/ሮ ማርታና አቶ ደመቀ ባያውቁም፣ አንድ ቀን መስማታቸው አይቀርም የሚል ስጋት አላቸው። ያ ደግሞ በሂደት በተለይ በአመለዘውድ ላይ ሊፈጥር የሚችለውን የመገለል ስሜትና ጭንቀት ባልና ሚስቱ አላጡትም። አመለዘውድ በተሻለ ጤንነት ላይ እንዳለች ካረጋገጡ በኋላ ከኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ጋር የሚኖሩ ሕፃናት የሚቀበል ድርጅት ማፈላለግ ጀመሩ።

አንድ የሕፃናት ማሳደጊያ (*የድርጅቱን ስም መጥቀስ አስፈላጊ ባለመሆኑ ተትቷል።*) እንደዚህ ዓይነት ልጆችን እንደሚቀበል ሰሙ። ከድርጅቱ ኃላፊዎችም ጋር ተነጋግረው ማለቅ ያለበትን ጉዳይ ጨረሱ።

ሁሉ ነገር ካለቀ በኋላ ወ/ሮ ማርታ አመለዘውድን ጠርተው፣ «ለእናንተ የሚሆን አንድ ጥሩ የህጻናት ማሳደጊያ አለ። እዚያ ወስደናችሁ ያቋረጣችሁትንም ትምህርት ትቀጥላላችሁ።» አሏት።

«እሺ» አለች አመለዘውድ ትምህርት ልትጀምር መሆኑ አስደስቷት።

እናም በ1996 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ እነአመለዘውድን ወ/ሮ ማርታ በመኪናቸው ወደ ህጻናት ማሳደጊያው ወሰዷቸው። ቡታጅራ አቅራቢያ እንዳለው የፕሮጀክት መርሲ ህጻናት ማሳደጊያ ሁሉ በዚህ ህጻናት ማሳደጊያም እንደእነሱ ወላጆቻቸውን በተለያየ ምክንያት ያጡ፣ አሳዳጊ የሌላቸው ልጆች ይኖራሉ።

ወደ ሕፃናት ማሳደጊያው እንደገቡ በመጀመሪያ እንደነሱ ያሉ ሕፃናት የሚኖሩበት መኝታ ክፍል ነበር እንዲተኙ የተደረገው። መዝሙር ከመማራቸው በስተቀር መደበኛ ትምህርት መማር ገና አልጀመሩም። ሚካኤልና ታደለ ሁልጊዜ ከሌሎች ሕፃናት ጋር ይጫወታሉ። ጓደኛ ለማፍራትም ጊዜ አልወሰደባቸውም። በግቢው ውስጥ ለህጻናት የሚሆኑ ብስክሌቶች ነበሩ። ብስክሌቶቹን እንደልብ እየነዱ ይደሰታሉ፣ ይዝናናሉ።

ከቁርስ በተጨማሪ ጠዋት በፌስታል ተሞልቶ የሚመጣ ብስኩት በልጆቹ ፊት ሲዞር ማንም ልጅ ትንሽ እጁ የቻለችለትን ያህል ብስኩቶች ማፈስ ይችላል። ሚካኤልና ታደለ የሕፃናት ማሳደጊያውን ወደዱት። ከሁሉም በላይ የወንድሞቿ ደስታ ለአመለዘውድ የሀሴት ምንጭ ሆነላት።

ወደ ሕፃናት ማሳደጊያው ከገቡ ከሦስት ሳምንታት በኋላ ግን አንድ ቀን ከነበሩበት የሕፃናት መኖሪያ ግቢ በአጥር ወደሚለይ የአዋቂዎች መኖሪያ ሕንፃ ተዛወሩ። አዲሱ መኝታ ክፍላቸው አንደኛ ፎቅ ላይ ነበር የሚገኘው። ከበታቻቸው፣ ምድር ባለው መኝታ ክፍል ህጻናት ልጆች ያሏቸው እናቶች ይኖራሉ። የእነሱ መኝታ ክፍል ተጋሪዎች ግን በሙሉ አዋቂ ሴቶች ነበሩ። ብዙዎቹ ጤነኞች አልነበሩም። አንዳንዶቹ ያስፈራሉ።

ከሴቶቹ አንዷ አንድ ጆሮዋ አብጦ የሥጋ ኳስ እንደ ሎቲ አንጠልጥላለች። ይህ ለልጆቹ የሚያስፈራ ትዕይንት ነበር። አለቅጥ ወፍራ ከአልጋ መውረድና መንቀሳቀስ የማትችል አንዲት ሴትም ነበረች። ሰውነቷ ላይ የተቆለለውን ጮማ አጥንቶቿ ለመሸከም አቅም አንሷቸዋል። ሽንት ቤት እንኳ መሄድ ስለማትችል የምትፀዳዳው (ይህ ቃል ግን ለሷ ተቃራኒ ነው) እዚያው አልጋ ላይ ነው። በዚህም ምክንያት የክፍሉ ጠረን ዘወትር ይበከላል።

ሌላ የአእምሮ ህመምተኛ የሆነች ሴት ደግሞ አለች። ትልልቅ ዓይኖቿ ሙጫ ናቸው። በድንገት አንድ ሰው ላይ ካረፉ፣ በቀላሉ አይነቀሉም። ፍጥጥ ብላ የምታየው ሰው መጨነቁና ምቾት ማጣቱ ግድ ነው። ትክታዋ በሕፃናቱ ልብ ውስጥ ፍርሃት ያሰርፃል። ጆርባ ቢሰጡት እንኳ ሰርስሮ የሚገባ የሚመስል አሸባሪ ነው።

አንዷ ደግሞ ሰው ሲቀርባት «ኡኡ» ብላ አገር ምድሩን በጩኸት ታደበላልቃለች። ምንም ቁጥብነት የሌለው ኃያል ጩኸቷ የሦስቱን ሕፃናት ልብ እንደ ደወል ምላስ በጎድን አጥንቶቻቸው መሀል ያላጋል። እጅግ ቀዝቃዛ ውሃ ሳያስቡት ላያቸው ላይ የተቸለሰ ያህል በድንጋጤና ፍርሃት ሰውነታቸውን ያንዘፈዝፋል።

በክፍሉ ያሉ «ጤነኛ» የሚባሉት ሴቶችም፣ በሦስቱ ሕፃናት ዓይን ጤነኝነታቸው ያጠራጥራል። ቀን ብቻ ሳይሆን በዕኩለ ሌሊትም ይለፋሉ፣ ይንጫጫሉ፣ ክፍሉ ውስጥ ይሯሯጣሉ፣ ይዘፍናሉ። መኝታ ክፍሉን ሠራተኞች ቀንም ሌሊትም የሚታትሩበት፣ ሃያ አራት ሠዓት የሚሠራ ፋብሪካ ያስመስሉታል። ለዕብደት አምስት ጉዳይ የሆነ ቀልድ ይቀልዳሉ። . . .

የፕላስቲክ ማስታጠቢያ ይዛ፣ «ትፊ! . . ትፋ!» እያለች በክፍሉ ያሉትን ሁሉ ከአልጋ አልጋ እየዞረች በማስተፋት «ቀለድኩ» ብላ የምታስብና


Sample output to test PDF Combine only



ያለአግባብ የምትደሰት አንዲት ሴት ነበረች። የመጀመሪያ ቀን ወደ ሚካኤል ማስታጠቢያ ይዛ ስትቀርብ ሚካኤል ግራ ገብቶትና በፍርሃት ተውጦ አንዴ እሷን፣ ቀጥሎ የብዙዎቹ የመኝታ ክፍል ተጋሪዎቻቸው ምራቅ የተመረገበትን ማስታጠቢያ፣ በሌላ አፍታ ደግሞ እህቱን ያይ ነበር።

«ትፋ እንጂ!» ስትል፣

«ተያቸው! እነሱ ሕፃናት ናቸው።» ተብላ አለፈቻቸው።

ሌላ ቀን ይህን አስቀያሚ ኮሜዲዋን ደገመችው። መጥታ ከፊታቸው ስትገተርና ምጽዋት በሚለምን የኔቢጤ ትዕግስት ስትጠብቃቸው ሕፃናቱ ምራቃቸውን ከማዋጣት በስተቀር ምርጫ አልነበራቸውም።

«ቱፍ! . . . ትፍ!»

ብዙ ጊዜ ለማደር ብቻ ነበር ክፍላቸው የሚገቡት። በተለይ ሚካኤል የመኝታ ክፍሉን እጅግ ጠልቶት ነበር። ጠዋት በማለዳ ውልቅ ብሎ ይወጣል፤ ማታ አምሽቶ፣ በአመለዘውድ ተለምኖ ይገባል።

«ኧረ ተው! ተው ሚካኤል! ብርድ ይመታሃል እንግባ!» ትለዋለች።

«እምቢየው አልገባም! እዚህ ውጪ ነው የማድረው።» ይላታል ትከሻውን እየሰበቀ።

«ምኑ ላይ ታድራለህ? ሲሚንቶና ድንጋይ አይደል እንዴ? ይቀዘቅዝሃል'ኮ።»

«እዚሁ ቁጭ ብዬ አድራለሁ።»

«አይሆንም ሚካኤል! ብርድ ይመታህና ያምሃል።»

«ልታመም!»

« . . . ደግሞ ብትታመም ያቺ ከአልጋ የማትወርደውን ወፍራም ሴትዮ አይተሃት አይደል? ልክ እንደ እሷ አልጋ ላይ ተኝተህ ስለምትውል ጭራሽ እንዲያውም ውጪ መውጣት አትችልም። . . . » የባሰ የሚጠላውን ነገር ነግራ ስለምታሳምነው ዝም ይላታል።

«በል ና! ተነስ! እንግባ!» እጇን በእጁ እንዲይዝ ትዘረጋለታለች።

ምርጫ የለውም ቅፍፍ እያለው ማታ ወደሚገባበት «ገሃነም» ይጎተትላታል።

«እኛ እዚህ መኖር አንፈልግም አልናቸው። ለምንድነው ወደ ሕፃናቶቹ ክፍል የማይመልሱን? ካልሆነ ለምን እነእማማን አይጠሩልንም?» አጥጋቢ መልስ ባትሰጠውም ሚካኤል ትንሽ ቆሽቱ እያረረች አመለዘውድን ይጠይቃል። እሷም የእሱን ያህል ክፍሉን እንደጠላችው ግን አሳምሮ ያውቃል።

«እስቲ ነገ ደግሞ ሲትየዋን አነጋግራታለሁ።» ትለዋለች።

ወደዚህ ክፍል ከተዛወሩ በኋላ የድርጅቱን አስተዳዳሪ አሁን ካሉበት ክፍል እንዲያስወጧቸውና ወደ በፊቱ ክፍላቸው እንዲመልሷቸው ደጋግመው ጠይቀዋል። አስተዳዳሪዋ ሌሊት ስላለው ረብሻና ጫጫታ፣ ስለክፍል ተጋሪዎቻቸው ማንነት በጥልቀት አያውቁም። እናም ለህጻናቱ አቤቱታ ተገቢ ትኩረት አልሰጡም።

«ለእናንተ የሚሆነው አሁን ያላችሁበት ክፍል ነው። እስክትለምዱት ነው።» ነበር በመጀመሪያ ያሏቸው።

«ለእናንተ የሚሆነው» የሚለው አባባላቸው አመለዘውድን ከነከናት።

«እኛ ምን ስለሆንን ነው ከሌሎች ልጆች የምንለየው?» ብላ ጠየቀች። መልሱን በከፊል ብትገምትም፣ ከሴትየዋ አንደበት መስማት ፈልጋ ነበር።

ሴትየዋ ለአፍታ ዝም ብለው አዩዋትና፣ «የተሻለ ቦታ እንፈልግላችኋለን።» አሉ።

«ለምንድነው መጀመሪያ ወደዚህ የመጣነው? ያጠፋነው ጥፋት አለ?»

«ጥፋት ስላጠፋችሁ አይደለም።»

«ታዲያ ለምንድነው?»

«የህጻናቱ ክፍል ስለሞላ ነው። በጣም ተጨናንቀዋል። እናንተን ምርጫ ስላልነበር ነው እዚያ ያቆየናችሁ።»

«እኛ ግን አልተጨናነቅንም ነበር እኮ»

«ሳይጨናነቅማ ወደዚህ አናመጣችሁም። ተጨናንቋል።»

አመለዘውድ አስተዳዳሪዋ የሚሉት ባያሳምናትም ዝም አለች።

በህጻናት ማሳደጊያው ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ ሕፃናት የሚያድሩባቸው ክፍሎች ቢኖሩም፣ ጢም ብለው ሞልተዋል፤ ለሦስቱ ሕፃናት ቦታ አልነበረም። ወደዚህ ወደአዋቂዎቹ መኖሪያ ከመምጣታቸው በፊት የሕፃናት ማሳደጊያው ቀደም ብሎ እነአመለዘውድን ያስገባቸው ከቫይረሱ ነፃ የሆኑ ሕፃናት የሚተኙበት መኝታ ክፍል ውስጥ ነበር። በኋላ ግን ሕፃናቱ ከሌሎቹ ሕፃናት ጋር ጓደኝነት ሲመሰርቱና አብረው ሲጫወቱ ሞግዚቶች ስጋት አደረባቸው።

ኤች.አይ.ቪ. አብሮ በመጫወት ባይተላለፍም፣ ስለበሽታው በቂ ግንዛቤ ስላልነበራቸው ሞግዚቶቹ፣ «አብረዋቸው የሚኖሩት ልጆች ሕፃናት ስለሆኑ ራሳቸውን ከኤች.አይ.ቪ. መጠበቅ አይችሉም። ባለማወቅ ቫይረሱን ሊያጋቡባቸው ስለሚችሉ ጓደኛ ሊያደርጓቸውና አብረዋቸው ሊጫወቱ ከማይችሉ አዋቂዎች ጋር ብናደርጋቸው ይሻላል።» በማለት ነበር አዋቂ ሴቶች ወደ ሚኖሩበት መኝታ ክፍል እንዲዛወሩ የተደረገው።

ልጆቹ ማታ ወደ መኝታ ክፍሉ ሲገቡ ቀጥታ ወደ አልጋቸው ያመራሉ።





«እሺ፣ እንዴት ነው ጎረምሳው? ለመሆኑ የት ነው የምትውለው? እኔ'ኮ ቀኑን ሙሉ እዚህ ክፍል ውስጥ አላየውም።» ትለዋች አንዷ ሚካኤልን፣ አልጋዋ ላይ ሆና ፀጉሯን በወፍራሙ ሽሩባ እየሰራች።

«ቤቱ እያለ ዙረት ለምዶ ይሆናል። ትንሽ ዱርዬ ሳይሆን አይቀርም።» ሌላዋ ጤነኛ መሳይ ሳቅ እያለች ትመልሳለች።

ያስጠሉታል። ጫማውን ቶሎ አውልቆ ብርድ ልብሱ ውስጥ በፍጥነት ገብቶ ይከናነባል። ትኩረታቸው ለአንዲት ደቂቃ እንኳ እሱ ላይ እንዲሆን አይፈልግም።

ታደለ በዕድሜ ለጋ መሆኑ ጠቅሞታል። ቶሎ እንቅልፍ ይወስደዋል። አመለዘውድና ሚካኤል ግን ሴቶቹ ከአልጋ፣ አልጋ ብቻ ሳይሆን ከክፍል፣ ክፍል በሚሻገር ድምፅ ጮክ ብለው ስለሚያወሩ ለማንቀላፋት ይቸገራሉ። ጤነኛ የሚመስሉት ሴቶች ክፍሉን በሶምሶማ እያቆራረጡ እንደ ሕፃናት ይላፋሉ። ጫጫታና ረብሻው ረገብ ብሎ፣ እነአመለዘውድ ድካም አሸንፏቸው ሸለብ ቢያደርጋቸው እንኳ በሌላ ከፍ ያለ የሚረብሽ ድምፅ ይነቃሉ። ወይ ያቺ ሰው ሲጠጋት ተሸብራ የምትጮህ የአእምሮ ህመምተኛ ጮኻለች፣ ካልሆነም ከጤነኛ መሳዮቹ ሴቶች አንዷ የቆየ ትዝታ የቀሰቀሰባትን ዘፈን በዕንባ ቀረሽ ተመስጦ ጮክ ብላ እያንጎራጎረች፣ ምናልባትም በጭብጨባና በዳንስ እየታጀበች ሊሆን ይችላል። እንዲህ ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ የመኝታ ክፍሉን የሚብለጨለጭ ብርሃን የሌለው የምሽት ጭፈራ ቤት ያስመስሉታል።

«አይተኙም እንዴ?!» ይላል ሚካኤል በብርድ ልብሱ ተከናንቦ ብስጭትጭት እያለ።

አመለዘውድ ብርድ ልብሷን እየገለጠች አንዴ ወደ ሴቶቹ፣ ሌላ ጊዜ ወደ ወንድሞቿ አልጋ እያየች ራሷን እስኪያማት ግራ ትጋባለች። የድርጅቱ አስተዳዳሪ ለአቤቱታቸው ፈጣን መልስ ባለመስጠታቸው ትናደድባቸዋለች። 'እናትና አባት ቢኖረን ኖሮ እንዲህ አንሰቃይም ነበር።' ብላ ሆድ ይብሳታል። ወላጆቿን ያጣች የሙት ልጅ መሆኗ አጥንቷ ድረስ ዘልቆ ይሰማትና ሐዘኗ ወሰን የለሽ ይሆናል። ዕንባዋን በብርድ ልብሱ ተከናንባ በብዛት ታፈስሳለች። ወንድሞቿ በጣም እንደፈሩ ካስተዋለች ወደ አልጋቸው ሄዳ ልታረጋጋቸው ትሞክራለች።

«አይዞህ ታዴ! . . . ሚካኤል! አይዟችሁ!» ትላለች።

አስተዳዳሪዋ ከዚህ ህይወት አንድ ቀን እንደሚላቀቁ ተጨባጭ ተስፋ ሊሰጧት ባለመቻላቸው ትበሳጫለች።



Sample output to test PDF Combine only

በሚቀጥለው ቀንም አቤቱታዋን ልታሰማ አስተዳዳሪዋ'ጋ ወንድሞቿን ይዛ ትሄዳለች:: ምንም የሚለወጥ ነገር ግን አልነበረም::

አንድ ቀን ወደ ህጻናቶቹ ክፍል እንዲመልሷቸው መጠየቁ ተስፋ አስቆራጭ መሆኑን አሰበች:: ሚካኤልን ይዛ ወደ አስተዳዳሪዋ ቢሮ ገባች::

«ወደ ቤተሰባችን ይደወልልን:: እዚህ መኖር አንፈልግም::» አለች የዕንባ ሳግ እየተናነቃት::

«ለምን?» አስተዳደሪዋ ግራ ተጋብተው ጠየቁ::

«ደጋግመን ነገርንዎት'ኮ:: የሚያስፈሩ ሴቶች አሉ:: ይጮኻሉ፣ ይሳፋሉ፣ ይጨፍራሉ:: መተኛት አልቻልንም::» አለች አለመዘውድ::

«አንፈልግም! እዚህ መኖር አንፈልግም!! ቤተሰባችን ይጠሩልን!» አለና ሚካኤል ጮክ ብሎ ማልቀስ ጀመረ::

አስተዳዳሪዋ ሕፃናቶቹን ተራ በተራ በዝምታ ሲያዩዋቸው ቆዩ:: እያሰቡ ነበር:: 'እነዚህን ልጆች ህጻናት ክፍል ሊገቡ አይችሉም:: አሁን ያሉበትን ክፍል ደግሞ እጅግ ጠልተውታል:: ለቤተሰቦቻቸው ተደውሎ እነሱ አንድ መፍትሄ ቢፈልጉ ይሻላል::'

«በቃ እሺ ለቤተሰባችሁ እደውላለሁ::» ብለው ሸኟቸው::

የእነወ/ሮ ማርታን የስልክ ቁጥር ከልጆቹ ፋይል ውስጥ አግኝተው ደወሉ:: ልጆቹ ህጻናት ማሳደጊያውን እንዳልወደዱትና እሳቸውን ሊያገኙዋቸው እንደሚፈልጉ ሲነግሯቸው ወ/ሮ ማርታ ደነገጡ:: ልጆቹ ወደ ቤት ተመልሰው መጥተው ከእነርሱ ጋር ሊኖሩ አይችሉም፤ የሕፃናት ማሳደጊያውን ኑሯቸውን ደግሞ ጠልተውታል::

«ምን ይሻላል? አሁን ሌላ ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ሕፃናትን የሚያሳድግ ድርጅት እንዴት ማግኘት እንችላለን?» ብለው ወ/ሮ ማርታ ከባለቤታቸው ጋር ተጨነቁ::

ባልና ሚስቱ ሌላ ለሶስቱ ልጆች የሚሆን የህጻናት ማሳደጊያ በትጋት መፈለግ ጀመሩ::

አመለዘውድ ብቻዋንም፣ ከወንድሞቿ ጋርም አስተዳዳሪዋን ከመጨቅጨቅ አልቦዘነችም:: «ሌላ ክፍል ቀይሩን» የሚለውን ሀሣብ ትተውታል:: «እዚህ መኖር አልፈልግም! ቤተሰባችን ይጠሩልን!!» ማለቱን ገፍተውበታል፣ ከለቅሶ ጋር::

«ደውዬላቸዋሁ:: እንመጣለን ብለዋል ይመጣሉ:: ስላልተመቻቸው ይሆናል::» ብለው አስተዳዳሪዋ ሊያረጋጓቸው ይሞክራሉ::





እዚህ አዋቂዎቹ ጋር ከመጡ ነፍስና ሥጋን በሚያሸብር ፍርሃትና ሰቆቃ መሠቃየታቸው ሳያንስ፣ ሕፃናቶቹ ክፍል እያሉ ከቁርስ በኋላ የሚበሉትን የሚወዱትን ብስኩት ማግኘት እንኳን አልቻሉም::

በሕንፃው ምድር ባለው መኝታ ክፍል ለሚኖሩት፣ ሕፃናት ልጆች ላሏቸው ሴቶች ፣ ለሕፃናት ልጆቻቸው ሲባል ብስኩት ይሰጣቸዋል:: እንደ አዋቂ ክፍል በሚታየው አንደኛ ፎቅ ላይ በሚገኘው የእነአመለዘውድ መኝታ ክፍል ምናልባት ከታችኞቹ የተረፈ ብስኩት አልፎ አልፎ ቢመጣ ነው:: ቢመጣስ እነአመለዘውድን ማን አስጠግቷቸው?! «አዋቂ» ተብዬዎቹ ብስኩት ለማግኘት ይራኮታሉ::

ሚካኤልና ታደለ የአዋቂና የሕፃናት መኖሪያውን ከሚለየው አጥር ማዶ በነበሩበት ጊዜ ብስክሌት ባሰኛቸው ጊዜ ይነዱ ነበር:: እዚህ በአዋቂዎቹ ግቢ ብስክሌት የለም:: ከላይኛው የሕፃናት ግቢ ብስክሌት እየነዱ ወደዚህ ግቢ የሚገቡ ሕፃናት ግን ነበሩ:: ሕፃናቱ የሚነዱትን ብስክሌት ሊለቁላቸው እንኳን ቢፈቅዱ በዚህ ግቢ ነዋሪ ስለሆነ ሚካኤል መንዳት እንደማይፈቀድለት ተነገረው:: ይማሩት የነበረው የሙዚቃ ትምህርትም እዚህ ግቢ ከገቡ በኋላ ቀርቷል:: ለልጆቹ ይህ በበደል ላይ በደል ነበር::

አመለዘውድ አስተዳዳሪዋ ችግራቸውን እየሰሙ ዝም ማለታቸው እጅግ ስላበሳጫት ጠፍታ ወደ ኮተቤ ስለመሄድ አሰበች:: በር ላይ 24 ሰዓት የሚጠብቁ ዘበኞች አሉ:: አጥጋቢ ምክንያት ከሌለ፣ በተለይ ልጆች ከግቢ መውጣት አይፈቀድላቸውም::

አንድ ቀን በሩ'ጋ አንድ የጭነት መኪና ቆሟል:: አመለዘውድ በጭነት መኪናው ተከልላ ወደ በሩ አድፍጣ ተጠጋችና በኋላ ጎማው ተከልላ ቆመች:: ዘበኛው ወደ ቤቱ ገባ ሲል ድምፏን ሳታሰማ ሹልክ ብላ ከግቢ ለመውጣት ነበር የተዘጋጀችው:: የዘበኛ ቤቱ በር ላይ ቁጭ ብሎ የነበረው ዘበኛ ድንገት ተነስቶ ወደ ቤቱ ገባ:: ሮጣ በሩን ከፍታ ለመውጣት ስትዘጋጅ የቆየች ቢሆንም እግሮቿ ተሳሰሩባት:: ወንድሞቿን ለአንድ ቀን ምናልባትም ለጥቂት ሰዓታት ብቻቸውን ጥላ መሄዱ ከበዳት:: በቆመችበት 'ልሂድ? ልቅር?' እያለች ስታመነታ የጥበቃ ሠራተኛው ተመልሶ ወጥቶ የቀኑን ብዙ ሰዓታት ተቀምጦ ከሚያሳልፍበት ወንበር ላይ ተጎለተ::

ዘበኛው ከተቀመጠበት ሳይነሳ የጭነት መኪናው ጭሱን አቡለቅልቆ ተንቀሳቀሰ:: የአመለዘውድ ጠፍቶ ወደ ኮተቤ የመሄድ ዕቅድ እንደ መኪናው ጭስ ተበትኖ ቀረ:: ከግቢው እንደምንም ብትወጣ ሰዎች ጠይቃ ኮተቤ የሚወስዳት የከተማ አውቶቡስ ላይ ለመሳፈር ተስፋ አድርጋ ነበር::



Sample output to test PDF Combine only

# ክፍል ሶስት

«ማሸነፍ የኔም ነው፤ መሸነፍ ግን አይደለም።»
አሙሰዘውድ

Sample output to test PDF Combine only

## -42-

*«በመጀመሪያ (እዚህ ስመጣ) ደስ ብሎኝ ነበር። ከዛ እንደገባሁ እህቴ የሆነ ነገር ነገሬችኝና ከፍቶኝ ነበር። ከዛ እየለመድኩት ስመጣ ደስ አለኝ።»*
*ሚካኤል ግርማ*

ለእነአመለዘውድ የሚሆን የተሻለ የህጻናት ማሳደጊያ ለማግኘት ሲያጠያይቁና ሲያፈላልጉ የሰነበቱት ወ/ሮ ማርታና አቶ ደመቀ «እናት በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት ማዕከል» ስለሚባል ድርጅት ሰሙ። እናት በተለይ ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ልጆችን የሚያሳድግ ድርጅት ነው። እነወ/ሮ ማርታ ከድርጅቱ ኃላፊዎች ጋር ተነጋገሩ። ኃላፊዎቹ ልጆቹን ለመቀበል ፈቃደኛ ሆኑ።

ጥሩ ነው ብለው አስበውት የነበረው አሁን ያሉበት ድርጅት ለልጆቹ ስላልተስማማቸው ያፈሩትና የተጨነቁት ወ/ሮ ማርታ ልጆቹን ራሳቸው ወደ እናት ሊወስዷቸው አልፈለጉም። የልጆቹን ዓይን ለማየት ፈሩ። ከባለቤታቸው ጋር ተመካከረው፣ እነርሱ ቤት አንድ ክፍል ሰጥተዋቸው የሚኖሩትን አሜሪካዊ ጓደኞቻቸውን ፔግና ቴሪን ለማስቸገር ወሰኑ። ባልና ሚስቱ ፔግና ቴሪ ኢትዮጵያዊ ጓደኞቻቸውን ለመርዳት ፈቃደኛ ሆኑ። አሜሪካውያኑ ህዳር 22፣ 1996 ዓ.ም. እነአመለዘውድን ወደ እናት የህጻናት ማሳደጊያ ወሰዱዋቸው።

በአዲሱ መኖሪያ ቦታቸው አንዳንድ በቆዳ በሽታዎች የተጠቁ ወይም ሰውነታቸው የከሳ ልጆች ቢኖሩም፣ በውድቅት ጮክ ብለው የሚዘፍኑ፣ አጉል ቀልድ የሚቀልዱ፣ መልካቸውና ሁኔታቸው የሚያስፈራ አዋቂዎች የሉም። ይህ ግቢ የልጆች ብቻ ነው። የልጆቹ ቁጥርም ጥቂት ነው፤ ሃያ አምስት ወይም ሰላሳ ቢሆኑ ነው።

ድርጅቱ ሁለት ግቢዎች አሉት። በአንደኛው ግቢ ዕድሜያቸው ከሰባት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት ይኖራሉ። የድርጅቱ አስተዳደር ሠራተኞች ቢሮም በዚሁ ግቢ ውስጥ ይገኛል። ሁለተኛው እነአመለዘውድ የሚኖሩበት ግቢ ከሰባት ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው ህጻናት የሚኖሩበት ነው። ታደሰ ሰባት ዓመት አልሞላውም፤ ግን ማነው እሱን ከአመለዘውድ ዓይን ለማራቅ የሚደፍር?!

አመለዘውድ ስትጠራጠር የነበረውን መራር እውነት በፊት የነበሩበትን የህጻናት ማሳደጊያ ከመልቀቃቸው በፊት በማያሻማ ሁኔታ ሰማች። አስተዳዳሪዋ ቢሮ አስጠርተዋት ወደ ሌላ ህጻናት ማሳደጊያ እነወ/ሮ ማርታ ሊወስዷቸው ስለሚመጡ እንዲዘጋጁ ነገሯት።



Sample output to test PDF Combine only

«እውነት?! . . . ውይ ታድለን!» አለች አመለዘውድ በጣም ተደስታ::
«ለእናንተ በተለይ ላንቺና ለወንድምሽ፣ ለዚያ ክፍ ለሚለው፣ የሚሆን ነው::»
«እንዴት?» አለች ፊቷ ላይ የደመቀው ፈገግታ እየፈዘዘ::
«አንቺና ሚካኤል ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ እንደሆናችሁ ታውቂያለሽ አይደል?» አሏት::

ደሟ በደም ስሮቿ ውስጥ መንሸራሸሩን ያቆመ ያህል ሰውነቷ ሲደነዝዝ ተሰማት:: ከው ብላ ነበር የደነገጠችው:: እነወ/ሮ ማርታ ቤት እያለች፣ «የማይድን በሽታ» የተባለው ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት እንኳ ትፈራ ነበር::

ዝምታዋን እንደ እሾ የቆጠሩት አስተዳዳሪዋ ቀጠሉ፣ «አሁን የተገኛችሁ ድርጅት እንደእናንተ ዓይነት ልጆች የሚኖሩበት ቦታ ነው::»
«ታደለስ?»
«ምን?»
«ትንሹ ወንድሜስ?»
«ትንሹ ወንድምሽ ከፈለግሽ እኛም'ጋ ባይሆን ሌላ ድርጅት መኖር ይችላል አንቺ ከፈቀድሽ::»
«ማለቴ እሱን አልያዘውም?»
«ምኑ? . . .» ሴትየዋ ግራ ተጋቡ:: «እስካሁን አታውቂም እንዴ?! እኔ'ኮ የሰማሽ መስሎኛል:: እሱማ ጤነኛ ነው::»
የሆነ ከባድ ሸክም በከፊል ሲቀልላት ተሰማት:: ከዚህ በላይ ብዙ ዝርዝር መስማት አላስፈለጋትም:: . . .

ወደ እናት ከመጡ ከአንድ ቀን በኋላ አመለዘውድ ሚካኤልን፣«እንዴት ነው? ይህን ቤት ወደድከው አይደል?» ብላ ጠየቀችው::
«አዎ፣ ጥሩ ቤት ነው::» አላት::
«ስለ እኔና ስላንተ አንድ ነገር ሰማሁ::»
«ምን?»
«እኔና አንተ ኤድስ ይዞናል::»
«ምን?!»
«እኔና አንተ ኤድስ ይዞናል::»
«ማነው እንደዚህ ያለው?»
«ሰማሁ::»
«ኤድስ ከያዘን ታዲያ ለምን አንሞትም?» ሚካኤል እህቱ የነገረችውን ማመን አልፈለገም::
«ኤድስ ቀስ እያለ ነው የሚገድለው::»
«ኤድስ እንዴት ነው የሚያደርገው?»



Sample output to test PDF Combine only



«በቃ ያማል፣ ያከሳል:: መድሃኒት የለውም::»
«እና እኛ ኤድስ ይዞናል!»
«አዎ»
«ታደለስ?»
«ታደለን አልያዘውም::»
«አንቺ ግን ማን ነገረሽ?»
«ሰማሁ::»

ሚካኤል ዝም አለ:: ኤድስ መጥፎ፣ የማይድን በሽታ መሆኑን ሰምቷል:: ኤድስ ሊይዘው እንደሚችል ግን አንድም ጊዜ አስቦ አያውቅም::

«እንዴት ግን ሊይዘን ቻለ?»
«እኔ እንጃ» አለችው ትከሻዋን እየሰበቀች:: አመለዘውድም ይህን ጥያቄ ራሷን ደጋግማ ጠይቃ መልስ አላገኘችም::
ሚካኤል ግራ ገባው:: ዝም ብሎ ቆይቶ፣ «በቃ ቶሎ እንሞታለን ማለት ነው?»
«ምናልባት:: . . . ግን አይዞህ እኔ እፀልያለሁ:: እግዚአብሔር ሊያድነን ይችላል::»

አመለዘውድ ወንድሟ እጅግ መከፋቱን ስታይ አዘነችለት::

«ታደለ እንዴት አልያዘውም?»
«እግዚአብሔር ይመስገን! እሱን እግዚአብሔር ጠብቆታል:: እኔ እንዲያውም ሁላችንንም ይዞናል ብዬ ፈርቼ ነበር:: ታደለ ነፃ ስለሆነ በጣም ደስ ብሎኛል::»

ለአፍታ በመካከላቸው ፀጥታ ሰፈነ::

«. . . እዚህ ያሉት ልጆች ብዙዎቹ እንደእኔና እንዳንተ ናቸው::»
ቀና ብሎ በመገረም አያት:: «ብዙዎቹ?!»
«አዎ፣ እንደዛ ሲባል ሰማሁ::»

ሚካኤል ምንም ቃል ሳይተነፍስ አቀርቅሮ ዝም አለ::

ከበርካታ ሰኮንዶች ፀጥታ በኋላ፣ «እኔና አንቺን ግን እንዴት ያዘን?» ብሎ ደግሞ ጠየቃት::

ከባድ ሐዘን ተጭኗት ስለቆየ በረጅሙ ተነፈሰችና፣ «እኔ እንጃ! እኔም ሊገባኝ ያልቻለው እሱ ብቻ ነው::» አለችው::

ሚካኤል አሳዘናት::

«አይዞህ ሚካኤል! ጌታ ኢየሱስ ያድነናል! አንተ ብቻ መጥፎ ልጅ አትሁን!» አለችው::

ሚካኤል ከፋው። በጣም አዘነ። ሐዘኑና መከፋቱ ግን ለረጅም ጊዜ አልቀጠለም።

የእናት ህጻናት ማሳደጊያ ኑሮዋቸውን ሁለቱም ወደዱት። ሚካኤል ራሱን ለማጽናናት የተወሰኑ ቀናት አስፈለጉት። እውነታውን ተቀበለው። በእናት የሚኖሩት ሌሎቹም ልጆች ከቫይረሱ ጋር እንደሚኖሩ ያውቃሉ። ግን ከቫይረሱ ጋር ስለመኖራቸውና ከኤድስ ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች አያወሩም። ከጠዋት እስከ ማታ እንደማንኛውም ልጅ ይጫወታሉ። ሚካኤልም ከእነሱ ጋር ይጫወታል። አንዳንዶቹ ልጆች ይታመማሉ፣ ሲታከሙና መድኃኒት በሞግዚቶቻቸው ክትትል ሲወስዱ ያያል።

አመለዘውድ ጨዋታ ብዙም አይስባትም። አንድ ቦታ ቁጭ ብላ ወይም አልጋዋ ላይ ጋደም ብላ መጽሐፍ ቅዱስና ሌላም እጇ የገባ መጽሐፍ ታነባለች። በተለይ ካገኘች ቡታጅራ እንደለመደችው የታሪክና የተረት መጽሐፍት ማንበብ ትመርጣለች። በማታነብበት ጊዜ ከሞግዚቶቹ ጋር ታወራለች። ወይም ወደ ማዕድ ቤት ሄዳ ምግብ አብሳዮቹን በሥራ ታግዛለች። የሚለቀም እህል ካለ ትለቅማለች፣ እንጀራ እየጋገሩ ከሆነም አንድ፣ ሁለት እንጀራ ታስፋለች . . .።

ለምትወዳቸው ምግብ አብሳዮችና ለሞግዚቶቿ ስለእናቷና አባቷ፣ ስለተሾመ፣ ስለትንንሾቹ ወንድሞቿ፣ ስለራሷም ቁጭ ብላ መተረክ ያስደስታታል። አብዝታ የምትወዳቸውን ስለራሷ ብዙ ስታወራላቸው የበለጠ እንደወደደቻቸው፣ የበለጠም እንደቀረበቻቸው ይሰማታል። ያ ስሜት የሚሰጣት ልዩ ዓይነት እርካታ ነበር።

ታደለ ኤች.አይ.ቪ. ኔጌቲቭ እንደመሆኑ በጉዲፈቻ ሊያሳድጉት ከሚችሉት ወላጆች ጋር መገናኘት ይችል ነበር። ግን አመለዘውድ ወንድሟ ከአጠገቧ እንዲርቅ በጭራሽ አትፈቅድም። እጅግ ትሳሳለታለች። ከራሷ አብልጣ ትወደዋለች።



Sample output to test PDF Combine only



# -43-

*. ማሚ ለምን ነው የማትመጪው?»*
*አመለዘውድ*

አመለዘውድ ቤቱን በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሱትን ባልና ሚስት ለመቅረብና «ፓፓ»ና «ማሚ» ብላ ለመጥራት ብዙ ጊዜ አልወሰደባትም። ጆሮዋ በደንብ ስለማይሰማ ከሰዎች ጋር እንደልቧ ለማውራትና የሆዷን ልታዋያቸው አትችልም። በዚህ የህጻናት ማሳደጊያ ደግሞ አስተዳዳሪዎቹ ሌላ ግቢ ስለሆኑ፣ እነሱን ዘወትር ማግኘት አትችልም። በሂደት በደብዳቤ ከፓፓና ማሚ ጋር በቀላሉ መገናኘት፣ ራሷንም በቀላሉና በጥሩ ሁኔታ መግለጽ እንደምትችል ተረዳች። ስትበሳጭ፣ ስታዝን፣ ስትደሰት፣ ስትጸጸት ውስጧ የታመቀውን ስሜት ደብዳቤ ላይ ስታሰፍረው ደስ ይላታል፣ እፎይታን ታገኛለች። እናም ለፓፓና ማሚ በየጊዜው ደብዳቤ ትጽፍላቸዋለች።

ወ/ሮ ማርታ ሊጠይቋቸው ስላልመጡ የሆነ የመጣል፣ ያለመፈለግ ስሜት ይሰማታል። እሷና ሚካኤል ከኤች.አይ.ቪ. ጋር እንደሚኖሩ በደሩ ማወቋ ደግሞ ይህን አስቀያሚ ስሜት እሹሩሩ እንድትለው አስገድዷታል። መውደድና መወደድ በጣም ትፈልጋለች። ሁለቱን ባልና ሚስት የድርጅቱን አስተዳዳሪዎች እንደ እናትና አባቷ ለማየት፣ ለማቅረብና ለማፍቀር ከፍተኛ ጉጉትና ምኞት ነበራት። ወላጆቿን፣ ታላቅ ወንድሟንና ወ/ሮ ማርታን ማጣቷ በህይወቷ የፈጠረውን ክፍተትና ባዶነት እንዲሞሉላት ትጓጓለች። ለማሚና ፓፓ በደብዳቤዎቿ ፍቅሯን ያለ ገደብ ትገልጽ ጀመር።

*24/7/96*

*በጣም የምወድሽ እናቴ፣ ለጤናሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ ጌታ ይመስገን በጣም ደህና ነኝ። ማሚዬ ባለፈው የጻፍኩልሽ ደብዳቤ እንደደረሰሽ ሠማሁ። እኔ የፃፍኩልሽ እናትዬ፣ እንድትፅናኚ* ብዬ ነው። ማሚ ትመጫለሽ እያለ ፓፓ ያጽናናል። በቀደም ትመጣለች ብዬ ደጅ ደጁን ሳይ ጨለመ። እና ማሚ ለምን ነው የማትመጪው? እባክሽ ለአንድ ቀን ነይና ቶሎ ትመለሻለሽ። አይንሽን ለማየት ጊዜው እርቆብኛል። ቶሎ ነይ! በማለት ልማፀንሽ ነው። በጣም ናፍቀሽኛል። ሚካኤልና ታደለ ደብዳቤ መጻፍ ስለማይችሉ ነው። «ናፈቀችኝ ማሚ» እያሉ ፓፓን ሁሌ ይጠይቁታል። እንዲሁም ቤቢ ተማሪዎች መፃፍ ስለማይችሉ ነው፤ ሁሉም ሠላም ብለውሻል። ጌታ ይባርክሽ* በተረፈ ልጆችሽን በሙሉ ሠላም በይልኝ። ያንቺው አመለዘውድ ነኝ።*

**አመለዘውድ እንድትፅናኚ የሚለውን ቃል በዚህ ደብዳቤ ውስጥ ለምን እንደተጠቀመች ማወቅ አልተቻለም፡ በወቅቱ እነማሚ ሃዘን ደርሶባቸው ይሆን?*

## -44-

*«ትንሽ ቆይተን ልናየቸው ሄድን:: በጣም አለቀሰች አመለዘውድ፣ በጣም!»*
*ወ/ሮ ማርታ ገብረጻድቅ*

ጥቂት ወራት፣ ብዙ ተራ ቀናት አለፉ:: ከዕለታት አንድ ቀን ግን እንደ ሌሎች ቀናት ተራ ሆኖ አላለፈም:: የቤተሰብ ቀን ነበር:: በዚህ ቀን በህጻናት ማሳደጊያው የሚኖሩ ህጻናት ቤተ ዘመድ ካላቸው ስልክ ተደውሎ ይጠራሉ:: እነአመለዘውድን ለመጠየቅ እነወ/ሮ ማርታ መጡ:: አመለዘውድ ወ/ሮ ማርታን ስታያቸው፣ ዓይኖቿን ማመን አልቻለችም:: ተንደርድራ አንገታቸው ላይ ተጠመጠመች:: አንገታቸውን እንቅ አድርጋ እንደያዘች ለብዙ ደቂቃዎች ተንሰቅስቃ አለቀሰች::

'ሁለተኛ አላያቸው ይሆን?' የሚል ስጋት ስታመነዥግ ነበር ያለፉትን ጥቂት ወራት የኖረችው:: እንደተዉዋቸው፣ ዳግመኛ እነሱን ፍለጋ እንደማይመጡ አዘውትራ በኃዘን ተውጣ ስታስብ ነበር የከረመችው:: ለወ/ሮ ማርታ ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት አላት:: እናቷ በሕይወት በነበረች ጊዜ፣ እሷ፣ እናቷ በድህነትና በሕመም በሚያንገላቱበት የስቃይ ዘመን እነርሱን ለመርዳት ቤት ድረስ አቶ ተከለን የላኩት እኮ ወ/ሮ ማርታ ነበሩ:: እናቷ ከሰው ዕኩል በሳጥን እንድትቀበር ያደረጉትም እሳቸው ናቸው:: እናቷ ከሞተች በኋላ ሁለት እጆቻቸውን ዘርግተው በፍቅር የተቀበሏቸውስ ወ/ሮ ማርታ አይደሉ? በሕይወቷ ከፍተኛ ትርጉም ከምትሰጠው መንፈሳዊ ሕይወት ጋር ያቆራኟት፣ በሕይወቷ የላቀ የምትለውን ስጦታ፣ የምትወደውን መጽሐፍ ቅዱስ የሰጧትስ እኚህ ትልቅ ሴት አይደሉ?

ወ/ሮ ማርታ እንባቸውን መገደብ አልቻሉም:: 'ይህቺ ያለዕድሜዋ የበሰለች ሕፃን የሚደንቅ ሥነ-ምግባር ያላት፣ ሰው አፍቃሪ ልጅ ለምን ፈተናዋ በዛ? ለምን በኤች.አይ.ቪ. እንድትያዝ እግዚአብሔር ፈቀደ?' ሲሉ ነበር ያዘኑላትና ያለቀሱት::

አመለዘውድ ግን እጅግ ስለተደሰተች፣ ኃይለኛ የሀሴት ስሜት ነበር ዕንባዋን ያገነፈለው፣ ያንሰቀሰቃት:: ወ/ሮ ማርታ እጅግ ናፍቀዋት ነበር:: ለወራት ከሕይወቷ ያጣቻቸውን፣ እጅግ በጣም የምትወዳቸውን ሴት በመጨረሻ መልሳ ማግኘቷ ነው ያስደሰታት፤ ያስፈነደቃትም:: በእርግጥ በዚህች ዓለም ያለ እሳቸው ማን አላት? ተሸመ እንደሆነ አንድም ቀን ጠይቋቸው አያውቅ::

'በዚህች ዓለም ላይ ጠያቂ ዘመድ የለኝም፣ የሚፈልገኝ ሰው የለም::' ብሎ እንደማሰብ የአንድን በእንለማውታን ውስጥ የሚኖር ልጅን አእምሮ



Sample output to test PDF Combine only



የሚያደማ ነገር ምን አለ? በተለይ የሌሎች ልጆች ቤተዘመዶች ሲመጡና የእነርሱ ሲቀሩ፣ ልብ የሚያቆስል ያለመፈለግ፣ የመጣልና የመረሳት ስሜት ይፈጥራል:: በወ/ሮ ማርታ መምጣት አመለዘውድ እነዚህ አቁሳይ ስሜቶች ተወገዱላት::

የቤቱን ሰው በሙሉ እየጠራች ደህንነታቸውን ጠየቀች::

«ዳንቴ ደህና ነው?» አለች ፊቷ ላይ ለዳንቴ ያላት ጥልቅ ፍቅር ከፈገግታ ጋር እየተንፀባረቀ::

«ደህና ነው::» አሉ ወ/ሮ ማርታ ፈገግ ብለው ውሻቸውንም መናፈቋ እያስገረማቸው::

«አባክዎ እማማ በሚቀጥለው ሲመጡ ይዘውት ይምጡ!»

«እሺ፣ አመጣዋለሁ»

ሁሉም የተደሰቱበትን ጥሩ ጊዜ አብረው አሳልፈው በመጨረሻ መለያየት ግድ ሆነ:: ወ/ሮ ማርታ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ በቤተሰብ ቀን ልጆቹን መጥተው ሊጠይቋቸው ቃል ገብተው ሄዱ::

ቃላቸውን አክብረው ከዚያ በኋላም ሊጠይቋቸው መጥተዋል:: አመለዘውድ እየጠየቀቻቸው አንድ ሁልጊዜ ያልሆነላቸው ነገር ግን ነበር:: የናፈቀችውን ውሻቸውን፣ ዳንቴን መውሰድ ይረሳሉ::

## -45-

*«መግባት የምፈልገው የመንግስት ትምህርት ቤት ነው፣ ማለትም አለመ የሚማርበት። መስማት የተሣናቸው አይሁን እንጂ የትኛውም ትምህርት ቤት ይሁን።»*
*አመለዘውድ*

ዋና መስሪያ ቤቱ በአሜሪካ የሚገኝ አዶፕሽን አድቮኬይትስ ኢንተርናሽናል (ኤ.ኤ.አይ.) የተባለ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆችን ከውጪ አገር፣ በተለይ ከአሜሪካ ከሚመጡ የጉዲፈቻ አሳዳጊዎች ጋር የሚያገናኝ ድርጅት ያጋጠመውን ችግር ተከትሎ ነበር የእናት መሠረት የተጣለው። ወደ ኤ.ኤ.አይ. የመጡ አንዳንድ ልጆች ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ መሆናቸው ታወቀ። በወቅቱ ለእንደነዚህ ዓይነት ልጆች የጉዲፈቻ አሳዳጊ ማግኘት እንኳን ቢቻል የአሜሪካ ኤምባሲ ቪዛ ይከለክል ነበር።

በኢትዮጵያ ለወላጅ ሞትና ለልጆች ያለ አሳዳጊ መቅረት ምክንያት ከሆኑት በሽታዎች ዋነኛው ኤድስ በመሆኑ ወደ ኤ.ኤ.አይ. የሚመጡ ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ ህጻናት ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጣ። ኤ.ኤ.አይ. ለእነዚህ ህጻናት ቤት ተከራይቶ ከሕዳር 1993 ዓ.ም. ጀምሮ የተለየ እንክብካቤ እንዲያገኙ ማድረግ ጀመረ። ይህን ድርጅቱ በራሱ በጀት የሚያንቀሳቅሰውን ጥቂት ልጆች የነበሩበትን የህጻናት ማሳደጊያ እንዲያስተዳድሩም ከድርጅቱ ሠራተኞች አንዷ የነበሩት ማሚ ተመረጡ። ማሚ ህጻናት ማሳደጊያውን በጥሩ ሁኔታ በብቃት ማስተዳደር ችለው ነበር። ምግብና ተገቢ የሆነ የህክምና ክትትል ስለሚያገኙ ልጆቹ የጤናቸው ሁኔታ መሻሻል ጀመረ።

የልጆቹ ቁጥር መጨመሩን ቀጠለ። ተጨማሪ ሞግዚቶችና ሠራተኞችም መቅጠር አስፈለገ። የኤ.ኤ.አይ. የኢትዮጵያ ፕሮግራም አስተባባሪ ካናዳዊቷ ወ/ሮ ጌይል ጎርፌ እና ኢትዮጵያዊ ባለቤታቸው አቶ ዮናስ ጎርፌ የህጻናት ማሳደጊያው በኤ.ኤ.አይ. በጀት የሚንቀሳቀስ ከሚሆን ራሱን የቻለ ድርጅት ሆኖ የራሱን በጀት ቢያንቀሳቅስ ጥሩ እንደሚሆን አመኑ። በአሜሪካ የሚገኘው የኤ.ኤ.አይ. ዋና መስሪያ ቤት ዳይሬክተር ሜርሊ ሪፕሊ በዚህ ሐሳብ ተስማሙ። ከዚህ በኋላ ነበር የኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ ህጻናት መኖሪያው ቤት «እናት» የሚል ስም ተሰጥቶት በፍትህ ሚኒስቴር ዕውቅና አግኝቶ ራሱን የቻለ አገር በቀል ድርጅት ሆኖ በየካቲት ወር 1994 ዓ.ም. ሥራ የጀመረው።

ማሚ የእናት ዳይሬክተር ሆኑ። ብዙም ሳይቆዩ ባለቤታቸው ፓፓ እንዲሁም ወንድ ልጃቸው ከእሳቸው ጋር በድርጅቱ መኖር ጀመሩ። የድርጅቱ የቦርድ አባላት የድርጅቱን እንቅስቃሴ ለመከታተልና ለመቆጣጠር





ፍላጎቱም፣ ጊዜውም የነበራቸው ሰዎች አልነበሩም። እነማሚም «ተቆጣጠሩን» ብለው በየጊዜው የቦርድ አባላቱን ለማሰባሰብ አልተጨነቁም።

የህጻናት ማሳደጊው በማሚ ቤተሰቦች ሙሉ ቁጥጥር ሥር ለመሆን ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። ወ/ሮ ጌይልና አቶ ዮናስ በማሚ ላይ እምነት ስለነበራቸው ድርጅቱም ራሱን የቻለ በመሆኑ የራሳቸው ሥራ ላይ አትኩረዋል። እናት ኖርዌይ፣ ካናዳና ስዊድን ከሚኖሩ በጎ አድራጊዎች የገንዘብ ድጋፍ ያገኝ ነበር።

ካትሪን ፐውፕ ኦልሰን የተባሉ አንዲት አሜሪካዊ ወይዘሮ ለኤ.ኤ.አይ. ኤች.አይ.ቪ. ፕሮጀክት ከተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች ገንዘብ ያሰባስቡ ነበር። ፕሮጀክቱ እናት በሚል ስም ድርጅት ሆኖ መንቀሳቀስ ከጀመረ በኋላ «የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት» የተባለ ድርጅት አቋቁመው ለእናት መንቀሳቀሻ ገንዘብ ማሰባሰብ ጀመሩ። ወደ ኢትዮጵያም መጥተው ልጆቹን ጎበኙ። በጉብኝታቸውም ወቅት የችግሩን ስፋትና ጥልቀት ይበልጥ በመረዳታቸው ልባቸው ተነካ። ወደ አገራቸው ተመልሰው የገንዘብ ማሰባሰቡን ሥራ አጠናክረው ቀጠሉ። ለእናትም ቋሚ ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ይልኩ ጀመር።

እናት ዓላማው ከኤች.አይ.ቪ. ጋር የሚኖሩ ልጆችን መርዳት ብቻ የነበረ ቢሆንም፣ ማሚና ቤተሰባቸው ከቫይረሱ ነጻ የሆኑ የደሀ ቤተሰብ ልጆችን «ወደ አሜሪካ እንልካችኋለን» ብለው ወደ ድርጅቱ ማስገባት ጀመሩ። ልጆችን ከአሜሪካዊ የጉዲፈቻ አሳዳጊዎች ጋር የማገናኘት ሥራ ለመስራት አስበው ነበር ይህን ያደረጉት። ድርጅቱ ያለው አንድ ሚኒባስ መኪና በቤተሰቡ ስም የተገዛ ሲሆን፣ መኪናው በይበልጥ የማሚና ፓፓን ቤተሰብ ያገለግላል።

ለጋሾች የገንዘብ አጠቃቀማቸውን የሚገልጽ የፋይናንስ ሪፖርት ቢፈልጉም እነማሚ አይልኩም ነበር። የድርጅቱ ገንዘብ በሚባክንበትና በማወቅ ወይም ባለማወቅ ከቤተሰቡ የግል ሃብት ጋር በሚቀላቀልበት ሁኔታ የፋይናንስ ሪፖርት ማዘጋጀት ለእናት አስተዳዳሪዎች ቀላል አልነበረም። ድርጅቱ በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳለ ካትሪን ፐውፕ ኦልሰን የመሰረቱት የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት የእናትን የገንዘብ አጠቃቀም ለማጥናት ተወካዮቹን ወደ አዲስ አበባ ላኩ። እነማሚ ተወካዮቹን በጥሩ ሁኔታ አላስተናገዷቸውም። የፋይናንስ ሪፖርት ሲጠይቁ፣ «ቆይ ዛሬ ከሰዓት በኋላ . . . »፣ ከሰዓት በኋላ ሲመጡ ደግሞ፣ «ቢቃ ነገ . . . » እየተባሉ ሪፖርቱን ሳያገኙ መሄጃቸው ቀን ደርሶ ወደ አሜሪካ ተመለሱ።



Sample output to test PDF Combine only

ሁኔታው እጅግ ያሳዘናቸው ካትሪን ለእናት የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ እንዲቋረጥ አደረገ:: ይህን ተከትሎ በነማሚ ላይ ጫና ተፈጠረ:: «ገንዘብ የለም» ብለው ለድርጅቱ ሠራተኞች ደመወዝ መክፈል አቆሙ:: ለልጆቹ እናት ወደ ክፉ እንጀራ እናት በፍጥነት ተቀየረችባቸው:: የሚቀርብላቸው ምግብ ዓይነትና ጥራት ቀነሰ:: ዳቦ ብቻ በልተው የሚውሉባቸው ቀናት በረከቱ:: አንዳንድ ቀን እንዲያውም ዳቦው ተቆራርሶ ለጥጋብ ሳይሆን ለህይወት ማቆያ ያህል ብቻ ነበር የሚሰጣቸው::

የተመጣጠነ ምግብ በተገቢው ሁኔታ ባለማግኘታቸው ህጻናቱ በሽታ የመቋቋም አቅማቸው ተዳከመ:: የተለያዩ ህጻናት በየጊዜው ይታመሙ ነበር:: ለልጆቹ መታከሚያ የሚሆን ገንዘብ አልነበረም:: አንዳንድ ጎብኚዎች መጥተው ሃምሳም ሆነ መቶ ዶላር ሲሰጡ መኪናውም እንደልብ ስለማይገኝ ከሰባት ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸው ህጻናት መኖሪያ ከሚገኝበት ቀራንዮ መድኃኒዓለም ቤተክርስቲያን አካባቢ ሞግዚቶች ህጻናቱን አዝለው በእግራቸው ወደ ሃኪም ቤት የሚሄዱበት አጋጣሚ ነበር:: ተገቢ የህክምና ክትትል ስላልነበረ በኤድስ በጣም የተጎዱ ህጻናት ይሞቱ ጀመር::

እነማሚ የቤት ኪራይ እንኳን መክፈል አቃታቸው:: አከራዮቹን፣ «በሚቀጥለው ወር» ይሉዋቸዋል:: «በሚቀጥለው» የተባለው ወር ሮጦ ሲደርስ ደግሞ፣ «አሁን ለጊዜው ገንዘብ ስለሌለን ነው:: ከውጪ በዚህ ወር ስለሚላክልን በሚቀጥለው ወር . . . » እያሉ ማባባልና መለማመጥ ነበረባቸው::

ብዙዎቹ ሞግዚቶች ደመወዝ ባይከፈላቸውም በዋንኛነት ልጆቹን ጥለው መሄድ ስለከበዳቸው፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ድርጅቱ ከእንደገና ያንሰራራል የሚል ጭላንጭል ተስፋ ታይቷቸው ልጆቹን በነጻ ማገልገል ቀጥለዋል:: ጥቂቶች ተስፋ ቆርጠው ሄድ፣ መጣ ማለት ጀምረዋል::

አመለዘውድ የጆሮዋ ችግር እየባሰባት እንጂ እየተሻላት አልሄደም:: እሷ የመስማት አቅሟ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መሆኑን በጭራሽ ማመን ባትፈልግም፣ መስማት እየተሳናት ነበር:: እነማሚ፣ «ገንዘብ የለንም» የሚሉበት ጊዜ ነበርና፣ «ቆይ ዛሬ፣ ቆይ ነገ» እያሉ አላሳከሟትም:: ከሞግዚቶቿ ጋር የአፋቸውን እንቅስቃሴም ሆነ ፊታቸውን እያነበበች መግባባት ትችላለች:: አዘውትራ የማታገኛቸውን ሰዎች ግን ለመረዳት ትቸገራለች::



Sample output to test PDF Combine only



ከልጆቹ መሀል አንድ ልጅ ከግቢ ውጭ ባለ መደበኛ ት/ቤት ይማራል:: አለሙ ይባላል:: አመለዘውድ የትምህርት ጥማት አላትና እንደ አለሙ ት/ቤት ገብታ መማር ፈለገች::

***ለአባቴ***

*እጅግ በጣም የምወድዎት አባቴ ለጤናዎት እንደምን አሉ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ::*

*ውድ አባቴ፣ እኔ በጣም እወድታለሁ:: እኔ ቤተሰቤም ይመጣና ይጠይቀኛል:: በአሁኑ ጊዜም ሊመጡ ይችላሉ:: 2 ወንድም አሉኝ፤ እዚህ ቤት:: አሁን እርስዎ ጋር አክስቴ*[1] ስትመጣ ይተዋወቃሉ:: ምንም አባቴ፣ ከዚህ ቤት ስመጣ ያቋረጥኩት ከ4ተኛ ክፍል ነበር:: ምንም አልተማርኩም:: መማር እፈልጋለሁ:: የመማር ግዴታ አለብኝ፤ ነገር ግን ጥቅምት*[2] ላይ ነበር የመጣሁት:: ይኸው ምንም ሳልማር ክረምት መጣ፤ ማለት አስተማሪያችን*[3] ቶሎ ስለወጣች:: አሁን ግን ውጪ 4ኛ ክፍል እንደ አለሙ መማር እፈልጋለሁ:: ጆሮዬን የመኛ ል:: «ቆይ ትታከሚያለሽ» ተብዬ ነበር፤ አልታከምኩም:: ከዚህ በተረፈ አባታችን በመሆንዎት በጣም ደስ ብሎኛል:: እኔ ለልጆች፣ «ከእንግዲህ ፓፓዬ ነው የምላቸው:: አባታችን ናቸው::» ስላቸው ነበር:: እግዚአብሔር ይመስገን፣ ለሁሉም ነገር! በተረፈ በጣም እወድዎታለሁ! ሁላችንም ነን የምንወድዎት::*

*ላንቺ አመለዘውድ*

*[1] ወ/ሮ ማርታን ይመስላል አክስቴ ማለት የመረጠችው*
*[2] ወደ እናት የገባችው በጥቅምት ሳይሆን በ1996 ዓ.ም. ህዳር መጨረሻ ላይ ነበር::*
*[3] አንዲት አስተማሪ ግቢው ውስጥ ልጆቹን ታስተምር ነበር:: ገና ፓፓና ማሚ በገንዘብ እጥረት ምክንያት ለሠራተኞቹ ደመወዝ መክፈል ከማቆማቸው በፊት የተሻለ ሥራ አግኝታ ለቅቃለች::*

ፓፓ ደብዳቤውን ካነበቡ በኋላ አመለዘውድ ጆሮዋ በደንብ ስለማይሰማ፣ በወቅቱ ት/ቤት እንደማይልኳት ቢያውቁም፣ እንዲሁ ለአፋቸው መስማት የተሳናቸው ሕፃናት ወደሚማሩበት ት/ቤት እንድትገባ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ ነገሯት:: አመለዘውድ በዚህ ዕቅድ ደስተኛ አልነበረችም:: የጆሮዋ ችግር ከሌሎቹ ልጆች የተለየች ተደርጋ እንድትታሰብ እንዲያደርጋት በጭራሽ አልፈለገችም:: ምንም እንኳ እነፓፓ ለጊዜው ሊያሳክሟት ባይችሉም፣ ወደፊት ጆሮዋን ታክማ እንደምትድን ተስፋ ታደርግ ነበር::

*እንግዲህ እንደተወሰዱ*[1] ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፡፡*

*ኤፌ. *[2]*

*እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፣ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ፣ በበደላችን ሙታን እንኳን በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሠጠን፡፡*
*ኤፌ.*

## *የሠላምታ ደብዳቤ*

*በጣም የምወድዎት አባቴ ለጤናዎት እንደምን አሉልኝ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ፡፡ ውድ አባቴ፣ እኔ መስማትን በጠቅላላ ጆሮዬ እምቢ አላለኝም፡፡ ስለዚህ መስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤት መግባት አልፈልግም፡፡ ምክንያቱም እኔ በማንበብና በማጥናት ጉበዝ ነኝ፡፡ ስለዚህ መግባት የምፈልገው የመንግስት ትምህርት ቤት ነው፤ ማለትም አለሙ የሚማርበት፡፡ መስማት የተሣናቸው አይሁን እንጂ የትኛውም ትምህርት ቤት ይሁን፡፡ በሁሉም የትምህርት አይነት ከሰነፍኩ እገባለሁ እንጂ አሁን ብሞት አልገባም! በቅርብ ጊዜ ጀምሮኝ አሁን፣ አሁን በአሁን እንዲህ መሆን አልፈልግም! ጌታ ካለ እታከምና እድናለሁ ብዬ እፀልያለሁ፡፡ በሕክምና ካይታይ መስማት የተሣናቸው ት/ቤት መግባት ይከብደኛል፡፡ ደግሞ እግዚአብሔር ያውቃል፡፡ አዋቂ ነው፡፡ ሁሉንም ነገር ያውቃል፡፡ አባዬ፣ የአማርኛና የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት መፅሐፍ ይግዙልኝ፤ ማለትም ለ3 ለ4 ምናምን የሚጠቅም፡፡ እንግሊዘኛ ማወቅ በጣም እፈልጋለሁ፡፡ ከትርጓሜው እንግሊዘኛ በደንብ አነባለሁ፡፡ የአማርኛ እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት መፀሐፍ አሁን ቢገዛልኝ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ ከሁሉም ነገር በፊት አመሠግናለሁ፡፡*

*ሰው ሆይ! በጌታ ደስ ሊልህ ይገባል፡፡*
*እንግዲህ ልጅ ሆይ አንተ በክርስቶስ ባለው ፀጋ በርታ፡፡*
*ጢሞቴዎስ*[3]

*[1] «እንደተወሰዱ» ያለችው «እንደተወደዱ» ለማለት ነው፡፡*
*[2]/[3] የጥቅሶቹን ምዕራፍና ቁጥር አልጻፈችም፡፡*

እነፓፓ ልጆቹን በሚገባ መመገብ እንኳን በማይችሉበት ሁኔታ አስጨናቂ አጣብቂኝ ውስጥ ነበሩ፡፡ ልጆቹ በበሽታ ብቻ ሳይሆን በተመጣጠነ ምግብ እጦት እየሞቱ ነው፡፡ ት/ቤት ልጆቹን መላክ በዚህ ወቅት የማይታሰብ ቅንጦት ነበር፡፡





## -46-

*«አባዬ፣ እኛ ያሉት ሠራተኞች ይበቁናል፡፡ ካልበቁን ሌላ ሠው ይግባ እንጂ ከወጡት አንድ ሰው አንፈልግም፡፡»*
*አመለዘውድ*

በእናት ህጻናት ማሳደጊያ የሚሠሩ አንዳንድ ሞግዚቶች ደመወዝ ስላልተከፈላቸው ስራ ለቀቁ፡፡ ብዙዎቹ ሞግዚቶች ግን ደመወዝም ባይከፈላቸው ከስራ አልቀሩም፡፡ እነዚህ ሞግዚቶች ስራ ያልለቀቁት ፓፓና ማሚ ደመወዛቸው ወደፊት እንደሚከፍሏቸው ነግረው ስላባበሏቸው ብቻ ሳይሆን፣ ልጆቹን ስለሚወዷቸውም ነው፡፡ ከእነርሱ መካከል አንዳንድ ቀን ከስራ የሚቀሩ ሞግዚቶች ቢኖሩም፣ ልጆቹን በነጻ ለመንከባከብ ፈቃደኞች ነበሩ፡፡

አመለዘውድ ከሌሎቹ ልጆች የተለየች መሆኗን ከመቼውም ጊዜ የበለጠ አሁን ራሷም እያስተዋለችው፣ በሌሎችም እየተስተዋለ ነበር፡፡ ጨዋታ አለመውደዷና በብዙ መልኩ የአዋቂ ባህሪ ያላት መሆኗ ልዩ አድርጓታል፡፡ ሞግዚቶቿና ሌሎች የህጻናት ማሳደጊያው ሠራተኞች እሷን እንደሌሎቹ ልጆች ለማየት ሁኔታዋ አልፈቀደላቸውም፡፡ ጥቂት ሁኔታዎቿ የልጅ ቢሆኑም፣ በአብዛኛው አነጋገሯና አስተሳሰቧ እንደ አዋቂ ነው፡፡ ለነፓፓ በምትጽፈውም ደብዳቤ ሌሎቹን ልጆች በራሷ ስልጣን የመወከል አዝማሚያ ይታይባታል፡፡

እንኳን ሌላ አዲስ ሞግዚት ለመቅጠር ይቅርና፣ ላሉትም በወቅቱ ደመወዝ ለመክፈል የድርጅቱ አስተዳዳሪዎች አቅም ባይኖራቸውም፣ አመለዘውድ የለቀቁት ሞግዚቶች ዳግመኛ እንዲመለሱ አልፈለገችም፡፡ ከለቀቁት ሞግዚቶች በተለይ አንዷ በጥፊ የምትማታ ስለነበረች፣ ሌላ የሷ ዓይነት ለልጆቹ ደህንነት የማትጨነቅ ሞግዚት ትመጣለች የሚል ሥጋት ነበራት፡፡ ከተቀጠሩም አዲስ ሞግዚቶች እንጂ የለቀቁት ተመልሰው እንዳይቀጠሩም አጥብቃ ታሳስብ ነበር፡፡

*ውድ አባቴ፣ እንደምን አረፈዱ? እኔ ደህና አድራለሁ፡፡ ሠላም ለእርስዎ እመኛለሁ፡፡ አባዬ፣ እኛ ያሉት ሠራተኞች ይበቁናል፡፡ ካልበቁን ሌላ ሠው ይግባ እንጂ ከወጡት አንድ ሰው አንፈልግም፡፡ ስለምትኬ ሁሉን ልጆች ጠይቀው ሠራተኞችን በርቱካንንና* ጥሩነሽን* ብቻ መጠየቅ ይችላሉ፡፡ አሁን ያሉት መስሐፍ ቅዱስ ያስተምሩናል፡፡ እነዛ በፊት ነበር የሚዘፍኑት፡፡ እኔ በጉር ሲሠሩ ከደከማቸው በጥፊ ይማታሉ፡፡ ማለትም እኔ ደግሞ በጥፊ መመታት በጣም እፈራለሁ፣ ለጆሮዬ ብዬ፡ ስለማሚን ብዙ ጊዜ በጥፊ*



Sample output to test PDF Combine only

መታታለች፣ ምትኬ የምትባለው:: ስለዚህ እኛ አንፈልጋቸውም! የሉት ይበቁናል:: ካልበቁ አዲስ ይምጣልን! በማለት በትህትና እጠይቃለሁ::

ከልጆች
አመሰዘውድ ግርማ
መልካም ቀን!

* ዘርቱካን ምግብ አብሳይ ናት::
* ጥሩነሽ ከልጆቹ ሞግዚቶች አንዷ ናት::



Sample output to test PDF Combine only



## -47-

«እናት እንዲፈርስና ልጆቹም በአዲስ አበባ ባሉ የተለያዩ የህጻናት ማሳደጊያዎች እንዲበተኑ ተወስኖ ነበር::»
አቶ ዮናስ ጎርፌ
«ዮናስ ድርጅቱን እንደገና ለማቋቋም እርዳን አለኝ::»
ዶ/ር አለሙ መኮንን

ከናካቴው ከሥራ ከቀሩት ከጥቂቶቹ በስተቀር የእናት ሠራተኞች ያለ ደመወዝ ለአራት ወራት ሠሩ:: እጅግ የተማረሩ አንዳንድ ሠራተኞች አቤቱታቸውን ለእናት መቆርቆር ምክንያት ለሆነው ለኢ.እ.አይ.፣ በተለይም በግል ለሚግባቧቸው ለአቶ ዮናስ፣ በተደጋጋሚ ያቀርቡ ነበር:: እናት ራሱን የቻለ ድርጅት በመሆኑ ኢ.ኢ.አይ. ጣልቃ ለመግባት የሚያስችል ህጋዊ መብት አልነበረውም:: በ1996 ዓ.ም. የፋሲካ ዕለት የሆነው ነገር ግን አቶ ዮናስ አንድ እርምጃ እንዲወስዱ የሚያስገድድ ሁኔታ ፈጠረ::

ለበዓሉ ለልጆቹ ሥጋ በበጎ አድራጊ ግለሰቦች ቀርቦ ወጥ ቤት ውስጥ ሲገባ ልጆቹ ካዩ በኋላ፣ ሥጋው በድርጅቱ ሚኒባስ ከግቢ ውጪ ተወሰደ:: ልጆቹ ዓመት በዓሉን ሥጋ ሳይበሉ አሳለፉ:: ይህ ሁኔታ እጅግ ያሳዘናቸው ሞግዚቶች ለአቶ ዮናስ ያዩትን ነገሯቸው:: አቶ ዮናስ ትዕግስታቸው ተሟጠጠ:: ተጨማሪ በደል በህጻናቱና በድርጅቱ ሠራተኞች ላይ ሲደርስ መስማት አልፈለጉም::

የህግ ባለሞያ ለሆኑት ለጓደኛቸው ለአቶ ተመስገን ገብረሥላሴ በእናት ስላለው ሁኔታ አብራርተው ነገሯቸው:: አቶ ተመስገንም በሁኔታው በጣም አዘኑ:: ያለምንም ክፍያ ሞያዊ ድጋፍ ለማድረግ በሙሉ ፍላጎት ተነሳስተውም ለጥቂት ቀናት ማስረጃ ሲያሰባስቡ ቆዩ::

ከሦስት ቀናት በኋላ አቶ ተመስገን ተጨባጭ የሆኑ ማስረጃዎችን ያዙ:: ከዚህ በኋላ ነበር ሁለቱ ሰዎች ወደ ፍትህ ሚኒስቴር በመሄድ በወቅቱ የማህበራት ምዝገባ ጽ/ቤት ኃላፊ ወደ ነበሩት አቶ ጌታቸው ጎንፋ ቀርበው በእናት የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅት እየሆነ ስላለው ነገር ነገሯቸው::

ነገሩ ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን የተረዱት የጽ/ቤቱ ኃላፊ እርምጃቸው ፈጣን ነበር:: በዚያው ዕለት ጠዋት አቶ ዮናስን ይዘው በቀጥታ ወደ እናት አመሩ:: በአጋጣሚ በዕለቱ ሁለት ልጆች፣ በትንንሾቹ ግቢ አንድ፣ ከፍ፣ ከፍ ባሉት ልጆች ግቢ ደግሞ ሌላ አንድ ልጅ፣ ሞተው ነበር:: በምግብ ዕጥረት የተጎዱ በርካታ ልጆችም ቆዳቸው በቁስልና ጠባሳ ተኈርጎርጉሯል:: አቶ ጌታቸው የልጆቹን ሁኔታ ሲያዩ ይበልጥ አዘኑ፣ ተበሳጩም:: እነማሚ

በአስቸኳይ እናትን ለቀው እንዲወጡ አዘዙ:: ድርጅቱ እንዲዘጋና ህጻናቱ በአዲስ አበባ በሚገኙ የተለያዩ የህጻናት ማሳደጊያዎች እንዲበተኑ መወሰናቸውንም ለአቶ ዮናስና ለአቶ ተመስገን አሳወቁ::

በወቅቱ በአዲስ አበባ ከኤች.አይ.ቪ. ጋር የሚኖሩ ልጆችን የሚቀበል ሌላ የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅት አንድ ብቻ ነበር:: አመለዘውድና ወንድሞቿ ቀደም ሲል የነበሩበት ይኸው የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅት ከአቅሙ በላይ በርካታ ህጻናትን የሚያስተናግድና የተጨናነቀ ስለነበር ተጨማሪ ልጆችን ለመቀበል ቦታ አልነበረውም:: እነአመለዘውድም በድርጅቱ ቆይታቸው ከአዋቂዎች'ጋ እንዲኖሩ የተገደዱት የተለየ ክፋት እንዲፈጸምባቸው ታስቦ ሳይሆን ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ልጆች የሚኖሩባቸው ክፍሎች በመጣበባቸው ምክንያት ነበር:: አቶ ዮናስ ጎርፌ ይህንኑ ሁኔታ ስለሚያውቁ ለፍትህ ሚኒስቴሩ ባለስልጣን፣ «ገንዘብ ካገኘንና አሠራሩን ካስተካከልን ልጆቹ እዚሁ እንዲኖሩ ቢደረግ ጥሩ ነው::» የሚል ሃሳብ አቀረቡ::

አቶ ጌታቸውም በዚህ ሃሳብ በመስማማታቸው አቶ ዮናስ በአሜሪካ የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት የተባለውን ድርጅት ለመሰረቱት ለካትሪን ፐውፐ ኦልሰን ደወሉ:: ካትሪን ከቢል ጌትስ ፋውንዴሽን ያገኙት ስድሳ ሺህ ዶላር እንዳለና ድርጅቱ አሰራሩ እስከተስተካከለ ድረስ ገንዘብ መላክ እንደሚችሉ ለአቶ ዮናስ አረጋገጡላቸው::

ድርጅቱን ከእንደገና በካትሪን ፐውፐ ኦልሰን ድርጅት ስም ለማቋቋምና ህጋዊ መሠረት ለማስያዝ አቶ ዮናስና አቶ ተመስገን ላይ፣ ታች ማለት ጀመሩ:: ለቅርብ ወዳጆቻቸው የህጻናቱን ሁኔታ ሲያስረዷቸው፣ ከነሱ የሚጠበቀውን ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን አረጋገጡላቸው:: እናት ስሙ ተቀይሮ የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት ተብሎም በአቶ ዮናስ ጎርፌ፣ በአቶ ተመስገን ገብረሥላሴ፣ በአቶ አምሃ መኮንን፣ በዶ/ር ዳንኤል ብስራት እና በአቶ ሰለሞን ቦጋለ የቦርድ አባልነት ተቋቁሞ በሰኔ 1996 ዓ.ም. ተመዘገበ::

አቶ ዮናስ ድርጅቱን ከእንደገና የሚያደራጅ ባለሙያ ማፈላለግ ጀመሩ:: ዶ/ር አለሙ መኮንን የተባሉ አንድ ሰው ይህንኑ ኃላፊነት በብቃት ሊወጡ የሚችሉ መሆናቸውን ሰዎች ጠቆሟቸው:: ዶ/ር አለሙ በወቅቱ ሥራ ይበዛባቸው ስለነበረ ድርጅቱን ከእንደገና የማዋቀሩን ሥራ ሊመሩ እንደማይችሉ ለአቶ ዮናስ ነገሯቸው::

«ልጆቹ ያሉበት ሁኔታ ጊዜ የማይሰጥ ነው:: አየሞቱ ነው:: ለእነሱ የሚሆን ሌላ ድርጅት ስለሌለ ድርጅቱን በፍጥነት መልሰን ማቋቋም አለብን:: አንተ ይህን ኃላፊነት ለመውሰድ ከለህ ብቃት አንጻር፣ እንደ



Sample output to test PDF Combine only



ኢትዮጵያዊነትህም የህጻናቱን ህይወት የማዳን የዜግነት ግዴታ አለብህ::» ብለው አቶ ዮናስ ዶ/ር አለሙን አሳመኗቸው::

ህጻናቱን በተሻለ ሁኔታ ለመንከባከብ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ኮሚቴ ተመሰረተ:: በወቅቱ የእናት ሁኔታ አንግብጋቢ ስለነበር ከአሜሪካ የሚላከውም ብር እስኪደርስ አቶ ዮናስ ከኤ.ኤ.አይ. በጀት ሦስት ሺህ ብር በብድር መልክ ጠይቀው ለድርጅቱ መንቀሳቀሻ በዶ/ር አለሙ ለሚመራው ኮሚቴ ሰጡ::

«ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ነው» እንደሚባለው ጉዳዩ በቀጥታ ቢመለከታቸውም እየሆነ ስላለው ነገር ልጆቹ አያውቁም ነበር:: ብዙም እስኪጠግቡ ባይበሉም፣ የሚበሉት ስላላጡ በማሚና ፓፓ አስተዳደር ስለመጎዳታቸውም አያስቡም:: እነአመለዘውድን ጨምሮ በርካታዎቹ እጅግ በከፋ ድህነት ውስጥ ስለኖሩም ሊሆን ይችላል ህጻናት ማሳደጊያው የነበረበት ሁኔታ ብዙም ያላስከፋቸው:: «ከፍትፍቱ ፊቱ» እንደሚባለው ከሞግዚቶቻቸው የሚያገኙት ፍቅር ደግሞ አልጎደለባቸውም::

የድርጅቱን አሰራር ለማስተካከል በዶ/ር አለሙ መኮንን የሚመራ የባለሙያዎች ቡድን ጥናት ጀመረ:: ያሉት ሞግዚቶችና ሠራተኞች እንዲቆዩ ለማድረግና ደመወዛቸውን ለመጨመር ሁለት መመዘኛዎች ጥቅም ላይ ዋሉ:: ሠራተኞቹ በሥራ ገበታቸው ላይ እንዲቆዩ፣ ልጆቹ ስለእያንዳንዱ የድርጅቱ ሠራተኛ ያላቸው ስሜት እየተጠየቀ ጥናት ተደረገ:: ልጆቹ ለአንዲት ሠራተኛ ጥሩ ስሜት እንዳላቸው፣ እንደሚወዷት ከተረጋገጠ፣ የሠራተኛዋን ደመወዝ ለማሻሻል የሠራችበትን ዓመት ብዛት ማወቅ በቂ ነበር:: ሥራው ቀላል የሚባል አልነበረም:: የማሚና ፓፓን ድክመት በማጋለጥ በዶ/ር አለሙ ለሚመራው ኮሚቴ ከፍተኛ ድጋፍ ያደረገ አንድ ሠራተኛ በህጻናቱ አይወደድም ነበር:: ኮሚቴው እሱንም ማባረር ነበረበት::

ከዚህ ከአንድ ወር በላይ ከፈጀ ጥናትና ድርጅቱን ዳግመኛ የማዋቀር ሥራ በኋላ የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ሕፃናት የእንክብካቤ ፕሮጀክት እንደ አዲስ ተቋቋመ::

ልጆቹ የሚወዷቸው ሞግዚቶችና ሌሎች የድርጅቱ ሠራተኞች ሥራ ቀጠሉ:: ለአራት ወራት ደመወዝ ሳይከፈላቸው፣ «ልጆቹን እንዴት ትተን እንሄዳለን?» ብለው በነፃ፣ ለሕሊናቸው ሲያገለግሉ የነበሩ ነባር ሞግዚቶች ያልተከፈላቸው ደመወዝ ተከፍሏቸው፣ ደመወዝ ጭማሪም ተደርጎላቸው፣ ደመወዛቸውን በየወሩ ማግኘት ጀመሩ::

ድርጅቱንም በዋና ዳይሬክተርነት እንድትመራ ወ/ት ስድሴ ቡሊ የተባለች የሃያ ስምንት ዓመት ወጣት በነሐሴ 1996 ዓ.ም. ተቀጠረች:: ሀልውናው አደጋ ውስጥ የነበረው ድርጅት፣ ከአዲሷ ዳይሬክተርና ከአዲሱ ስሙ ጋር ማንሰራራት ጀመረ:: ለልጆቹ የሚደረገው እንክብካቤና ድጋፍ የተሻለ ሆነ:: ተመጣጣኝ ምግብና ተገቢ የህክምና ክትትል ማግኘት ጀመሩ::

በ1997 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ ት/ቤት መሄድ የሚችሉት ልጆች በሙሉ ከግቢ ውጪ በሚገኝ ት/ቤት ትምህርት ጀመሩ:: ለልጆቹ በጣም የሚያስደስት ጊዜ ነበር:: ት/ቤት ደርሶ መምጣት፣ ከህጻናት ማሳደጊያው የግንብ አጥር ውጪ ያለውን ዓለም አዘውትረው ለማየትና ከሌሎች ብዙ ልጆች ጋር ለመገናኘት ዕድል ሰጣቸው::

አመለዘውድ ሶስተኛ ክፍል ገባች:: አባቷን አጥታ፣ ለቤተሰቦቿ ስትል ትምህርት ባቋረጠችበት ጊዜም ቢሆን ወደፊት ትምህርቷን ተምራ፣ ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሳ፣ እናቷንና ወንድሞቿን በሰላምና በደስታ በአንድ ጣሪያ ስር ለማኖር ትመኝ ነበር:: እናቷን ብታጣም ወንድሞቿ አሉላት:: ለምኞቷ መሳካት መሠረት እንደሆነ የምታስበውን የትምህርት ዕድል ስታገኝ ሙሉ ትኩረት ሰጥታ በታላቅ ፍላጎትና ጉጉት መማር ጀመረች:: ሆኖም ህመሟ ትልቅ እንቅፋት ሆነባት:: ገና ትምህርት በጀመረችባቸው የመጀመሪያ ሳምንታት በውጋትና የጆሮ ህመም መሰቃየት ጀመረች::

የአስተዳደር ሠራተኞች ቢሮ ሌላ ራቅ ያለ ግቢ ውስጥ በመሆኑ አመለዘውድ ከስድሴ ጋር በየዕለቱ ለመገኛኘት ዕድል ባይኖራትም ስድሴ ሥራ በጀመረች በጥቂት ወራት ውስጥ ሁለቱ በጣም ተቀራርበው ነበር:: ደብዳቤም በየጊዜው ይጻጻፉ ነበር::

*መስከረም 19፣1997*

*እናቴ ማሚ ስድሴ፣*

*እንደምን አለሽ? ለሊት እንቅልፍ በዓይኔ ሣይዞር አደርኩና ቀን ተኛሁ:: ሲወጋኝ እንቅ፣ ልቅቅ ሲያደርገኝ ነው:: ሳለቅስ አደርኩ:: ሣኘክና አፌን ስከፍት ይወጋኛል:: የሚጠጣ ምግብ ይሻለኛል:: ንፁህ በሶ ግዢልኝ:: ማሚ ስድሴ ጆሮዬን እንደዚህ ከሚያመኝ ሞትን እመርጣለሁ:: እንዴት እንደሚያመኝ እኔ ነኝ የማውቀው:: ስለፃፍሽልኝ በጣም አመሠግናለሁ:: አንቺንም ጌታ ይባርክሽ! ጆሮዬን ሲሻለኝ እፅፍልሻለሁ:: የምነግርሽ ነገር አለኝ፣ በፅሑፍ ነው የምነግርሽ:: ፀልይልኝ::*

*ቻው*



Sample output to test PDF Combine only



አመለዘውድ ህመሟን ችላ ጠንክራ ታጠና ስለነበረ መጀመሪያ በተፈተነቻቸው ፈተናዎች አስር ከአስር አመጣች::

*02/03/97*

*የሠላምታ ደብዳቤ*

*ለውድ እናቴ ማሚ ስድሴ፣*

*ይድረስ በጣም ለምወድሽ እናቴ ማሚ ስድሴ፣ ለጤናሽ እንደምን አለሽ? እኔ ጌታ ኢየሱስ ይመስገን በጣም ደህና ነኝ:: ማሚ ስድሴ፣ እኔ በትምህርቴ ጐበዝ እየሆንኩኝ ነው:: በፈተና አማርኛ 10፣ ሒሳብ 10፣ እንግሊዘኛ 10 አመጣሁ:: የደብተር ማርክም ደፈንኩት:: አስፈርሙ ተብሏል:: ፈርሚልኝ:: ከሰር አስፈላጊ ነው:: ለስዕል እምጡ ተብሎ ነበር:: «ማሚ ስድሴን አስፈቅጂና እሰጥሻለሁ» ብላለች:: «ማሚ ስድሴ ስጪ ካለችኝ ይሰጥሻል» አለችኝ ከቤ*[1]:: ስለዚህ ፍቀጂልኝ:: ደግሞ ብርድ ልብስ የለኝም:: እኔ የምለብሰው ብርድ ልብስ አይደለም:: ለባልቻ ከአሜሪካን የተላከላት ፎጣና የአልጋ ልብስ ነበር:: አሁን በጣም ይበርደኛል:: ብርድልብስ ፈልጊልኝ:: ስለሚበርደኝ መሠለኝ የሚያመኝ:: ደግሞ ማሚ ስድሴ በናትሽ! በምትወጂው አምላክ! ባለ 5 ብር ወይም 3.50 የሚሸጠውን ሠዓት ግዢልኝ! ለማንም ማሚ ስድሴ ነች የገዛችልኝ አልልም:: ማሚ ስድሴ በጣም እወድሻለሁ! በናትሽ አንድ ሁለት ቁጥር የሚቆጥረውን ግዢልኝ! ሲባል የሠማሁት 3.50 ነው:: ሠዓቱ ትንሽ አይደለም፣ ትልቅ ነው:: እኔ ቤተሰቤን ግዙልኝ ከምል፣ አንቺን ብል ይቀለኛል:: የ11*[2] ዓመት ልደቴ ጥቅምት 19 ነበር፣ ሣይከበር አለፈ:: አክስቴ*[3] ተነጋግረን ይከበራል ብላ ነበር:: ይሁን ያልኩሽን ሠዓት አደራ ግዢልኝ! ግን በአደራ አይደለም በልመና ነው::*

*ጌታ አብዝቶ ይባርክሽ!*

*[1] ከቤ (ከበቡሽ) ግቢው ውስጥ በተለይ ፊደልና ቁጥር ያለዩ ህጻናትን የምታስተምር መምህር ናት::

*[2] አመለዘውድ በትክክል ዕድሜዋን ሳታውቀው ትችላለች ግን በዚህ ዓመት የአስራ ስድስት ዓመት ልጅ ነበረች::

*[3] እዚህም ደግሞ አክስቴ ያለችው ወ/ሮ ማርታን ይመስላል::

## -48-

*«እኔ እግዚአብሔር እዚህ ቦታ እናት አድርጎ አስቀምጦኛል ብዬ ነው የማምነው:: ለሁሉም እኩል የልጆቼ ፍቅር አለኝ ብል በእውነት ነው:: የሷ ትንሽ የሚለየው አንድ አትሰማም፣ እንደልጆች እንደልብ መሆን አትችልም፣ በሽታ በጣም ያጠቃታል::»*
*ወ/ሮ ገነት ገብረጻድቅ*

በ1997 ዓ.ም. ሕዳር ወር ወ/ሮ ገነት ገብረጻድቅ የተባለች የአስተዳደር ሠራተኛ በድርጅቱ ተቀጠረች:: ወ/ሮ ገነት ዘወትር ልባዊ ፈገግታ የሚታይበት ክብ የቀይ ዳማ ፊት ያላት፣ አጠር፣ ወፈር ያለች ባለትዳርና የአራት ልጆች እናት ናት:: ድርጅቱ የሚያሳድጋቸውን ልጆች ቀረበቻቸው:: ከልቧ ታገለግላቸው፣ ትመክራቸው፣ የእናትነት ፍቅር ትሰጣቸውም ጀመር:: በሕፃናቱ ለመወደድም ብዙ ጊዜ አልወሰደባትም:: ልጆቹ ከወደዷቸው አፍቃሪዎች ናቸው::

ለየት ባለ ፀባይዋ አመለዘውድ የወ/ሮ ገነትን ትኩረት ለማግኘት ቀዳሚ ሆነች:: ከሁሉም በላይ በየጊዜው መታመሟ፣ የጆሮዋም ችግር ወ/ሮ ገነት ሕሟን በቅርብ ሆና ለመርዳት አነሳሳት:: ታማሚ መሆኗ ብቻም ሳይሆን የአመለዘውድ ብስለት፣ ፍቅርን ለማስጣት ሙሉ ፍቅር የምትሰጥ መሆኗ፣ ስለመጽሐፍ ቅዱስና ስለመንፈሳዊነት ያላት ከሌሎች ልጆች የላቀ ግንዛቤ ወ/ሮ ገነት በልጅቷ እንድትሳብ የሚያስገድዱ ሁኔታዎች ነበሩ::

ወ/ሮ ገነት፣«እግዚአብሔር እዚህ መሥሪያ ቤት ያስገባኝ ለልጆቹ እናት እንድሆናቸው ነው::» ብላ አመነች:: ለልጆቹ የምታደርገው መልካም ነገር ሁሉ እጅግ ያስደስታታል:: ለልጆቹ ጊዜዋንና ጉልበቷን መሠዋት፣ የእናትነት ፍቅሯን አብዝታ መስጠት ያረካታል:: ወደዚህ ህጻናት ማሳደጊ ከመጣች ጀምሮ ትርጉም ያለው ህይወት እየኖረች እንደሆነም እየተሰማት ነው::

አመለዘውድ ታማሚ በመሆኗ፣ እንደሌሎች ልጆች ለመጫወት ግቢው ውስጥ ስለማትሯሯጥ ከሷ ጋር በመነጋገር የበለጠ ጊዜ ታሳልፋለች:: አመለዘውድ ወ/ሮ ገነት ለሷ ያላትን ልባዊ ፍቅር ለመረዳት ረጅም ጊዜ አልወሰደባትም:: እናም እሷም አዲሷን የድርጅቱን ሠራተኛ በጣም ወደደቻት::



Sample output to test PDF Combine only



## -49-

*«ሳትታመም ምትቆየው አንድ ወር ቢሆን ነው:: በየጊዜው ትታመማለች:: ት/ቤት እየታመመችም ትሄዳለች»*
*ጫልቱ ጌታሁን (ሞግዚቷ)*
*«የፈለገ ብታቀርብላት እምቢ ካለች፣ በጣም የሚገርምህ ብታባብላት አትበላም::»*
*ወ/ሮ ገነት ገብረጻድቅ*

አመለዘውድ በ1997 ዓ.ም. የሦስተኛ ክፍል ትምህርቷን በትጋትና በንቃት ለመከታተል ብትሞክርም፣ በየጊዜው ትታመም ነበር:: የህመሟ ዓይነትና ክብደት ይለያይ እንጂ ሳትታመም ያሳለፈችው ወር አልነበረም:: በየጊዜው ሆስፒታል ትመላለስ፣ አንዳንድ ጊዜም ለጥቂት ቀናት ትተኛ ነበር:: ለመማር ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበራት እያመማትም ት/ቤት የምትሄድባቸው ቀናት ጥቂት አልነበሩም:: አንዳንድ ጊዜ ት/ቤት ሄዳ ህመሟ ልትቋቋመው ከምትችለው በላይ ሲሆንባት ከክፍል ትምህርት አቋርጣ ትወጣለች::

*ገንዬ ምነው ጠፋሽ? እኔ ይሄን ሠሞን አይቼሽ አላውቅም:: ደህና ነሽ ወይ? ሁላችሁም ደና ናችሁ? ማሚ ስድሴስ? ደህና ናት ወይ? ካለች ሠላም በይልኝ:: እኔ በጣም ደህና አይደለሁም:: ቅዳሜና እሁድ ሆዴን ያመመኝ፣ ዛሬም አሞኝ ከትምህርት ቤት በ4:00 ወጣሁ:: አፍንጫዬም በጣም ይደማል:: ማታ፣ ማታ አንሶላዬና ትራሴ ተለቅልቆ ነው የሚያድረው:: ይህንን የፃፍኩልሽ ለሠላምታ ነው:: አሁን በጣም ናፍቀሽናል:: ደግሞ ቅዳሜ ለምን ቪዲዮ አላከሽም? ደብሮን ነበር የዋለው:: በይ በሰላም እንገናኝ:: ፓፓዬ ለይድነቃቸው ገዝተሽ ላኪልኝ:: በተረፈ ቻው:: ጫማዬን እንዲያሰፋልኝ ለይርኔ* ንገሪው::*

*ቻው*
*ከአመለዘውድ፣ ለገነት*

*ጥቅስ*
*አምላኬ እንደባለጠግነቱ መጠን የሚያስፈልጋችሁን ይሙላ ላችሁ!*
*ጌታ ይባርካችሁ! ቢሮ ያላችሁትን በሙሉ::*

**የድርጅቱን ሹፌር ይድነቃቸውን ስታቆላምጠው፣ «ይድኔ» ሳይሆን ፣ «ይርኔ» ነበር የምትለው::*

አመለዘውድ ምግብ በእጅጉ ታማርጥ ነበር፡፡ የምግብ ፍላጎት አልነበራትም፡፡ እንዲዘጋጅላት ጠይቃ የቀረበላትን ምግብ እንኳን ትንሽ በልታ ትተውዋለች፡፡

አንድ ቀን አመሻሽ ላይ ወ/ሮ ገነት ልጆቹን ለማየት ወደሚኖሩበት ግቢ ስትመጣ አመለዘውድ እንጀራ በበርበሬ ስትበላ ደረሰች፡፡ ዓይኗን ማመን አልቻለችም፡፡

«እንዴ ለምንድነው እንጀራ በበርበሬ የምትበዪው?» ብላ ጠየቀቻት፡፡

«እንጀራ በበርበሬ ስላሰኘኝ ነው፡፡ ሌላ የምፈልገው ምግብ የለም፡፡» አለቻት አመለዘውድ፡፡

ወ/ሮ ገነት ሞግዚቶቹ አመለዘውድን የበደሏት መሠላትና እጅግ አዘነች፡፡

«የፈለገ ነገር ቢሆን እንዴት እንጀራ በበርበሬ በልተሽ ታድሪያለሽ?» አለች ከፍቅሯ ብዛት ሐዘንና ቁጣ በውስጧ እየተተራመሰ፡፡

ሄዳ ከሞግዚቶቿና ከምግብ አብሳዩዋ ጋር ተፋጠጠች፡፡

«ለምንድነው ለአመለዘውድ ደረቅ እንጀራ በበርበሬ የሰጣችኋት?»

«የአዘጋጀነውን ምግብ አልበላም አለች፡፡ እንጀራ በበርበሬ ስጡኝ ብላን ነው፡፡» አለች ከሞግዚቶቹ አንዷ፡፡

አመለዘውድ ምግብ በጣም ስለምትመርጥ ብዙ ጊዜ ሞግዚቶቹ እንዲሰጧት የምትጠይቀው ምግብ ይጠቅማታል ወይስ አይጠቅማትም ብለው ለማሰብ ጊዜውም፣ ሁኔታውም አይፈቅድላቸውም፡፡ እናም በተቻለ አቅም የጠየቀችውን ሊሰጧት ይሞክራሉ፡፡ የምግብ ምርጫዎቿ አንዳንድ ጊዜ ግራ የሚያጋቡ ናቸው፡፡ ቆሎ፣ ቂጣ፣ ድንች ቅቅል በበርበሬ፣ እንጀራ በበርበሬ፣ ሙዝና ዳቦ እንደምትጠይቀው ሁሉ ወተት፣ *ሥጋ* ጥብስ፣ እንቁላልም እንዲሰጧት ትጠይቃለች፡፡ የጠየቀችው ቢቀርብላትም ትንሽ በልታ፣ «በቃኝ!» ትላለች፡፡ ምግቡ ቢያምራትም በቂ የምግብ ፍላጎት ስለሌላት ብዙ አትበላም፡፡ ስለማትበላ ሠውነቷ ደቃቃ ነው፡፡

ወ/ሮ ገነት ሐዘንና ንዴቷ ከልክ ያለፈ ስለነበር ራሷን መቆጣጠር ስላልቻለች ማልቀስ ጀመረች፡፡

«ስለጠየቀች ተብሎ'ኮ ለልጅቷ የማይጠቅም ምግብ መሰጠት የለበትም፡፡ ታማሚ መሆኗን መቼስ የረሳችሁት አይመስለኝም፡፡» አለች፡፡

«እሷ'ኮ *ሥጋም* ብትል ስናቀርብላት አትበላም፡፡ ትንሽ ቀምሳ ነው የምትተወው፡፡ የጠየቀችውን ምግብ ደግሞ ቆሎም ይሁን ጥብስ ማግኘት ትፈልጋለች፡፡» አለች ሌላዋ ሞግዚት፡፡





ወ/ሮ ገነት ሞግዚቶቹ ያሏት አልተዋጠላትም፡፡

«ቢሆንም እሷ ስጡኝ ብትልም፣ ራቷን እንጀራ በበርበሬ መብላት የለባትም፡፡» ብላ ተቆጣች፡፡

ወደ አመለዘውድ ተመልሳም፣ «አመለዘውድ ካሁን በኋላ ማንኛውንም ምግብ ስትፈልጊ ለኔ ንገሪኝ፤ እኔ እገዛልሻለሁ፡፡ ከቤቴም ቢሆን አመጣልሻለሁ፡፡ የምትፈልጊውን ምግብ ሁሉ ጠይቂኝ እሺ! እንጀራ በበርበሬ አይጠቅምሽም፡፡ ሌላ የሚያወፍርሽ፣ ጤነኛ የሚያደርግሽን ምግብ ነው መብላት ያለብሽ፡፡»

«እሺ ገንዬ!» አለች አመለዘውድ ፈገግ ብላ፡፡ ወ/ሮ ገነት ለእሷ ያላትን ፍቅርና መቆርቆር ይበልጥ በመረዳቷ ደስ ብሏታል፡፡

እሷ ለራሷ ከምትጨነቀው የበለጠ የምትጨነቅላት ሴት እንደሆነች ገባት፡፡ ከዚያች ምሽት በኋላ አመለዘውድ ወ/ሮ ገነትን የምትፈልገውን ምግብ ሁሉ እንዲገዛላት ትጠይቅ ጀመር፡፡ ብዙ ጊዜ፣ «ልቤንና ጨጓራዬን ያቃጥለኛል» ትል ነበር፡፡ ሙዝና ዳቦ ለመብላት ያላትን የተሻለ ፍላጎት ከደብዳቤዋቿና ከአጫጭር መልዕክቶቿ በግልፅ መረዳት ይቻላል፡፡ ከገነት ጋር የእናትና ልጅ ዓይነት ቅርበት ስለነበራቸው፣ እንዲሁም ህመሟ ከባድ ስለነበር የጠየቀችው ምግብ በወቅቱ ካልተገዛላት በደብዳቤዎቿና በአጫጭር መልዕክቶቿ ትቆጣና ትነጫነጭ ነበር፡፡

*ቀን 22/6/97*

*ለውድ እናቴ ገነት፣ እንደምን አለሽ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን፣ በጣም ደና ነኝ፡፡ በቀደም ለታ (ምን) ትፈልጊያለሽ አላልሽኝም ነበር ወይ? ያልኩሽን መቼ ገዛሽልኝ? እረስተሽው ነው? ወይስ ምን ሆነሽ ነው? ለኔ ሙዝ አልገዛሽልኝም፡፡ ዛሬ ሐኪም ውዬ ነው የመጣሁት፡፡ ሙዝና ዳቦ ለይድነቃቸው ዛሬ ማታ ላኪልኝ፡፡ የሚጠበስ ሥጋ ግዢ፡፡ እኛ ጋር ያለው የተፈጨ ነው፤ ስለዚህ ቀይ ወጥ ሲሠራ መብላት አልቻልኩም፡፡ ስለዚህ እባክሽን በተቻለሽ መጠን ያልተፈጨ ሥጋ ላኪልኝ፡፡ ለኔ ብቻ 1 ኪሎ ለ4 ቀን ምናምን ይበቃኛል፡፡ ማታ ግን ሙዝና ዳቦ ላኪልኝ፡፡ በተረፈ እንዳትረሺው፡፡*

*ቻው*

*ቻው*

*ጌታ ይባርካችሁ!*



Sample output to test PDF Combine only

14/7/97

*ለውድ እናቴ ገነት፣*

*እንደምን አለሽልኝ? ጠዋት መጥተሻል ወይ? እኔ እያጠናሁ ስለነበረ አላየኹሽም:: እኔ በጣም ደህና ነኝ:: ኢየሱስ ይመስገንልኝና ገንዬ በደንብ እየፀለይኩ ነው:: እናንተም ፀልዩልን:: ጌታ እንደሚያድነን ተስፋ አለኝ:: ለይድነቃቸው ሙዝና ዳቦ ገዝተሽ ላኪልኝ:: ይድነቃቸው ማታ ሲመጣ ያመጣልኛል:: በተረፈ አንቺን ማሚ ስድሴን ኤደንን* ጌታ ይባርካችሁ! ኤደንንና ስድሴን ሠላም በይልኝ::*

*ጥቅስ*

*የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና::*

*ቻው ቻው*

*ለኤደንና ለማሚ ስድሴ፣ ለገንዬ «ከአንተ ሌላ የለኝም ወዳጅ» የሚለውን መዝሙር ጋብዣችኋለሁ::*

*ኤደን በወቅቱ የድርጅቱ ሂሳብ ሠራተኛ ነበረች::

17/8/97

*የምወድሽ ገነት እንደምን አለሽልኝ?*

*እኔ በጣም ደህና ነኝ::*

*ገነት አርብ ለት ዳቦና ሙዝ ብዬሽ አሁን ለይድነቃቸው እልክልሻለሁ ብለሽኝ አልነበረ? መቼ ላክሽልኝ? ገነት፣ እኔኮ እንጀራው ጨጓራዬን እያቃጠለኝ ምሳዬን አልበላም:: ለቁርስ የተገዛ ከተረፈ ለኡስማን ነው የሚሰጠው:: ስለዚህ ለምን ዝም አልሽኝ? ወይስ እየረሳሽኝ ነው? ለምን አትልኪልኝም? ጫማዬንም አስፈልጊኝ:: ዛሬ ማታ ለይድነቃቸው ሙዝና ዳቦ ላኪልኝ ግን እንዳትረሺው:: በተረፈ ማሚ ስድሴን ሠላም በይልኝ:: «ኡስማን ሙዝ አይፈልግም፤ ሆዱን ያመዋል::» ብላለች አሰፋ*:: እሱም ከዚህ በፊት የገዛሽለትን እምቢ ሲል ለልጆች ሠታቸዋለች:: የሚበላው ምሳ ዳቦ ስለሆነ ለኔ ሙዝና ዳቦ፣ ለሱ ዳቦ ላኪልን:: እንዳትረሺ! ከረሳሽው አልፅፍልሽም:: በተረፈ ጌታ ይባርካችሁ!*

*ቻው ቻው*

*አሰፋ (አመለዘውድ አሌ እያለች ታቆላምጣታለች) ምግብ አብሳይ ነች::

Sample output to test PDF Combine only




አመለዘውድ የፈለገችው ምግብ ይገዛላታል፣ ወይም ይሠራላታል:: ወ/ሮ ገነት እንደተቀጠረች ሰሞን ምግብ ከቤቷም አዘጋጅታ ታመጣላት ነበር:: ግን የጠየቀችውም ቀርቦላት በደንብ አትበላም፤ ትንሽ ቀምሳ ትተወዋለች:: ወ/ሮ ገነት ስትመጣ አመለዘውድ ጠይም ፊቷ በውብ ፈገግታዋ ይደምቃል:: ወዳታለች:: በደብዳቤም ፍቅሯን ያለመታከት ትገልጽላታለች::

*ለውድ እናቴ ገንዬ፣ እንደምን ዋልሽልኝ? ገንዬ፣ አንቺ ለኔ በጣም ደግ ነሽ:: ሲያመኝ ከጉኔ ሳትለይ ከቤትሽ የምፈልገውን በማምጣት አስታመሽ ለዚህ ያበቃሽኝ:: አመሠግናለሁ! እግዚአብሔር ይባርክሽ! የምትፈልጊውን ይስጥሽ! ገንዬ፣ ከምር ነው አንቺ ለኔ እናቴ ነሽ:: ልክ እንደእናቴ ነው የምትጨነቂልኝ:: እኔም ግን ከበፊቱም እወድሻለሁ:: ገንዬ፣ ጠዋት፣ ጠዋት ቁርስ የፈረንጅ ዳቦ ነው፤ እኔ ግን አስጠላኝ:: ስለዚህ አንባሻ ከውጭ ቢገዛልኝስ? አሳ ስለገዛሽልኝ በጣም አመሠግናለሁ:: ቡርትዬ፣ «ነገ እሠራልሻለሁ» ብላኛለች:: ገንዬ፣ ዛሬ ለይድነቃቸው ሽንብራና ሰንዴ ላኪልኝ:: ለምን መሰለሽ? ቆሎ በጣም ስላማረኝ ነው:: ኦቾሎኒ ደግሞ አልወድም:: ስለዚህ ማታ አሌ ትቆላልኛለች:: ሽንብራና ሰንዴ ለይርኔ ላኪልኝ:: ገንዬ በናትሽ እንዳትረሺው! ለይድነቃቸው ላኪልኝ! በተረፈ ጌታ ኢየሱስ በስራሽ ይርዳሽ! ከአንቺ ጋር ይሁን! ትንሽ ስለተሻለኝ ነው የፃፍኩልሽ::*

*ጌታ ይባርክሽ!*

*ከጌታ ጋር ሁኚ!*

*ገንዬ ለዘላለም እወድሻለሁ!*




አንድ ቀን ጥብስ እንዲዘጋጅላት ጠይቃ የጠየቀችው ቀርቦላት ትንሽ በልታ ተወችው:: ወ/ሮ ገነት ብዙም እንዳልበላች ከሞግዚቶቿ ሰማች::

«ዛሬ እንዴት ነሽ?» አለቻት::

«ትንሽ ተሽሎኛል ገንዬ!»

«ምግብ አሁንም አይበላልሽም?»

«አዎ፣ ብዙም አይበላልኝም::»

«አንቺ ግን ለምንድነው የማትበይው አመለዘውድ? ህመሙን መቋቋም የምትችዪው እኮ ስትበዪ ነው::» ወ/ሮ ገነት ከልብ ተጨንቃ ጠየቀቻት::

«ድሮ ከእናቴ ጋር ስኖርም አይበላልኝም:: ትንሽ ነበር የምበላው::»

«ለምን ነበር የማትበይው?»

«እኔ እንጃ» አለች።

«እኔ እንጃ» ትበል እንጂ መልሱን ግን ወዲያው አስታወሰችው። ብዙ ጊዜ ቤታቸው ውስጥ በቂ ምግብ አይኖርም ነበር። ምግብ ሲኖርም በህመሟ ምክንያት የምግብ ፍላጎቷ ዝቅተኛ በመሆኑ አትበላም።

«አሁን ግን መብላት አለብሽ አመለዘውድ። መብላት አለብሽ! አለዚያ ትታመሚያለሽ፤ ቶሎ አትድኚም።»

«እሺ፣ እበላለሁ ገንዬ።» አለቻት። ልትታዘዝ ብትፈልግም የምግብ ፍላጎት ስለሌላት ከጥቂት ጉርሻዎች ያለፈ ለመብላት ትቸገራለች።

በወ/ሮ ገነትና በአመለዘውድ መካከል ያለው ፍቅር እየጠነከረ መጣ። አመለዘውድ የወ/ሮ ገነትን ከፍተኛ ትኩረት ስለምታገኝ፣ ወ/ሮ ገነትን የራሷ ብቻ አድርጋ እስከማሰብ ደርሳ ነበር። ፍቅሯን ሌሎች ልጆች እንዲሻሙባት አትፈልግም። ለሷ የምትሰጠውን ትኩረት ለሌሎች ልጆች ስትሰጥ ካየች፣ ብዙዎችን የሚያስደምም ብስለቷ ገደል ይገባል። ድንገት ቀናተኛና ራስ ወዳድ ሕፃን ትሆናለች።

አንድ ቀን ወ/ሮ ገነት እታገኝ ለምትባለው የአመለዘውድ የቅርብ ጓደኛ የበዛ ፍቅር ስትሰጣት አይታ ቀናች። ወ/ሮ ገነት ከሄደች በኋላ አጭር ደብዳቤ ፃፈች፤ «ለእታገኝ ታዳያለሽ» የሚል መልዕክት የያዘ ነበር። ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች የሚኖሩበት እጓለማውታን ውስጥ ሁሉም ህጻናት ፍቅርና ትኩረት የተጠሙ ናቸው። ወ/ሮ ገነት እንደሌሎቹ የድርጅቱ ሠራተኞች በተቻለ መጠን ለማንም ላለማዳላት ትጠነቀቃለች። ለአመለዘውድ የበለጠ ትኩረት የምትሰጠው ግን «ታማሚ ስለሆነች የበለጠ እንክብካቤ ያስፈልጋታል» ብላ ስለምታምን ነው። አመለዘውድ፣ «ታዳያለሽ» ስትላት በጣም ተበሳጨች። የሚከተለውን ደብዳቤ ለአመለዘውድ ፃፈችላት።

*አመለዘውድ፣ እኔ ለአንቺ እንደማደርግልሽ ለሌላው አድርጌ አላውቅም። ለምሳሌ መፅሐፍና ከፍያ . . . ወዘተ የጠየቅሽኝን ስሰጥሽ፣ ሌላው፣ «ለሷ ታደያለሽ» ሲሉኝ፣ «አያገባችሁም» እያልኩ ብዙ ጊዜ እጣላለሁ። ግን አንቺም ዞረሽ፣ «ለእታገኝ ታደያለሽ» አልሽ። ግን ከዛሬ ወዲህ ሁላችሁም ለኔ እኩል ናችሁ። ስለዚህ ለይቼ ለማንም ምንም አልሠጥም። ድሮም ቢሆን ላንቺ ስሰጥ አዳልቼ አይደለም፤ ልጆቹ እንደሚሉት። ለኔ ሁላችሁም እኩል ናችሁ። ግን አንቺ ጥሩ ልጅ ነሽ። እንደገና ጥሩ ጭንቅላት ስላለሽና ስለምትቀርቢኝ በጌታ እንደ እህቴ አይቼሽ ነበር። ግን እያደር ጥሩ ነገር አላይብሽም። ለዚህ እንደጠበቅኩት አልሆንሽም። ለሷ እንኳን ብሠጣት እንዲህ መናገር ካንቺ አልጠብቅም። ለምን? መፅሐፍ ቅዱስ፣ «ባልንጀራህን*



Sample output to test PDF Combine only



*እንደራስህ ውደድ» ይላል። ስለዚህ እታገኝ እህትሽ ናት። ለሷ መልካም ነገር ሲደርግ አንቺን ልክ ላንቺ እንደተደረገ ሊያስደስትሽ ይገባ ነበር፤ እንደ ክርስቶስ ልጅ። አንቺ ግን በቁጣ ተናገርሽ። በጣም የማዝነው እዚህ ግቢ ለአንዱ እንደ እድል ሆኖ ጥሩ ነገር ከደረሰው፣ ሌላው ይናደዳል፤ ልክ ለጠላቱ እንደተደረገለት። ግን እንደወንድምና እህት እየተያያችሁ ላንዱ በሚደረገው ጥሩ ነገር ሌላው ሊደሰት ይገባል።*

*እህትሽ ገነት*

አመለዘውድ እንኳንስ እጅግ የምትወዳትን ገነትን፣ ሌሎች ተንከባካቢዎች ልጆችንና ብዙም የማይቀርቧትን ማስከፋትና ተጣልታ መቆየት ስለማይሆንላት ጊዜ ሳትፈጅ ይቅርታ ጠይቃት የወ/ሮ ገነትን ፍቅርና እንክብካቤ ማግኘት ቀጠለች።

አንዳንድ ቀን አመለዘውድ ህመሟ እጅግ ሲያሰቃያት፣ ሞትን ትመኝ ነበር። የሚደንቀው ግን ፈጣሪን አንድም ቦታ ከልቧ ስታማርር አለመገኘቷ ነው። በእግዚአብሔር ተስፋ ታደርግ ነበር። ከበሽታዋ እንደሚያድናት፣ ያ የማይሆን ከሆነ ደግሞ ከሞት በኋላ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ከሚኖሩት መካከል አንዷ እንደምትሆን ጽኑ እምነት ነበራት።

*ይድረስ በጣም ለምወድሽ ገንዬ፣ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ የጨጓራዬ ማቃጠል መቼ እንደሚለቀኝ ይጨንቀኛል። ገንዬ፣ ልቤን በጣም ያቃጥለኛል። በቀደምም አሞኝ ሲስተር ጤና ፓፓዬ 3 ብር ገዝታልኛለች። ብሩን መልሽላት። እንቁላል ስላለ ዳቦና ሙዝ ግዢልኝ። ልቤን የሚያቀዘቅዝልኝ ነገር ካለ ካገኘሽ ግዢልኝ። ጭማቂ ማንጉ አልወድም። አብወለድ ብስኩት ግዢልኝ። እንጀራ በጭራሽ አላስበላ ብሎኛል። ያቃጥለኛል። ገንዬ ስለአስቸገርኩሽ ይቅርታ። ጌታ ይባርክሽ!*

*ገንዬ፣ አሁንስ ሞት ይሻለኛል። እንዴት እንደሚያቃጥለኝ እኔና ልቤ እናውቀዋለን። ገንዬ፣ ምሣ እንጀራ ከበላሁ በኋላ አልታገሠኝም፤ እንዲሁ ያቃጥለኛል። ስለዚህም ምሣ እንጀራ መብላት አልቻልኩም። ገንዬ፣ «በቤቴ ለዘላለም ትኖራላችሁ» ይላል ኢየሱስ። ከሚያቃጥለኝ ቢወስደኝ ይሻለኛል። የፃፍኩልሽ ሆዳቤን ነው። እንዲህ መቃጠል ሠልችቶኛል።*

*ቻው ቻው*

ወ/ሮ ገነት በተለያዩ ቀናት በዕድሜ ከፍ ያሉት ልጆች ግቢ ስትሄድ አመለዘውድ ታማ ተኝታ ታገኛታለች::

አንድ ቀን፣ «አሁንስ በቃኝ! ጌታ ኢየሱስ'ኮ ቢወስደኝ ጤነኛና ደስተኛ ሆኜ እንደምኖር አውቃለሁ::» አለቻት::

ወ/ሮ ገነት ደነገጠች::

«አይዞሽ አመለዘውድ! ስለመሞትማ አታስቢ:: አንቺ ጥሩ ሰው ስለሆንሽ እግዚአብሔር ይምርሻል::» ብላ አፅናናቻት::

ሁልጊዜ ነው እንዲህ የምታጽናናት:: ከልቧ ነበር እንዲህ የምትላት:: አመለዘውድ ለእግዚአብሔር ካላት ፍቅር አንፃር፣ ሀቀኛ ስለሆነች፣ ሰውን ለመጉዳት ወይም ለማስከፋት ብላ ምንም ክፉ ነገር ስለማታደርግ፣ ከተንኮል የራቀች ስለሆነች . . . ወ/ሮ ገነት እግዚአብሔር ይምራታል የሚል የፀና እምነት ነበራት::



Sample output to test PDF Combine only



## -50-

*«ወደዚያ የሚመጡ ብዙ እንግዶች በሷ ይማረኩ ነበር::»*

*ከብነሽ ጫላ*

*«ጨኸት አትወድም::»*

*በህጻናት ማሳደጊያው የሚኖሩ ልጆች*

ጥቂት በጎ ፈቃደኞች ወደ ድርጅቱ እየመጡ ከልጆቹ ጋር የተወሰነ ጊዜ ያሳልፋሉ:: ልጆቹን ያጫውቷቸዋል፣ ፍቅር ይሰጧቸዋል፣ መዝሙር፣ ፊደልና ቁጥር . . . ወዘተ ያስተምሯቸዋል:: ብዙዎቹ ወደ ኢትዮጵያ ለአጭር ጊዜ ጉብኝት ወይም ለሥራ የመጡ የውጪ ዜጎች ናቸው::ወደ ህጻናት ማሳደጊያው የሚመጡ በርካታ በጎ ፈቃደኞችና እንግዶች በአመለዘውድ ይማረካሉ:: ግቢያቸውን የምታስጎበኛቸው እሷ ነበረች:: እውነተኛ ፍቅርም ታሳያቸዋለች:: እንደሌሎች ሕፃናት ለጨዋታ ስሜት ስለሌላት፣ ከትልልቅ ሰዎች ጋር ቁጭ ብላ ቁም ነገር ማውራት ከሁሉም በላይ ያስደስታታል:: እናም ለሰዎቹ ሙሉ ትኩረቷን ትሰጣለች:: ጥሩ ፈገግታ ታሳያቸዋለች:: ቁጭ ብለው እንዲያዋሯት ሁኔታዎችን ታመቻችላቸዋለች:: በዚህ ምክንያት ብዙዎቹ ይወዷታል:: አንዳንዶቹ የውጪ ዜጎች ወደ አገራቸውም ከተመለሱ በኋላ ደብዳቤ ይፅፉላታል::

ከእነዚህ በጎ ፈቃደኞች አንዷ ሲንዲ ማክኪኒ የተባሉ አሜሪካዊ ሴት ናቸው:: የመስማት ችግር ስላለባቸው በሁለቱም ጆሯቸው ላይ የሚሰካ ማዳመጫ (ሂሪንግ ኤይድ) ይጠቀማሉ:: የጤነኛ ጆሮን ያህል ባይሆንም በማዳመጫው፣ ከሰዎች ጋር ያለብዙ ችግር ተግባብቶ መኖር ይቻላል:: አመለዘውድ ማዳመጫው ቢኖራት ለመስማት እንደምትችል ሲንዲ ለስድሴ ነገሯት:: ስድሴ አመለዘውድ ማዳመጫው እንዲኖራት ለማድረግ ወሰነች:: ሲንዲ ወደ አሜሪካ ከመመለሳቸው በፊት የአመለዘውድ ጆሮ ቅርጽ (ኢር ሞልድ) ከተዘጋጀ ማዳመጫውን አሜሪካ ከሚገኝ የማዳመጫ ማምረቻ ፋብሪካ ለማሰራትና ለመላክ ዝግጁ እንደሆኑ ለስድሴ ገለፁላት::

አዲስ አበባ ውስጥ ወዳለ አንድ ክሊኒክ ከተደረገ ብዙ ምልልስ በኋላ የአመለዘውድ ጆሮ ቅርጽ (ኢር ሞልድ) ተዘጋጀ:: ሞልዱ በጥንቃቄ በጆሮዋ ልክ ካልተሰራና በሞልዱ ቅርጽ መሠረት የሚሰራው ማዳመጫ ጆሮዋ ውስጥ ልክክ ብሎ ካልገጠመ፣ በጆሮዋ ውስጥ ስለሚተሻሽና ስለሚንቀሳቀስ የሚረብሽ ድምጽ ይፈጥራል:: ሲንዲና ስድሴ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰራው ሞልድ መሰረት ማዳመጫውን የሚያዘጋጀው አሜሪካ ውስጥ ያለ ድርጅት እንዲሰራላት ለማድረግ በርካታ የኢ-ሜይል መልዕክቶች መለዋወጥ ነበረባቸው::

ሲንዲ አመለዘውድን ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኙዋት በጥቅምት ወር 1997 ዓ.ም. ነበር:: ማዳመጫው ከሚመረትበት ካምፓኒ በሲንዲ ጥረት በነጻ የተገኘ

ውና ከአሜሪካ ተልኮ በአመለዘውድ እጅ የገባው ግን ከስድስት ወራት በኋላ በሚያዚያ 1997 ዓ.ም. ነው።

አመለዘውድ ትምህርቷን በተገቢ ሁኔታ እንዳትከታተል ዋና እንቅፋት የሆነው የጆሮዋ የመስማት አቅም በጣም መቀነስ ነበር። ክፍል ውስጥ ትምህርቷን ለመከታተል ማዳመጫው ጠቀማት። በህጻናት ማሳደጊያው ውስጥ በደንብ ለመከታተል የምትፈልገው ወሬ፣ ጨዋታ ወይም ውይይት ካለም ጆሮዋ ላይ ትሰካዋለች። ማዳመጫውን ት/ቤት ለአንድ ወር ብቻ እንደተጠቀመችበት ግንቦት 1997 ዓ.ም. ላይ በጠና ስለታመመች ከት/ቤት ለመቅረት ተገደደች።

የጆሮዋ ችግር ቢባባስም፣ ማዳመጫውን ሳትጠቀም የሞግዚቶቿን የአፍ እንቅስቃሴ በማየት የሚሉት ይገባታል። ከሌሎች ሕፃናትም ጋር ከሞላ ጎደል ትግባባለች። በየጊዜው ስለምትታመም፣ ብዙ ጊዜ ልጆቹ በጋራ እንደሳሎን የሚጠቀሙበት ክፍል ረጅሙ ሶፋ ላይ ጋደም ብላ ቀኑን ታሳልፋለች። ታዲያ ከእጇ መጽሐፍ ቅዱስና ደብተሮች አይጠፉም።

ልጆቹ ውር፣ ውር ሲሉና ሲላፉ ስታይ ትበሳጫለች። በተለይ ቴሌቪዥን እያየች ከሆነ ቁጣዋ ኃያል ይሆናል።

«እናንተ አታርፉም!» ብላ ትጮህባቸዋለች። ልጆች ስለሆኑ ቁጣዋን ወዲያው አይሰሙም። «እረፉ እኮ ነው የምለው! ለምንድነው የምትንጫጬት!»

ማዳመጫዋን ጆሮዋ ላይ ካላደረገች የልጆቹ ድምጽ ስለማይሰማት በጣም እንደሚጮኹና አካባቢውን እየረበሹ እንደሆነ ታስባለች። አንዳንዴ ሲሳሳቁ ስታይ፣ እሷ ላይ የሚያሾፉ ስለሚመስላት ብስጭቷ ከቁጣ ያለፈ ይሆናል። የጤናዋ ሁኔታ ከፈቀደላት ተነስታ ትማታለች።

«ኃይለኛ ናት» ይሏታል ሞግዚቶቿ። «ጥፋት አታልፍም።»

—





## -51-

*«አንዳንዴ ራሷን የሾመች አለቃ ትሆናለች።»*

*ስድሴ ቡሊ*

*«'ልብስ ቀይሪ ስትለኝ'! እኔ ደግሞ 'አልቀይርም' ስላት፣ ብረት ወርውራ ከግድግዳው ጋር አጋጭታ መታችኝ። . . . 'እኔ አልመታሁሽም' አለች። . . . ሌላ ቀን ይቅርታ ብላኛለች።»*

*ጽጌረዳ*

አመለዘውድ አስፈላጊ ሲሆን ማንም ያልሾማት አለቃ ትሆናለች። በማሳደጊያው ውስጥ ካሉት ልጆች በዕድሜም፣ በብስለትም የምትበልጠው እሷ ስለሆነች በድርጅቱ ሠራተኞችም፣ ከውጪ በሚመጡ እንግዶችም የተከበረችና የተወደደች ናት። ምናልባት ይህ ሁኔታ ይመስላል ለራሷ ከፍተኛ ግምት እንዲኖራት ያደረጋት። ከአባቷ ሞት በኋላ የቤተሰብ ኃላፊነት መሸከሟና ቤተሰብ መምራቷ ያመጣው ተጽዕኖም ሊሆን ይችላል።

የግቢው የጥበቃ ሠራተኞች እነአቶ ካሱ ልጆቹን ሰብስበው አብረዋቸው ይፀልያሉ። የሚያውቁትን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለልጆቹ ይነግሯቸዋል። እነካሱ ከወንድና ከሴት አንዳንድ የፀሎት መሪ ሲመርጡ፣ አዘውትረው አመለዘውድን ስለሚመርጡ፣ ልጆቹን የምታሰባስበውና የፀሎት ስነሥርዓቱን የምትመራው እሷ ነበረች።

በአመለዘውድ የአለቅነት ባህሪ አንዳንድ ልጆች ይናደዳሉ። ጽጌረዳ አመለዘውድ እንደአለቃ እንድትሆንባቸው ከማይፈልጉ ህጻናት አንዷ ናት። አመለዘውድ ጽጌረዳን በዕድሜ በአራት ወይም በአምስት ዓመት ትበልጣታለች።

አንድ ቀን የግቢው በር ተንኳኩቶ የጥበቃ ሠራተኛው ከፈተ። ከግቢው ወጣ ብሎም ከመጣው እንግዳ ጋር ሲያወራ፣ ጽጌረዳ ማን እንደመጣ ለማየት ጓጉታ ከግቢው ወጣች። የጽጌረዳን መውጣት አመለዘውድ ከርቀት ትከታተል ነበር። የጥበቃ ሠራተኛው እንግዳውን ሸኝቶ ከጽጌረዳ ጋር እንደገቡ፣

«ጽጌረዳ! ነይ!» ብላ አመለዘውድ በቁጣ ጠራቻት።

ጽጌረዳ የአመለዘውድን ቁጣ ሳታስተውል ወደ እሷው ሄደች።

«ምነው?»

«ለምንድነው የወጣሽው?»

«ማን እንደመጣ ለማየት? »

«ትምህርት ቤት ስትሄጂ ከምትወጪው በስተቀር እንዳትወጪ አልተባልሽም?»



Sample output to test PDF Combine only

«ብወጣ ባልወጣ አንቺ ምን አገባሽ?»
«ሁለተኛ እንዳትወጪ! ሂጂ ከዚህ!» ብላ ትከሻዋ ላይ መታቻት::

ጽጌረዳ ብልጭ ብሎባት ድንገት የአመለዘውድን ልብስ አንገቷ አካባቢ ጨምድዳ ያዘች:: ተያያዙ:: መደባደብ ጀመሩ:: ገላጋይ እስኪመጣ በጡጫም፣ በጥፍርም፣ በጥፊም ተሞካከሩ:: ከተገላገሉ በኋላ የጽጌረዳ አንድ የጆሮ ጌጥ ጠፋ::

ሌላ ቀን ደግሞ ጽጌረዳና አመለዘውድ ከዋናው ቤት በረንዳ አጠገብ ቆመዋል:: ሁለት ሞግዚቶች እዚያው ከበረንዳው በታች አጠገባቸው ቁጭ ብለው የሁለት ሴቶች ልጆች ጸጉር ሽሩባ ይሰራሉ::

«ጽጌረዳ ይህን ቀሚስ ቀይሪ! አያምርብሽም::» አለቻት አመለዘውድ::
«እምቢ! አልቀይርም!» አለች ጽጌረዳ ትከሻዋን በእምቢታ ሰቅላ እያወረደች::
«አያምርብሽም አልኩሽ'ኮ»
ትንሽ ተጨቃጨቁ፣ ተሰዳደቡም::
ጽጌረዳ፣ «አልቀይርም! የፈለግኩትን ብለብስ አንቺ ምን አገባሽ?» ብላ በእምቢታዋ ፀናች::

አመለዘውድ በጣም ተናደደች:: ጎንበስ ስትል አጠገቧ በቅርቡ የተሰበረ የአንድ ወንበር የብረት እግር አገኘች:: ምን እንደሆነ፣ ምን ዓይነት ጉዳት ሊያደርስ እንደሚችል ለማመዛዘን ጊዜ አልነበራትም:: አንስታ ወደ ጽጌረዳ ወረወረችው:: በንዴት የወረወረችው ውስጠ ክፍት ብረት ከግድግዳ ጋር ተጋጭቶ የጽጌረዳ አናት ላይ አረፈ::

ጽጌረዳ፣ «ወይኔ!» ብላ ራሷን ስትይዘው ፈሳሽ ነገር እጇ ላይ ተሰማት:: ደምታለች!

ደሙን ስታይ ጮክ ብላ ማልቀስ ጀመረች:: ሞግዚቶቹ ቀና ብለው ሲያዩ ጽጌረዳ እየደማች ነው:: ደንግጠው ከተቀመጡበት ተነሱ::

የአመለዘውድ ንዴት ወደ ድንጋጤ ለመቀየር አፍታም አልፈጀ::

«ምነው አመለዘውድ? ትልቅ ሰው አልነበርሽ እንዴ?» ሞግዚቶቹ ጽጌረዳን ከበው አመለዘውድ ላይ አፈጠጡባት::

አመለዘውድ ምንም ሳትናገር ወደ መኝታ ክፍሏ ገባች::





ጽጌረዳ መፈንከቷን ሲሰሙ ስድሴና ሌሎች የቢሮ ሠራተኞች ተቆጡ:: አመለዘውድ አስተዋይና ከሁሉም ልጆች በተሻለ ሁኔታ ማመዛዘን የምትችል እንደሆነች በሁሉም ዘንድ የታወቀ በመሆኑ፣ ጥፋቷን «ልጅ ናት» ብለው አላለፉትም::

ቁጣና ተግሣፅ በቃልም፣ አንዳንዴ በቃል የሚነገራትን ደግሞ በጆሮዋ ችግር ምክንያት በደንብ ስለማትረዳ፣ በደብዳቤም ደረሳት::

*አመለዘውድ!*

*ዛሬ ባረግሽው ተግባር ሁላችንም በጣም አዝነንብሻል:: ልጆች ሲያጠፉ ከመምታት ይልቅ በጊዜው ላለ ታላቅ ሰው መናገር መልካም አማራጭ ነው:: አንቺ ደግሞ ሁልጊዜ ስትቆጪና ስትናደጂ ለጤናሽ ጥሩ አይደለም:: እልኸኛነት ለጤና ጥሩ አይደለም:: የሱስም አይወደውም፤ «በቁጣችሁ ፀሐይ አይግባበት» ይላልና::*

*ስለዚህ ከዛሬ ጀምሮ ማንንም ልጅ እንዳትመቺ ነው ይህን የፃፍኩት:: ዛሬ አሁን ጽጌረዳ ስትደማ በጤናዋ ላይ መሰናከል ሊፈጥርባት ይችላል:: ይህን ደግሞ ካንቺ አንጠብቅም:: ሰው ሲማታ በስሜቱ ደስ ይለው ይሆናል፤ ነገር ግን እግዚአብሔርን ያሳዝናል:: ለወደፊቱ እንዲህ አይነት ነገር እንዳትደግሚ:: ከደገምሽ ግን መልካም እንዳልሆነ አስገነዝብሻለሁ::*

*እናትሽ ማሚ ስድሴ*

አመለዘውድም መልስ ፃፈች::

**የደብዳቤው የመጀመሪያ ገጽ ጠፍቷል::*

*. . . ሌላው ቢሰድቡት ዝም ይላል ወይ? እነ ዘሪሁን ቢሰድቧቸው ይናገራሉ? ሁሌ የሚማቱት ተናግረው ነው? «አመለዘውድ ልጆቹን ትመታለች» ሲሉሽ ታምኛለሽ:: «ትልልቆቹ ሰደቡን፣ መቱን» ቢሉሽ አታምኚም:: ገነት እራሷ፣ «ይፈሩሻል፤ አሰቃየሻቸው::» የምትለኝ ለምንድን ነው? ይሄን ያህል ሰይጣን አይደለሁም:: ነገር ግን አንቺ መታችኚለች ብለሽ ብትታዘቢኝ ምንም አይደለም:: እኔ ሰው የመምታት ስሜት የለኝም:: ስለዚህ ጽጌረዳን ከመሬት ተነስቼ አልመታኋትም:: «ጥሩ ልብስ ልበሽ» ስላት፣ «እምቢ» ብላ ስትወጣ ግርግዳ ራሷን መታት:: ብረት ወርውሬያለሁ፤ እንጂ አልመታትም:: የሰው ወሬ ብታምን ምንም አይመስለኝም::*



Sample output to test PDF Combine only

*እነሰላሙን እነበለጡን እንደዛ ቢሉ ዝም ይሏቸዋል:: እነሱ ይወዷቸዋል:: እኔ ግን ጠላታቸው ነኝ:: ይሁን እናትና አባቴ ቢኖሩ እዚህ አልገኝም:: አሁንም ቢሆን እግዚአብሔርና ወንድሜ አለኝ:: ስሜ ከሚጠፋ መሄድ ይሻለኛል:: ወንዶች ሲቀጠቅጡአቸው አንቺ አታምኚም:: የኔን ነገር ግን አባብለው ነገሩሽና አመንሽ:: በመጀመሪያ፣ «ሥነ ሥርአት» ብዬአታለሁ:: እምቢ ብላ ወጣች::*

በደብዳቤ ጥፋቷን ለመቀበል ብታመነታም፣ አመለዘውድ ጽጌረዳን ይቅርታ ጠየቀቻት::

ቀረብ ብለው የሚያውቋት አመለዘውድ ከአዋቂ ባህርይዋ ጎን ለጎን አንዳንድ ንፁህ የልጅ ባህርይዎች እንደነበሯት ያስተውሉ ነበር:: አንዳንዴ አሻንጉሊት ለልጆቹ መጥቶላቸው ሲታደል፣ እሷ ትልቅ ናት ተብሎ ሳይሰጣት ከቀረ ታኮርፋለች::

የሚከተለው እቤቱታም፣ ማስጠንቀቂያም የሚመስል ደብዳቤዋ ልጅነቷን ያንፀባርቃል:: በተለያዩ ሰዎች ነገረኛ መባሏ ያስመረራት ይመስላል:: ሁልጊዜ አጻጻፏ እንደምትናገረው ቢሆንም ይህ ደብዳቤዋ ከሌሎቹ በተለየ ሁኔታ የአመለዘውድን ድምጽ የመስማት ያህል ፍፁም የንግግር አማርኛ ነው::

*ማሚ ስድሴ፣*

*ይኼ ጥቁሩ ኢሳያስ የተሠጠኝን ሸራ ጫማ አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ስንመጣ ጭቃ ነክቶን፣ አይናለም ጫማችሁን አውልቁ ስትለን ፣ አውልቄ ስገባ፣ ጥቁሩ ኢሳያስ ወስዶብኝ ሲያረገው፣ ሲያለፋው ቀደደው:: አሁን ሸራ የለኝም:: ስለዚህ አላውቅም ሸራዬን ያምጣ! አሁን ብርድ ስለሆነ ሸራዬን አዲስ አድርጐ ባያመጣ እጣላለሁ:: ነገር ሳልፈልግ ሸራዬን ያምጣ! ገና እንደተሰጠኝ በአዲስነቱ ነው የወሰደብኝ:: ስፈልገው፣ ስፈልገው ሳለቅስ፣ ሳለቅስ ነበር:: ከዛን ገኒ ስትሠጠኝ ኤ.ጂ. የፃፈችበትን የተቀደደው ጫማ ኢሳያስ አድርጐት አየሁት:: ስጠይቀው፣ እንዳልሠማ ሰው በኔ ጆሮ እያሾፈ «አይሠማኝም» ይለኛል:: እኔ በምን ነገር ፈለገችኝ እንዳይባል መጀመሪያ ለአንቺ ልንገርሽ ብዬ ነው::*

*በተረፈ*

*ቻው*

*ቻው*

አመለዘውድ በሌሎች ደብዳቤዎቿ ጥፋቶቿን ለማስተባበል ብትሞክርም በ1997 ዓ.ም. የትንሳኤ በዓል ዕለት ለወ/ሮ ገነት በጻፈችው ደብዳቤ ግን



Sample output to test PDF Combine only



ድክመቷን እያመነች፣ ፀባዩዋን ለማሻሻልና ታዛዥ ለመሆን ፍላጎት እንዳላት ገልጻለች::

**እወድሻለሁ**

*(ከደብዳቤው እናት ጎላ አድርጋ ነው የጻፈችው)*

*ይድረስ ለምወድሽ ገንዬ፣ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ በጣም ደህና ነኝ:: ለምን ጠፋሽ? እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው በሰላም አደረሰሽ! ገንዬ፣ እኔማ እንደ ማሚ ስድሴ ትመጫለሽ ብዬ ፖስት ካርድ አዘጋጅቼ ነበር፣ ግን አልመጣሽም:: የጠዋት ተማሪ ስለሆንኩ በጠዋቱ ከመጣሽ አንገኛኝም፤ ስለዚህ በይድነቃቸው እልክልሻለሁ ብዬ አሰብኩኝ::*

*አሁን ጤንነቴ ጥሩ ነው:: አሞኝም አያውቅም:: ሁሌ አንቺ እንደነገርሽኝ እፀልያለሁ:: ፀባዬንም አሻሽላለሁ:: ታዛዥ መሆን ፈልጌያለሁ፣ ለሁሉም እሺ ለማለት:: ሳልጣላ እፀልያለሁ:: ካልተጣላሁ፣ ካልተሳደብኩ ኢየሱስ ይሰማኛል አይደል? ስለዚህ ጥሩ ልጅ እሆናለሁኝ:: እሺ፣ በተረፈ አንቺም ፀልይልኝ:: በተረፈም ፀሎት ቤት ውሰጅኝ:: እንወድሻለን!*

*ጌታ ይባርክሽ!*
*ፖስት ካርድ ልኬልሻለሁ::*[1]*
*ቻው! ቻው!*
*25-8-97*[2]*

*[1] ራሷ ስዕል ስላ የሠራችውን ፖስት ካርድ ነበር ለወ/ሮ ገነት የላከችላት::*
*[2] ከደብዳቤው ግርጌ ከማይነበብ ፊርማ በታች የተጻፈ ቀን::*

የአመለዘውድ ቁጣና ኃይለኝነት እንዲሁም አለቃ የመሆን ስሜት ሁልጊዜ፣ «እኔ ከእናንተ የበለጠ ስለማውቅ፣ እኔን ስሙኝ» ከሚል አመለካከት የመነጨ አይደለም:: አንዳንድ ጊዜ ደስ የማይል ቀልድና ተንኮል የሚያዘወትሩ ልጆችን አጥብቃ ትቃወማለች:: ጥፋት ከሚያጠፉና ከሚያናድዷት ልጆች ጋር እንኳን ተጣልቶ መቆየትና መኮራረፍ ግን አትፈልግም:: እሷ እውነትና ትክክል የምትለው እንዲሆን ከመፈለግ በስተቀር፣ ልጆችን የመጥላትና ከእነርሱ ጋር የመኮራረፍ ፍላጎት አልነበራትም::

*ይድረስ በጣም ለምወድሽ እናቴ ስድሴ፣ ለጤናሽ እንደምን አለሽ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ።*

*ማሚ ስድሴ እኔ በጣም እወድሻለሁ! ከዚህ በመቀጠል የምገልፅልሽ ነገር ቢኖር ይህን ይመስላል። ከዚህ በፊት እኔና ሰናይት በፍቅር እንኖር ነበር። በጣምም እንረዳዳ ነበር። ከዛን አንድ ቀን ምሣ ስንመገብ እያለን፣ ሰናይት ለማመስገን እንፀልይ ሳይባል በፊት በእጅዋ ላይ ምራቅ ተፍታ፣ ደረቅ ብጣቂ እንጀራ በምራቋ እድቦልቡላ፣ «እንፀልይ» ሲባል ሁሉም ዓይኑን ሲጨፍን፣ በምራቅ አጨማልቃ 'ምን ታደርገዋለች? ትጨምርብናለች?' ብዬ ዓይኔን ሣልጨፍን፣ ዓይኔን እጄን ከልዬ ሣያት፣ በቀለች ላይና ሰሎሜ ላይ ጨመረችባቸው። ከዛን ፀሎት ሲያበቃ በቀለች፣ «ማን ነው የጨመረብኝ?» ብላ አፈጠጠችብን። እኔ፣ «ሰናይት ለምን እንደዚህ ታደርጊያለች?» ስላት ተቆጣችና፣ አልሠማኋትም የሆነ ነገር አለችኝ። ዝም አልኩኝ። «የበቀለችን በምራቄ አላጨማለኩም። የሰሎሜን ነው።» አለችኝ። «የበቀለች ቢሆን፣ የሰሎሜ ቢሆን ነውር ነው። እንኳን በምራቅ፣ የተገመጠ እንኳን ካልፈለኩ አይሠጥም። አንቺ ግን ሲፀልዩ፣ ዓይናቸውን ሲጨፍኑ ነው የጣልሽባቸው።» አልኳት። ከዛን ተረሣ ብዬ ዝም አልኩኝ። ለካ እሷ አኩርፋለች። እቃዋን ለብቻዋ አድርጋ የኔንም መለሠችልኝ። አሁንም በሌላ ቀን ሽሮ ነበር ምሣ የበላነው። ከአፏ ውስጥ ሽንኩርት አውጥታ በቀለች ጉንበስ ብላ ስለምትበላ ሳታያት ሠሀኗ ላይ ጨመረችባት። «ሰናይት ያምሻል?» አልኳት። ስለአኮረፈችኝ ዝም አለችኝ። እኔ ግን፣ «በቀለች! ይህን ነገር አንሺና ጣይው!» አልኳት። እሷም ጣለችው። በዚህ በጣም ተጣላችኝ። እኔ ግን በመሀከላችን ድንገት የሚያመው ቢኖር ጥሩ አይደለም ብዬ ነው። አታናግረኝም። ለልጆቹ «የየራሳችሁን ነገር ማድረግ አለባችሁ» ብያቸዋለሁ። በዚህ ተቀይማኛለች። በሚቻልሽ መጠን የበደልኳትን ጠይቂያት፤ በማለት በትህትና እጠይቃለሁ።*

*ጌታ ይባርክሽ!*







# -52-

*«ለእያንዳንዱ ሰው የምትወስደው የራሷ ግምት አላት።*
*ማንም ሰው እንዲጎዳባት አትፈልግም።»*
*አጸዱ ውብሸት (ምግዚቷ)*
*«ለገነት፣ ቢሮ ይነበብ! በቶሎ! በደንብ! ችግር አለበት።*
*እሺ፣ ገንዬ፣ ለዚህ ነው።»*
*አመለዘውድ*

አመለዘውድ በአብዛኛው የአዋቂ ባህርይ ያላት መሆኗ ከአዋቂዎች ጋር በቀላሉ ለመግባባትና ለመቀራረብ አስችሏታል። ይህ የአዋቂ ባህርይዋ ችግርም አምጥቶባታል። አዋቂዎች ስታጠፋ ወይም በሆነ ምክንያት ስታስከፋቸው ሊያመሩባት ይችላሉ። እንደሌሎቹ ልጆች፣ «አይ የልጅ ነገር!» ብለው በቀላሉ አያልፏትም። በአንድ ወቅት አንዲት ምግብ አብሳይ አኩርፋት፣ አመለዘውድ እጅግ ተጨንቃ ገነት እንድታማልዳት ደብዳቤ ጽፋ ነበር።

*(ደብዳቤው የተጻፈበት የተጣጠፈ ወረቀት አንድ እጥፋት ላይ ይህ መልዕክት ይነበባል።)*

***ለገነት፣ ቢሮ ይነበብ!***
***በቶሎ! በደንብ!***
***ችግር አለበት።***
***እሺ፣ ገንዬ ለዚህ ነው።***

4-10-97 E.C

*ለውድ እናቴ ገንዬ፣ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ?*

*እኔ በጣም ደህና ነኝ። ገንዬ ከዚህ በፊት አንቺ፣ «ለአስማንና ለናሆም እንቁላል ሲሰጣቸው፣ ለኔም ስጡኝ በይ» ብለሽኝ አልነበር? ከዛን በፊት ሲሰጣቸው እንቁላል ለኔ አልተሰጠኝም ነበር። አሁን አንድ ቀን አረጋሽ ለነናሆም ስትሰጣቸው ለኔ አልሠጠችኝም ነበር። ስለዚህ «ለኔም ስጪኝ» ስላት፣ «ለነሱ ማን ሠጣቸው አለሽ?» አለችኝ። «ማንም አላለኝም። ትናንትና ሁለት ጊዜ ወተት ስትሠጫቸው ለኔ አልሰጠሽኝም። ገኒ 'ስጡኝ በይ። እንቁላልም ሆነ ምንም እገዛለሁ።' ብላለች።» ስላት፣ «አላቅም! ወሬ አልፈልግም!» አለችኝና «እሺ» አልኳት። ከዛን ጊዜ ጀምሮ በጣም ዘግታኛለች። አረግዬን በጣም ነው የምወዳት። ስለዚህ ገንዬ ለምን ዝም አለችኝ? ብታይ በፊት ሁሌ ጨዋትም ሆነ ማታ ሠላም እንባባል ነበር። ወደ*

ቤቷ ስትሄድ እንኳን ቻው ትለኝ ነበር:: አረግዬ ሲያመኝ እንኳን ትጨነቅልኛለች:: ስለዚህ አረግዬ ለምን እንዲህ ሆነችብኝ? እኔ'ኮ አንቺ ስትጠይቂኝ፣ «አይሠጠኝም» አላልኩም:: እንደውም ሳይሰጡኝ «ለነአስማን ሲሰጣቸው ይሠጠኛል» ነው ያልኩሽ:: አሁን ግን ለነናሆም ሲሰጥ ይሰጠኛል:: ግን አረጉ በጣም ስሜን እንኳን ጠርታ አትሰጠኝም:: «ጥፎት» ብላ ነው የምታስጠራኝ:: ይኼን ያህል ምን አጠፋሁ? አሁን እኔ የምፈልገው አንቺ ጠይቀሻት ጥፋቴን ነግራኝ ይቅርታ እንድጠይቃት ነው:: ገንዬ በፍፁም ጊዜ አታሳልፊ! ጥፋተኛ ከሆንኩ ይቅርታ እጠይቃታለሁ:: ግን ባጠፋም እንዲህ ልትሆን አይገባትም:: ጥፋተኛነቴን ለእኔ መንገር አለባት:: ደግሞ «ለኔም ሰጪኝ» ማለት አያስኮርፍም:: ከሌለ፣ የለም ነው ማለት::

መሃሬ ለምን መሰለሽ? መኮራረፍ በጌታ ዘንድ ስለማይፈለግ ቢሆንም፣ አረግዬን ስለምወዳት ነው:: ነይና አስታርቂን! ጊዜ አትስጪው::



Sample output to test PDF Combine only



# -53-

*«ታደለንም ሆነ እኔን ሲመቱኝ አትምቱት ብላ ትከራከራለች:: . . .*
*'ሩዝ አልበላም' ብዬ ባለፈው፣ 'ተው፣ ተው' እያለች ትመክረኛለች::»*
*ሚካኤል ግርማ*
*«ታናድደኛለች:: ልጆቹን ትማታለች:: ወንድሜን (ታደለን)*
*በትንሽ ነገር እንዲነኩባት አትፈልግም::»*
*በህጻናት ማሳደጊያው የሚኖር ልጅ*

የአመለዘውድ ከፍተኛ ድክመት ብለው የግቢው ልጆችና አንዳንድ ሠራተኞች ከሚያስቧቸው ፀባዮቿ ዋነኛው ለወንድሞቿ በጭፍን ማዳላቷ ነው:: በተለይ ታደለን የሚነካባት ልጅ ምንም ዓይነት አሳማኝና በቂ ምክንያት ቢኖረው፣ ልትቀበለው ፈቃደኛ አትሆንም:: ታደለን የሚመቱትን በመቆጣት ብቻ አታልፋቸውም፤ ብዙ ጊዜ ትመታቸዋለች:: ሁሉም የግቢው ነዋሪዎች ለትንሹ ወንድሟ ምን ያህል እንደምትንሰፈሰፍለት ያውቃሉ::

ለሚካኤልም ከፍተኛ ፍቅር አላት:: ከሕፃናቱ ጋር በራሱ ጥፋት ቢጣላም፣ «ለምን መታኸው?. . .» ብላ በተጣላው ልጅ ላይ ታፈጣለች:: ለደቂቃዎችም ትከራከራለች::

አመለዘውድ በአብዛኛው፣ «አርቃ የምታስብ፣ የምታግናገዛብ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላት ልጅ ሆና እንዴት እንዲህ ለወንድሞቿ በግልፅ ታዳላለች?» በሚል አንዳንድ ልጆችና ጥቂት የድርጅቱ ሠራተኞች ይናደዱባታል፤ ይገረማሉም:: በአደገችበት ሰፈር ውስጥ እነሱ ደሃ በመሆናቸው ይሰማት የነበረው ራሷንና ቤተሰቧን በተለየ ዓለም ውስጥ እንደሚኖሩና እንደተበደሉ የማሰብ አባዜ በህጻናት ማሳደጊያውም ውስጥ አለቀቃትም:: በድህነታቸው ምክንያት እሷና ቤተሰቧ ሲናቁ፣ ሲገፉና ሲገለሉ ኖረዋል:: ይህ ሁኔታ በአስተሳሰቧ ላይ የፈጠረባት ጫና አመለዘውድ ለወንድሞቿ እንስፍስፍ እንድትሆን፣ በጭፍን እንድታዳላና በተለየ ሁኔታ እንድትንከባከባቸው ያስገደዳት ይመስላል::

ሚካኤል በአንድ ወቅት ሩዝ አልበላም አለ:: ሩዝ ሲሰራ ባዶ ሆዱን እንደሚውል አመለዘውድ ሰማች፣ አየችም::

«መብላት አለብህ!» ብትለውም ሚካኤል የሚሰማ አልሆነም:: ከሌሎች እቤቱታዎች ጋር የሚካኤልን ሩዝ አለመብላት ለወ/ሮ ገነት በደብዳቤ እስከማሳወቅ ደርሳ ነበር::

*የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና::*
*ዕብራውያን 4:14*

*ይድረስ በጣም ለምወድሽ እናቴ ገነት፣ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ:: ከሰላምታዬ ቀጥዬ የምገልጽልሽ ነገር ቢኖር ይህን ይመስላል:: የትልልቆች ክፍል ወንዶች፣ «አመለዘውድ ለምን ያቃጥለኛል እያለች . . .» እያሉ ወጥ ቤቶቹን የሚቀርበውን ምግብ አንበላም እያሉ ስለሆነ እባክሽ የሚቻልሽን ንገሪያቸው:: ለምን? ብርቱዬንና አሴን እያስቸገሩ ነው:: ያለበለዚያ መመገብ አልቻልኩም:: ከዚህ በፊት ነበር እንዲህ ማለት የጀመሩት:: መናገር አልፈለግኩም ነበር እንጂ ቆይተዋል ማለት ከጀመሩ:: እነሱ አያማቸውም:: የሁሉንም ዓይነት ምግብ መመገብ ይችላሉ:: ስለዚህ እኔ በእነሱ መናደድ አልፈልግም:: ስለእግዚአብሔር ቃል ቢነግሩዋቸው አይሰሙም:: በተለይ ሚካኤል ሩዝ አልበላም እያለ ቡርትዬን እያናደዳት ነው:: በተቻለሽ መጠን ምከሪያቸው:: ግን ኢየሱስን እንዲያመልኩ ነው:: እኔ ደግሞ ፀሎት ቤት መሄድ እፈልጋለሁ:: እዚህ ቅርብ የሚገኝ ጋር ካሱ*[1] እየወሰደ ያፀልይልኛል:: ስለዚህ እሁድ፣ እሁድ እንድሄድ ከማሚ ስድሴ ጋር ተነጋግራችሁ እንድሄድ ፍቀዱልኝ:: እዚህ እኮ በደንብ አንፀልይም:: ለምን? ሁሉም ልቡ ወደ ፀሎቱ ስለማይሄድ ካሱና ገረመው*[2] ይተውታል:: ወሬ ያወራሉ፣ በደንብ አይፀልዩም፣ አይዘምሩም:: እኔ ሀሎት ቤት መሄድ እፈልጋለሁ:: ቢፀለይልኝ ይሻለኛል:: በተረፈ አንቺም አስቢበትና ንገሪኝ::*

*ቻው ቻው*

**[1]/*[2] ካሱና ገረመው የህጻናት ማሳደጊያው የጥበቃ ሠራተኞች ናቸው::*

አንድ ቀን አመለዘውድ፣ ምናልባትም ለሶስተኛ ወይም ለአራተኛ ጊዜ፣ «ምን ነክቶህ ነው ግን ሚካኤል ሩዝ የማትበላው?» ብላ ወንድሟን ጠየቀችው::

«ሩዝ አልወድም» ደጋግሞ የሰጣትን መልስ መለሰላት::

«እና ሩዝ ሲሰራ ፆምህን ትውላለህ?»

«አዎ»



Sample output to test PDF Combine only



«እንደሱማ አይሆንም ሚካኤል:: እኛ'ኮ በአንድ ወቅት እንራብ ነበር:: አሁን ምግብ ስታገኝ ማማረጥማ ግፍ ነው:: ደግሞ በሽታችን ምግብ ካልበሉበት መጥፎ እንደሆነ ስምተሃል አይደል? »

«አዎ፣ ግን እኔ ሩዝ አልወድም::»

«በበሽታችን ምክንያት ምግብ መብላት ግዴታ ስለሆነ ግን መብላት አለብህ:: አንተ እንደእኔ አያምህም:: መብላት ትችላለህ:: ፆምህን መዋል የለብህም:: መብላት አለብህ! ሲርብህ ስለሚደክምህ በሽታውን አትችለውም፤ ሊያምህ ይችላል:: ሚኪዬ እኔ እንድትታመምብኝ አልፈልግም:: አባቴና እናቴ ሞተውብኛል:: ሚኪ ትሰማኛለህ! አንተም እንድትሞትብኝ አልፈልግም!» ፊቷን ወደፊቱ አቅርባ ነበር የምታናግረው::

የመጨረሻው ዓረፍተ ነገር አስደንግጦት ቀና ብሎ አያት:: ፊቷ ላይ ያነበበው ለሱ ያላት ፍቅር አድርግ የምትለውን እንዲያደርግ የሚያስገድድ ኃይልና ጉልበት ነበረው::

«እና መብላት አለብህ እሺ!»

ሚካኤል ወደ ፊት ለፊት እያየ በዝምታ ተቀመጠ:: በዝምታው «እሺ!» የሚል መልስ እንደሰጣት አመለዘውድ ተረዳች::

አመለዘውድን ከዚህ ቀን በፊት በተደጋጋሚ ብትመክረውም፣ እንደ ዛሬ ግን በኃይል ተናግራው አታውቅም:: ከዚህ ዕለት ጀምሮ ሚካኤል የእህቱን ማስጠንቀቂያ ሰምቶ በተሻለ ፍላጎት የሚቀርብለትን ሩዝ ይበላ ጀመር::

አመለዘውድ ለታደለ የምታደርግለት እንክብካቤ የላቀና የተለየ ነው:: ምግብ ሲበላ ዓይኖቿ እሱ ላይ ናቸው:: ትንሹ ወንድሟ በደንብ መመገቡን ዘወትር ማረጋገጥ ትፈልጋለች:: ኤች.አይ.ቪ. በምን፣ በምን እንደሚተላለፍ ስለምታውቅ አንዳንድ ጊዜ ታደለ የሌሎች ሕፃናትን የጥርስ ብሩሽ በስህተት ወይም በግድየለሽነት ተጠቅሞ ለቫይረሱ እንዳይጋለጥ ትሰጋለች::

«ታዴ የአንተን ብሩሽ አየኸው?» ትለዋለች ብሩሹን በእጇ ይዛ:: «በዚህ ብሩሽ ብቻ ነው አንተ ጥርስህን መፋቅ ያለብህ:: የሌላ ልጅ ብሩሽ እንዳትጠቀም እሺ! የሌላ ልጅ ብሩሽ የአንተ አይደለም:: የአንተ ያልሆነን ንብረት ደግሞ መጠቀም የለብህም አይደል?»

አመለዘውድ በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች በግቢው ውስጥ አብረዋቸ የሚኖሩ ልጆችን ልትመታ ትችላለች:: አንደኛ ወንድሞቿን በተለይ ታደለን ሲመቱባት፣ ሁለተኛ ልጆች ሲጣሉ ስታይ፣ ሦስተኛ እንዲሁ የተበሳጨች ቀን

እሷ ያለችውን አልሰማ ሲሉ ትማታለች:: ለመቆጣት ደግሞ ልጆች ሲላፉና እየተቀላለዱና እየተሳሳቁ ሲያጠሩ ማየት ይበቃታል::

ትልቁ ወንድሟ ተሾመ አዘውትሮ ይናፍቃታል:: «ዱርዬነቱ» እና «ሃሣብ የለሽነቱ» በእጅጉ ያበሳጫታል:: የምትበሳጭበትን ያህል ደግሞ ለታላቅ ወንድሟ ጥልቅ ፍቅር አላት::

ለእሱ ያላት ፍቅር ፈንቅሏት፣ ሰንባ እየተናነቃት የፃፈችለት ይህ ደብዳቤ ለወንድሟ ሳይላክ እሷ'ጋ ቀርቷል::

*ቀን 4-7-97 ዓ.ም.*

*ይድረስ በጣም ለምወድህ ወንድሜ ተሾመ ግርማ፣ ከተለያየንበት ቀንና ሰዓት ጀምሮ ለጤንነትህ እንደምን አለህልኝ? ተሽዬ፣ እኔ ጌታ ኢየሱስ ይመስገን ከነወንድሞቼ በጣም ደህና ነኝ:: ተሼ፣ አንተስ እንደምን ነህ? የሚረዳህ ሳይኖር በማለት በጣም እየተጨነቅሁ ሲሆን፣ ነገር ግን ወደ እግዚያብሔር ሁሌ እፀልይልሀለሁ:: ተሽዬ፣ አንተ ብቸኛ ነህ:: አባትህና እናትህ ሞቱብህ፤ እህትና ወንድሞችህ ከአንተ ተለዩ:: ውዱ ወንድሜ፣ በውነቱ አንተን ኢየሱስ ይወድሀል:: ነገር ግን አንተ እሱ ለሀጢያትህ እንደተሰቀለ እስካሁን አላመንክም:: ለሚረዱንና ከችግር ለሚያወጡን ለማርታ እንኳን አልታዘዝህም:: እኔ በአንተ ነገር ሁሌ እንባዬን አፈስሳለሁ:: አንተ እስካሁን የት በደረስህ ነበር:: ተሼ፣ አስታውስ እስኪ እኔ ከአንተ እበልጣለሁኝ? ታላቅና አባትህ ብርታት ባለው ጊዜ የተወለድህ ነህ:: በሀብታችን ጊዜ አባትህ ተማር እያለ በአንተ ስንት መከራ አይቷል:: ግን አንተ ከእኔ ትሻላለህ፣ ብዙ ነገር ታውቃለህ፤ አባታችን የልጆቹ ነገር እንደማይዋጥለት ታውቃለህ:: ማታ ሲመጣ፣ «ተሽዬ» እያለ እንደሚገባ ልትረሳ አትችልም:: ተሽዬ፣ አሁንም የምመክርህ ወ/ሮ ማርታ ጋር ግባና ስለጥፋትህ ይቅርታ ጠይቅ:: እነሱም አንተ እኛን እንድታየን ይፈቅዱልሀል:: አንተ እምቢ አልክ እንጂ እነሱ አንተን እንዴት እንደሚወዱህ ጌታ ያውቃል:: ተሾመ፣ እባክህ ዘመኑ በጣም ከፍቷል:: ተጠንቀቅ! በጊዜ ወደ ቤትህ ገብተህ ፀልይ! ኢየሱስን እመን! እሱም አንድ ነገር ያደርግልሀል:: ይህን ደብዳቤ ስፅፍ እንባዬ እየተናነቀኝ ነው::*

*እንዴት እንደምወድህና ስለአንተ እንደማለቅስ የልቤን የሚያይ አምላክ ያውቃል:: የቤቱን ነገር ሁሉንም ነገር ከተቻለህ ፃፍልኝ በተረፈ ሀናን፣ የሺን፣ ማሕዛን፣ አለም አገኘን፣ አገሬን፣ ደመቀን፣ ሻሼን፣ ጋሽ ጥላሁንን፣ ታደሰን ሁሉንም የሠፈር ልጆች ሠላም በልልኝ::*

*በተረፈ ጌታ ከአንተ ጋር ይሁን!*

*አሜን!*

*ቻው ቻው*

አመለዘውድ ለሞግዚቶቿና ለሌሎች ሰዎችም ስለተሾመ ስታወራ ትበሳጫለች፤ ትቆጫለችም:: «እሱ ዱርዬ ነው:: አይጠይቀንም::» ትል ነበር:: ይህ ቁጣዋ ግን ከፍቅርና ለእሱ ካላት ሀዘኔታ፣ ለእሱ ከመጨነቅ የመነጨ እንደሆነ ለስድሴ ከፃፈችው ሌላ ደብዳቤ መረዳት ይቻላል:: ይህን ደብዳቤ የጻፈችበት ዋና ምክንያት ግን እሷ ሐዘንተኛ፣ ዝምተኛና ብቸኝነትን የምትመርጥ የሆነችው ስለወንድሟ ስለምታስብና ስለምትጨነቅ ስለሆነ ይህንኑ ስድሴ ተረድታ የነፈገቻትን ትኩረት እንድትሰጣት ለመጠየቅ ነው::

*ሁሉን ታደርግ ዘንድ ቻይ እንደሆንክ ዕቅድህም ከቶ እንደማይሰናከል አወቅሁ:: ኢዮብ*
*(ከደብዳቤው በላይ የጻፈችው ጥቅስ)*

**10/7/97**

*ሁሉ በእርሱ ሆነ::*

*ውድ እናቴ ማሚ ስድሴ፣ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ደህና ነኝ ጤንነቴም በጣም ጥሩ ነው:: ግን ማሚ ስድሴ፣ በአንድ ነገር ያስጨነኩሽ ይመስለኛል:: ለምን በፊት በጣም ደስተኛ ነበርኩ:: አሁን ግን የተለያዩ ሀሳቦች ስለሚመጡብኝ፣ ዝምተኛ ከመሆኔ በላይ ጨፍጋጋ፣ የማልስቅ እየሆንኩ ነው:: ለምን መሰለሽ? የታላቅ ወንድሜ ነገር በጣም ያሳስበኛል:: ለሊት፣ ለሊት ሳለቅስ ነው የማድረው:: በምተኛበት ጊዜ የወንድሜ መልክ ይታየኛል:: ደግሞ ሲያለቅስ፣ ሲታመም፣ ሰለኛ ሲያስብ፣ ብቻ ነው በሀሳቤ የሚታየኝ:: ስለዚህ ትምህርት ቤት እንኳን እንግሊዝኛ ንባብ ለማንበብ፣«V. Good» ተባልኩና፣ «ኤክሰለንት አጨብጭቡ» ሲባልልኝ፣ ዝም ብዬ ስገባ አስተማሪው፣ «ደስ አይልሽም ወይ?» ብለውኝ የባሰውን አለቀስኩኝ:: እኔን አንቺ ታለብሽኛለሽ፣ ታስተምሪኛለሽ:: እሱን ግን የሚጠይቀው የለም:: ለምን መሰለሽ? ወይ ማርታ ጋር አይስማማም:: «እህቶቼ አይለዩኝ» ብሎ ሲለምናቸው፣ «አይሆንም» ብለውት ስለነበረ፣ ሰንናፍቀው ያለቅሳል እንጂ እነሱ ቤት አይሄድም:: ስለዚህ እኔ ስጫወትና ሲደሰት እሱ ትዝ እያለኝ ስለሆነ አልስቅም:: ለዚህ ደግሞ ስለሆነ አንቺ*





Sample output to test PDF Combine only

*አመለዘውድ እንዲህ እየሆነች ነው አትበይ:: «ለምን ሰው ሳይርበው፣ ሳይጠማው እየኖረ እንዴት እንዲህ ይሆናል?» ብለሽ ማለቴ ነው:: እኔ እንደዚህ የምሆነው ለሀሳቤ ነው እንጂ ለሌላ ነገር አይደለም:: ብታይ እናታችንን* ብትጠይቂያት፣ «ሌሊት ስትጮሂ ነው የምታድሪው:: መጥቼ ሳይሽ ተኝተሻል» ትለኛለች::*

*በዚህ ምክንያት ነው:: የምኮሳተር አይደለሁም:: ሀሳብ እየያዘኝ ስለሆነ ሌላ ነገር አይሰማሽ:: ደግሞ ፎቶ አንሺኝና ለወንድሜና ለአሜሪካን ደብዳቤ ለፃፉልኝ ልላክላቸው:: ከዚህ በኋላ የምገልፅልሽ ቢኖር እንደሚከተለው ነው:: ዝም አትበይኝ:: አንቺ'ኮ ስትመጪ እነታገኝና እነሰናይትን ብቻ ታናግሪያቸዋለሽ:: እኔ ደግሞ እንደልማዴ ዝም እልሻለሁ:: ለምን መሰለሽ? ባንቺ በኩል ጆሮዬ ስለማይሆነልኝ ብለሽ ሊሆን ይችላል:: ይህ ግን ለኔ ከፍተኛ ተፅኖ አለው:: እንድታናግሪኝና እንድታጫውቺኝ፣ ችግሬን እንድትጠይቂኝ እፈልጋለሁ:: በመሆኑም አንቺ ፀባይ የሌለኝና ሁሌ የምኮሳተር አይምሰልሽ:: እኔን እንዲ ያደረገኝ ሀሳብ ነው:: በተለይ እኔና ሚካኤል ያለንበት ደረጃ በጣም ያሳዝነኛል:: መፅሐፍ ቅዱስ ሳነብ የምንድን ነው የሚመስለኝ:: ግን ሁሉንም ነገር ጌታ በጊዜው ይፈፅመዋል:: ግን አለቅስ ነበር:: አሁን ግን ሁሉንም ነገር ለጌታ ሰጥቸዋለሁ:: የወንድሜ ነገር ብቻ በሀሳቤ እየመጣ ነው:: ማሚ ስድሴ፣ ለምን ግን ከፀሎት ቤት የእግዚአብሔርን ቅባት ቀብቶ የሚፀልይልን አታመጪም? ደግሞ ወንዶችን በተቻለሽ መጠን ምከሪያቸው:: ሲፀለይ አይረብሹ:: ማሚ መልሱን በሚመችሽ ቀን ፃፊልኝ ወይም ንገሪኝ:: በደብዳቤው የተቀየምሽበት ካለ ይቅርታ አድርጊልኝ! እኔ በጣም እወድሻለሁ! አንቺም እንደምትወጂኝ ተስፋ አለኝ:: ጌታ ይባርክሽ! በተረፈ እታገኝ ሠላም ብላሻለች::*

*ቻው*

*ቻው*

*በተረፈ «አመሰጥኩት» የሚለውን መዝሙር ጋብዤሻለሁ::*

**ከግቢው ሞግዚቶች አንዷ የሆነችውን አፀዱ ውብሸትን የምትጠራት «እናታችን» ብላ ነው::*

አንድ ጊዜ አመለዘውድ ወደ ቤቷ ለመሄድ ሞክራ አልተሳካም:: ወደ ቤት መሄድ የፈለገችው ከሁሉም በላይ ታላቅ ወንድሟ ስለናፈቃት ነበር::





*11-9-97*

*ይድረስ በጣም ለምወድሽ እናቴ ማሚ ስድሴ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ በጣም ደህና ነኝ::*

*ማሚ ስድሴ አንድ ቀን፣ «ለምን ቤታችን ደርሶ ሲመጣ እኔን አልወሰደኝም» ስልሽ፣ «ቤታችሁ ሶስታችሁም ትሄዳላችሁ» ብለሽኛል:: እንደውም ይድነቃቸው የቤተሰባችን ቤት የሄደ ጊዜ ነበር:: ይድነቃቸው ሲሄድ፣ «ወይኔ! እኛ ቤት ደርሰህል!» ስለው፣ ሰቀባጥር ለካ ለሱ መንገዱን እየነገርኩት ነው:: አሁን ትንሽ ሄደና፣ «በዚህ ነው?» አለኝ:: «አይደለም:: በዚህ» ብዬ አሳየኹት:: የቤቱን መንገድ በደንብ ሲያገኘው፣ «ስድሴ ልካኛለች በሉ:: እዚህ ውረዱና ጠብቁኝ::» ብሎ ሲስተር ጤናንና እኔን ሜዳው ላይ አውርዶ ሄደና መጣ:: አይገርምም?*

*በፊቱንም ማን ለፍልፊ አለኝ? በነገራችን ላይ ማሚ ስድሴ፣ «ቤታችሁ ትሄዳላችሁ» ብለሽኝ ነበር:: መቼ ነው? እነሱም (እነወ/ሮ ማርታ) ብለውኛል:: ትምህርት ሲዘጋ ቢሆን ነው የምንፈልገው:: ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ትምህርት ሲዘጋ እንድንሄድ ፍቀጂ:: በተለይ በጣም የሚናፍቀንን ወንድማችንን ለማየት ነው:: ተመልሰንም እንመጣለን:: ደግሞ እግዚአብሔር ከፈቀደና በሕይወት ከኖርን፣ በሌላ ዓመትም እንሄዳለን:: ግን ማሚ ስድሴ የምንሄድበትን ጊዜ መስነሽ ንገሪያቸው:: ስለዚህ በጣም አመሠግናለሁ:: የፀሎት ቤት የፃፍኩልሽን ደብዳቤ ምን አልሽ? መልሰ አትነግሪኝም? ደግሞ እኔ አጥሚት አልወድም:: እነሱ በየቀኑ ሲጠጡ፣ እኔ ግን እየተጐዳሁ ነው:: ስለዚህ በአጥሚት ፈንታ በሶ ግዢልኝ:: ለምን መሰለሽ? እነሱ ሲጠጡ፣ እኔ ከተጀመረ ጀምሮ ጠጥቼ አላውቅም:: ከዚህ በፊትም መጥቶ የነበረ ጊዜ አልጠጣሁም:: ለምን? አልወድም ነበር:: ደግሞ ማሚ ስድሴ እንጀራ ስበላ ልቤን በጣም እያቃጠለኝ ነው:: ስለዚህ የምበላው ነገር አዘዢልኝ:: ለምን መሰለሽ? ምሳዬን የ1 ቁርጥ ግማሽ እንኳን አልበላም:: ያቃጥለኛል፣ ልቤን:: ለገነት ቢሮ ፅፌ ነበር:: አሁን በዚህ አበቃለሁ:: በነገራችን ላይ ለፃፍኩልሽ መልስ እንዳትረሺ:: የአሜሪካን ልጆች ደብዳቤም የሚረዳኝ ስለሌለ አልፃፍኩም::*

*ኢየሱስ ይባርክሺ!*

*ቻው*

*እወድሻለሁ::*



Sample output to test PDF Combine only

## -54-

*«እኔ መስራት የምፈልገው የፊልም አይነት በጥሩ አበቦች መካከል መዝሙር ከፊልም ጓደኞቼ ጋር መዘመር ነው፡፡»*
*አመለዘውድ*

ጆሮ ላይ የሚሰካውን ማዳመጫ እንድታገኝ የረዷት የአሜሪካዊቷ ሲንዲ ማክኪኒ ልጅ ጄሰን ማክኪኒ በኮሎራዶ ግዛት፣ ፎርት ኮልንስ በተባለ ከተማ በአንድ ት/ቤት ሳይንስ አስተማሪ ነበር፡፡ እናቱ ስለአመለዘውድና ስለሌሎቹም ህጻናት ከነገሩት በኋላ፣ ለስድስት ወራት የገንዘብ ዕርዳታ በአመለዘውድ ሥም ለድርጅቱ ሰጠ፡፡ ከሚያስተምራቸው ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ከሚማሩ ልጆች ጋር ደብዳቤ እንድትጻጻፍም ሁኔታዎችን አመቻቸላት፡፡

አመለዘውድ አሜሪካዊ የብዕር ጓደኞቿ የሚፅፉት እንግሊዝኛ በደንብ ባይገባትም፣ በስሜት ታነበዋለች፡፡ በእንግሊዝኛ የተጻፈላትን አንብበው በመተርጎምና እሷ በአማርኛ የጻፈችውን መልስ በእንግሊዝኛ በመፃፍ ክብነሽና ሌሎች የቢሮ ሠራተኞች እንዲሁም አንዳንድ በጎ ፈቃደኞች ይረዷታል፡፡

*በጣም የምወድሽ እናቴ ገነት! እንደምን ነሽ? እኔ ኢየሱስ ይመስገን በጣም ደህና ነኝ፡፡ ገንዬ! ትናንትና የፃፍኩልሽ ደብዳቤ ደረሰሽ? ዝም ብዬ ነው የጻፍኩልሽ፣ ለሠላምታ ነው፡፡ ገንዬ በናትሽ ይድነቃቸው እናንተ ጋር ሲመጣ እኔም የጠዋት ስለሆንኩ ከሰዓት ቢሮ ልምጣ፡፡ ለምን መሰለሽ? የሆነ ነገር ለማድረግ ነው፡፡ ስለደብዳቤ ነው፡፡ ለመፃፍ፣ በእንግሊዝኛ ነው፡፡ ለይርጌ ንገሪውና ልምጣ፤ ህፃናት ሲመጡ፡፡ ክብነሽን እፈልጋታለሁ፣ «ነይና እንፅፋለን» ብላኝ ነው፡፡ ስለዚህ እባክሽ ልምጣ!*

*በጌታ የምወድሽ ልጅሽ አመለዘውድ ነኝ፡፡*

ለአንዳንዶቹ የብዕር ጓደኞቿ ራሷ በእንግሊዝኛ ልትጽፍላቸው ትሞክራለች፡፡ ደብዳቤ መጻፍ ከማንበብ ቀጥሎ ዋና የጊዜ ማሳለፊያዋ ስለነበር ከብዕር ጓደኞቿ ጋር መጻጻፍ ያስደስታት ነበር፡፡

ለብዙዎቹ የብዕር ጓደኞቿ በፃፈቻቸው የመጀመሪያ ደብዳቤዎች ላይ ራሷን ስታስተዋውቅ፣ ሦስቱንም ወንድሞቿን ጠቅሳለች፡፡ ስለዕድሜያቸው በትጽፍ የራሷን 10፣ 11፣ 12 ወይም 13 ሊሆን እንደሚችል ነው የምትነግራቸው፡፡ በተወሰኑት ደብዳቤዎች ላይ የወንድሞቿን ዕድሜ እንደማታውቀው ገልጻለች፡፡ የራሷን ዕድሜ ዝቅ የምታደርገው የብዕር ጓደኞቿ በአስራ ሁለትና በአስራ ሶስት ዓመታቸው የሰባትና የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች መሆናቸው፣ እሷ ግን ገና የሰስተኛ ክፍል ተማሪ መሆኗ





ስለሚያሳፍራት ይመስላል፡፡ የብዕር ጓደኞቿ ጤነኞችና ከህጻንነታቸው ጀምሮ የተመጣጠነ ምግብ እየበሉ ስለኖሩ ሰውነታቸው ከሷ ጋር ሲነጻጸር ግዙፍ ሆኖ ስለሚታያት እሷ ኮስማና ሆና የእነሱ እኩያ ወይም ታላቅ መሆኗ ግራ ስለሚያጋባትም ሊሆን ይችላል፡፡ በየትኛውም ደብዳቤዋ ከኤች.አይ.ቪ. ጋር እንደምትኖር አልጻፈችም፡፡ ወላጆቿን ማጣቷን ግን ለአንዳንድ የብዕር ጓደኞቿ ጽፋለች፡፡

*ውድ ሎውራ፣*

*ለኔ በመፃፍሽ ደስ ብሎኛል፡፡ ከእናንተ ጋር ብዙ ልጆች ፅፈውልኛል፡፡ እስቲከርም ልከውልኛል፡፡ በዚህ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ እኔ ድመት አለችኝ፡፡ ስሟ ውሮ ይባላል፡፡ ሌላም ስም አውጥቼላት ነበር! አታውቀውም፡፡ የሠጠችኝ ጓደኛዬ ናት፡፡ ድመቷ ህፃን ናት፡፡ እኔ እስፖርት እወዳለሁ፡፡ እግር ኳስ እጫወታለሁ፡፡ አንቺ በጣም ቆንጆ ነሽ፡፡ ክሌርም በጣም ቆንጆ ናት፡፡ ፀጉርሽ እንደ ኢትዮጵያ* ነው፡፡ በቃ በጣም ቆንጆ ነሽ፡፡ እኔ 2 ወንድሞቼ፣ አንዱ 8 አመቱ ይመስለኛል፡፡ የእኔ 11 ነው፡፡ የትንሹ 5 ይመስለኛል፡፡ ግን በደንብ አላውቀውም፣ እድሜያቸውን፡፡ ማንበብ እወዳለሁ፡፡ በአብዛኛው የማነበው መፅሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ስለአመመኝና ፈተና፣ የትምህርት ስለነበረብኝ ነው ቶሎ ያልፃፍኩላችሁ፡፡ ለሁሉም ይቅርታ ብለሽ ንገሪያቸው፤ ለሚፅፉልኝ በሙሉ፡፡*

*ጓደኛሽ*
*አመለዘውድ ግርማ*

*ብዙ ጊዜ በድራማና ሙዚቃ ዝግጅቶች ላይ ኢትዮጵያን እንዲወክሉ የሚደረጉ መልከመልካም ሴቶች ፀጉራቸው ረጅም ስለሆነ ይሆን፣ «ፀጉርሽ እንደ ኢትዮጵያ ነው፡፡» ያለችው?

አመለዘውድ ለአንድ ብዕር ጓደኛዋ በፃፈችው ደብዳቤ፣ «እዚህ ህይወት አስደሳች አይደለም፣ ግን እግዚአብሔር ስለሁሉም ነገር ይመስገን፡፡» ብላለች፡፡

ለዲዩን ስሚዝ በፃፈችው ደብዳቤ ደግሞ ስለራሷና ቤተሰቦቿ እንዲህ ፅፋለች፡፡ «ኢትዮጵያ ውስጥ በአንድ ህጻናት ማሳደጊያ ድርጅት ውስጥ እኖራለሁ፡፡ ምክንያቱም ወላጆቼ ሞተዋል፡፡ ከሁለት ወንድሞቼ ጋር ነው የምኖረው፡፡ ጎበዝ ተማሪ ነኝ፤ ጥሩ ውጤት አለኝ፡፡ ሽልማት ተሰጥቶኛል፡፡»

ክሌር ለምትባለው ጓደኛዋ፣ «ሩጫ ደስ ይለኛል፣ ግን ስለሚያመኝ በፍጥነት መሮጥ አልችልም፡፡» ብላ ጽፋለች፡፡



Sample output to test PDF Combine only

ለሳንድራ ፎንታኒ በፃፈችው ደብዳቤ ደግሞ ትምህርት ቤት ለመሄድ ያላትን ጉጉት፣ «ት/ቤት ልሄድ ስል ከዘነበ እናደዳለሁ» ስትል ተገልጻለች::

ለኤልዛቤት ያንግ በላከችው ደብዳቤ ፎቶ ግራፍ አንሺ መሆን እንደምትፈልግ ጽፋለች:: ለወንድሞቿ ያላትን የእናትነት ስሜት ከደብዳቤው ማስተዋል ይቻላል::

*ውድ ኤልዛቤት፣ እንደምን ነሽ? ስሜ አመለዘውድ ግርማ ይባላል:: 10 ዓመቴ ነው:: የ3ተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ:: የምወደው የትምህርት አይነት እንግሊዘኛ፣ አማርኛ፣ ሣይንስ ሌሎችንም የትምህርት አይነቶች እወዳለሁ:: እኔም የተለያዩ እንስሳትን መሣል እወዳለሁ:: ስፖርት በጣም እወዳለሁ:: ሩጫና እግር ኳስ እወዳለሁ:: እጫወታለሁ:: ቴኒስ መጫወት እፈልጋለሁ:: ነገር ግን እኛ አናገኝም:: አዎ፣ ፎቶ ግራፍ ማንሣት እፈልጋለሁ፤ ከወንድሞቼ ጋር በመሆን ስለታሪካችን፣ ማለትም ስናጠና፣ ስንፀልይ፣ ስንዘምር፣ ስንጫወት:: ወንድሞቼ አባት ወይም እናት ስለሌለን፣ እኔ እነሱን አስደስቼ፣ ሲያድጉ ፎቶውን ማስታወሻ እንዲሆናቸው ስለማስብ ነው:: በተጨማሪ በኢትዮጵያ ስላሉት ነገሮች ፎቶ አንስቼ ልልክልሽ እስቤያለሁ:: ካሜራ ፊልም የለኝም:: ቢኖረኝ በጣም ደስ ይለኝ ነበር:: ፎቶ ማንሣት ችሎታዬ እንዲሆን እመኛለሁ:: ፎቶ ማንሣት አሁንም እችላለሁ:: የምወደው ምግብ ዳቦ በሻይና በወተት፣ እንጀራ በሥጋ ወጥ ነው:: ፎቶው እና ምስሎቹ ደርሠውኛል:: በጣም ነው የምወደው፤ መልክሽ በጣም ቆንጆ ነው:: ፀጉርሽ እረጅም ነው:: እኔ ረጅም ፀጉር እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ:: ቀሚስ የምወደው በጣም የምታምር የጅንስ ቀሚስ ከነአለባበሷ አጠር ያለ ነው ፍላጎቴ:: አንቺም የለበሽው በጣም ያምራል:: አስታውሠሽ በመላክሽ በጣም አመሰግናለሁ::*

*ያንቺው*
*አመለዘውድ ግርማ*

የብዕር ጓደኞቿ በሕይወታቸው የሚያጋጥማቸውንና ወደፊት ምን መሆን እንደሚፈልጉም ይፅፋሉ:: ጃሮድ የተባለው ጓደኛዋ የሚከተለውን ደብዳቤ ፅፎላት ነበር::





*ውድ አመለዘውድ፣*

*ሃይ! ስሜ ጃሮድ ይባላል:: ፎርት ኮልንስ፣ ኮሎራዶ ውስጥ በቅዱስ ዮሴፍ ት/ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ ነኝ:: ትምህርት ትወጃለሽ? እኔ የቤት ሥራ የሚባል ነገር ከመጥላቴ በስተቀር ትምህርት ደስ ይለኛል:: የምወደው የትምህርት አይነት ቪዲዮ ቴክ ነው:: በዚህ ትምህርት ስለ ት/ቤት ዜና መሳይ ነገሮች እሰራለሁ:: እንግሊዝኛ አልወድም:: አንዳንድ ጊዜ ከባድ ነገር ይሆንብኛል::*

*መቀለድ እወዳለሁ:: በቴሌቪዥን የኮሜዲ ዝግጅቶችን ማየትም ደስ ይለኛል:: ፎቶግራፍ ማንሳት እንደምወድ እገምታለሁ፣ ምክንያቱም ሳድግ ፊልም መሥራት እፈልጋለሁ::*

*እኔ በጣም የሚያወሩ (ለፍላፊ) ሰዎች አልወድም:: ሊያናድዱኝም ይችላሉ:: ከዚህ በተጨማሪ እኔ በአብዛኛው አዳማጭ ነኝ:: ጥሩ ሰው ትመስያለሽ::*

*ሁሉም ሰው ሳይወድሽ አይቀርም:: እኔም መሸነፍ እጠላለሁ:: ማሸነፍ በጣም የተሻለ ነው:: እኔም ማንበብና መፃፍ እወዳለሁ:: በማንበብና በመፃፍ አዳዲስ ዓለማትን ማሰስ ትችያለሽ::*

*ያንቺው ጃሮድ*

አመለዘውድ ለዚህ የጃሮድ ደብዳቤ የጻፈችው መልስ የሚከተለው ነው::

*ሄሎ! ስሜ አመለዘውድ* ይባላል:: የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት የእንክብካቤ ፕሮጀክት ኢትዮጵያ ውስጥ የ3ተኛ ክፍል ተማሪ ነኝ:: ትምህርት በጣም ነው የምወደው:: የቤት ሥራ መስራት በጣም ጉበዝ ያደርጋል:: እቤት መሥራት ካልፈለግህ ትምህርት ቤት ሆነህ የቤት ሥራህን መሥራት አለብህ:: ካልሠራን እኛ ጋር ቅጣት አለ:: በቪዲዮ መማር እኔም እፈልጋለሁ:: ግን አንማርም:: በብላክቦርድ፣ በሬዲዮ ነው የምንማረው:: እኔ እንግሊዝኛ ትምህርት ይገባኛል፤ እወዳለሁ:: ሒሳብን እኔ አልወደውም:: እኔም በቲቪ ተረቶችን፣ የሚያስቁ ነገሮች መከታተል እወዳለሁ:: ፎቶ ግራፍ እኔ በጣም እወዳለሁ:: ያንተን ፎቶ ላክልኝ:: እኔም ፎቶ የሚያነሣኝ ካገኘው እልክልሀለሁ:: እኔም ፊልም ለመሥራት እጓጓለሁ:: ሳድግ አብረን የምንፈልገውን ዓይነት ፊልም እንሠራለን:: እኔም ብዙ የሚያወራ ሰው አልወድም:: «ብዙ ከማውራት ጥቂት መሥራት ይጠቅማል::» የሚል ፅሑፍ አውጥቻለሁ:: እኔ ጥሩ*



Sample output to test PDF Combine only

*የሆንኩት፣ ባባትና በእናት ማጣት ነው። እንደፈለኩ ሣልሆን ጥሩ ሆኜ ማደግ ነው የመረጥኩት። አንተም ጥሩ ሁን! እግዚአብሔርም ይወድሀል። ማሸነፍ የኔም ነው፤ መሸነፍ ግን አይደለም።*

**ከላይ ከሚነበበው የጃርድ ደብዳቤ አመለዘውድ ቀደም ብላ እንደጻፈችለት መገመት ይቻላል። አመለዘውድ ምናልባት ለበርካታ ልጆች ስለምትጽፍ ለጃርድ እንደጻፈችለት ረስታ ሊሆን ይችላል በዚህ ደብዳቤ ደግማ ራሷን ለማስተዋወቅ የፈለገችው።*

ጃሮድ የፃፈላት መልስ ባይገኝም፣ እሷ በፃፈችለት ሌላ ደብዳቤ ምክር መስጠቷን ገፍታበታለች።

*ውድ ጃሮድ፣*

*በደብዳቤዬ በመደሰትህ እኔም ደስ ብሎኛል። እኔ መስራት የምፈልገው የፊልም አይነት በጥሩ አበቦች መካከል መዝሙር ነፊልም ጓደኞቼ ጋር መዘመር ነው። አክሽን በሞተር ሳይክል ላይ መስራት እፈልጋለሁ፤ ግን ድብድቡን አልወደውም፣ ያስፈራኛል። የአንተ ከጓደኞችህ ጋር መዘነጥህና ፊልም ማየትህን ወድጄዋለሁ፤ ግን ጥሩ ጓደኛ ሊኖርህ ይገባል። የምታየው ፊልምም ትምህርት ሊኖርበትና ለአንተ የሚሆን መሆን አለበት። የአንተ ጓደኛ በጣም የምታነብ መሆኗን ገልፀህልኛል፤ ግን ማንበብ ለአንተም በጣም ጠቃሚ ነው። የሀገር መሪ እኮ ብዙ ንባብ ካላነበበ ማስተዳደር አይችልም። ስለዚህ በተቻለህ መጠን በትንሽ ጊዜ ማንበብ ልመድ፣ ብዬ የምመክርህ እህትህ ነኝ። በል ደህና ሁን። መልካም ጊዜ እመኝልሀለሁ። እግር ኳስ ጨዋታን እጫወታለሁ። ቤተሰቦችህን በሙሉ እወዳቸዋለሁ።*

በዚህ ደብዳቤ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ደብዳቤዎች እግር ኳስ መጫወት እንደምትወድ ገልፃለች። በህጻናት ማሳደጊያው ያሉ ልጃገረዶች እግር ኳስ ይጫወታሉ። የህጻናት ማሳደጊያው የራሱ የወንዶች ልጆችና የልጃገረዶች የእግር ኳስ ቡድኖች ያሉት ሲሆን አልፎ፣ አልፎ ከግቢ ውጪ ከሌሎች ቡድኖች ጋር ይጋጠማል። አመለዘውድ ከከፋ የጤና ችግሯ አንጻር አዘውትራ ባትጫወትም፣ ብዙ ባትሮጥም አንዳንድ ጊዜ የህጻናት ማሳደጊያው ግቢ ውስጥ ኳስ መጫወት ያስደስታት ነበር።





## -55-

*«ቤተሰብ ውስጥ ሁላችንም እንስማትና እናከብራት ነበር። ለዚህ ሊሆን ይችላል በራሷ የምትተማመን የሆነችው።»*
*ተሾመ ግርማ*

አመለዘውድ ብዙዎችን የሚያስደንቅ በራስ መተማመንና ድፍረት ነበራት። የተለየ ምክንያት ከሌለ በዓመት አራት ጊዜ በሚዘጋጅ የቤተሰብ ቀን ካልሆነ በስተቀር፣ በህጻናት ማሳደጊያው ያሉ ህጻናት ቤተሰብ በየጊዜው እንዲጎበኛቸው አይፈቀድም። ቤተሰብ የሚባሉት አክስት፣ አጎት፣ አያት የመሳሰሉት ሲሆኑ በአብዛኛው ልጆቹን ለማሳደግ አቅም የሌላቸው ናቸው። ድርጅቱ ለልጆቹ የሚያስፈልገውን ምግብ፣ ልብስና የትምህርት መሳሪያዎች ለመርዳት፣ ነጻ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ ቢሆንም፣ ልጆቹ አድልዎና መገለል በጎረቤትና በአካባቢያቸው ሰዎች እንዳይደርስባቸው ስለሚሰጉ፣ አንዳንዶቹም ከግንዛቤ ማነስ ቫይረሱ ሊተላለፍብን ይችላል ብለው ስለሚፈሩ ልጆቹን ለማሳደግ ፈቃደኛ ያልሆኑ ናቸው። የቤተሰብ ቀን በዓመት አራት ጊዜ ብቻ እንዲሆን የተወሰነው አዘውትረው በቤተሰብ የሚጎበኙ ልጆችን እያዩ ቤተሰብ የሌላቸው ወይም በተደጋጋሚ በዘመድ የማይጠየቁ ልጆች ስሜታቸው እንዳይጎዳ በሚል ነው። ዘመድ የሌላቸውን ልጆች እንዲጎበኙ ድርጅቱ እንደ ሥጋ ዘመድ ሆነው የሚጎበኟቸው በጎ ፈቃደኞችን በዕለቱ እንዲገኙ ይጋብዛል።

የቤተሰብ ቀናት በህጻናቱ ዘንድ በጉጉት የሚጠበቁ ናቸው። በአንድ የቤተሰብ ቀን እነወ/ሮ ማርታ አልመጡም። አመለዘውድ ላለመምጣታቸው ምክንያት የድርጅቱ የአስተዳደር ሠራተኞች ድክመት መሆኑን በደብዳቤ እንዲህ ተችታለች።

5/9/97

*ኢየሱስ ይባርክሽ!*
*(ከደብዳቤው አናት ላይ የተጻፈ)*

*ይድረስ በጣም ለምወድሽ እናቴ ማሚ ስድሴ፣ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ ኢየሱስ ይመስገን በጣም ደህና ነኝ። ጤንነቴም ጥሩ ነው። ግን ፀሐዩ ሲያቃጥለኝ፣ አፍንጫዬን እየነሰረኝ ብቻ ነው። በሌላውም ነገር ጥሩ ነው። ለሁሉም ኢየሱስ ያውቃል። ማሚ ስድሴ፣ የፃፍኩልሽ ደብዳቤ ደርሶሻል፣ አልደረሰሽም? ከደረሰሽ ለምን ዝም አልሽኝ? እመጣለሁ ብለሽኝ ነበር። ከቤተሰብ ቀን በኋላ አላየሁሽም። በብዙ ነገር ደስተኛ ባልሆንም ጌታ ያውቃል። አሁን ይቅርታ፤ ለመፃፍ ከፈቀዱት እየወጣሁ ነው። የመጀመሪያውን*



Sample output to test PDF Combine only

*የፃፍኩልሽ መልስ ለምን አልሰጠሽኝም? ቤተሰባችንስ የሚመጡት መቼ ነው? ለቤተሰቦች ስልክ ሲደወል ለኛ ቤተሰብ ግን አልተደወለም? ለምን አልደወላችሁም? «እኔ ከሌለሁ፣ ሰው እልካለሁ» ብለዋል:: የሚነበብ ደብዳቤ ማለትም ስለኔና ስለቤት ፅፌልሽ ነበር:: ሳነበው ያስለቅሰኛል::: ስለዚህ፣ «ኢየሱስ ያውቃል» ብዬ ቀደድኩትና መፀለይ ጀመርኩ:: ባልሆነ ነገር ብጐዳም፣ የሰውን ልብ የሚያይ አምላክ ሁሉንም ነገር ይየው:: ግን ቤተሰባችን ቢመጡ ደስ ይለኛል:: አመሠግናለሁ:: በዚህ ይብቃኝ::*

*ኢየሱስ አያዳላም፤ ሁሉንም ይወዳል::*
*ኢየሱስ ጌታ ነው::*
*ባይ! ባይ!*
*ኢየሱስ በነገር ሁሉ ከሁላችን ጋር ይሁን! አሜን!*





## -56-

*«ታማ ተይ ይቅርብሽ! ሲሻልሽ ትማሪያለሽ ስንላት፣ አልቅሳ ሄዳ ተፈተነች::»*
*ወ/ሮ ገነት ገብረጻድቅ*
*«በጣም ትፀልያለች፤ መጽሃፍ ቅዱስ ታነባለች:: እንደዛ አሟት ራሱ ግድግዳ አስደግፋ ነው የምታነበው:: በጣም የሚገርም ነው::»*
*ትዕግስት ቶሎሳ (ምግዚት)*

አመለዘውድ በትምህርቷ ጎበዝ ናት:: ለነገሩ እንኳን አሁን እሷ ብዙ መሯሯጥ ሳይኖርባት፣ የጣመና የላመ ምግብ ተዘጋጅቶ እየቀረበላት፣ ገና በፊት እናቷንና ወንድሞቿን የመንከባከብና የመመገብ ኃላፊነት በሕፃን ትከሻዋ ለመሸከም በተገደደችበት ወቅትም በትምህርቷ ውጤታማ ነበረች:: ደብተሮቿን በማጥናት ላይ ብቻ የምታተኩር ተራ ተማሪ ግን አልነበረችም::

ጥሩና አስተዋይ አንባቢ እንደሆነች ደብዳቤዎቿ ምስክር ናቸው:: በጆሮዋ ችግር ምክንያት ከሰው ጋር የበለጠ ለመግባባት የጀመረችው ደብዳቤ አዘውትሮ የመጻፍ ልምድ፣ ከንባብ ፍቅሯ ጋር ተደምሮ ራሷን በጽሁፍ በደንብ መግለጽ እንድትችል የረዳት ይመስላል:: ለማግኘት አትችልም ነበር እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ልብወለዶችና ሌሎች የስነጽሁፍ ስራዎች የማንበብ ዕድል ቢኖራት ኖሮ ምናልባት የተሻለ የቃላት አጠቃቀምና አገላለጽ ከደብዳቤዎቿ ማስተዋል በተቻለ ነበር::

ደብዳቤዎቿ ለምትጽፍላቸው ሰዎች ፍቅሯን፣ ደስታዋን፣ ቁጣዋን፣ ሐዘንና ጭንቀቷን . . . የምትተነፍስባቸው፣ ከንግግር ይልቅ አንጀቷን የምታርስባቸው የስሜት መግለጫዎቿ ናቸው:: በእርግጥም ደግሞ የተጻፈ ነገርን ደጋግሞ ማንበብ ስለሚቻል ከሷ ደብዳቤ የሚደርሳቸው ሰዎች ስሜትና ፍላጎቷን፣ ማስተላለፍ የፈለገችውን መልዕክት የበለጠ ይረዱላታል::

የእጅ ጽሁፏ በምትጽፍበት ጊዜ እንደሚያንገበግባት የስሜት ድባብ ከደብዳቤ ደብዳቤ የተለያየ ነው:: ጥልቅ ፍቅሯን ለመግለጽ የምትጽፋቸው ደብዳቤዎች ቀጥ ባሉ፣ ለዓይን በሚማርኩ፣ ለማንበብ በሚጋብዙ ውብ ፊደላት ትጽፋቸዋለች:: ጊዜ ካላት የተለያየ ቀለም በምትቀባቸው የአበባ ስዕሎች ታሸበርቃቸዋለች:: የልብ ቅርጽን እንደ ፍቅር መግለጫ ትጠቀማለች:: በቁጣ የምትጽፋቸው መልዕክቶች ፊደላቸው ወደ አንድ ጎን ገደድ ይላል፤ ተለቅ ተለቅም ታደርጋቸዋለች:: በፍጥነት የምትቸከችካቸው ይመስላሉ:: በደስታ ስሜት ተውጣ ስትጽፍ እንደ ጸሎት መጽሃፍ ስማያዊና ቀይ ብዕሮችን እየቀላቀለች ደብዳቤዋን አኀርጎርጉራ ታሳምረዋለች:: ታማ የምትጽፋቸው ደብዳቤዎች ደግሞ ፊደሎቻቸው ከፍ፣ ረዘም፣ ሰፋ ብለው ይታያሉ::



Sample output to test PDF Combine only

አመለዘውድ ከት/ቤት መቅረት አትወድም:: ህመሙ አልጋ ላይ የሚያውልና ከባድ ካልሆነ በስተቀር፣ እያመማት እንኳን ት/ቤት ትሄዳለች:: ደብተሮቿንም አዘውትራ ታጠናለች::

ግንቦት ወር 1997 ዓ.ም. ላይ ግን ህመሟ ፀንቶ ትምህርት ቤት መሄድ አቃታት:: ለመታከም ሆስፒታል መተኛት ነበረባት:: የሚከተለው ደብዳቤ ዘውዲቱ ሆስፒታል በተኛችበት ጊዜ ሆስፒታሉ በር ላይ ሆና ስድሴ የጻፈችላት ነው::

*ግንቦት 17/1997*

*ውድ አመለዘውድ፣*

*ላይሽ መጥቼ አንዴ ተኝተሻል:: አንዴ ደግሞ አላስገባ አሉኝ:: በጣም አዝናለሁ:: ቢሮ እየመሸብኝ ነው፤ ነገር ግን ሁሌም ፀልዬልሻለሁ:: ለነገሩ ስለልጆቼ፣ ስለሁላችሁም ሁሌም እፀልያለሁ:: ዛሬ የመንግሥት ቢሮ የሆነ ቀጠሮ ስላለኝ ሰዓቱ ረፈደ:: ከዛ ደግሞ ልትወጪ ስለሆነ ቤት እመጣለሁ:: አሁንም የበለጠ ጌታ እንዲፈውስሽ እፀልያለሁ::*

*ግን አመለዘውድ አትጨነቂ:: ጭንቀት ራሱ አንዱ መንስኤ ነው:: ደግሞ መጨነቅ የሚለውጠው ነገር'ኮ የለም፣ የኔ ልጅ:: ሁሉን ለሚችለው በርሱ ለሚያምኑ ማሰብ፣ መብሰልሰልና መጨነቅ የሰይጣን ማታለያ ነው:: በሃያሉ የሱስ የሚያምኑ፣ ሁሉን ለርሱ በማስረከብ ማረፍ አለባቸው:: «ሸክም የበዛባችሁ ወደኔ ኑ! በኔም እረፉ» ይላል:: ስለዚህ በሱ ላይ እረፊ::*

*ሌላ ደግሞ የቤተክርስቲያኑን ጉዳይ ስመጣ እንነጋገራለን:: በደንብ ሲሻልሽ ብንነጋግርስ? አይሻልም? ለማንኛውም ቅዳሜ እናንተ ጋር ፕሮግራም ስላለ እዛው እውላለሁና እናወራለን::*

*እስከዛው ግን የኔ ቆንጆ! ራስሽን አታስጨንቂ፣ አትረብሺ:: ለማንኛውም ቻዎ:: ጌታ ይባርክሽ! ካንቺ ጋር ይሁን!*

*ያንቺው*
*ማሚ ስድሴ*

አመለዘውድ በሆስፒታል ስትረዳ ቆይታ ወደ ህጻናት ማሳደጊያው ተመለሰች:: ግን አሁንም ከአልጋ መነሳትና መንቀሳቀስ ከበዳት:: ተኝታም



Sample output to test PDF Combine only



ሻል ያላት ሲመስላት ደብተሮቿን ከማገላበጥና ከማንበብ ግን አልቦዘነችም:: ከደብተሮቿ ጎን ለጎን መጽሃፍ ቅዱስ ታነባለች:: መጽሃፍ ቅዱስ ስታነብ የምትድን ይመስላት ነበር:: በእጇ መያዝ ባትችል እንኳን መጽሃፍ ቅዱሱን ግድግዳ አስደግፋ ታነባለች:: ተግታ ትፀልይም ነበር:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለች የፈተና ጊዜ ደረሰ:: አመለዘውድ ስታስበው በሚቀጥለው ዓመትም ሶስተኛ ክፍል ልትማር ነው::

'ሶስተኛ ክፍልን አራት ዓመት ልማር?! . . . እንደዛማ አይሆንም!' ብላ አሰበች፣ በቁጭት ከንፈሯን እየነከሰች::

ገና ኮተቤ ከእናቷ ጋር ስትኖር ሶስተኛ ክፍልን በብቃት ተምራ ወደ አራት አልፋ ነበር:: ቡታጅራ ለሁለተኛ መንፈቀ ዓመት ትምህርት ስለነበር የደረሱት ሶስተኛ ክፍል መግባቷ ግድ ሆነ:: በህመም ምክንያት ሴሚስተሩን አልጨረሰችም:: አሁን ያለችበት የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅቱ እንደ አዲስ ተቋቁሞ ትምህርት እንዲቀጥሉ ሲወሰን፣ ወደ አራተኛ ክፍል ማለፏን የሚጠቁም የትምህርት ማስረጃዋ በእጇ አልነበረም:: የትምህርት ማስረጃ የሌላቸው ልጆች ተፈትነው ወደሚመጥናቸው ክፍል እንዲገቡ ነበር የተወሰነው:: አመለዘውድ ትምህርት አቋርጣ ስለቆየች፣ ለአራተኛ ክፍል የተዘጋጀው ፈተና ሊከብዳት እንደሚችል ስለታሰበ፣ ለሶስተኛ ክፍል የተዘጋጀውን ፈተና እንድትወስድ ተወሰነ:: እሷም አልተቃወመችም:: ፈተናውን አልፋ ሶስተኛ ክፍል ገባች:: ያለፉትን ስምንት ወራት ከህመሟ ጋር እየታገለች ትምህርት ቤት ተመላለሰች:: ዓመቱ ማለቂያ ላይ ግን ብትታገልም ት/ቤት ተመላልሶ መማር የሚያሙለጨልጭ ገደል እንደመውጣት አዳጋች ሆነባት፤ አልቻለችም:: ህመሟ አሸንፏት የአልጋ ቁራኛ ሆነች::

አመለዘውድ ለሌላ አራተኛ ዓመት ሶስተኛ ክፍልን መማር በጭራሽ አልፈለገችም:: ቢያማትም ለመፈተን ወሰነች:: አብሮ አደጎቿን እነእሙሻን፣ እነፋይልን አሰበች:: ካልወደቁ እነሱ ስምንተኛ ወይም ዘጠነኛ ክፍል ይደርሳሉ:: እሷ ግን ብሩህ ጭንቅላት፣ ከፍተኛ የመማር ፍላጎትና ጉጉት እያላት፣ ታማሚ ስለሆነች በሰላም መማር አልቻለችም:: ይህ ዕጣ ፈንታዋ ብዙ ጊዜ ያሳዝናታል:: ተምራ ትልቅ ደረጃ ላይ የመድረስ፣ ለቤተሰቦቿ አለኝታ ከመሆን አልፋ እንደእሷ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆችን ድርጅት አቋቁማ የመርዳት ህልምና ዓላማ ነበራት:: ግን ጤና ሳይኖራት ይህ መልካም ራዕዩዋ ዕውን ይሆናል?

የፈተና ጊዜ በቀረበበት ወቅት አንድ ቀን ገነት እሷ የምትኖርበት ግቢ ስትመጣ፣ «ገኒ፣ ፈተና መፈተን እፈልጋለሁ::» አለቻት::

«የምን ፈተና?»

«የትምህርት ቤት ነዋ»
«እንዲህ እያመመሽ?!»
«አይ መፈተን አለብኝ:: በሚቀጥለውም ዓመት ሶስተኛ ክፍል መሆን አልፈልግም::»
«ሲሻልሽ፣ ጤነኛ ስትሆኚ ትማሪያለሽ::»
«አይ መፈተን አለብኝ:: እፈተናለሁ!»
«እንዲህ እያመመሽ?! ኧረ አይሆንም:: ፈተናውን ስትፈተኚ ቢያምሽስ?»
«አያመኝም:: ቢያመኝም እንደምንም ፈተናውን መሥራት አያቅተኝም::» የመጨረሻው ቃል በለቅሶ ሳግ የተዋጠ ነበር፣ ማልቀስ ጀመረች::

ወ/ሮ ገነት ደነገጠች፣ ግራም ገባት::
«እንዴ ለምንድነው የምታለቅሺው?»
«አብሮ አደግ ጓደኞቼ የትና የት ደርሰዋል:: እኔ ግን ገና ሶስተኛ ነኝ:: ሶስተኛን በሚቀጥለውም ዓመት ደግሜ መማር አልፈልግም::» ዕንባዋ ከዓይኖቿ ሲፈልቅ ከስር ከስር ብትጠርገውም፣ እየተንፎለፎለ ወረደ::

«በቃ! በቃ! አመለዘውድ በቃ ትፈተኚያለሽ» ወ/ሮ ገነት እጇን የአመለዘውድ ቀጭን ትከሻ ላይ አሳርፋ ልታባብላት ሞከረች::
«ትምህርት በጣም እወዳለሁ፤ ግን መማር አልቻልኩም:: እናቴ ስትታመምብኝ ለሷ ስል አቋረጥኩ:: አሁን ደግሞ መማር በምችልበት ጊዜ ያመኛል::» ተንሰቀሰቀች::

ወ/ሮ ገነት አዘነችላት:: የእሷም ዓይኖች በዕንባ ተሞሉ:: «በቃ ትፈተኛ ለሽ አልኩሽ'ኮ አመለዘውድ! በቃ ዝም በይ!»

አመለዘውድ በቀላሉ የምትፅናና አልሆነችም:: . . .

ለመፈተን በመቁረጧ ስድሴም ፈቃዷን ለመሙላት ወሰነች:: የኮንትራት ታክሲ በፈተናው ቀን ት/ቤቷ ድረስ እንዲያደርሳት ተደረገ:: ህመሟን ችላና ጥርሷን ነክሳ ፈተናውን ተፈነች:: ስላጠናች፣ የታመመችው ግንቦት ወር ላይ ስለነበረና ትምህርት ብዙም ስላላመለጣት ፈተናው አልከበዳትም::

የትምህርት ቤት የውጤት ካርድ የምትቀበልበት ቀን በተቃረበበትም ጊዜ ልቧ ጤነኛ ባልሆነ ሁኔታ ይመታባትና አቅም ያንሳት ነበር::

*ለውድ እናቴ ገንዬ እንደምን ዋልሽ? እኔ ደህና ነኝ:: ገንዬ፣ ቅድም ላናግርሽ ነበር ቶሎ ሄድሽ:: ልትሄጂ ስትይ፣ «ገንዬ!» ስልሽ አልሠማሽኝም:: ቸኩለሽ ነበር መሰለኝ:: አሁን ወደ ንግግር እሄድና ገንዬ ማንጐ የሚጠጣ ሳይሆን ፍሬውን ለይድነቃቸው ማታ ላኪልኝ::*



Sample output to test PDF Combine only



*ገንዬ፣ ይኼን፣ ይኼን ላኪልኝ ስልሽ አስቸርግሻለሁ ብዬ በጣም እፈራለሁ:: አንቺ ስለምትወጂኝ፣ ላስቸግርሽ ደስ አይለኝም:: ገንዬ፣ እሁድ ካርድ ስለሚሠጥ ት/ቤት ልሂድ ወይ? ትንሽ እንደሄድኩ ልቤ ድው፣ ድው ይላል፣ ጉልበቴም ይንቀጠቀጣል:: በኋላ በር ያለውን ደረጃ ስወጣ ልቤ ድው፣ ድው ይላል:: ጌታ ኢየሱስ ያድነኛል! ማታና ጠዋት እየፀለይኩና መፅሐፍ ቅድስ እያነበብኩ ነው! በቃ ቻው!*
*ማንጐውን ለይርኔ ላኪልኝ!*

*ቻው*

*ማሚ ስድሴ ካለች ሠላም በይልኝ::*
*እወድሻለሁ ገንዬ!*
*ቻው ቻው*

የሚከተለው አጭር መልዕክቷ ደግሞ የት/ቤት ሪፖርት ካርድ በተቀበለችበት ቀን ማግስት በጥድፊያ የጻፈችው ይመስላል::

*በጣም የምወድሽ ገነት፣ እንደምን አለሽ? ሙዝ ላኪልኝ! ልቤን ያቃጥለኛል:: 5ተኛ ወጥቻለሁ፤ በትምህርት::*

*ቻው ቻው መኪና ሊሄድ ስለሆነ ነው::*

ከላይ በአጭር መልዕክቷ እንደገለፀችው አመለዘውድ በሁለተኛ ሴሚስተር ሰባተኛ፣ በሁለቱ ሴሚስተሮች አማካይ ውጤት ደግሞ አምስተኛ ወጥታ ወደ አራተኛ ክፍል አለፈች:: ውጤቷ ስድሴን፣ ወ/ሮ ገነትን፣ ሞግዚቶቿንም፣ ሌሎች የሚያውቋት ሰዎችን ሁሉ የሚያስደንቅና የሚያስደስት ነበር::

አመለዘውድ ወደ አራተኛ ክፍል በማለፏ ብትደሰትም፣ ጤነኛ ብትሆን ደግሞ የተሻለ ደረጃ ሊኖራት እንደሚችል አስባ መቆጨቷ አልቀረም::

*ለውድ እናቴ ማሚ ስድሴ፣ እንደምን ነሽ? እኔ አሁን በጣም ደህና ነኝ:: ሠሞኑን ገነት ከቤቷ የምፈልገውን እያመጣችልኝ ስበላ፣ ስበላ በደንብ ተሻለኝ:: መርፌም 14 ጨረስኩ:: አሁን ልቤን ብቻ ያቀጥለኛል እንጂ ጤነኛ ሆኛለሁ:: እግዚአብሔር ይመስገን! አሁን በፊት ለልጆቹ ልብስ ሲሰጥ ለኔ ሠፍቶኝ፣ ገኒ ትንሿ*[1]፣ «ሌላ ከዚህ ስጪኝ» ብያት ነበር:: «እሺ» ብላኛለች:: እሷ ስትመጣ ተቀብዬ ወደ*

*ቤት ለመሄድ ፈልጌያለሁ:: ሲ/ር ጤና*[2]፣ «ትምህርት*[3] አለ:: በጣም ካላመመሽ ተማሪ» ብላኛለች:: እኔም መማር ፈልጌአለሁ:: ደግሞ የወጣሁት 7ተኛ ነው:: አያሳዝንም?! ለመሆኑ ሽልማት 1-5 ነው ተብሏል? ከባልቻና ከእታገኝ ሌላ ማንም አይሸለምም ማለት ነው? ለሁሉም እግዚአብሔር ያውቃል::*

*[1] በድርጅቱ የምትሰራ ሌላ ገነት የምትባል ወጣት የቢሮ ሠራተኛ ለለች::*
*[2] ሲ/ር ጤና የህጻናት ማሳደጊያ ድርጅቱ ነርስ ነበረች::*
*[3] በክረምት ግቢው ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት ነበር::*







## -57-

*«ማሚ ሰድሴ፣ እኔ'ኮ በጣም እወድሻለው፣ ግን ደስተኛ አይደለሁም::»*
*አመለዘውድ*

አመለዘውድ በ1997 ዓ.ም. ክረምት ብዙም ጤና አልነበራትም:: እኔም (የዚህ መጽሃፍ ፀሐፊ) ነሐሴ ውስጥ ሳገኛት በጣም ባትደክምም የአልጋ ቁራኛ ነበረች:: ልቤንና ጨጓራዬን ያቃጥለኛል፣ ጎኔን ይወጋኛል፣ ራሴን ያመኛል . . . ማለት ታዘወትር ነበር:: የሰውነቷም ክብደት እየቀነሰ ነበር:: ለጤና ችግሯ መፍትሄ አለመገኘቱ ብስጩ ያደረጋት ይመስላል።

*ለምወድሽ እናቴ ማሚ ሰድሴ፣ ለጤናሽ እንደምን አለሽ? እኔ በጣም ደና ነኝ:: እኔ በጣም እወድሻለሁ! አንቺም በጣም እንደምትወጂኝ አውቃለሁ:: ጌታ ይባርክሽ! ከሠላምታዬ ቀጥሎ የማሳስብሽ ነገር ቢኖር እንደሚከተለው ይሆናል:: ማሚ፣ ልቤን በጣም ለሞኛል:: ያልበኛል፣ ያቃጥለኛል፣ መብላትም አልቻልኩም:: ጮክ ብሎ መናገር አልቻልኩም:: ያመኛል፤ በደንብ መተንፈስ አቅቶኛል:: ብዙ ጊዜ ነገርኩሽ፤ ዝም አልሽኝ:: ምንድን ነው ነገሩ? ምግብ ባለመብላቴ ኪሎዬ በጣም ቀንሶአል:: በፊት 34 ኪሎ ነበርኩ:: አሁን 29 kg ሆኛለሁ:: ሣይብስብኝ ለቤተሰቤ ንገሪልኝ:: እንደውም አሜሪካ ከመሄዳቸው በፊት፣ «እንሄዳለን» ብለው ነግረውኛል:: እባክሽን ከመሄዳቸው በፊት እንደሚያመኝ አሳውቂያቸው:: ነገር ግን ከ2 ወር በኋላ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ:: ቤታቸው አዲስ አበባ ኮተቤ ነው:: ልጆቻቸው አሜሪካ ስለሆኑ ነው:: በጣም ለሞኛል:: መቀመጥ አልቻልኩም:: ለሰው ደና ሆኜ የምታየው ችዬው ነበር:: አሁን ግን አልቻልኩም:: ስታይኝ ደና እመስልሻለሁ፤ ውስጤን እንዴት እንደሚያመኝ እኔ አውቃሁ:: ያቺኛዋ ማሚ ሣትሄድ በፊት ነው የጀመረኝ:: ስለዚህ ይብስብኛል ብዬ እፈራለሁ:: እና ለቤተሰቤ ንገሪልኝ:: በተረፈ ጌታ ይባርክሽ! ማሚ ቻው፣ ቻው:: እባክሽን ያልኩሽን ቶሎ ፈጽሚልኝ! ጆሮዬንም ይበላኛል:: ከሣምንት በፊት ውሃ የሚመስል ነገር ወቶ ነበረ:: አሁን ግን የለም:: ይበላኛል፤ ዝንብሎ:: በቀደም ለቤተሰቤ ላስረዳቸው ነበር:: መጀመሪያ ለእናቴ ማሚ ልንግራት ብዬ ነው:: በዚህ አበቃሁ::*

ሰድሴ ሁለተኛ ዲግሪዋን እንደያዘች ሰምታ በጻፈችው ሌላ ደብዳቤም ክብደቷ መቀነስ መቀጠሉን ገልጻለች:: ከደብዳቤው በላይ ያስፈረችው ጥቅስ የእግዚአብሔርን ምህረት በትዕግስት ለመጠበቅ ዝግጁ እንደሆነች የጠቆመችበት ይመስላል:: ብዙዎቹ ደብዳቤዎቿ ላይ የምታስፍራቸው የመጽሃፍ ቅዱስ ጥቅሶች፣ እንደእሷ በቀላሉ በማይድን በሽታ ለሚሰቃዩ ሰዎች ትርጉም የሚሰጡ ዓይነቶች ናቸው::

*07/12/97*

*እግዚአብሔር ለሚታገሱት ሁሉ ቸር ነው።*

*ለውድ እናቴ ማሚ ሰድሴ ለጤንነትሽ እንደምን አለሽልኝ? እኔ አሁን ተሽሎኛል ግን ምግብ በደንብ አልመገብም። ለምን መሰለሽ? ትንሽ እንደበላሁ ሆዴን ያመኛል። ደግሞ ራሴን ያዞረኛል። ምንም ቢሆን እግዚአብሔር ማመስገን ይገባኛል አይደል? እንዳመመኝ፣ 'ብሞትስ' እያልኩ አስባለሁ። ኪሎዬ በጣም ቀንሷል። በመጀመሪያ 30 ነበር፤ ከዛ 29 ሆነ። አሁን ግን 24 ሆኖአል። ማሚ ሰድሴ፣ ቤተሰባችን ለምን አይመጡም? ከመጡ'ኮ በጣም ቆይተዋል። ለእንቁጣጣሽም ላይጠይቁን ነው? ለመሆኑ ቶሎ፣ ቶሎ እንደሚያመኝ ያውቃሉ? በጣም ይናፍቁኛል። በተለይ የእመቤቴ አባት ማለትም የወ/ሮ ማርታ ገ.ፃዲቅ ባለቤት ደመቀ ተክለወልድን በጣም እወዳቸዋለሁ። ብታይ አይቆጡ፣ ሁሌ በመሳቅ ያስቁን ነበር። ማሚ ሰድሴ፣ በመጀመሪያ ልፅፍልሽ የፈለኩት በመመረቅሽ ደስታዬን ለመግለፅ ነው። እንኳን ደስ አለሽ! አዲሱ ዓመት መልካም የሥራ ዘመን እንዲሆንልሽ ከልብ የምመኝልሽ ልጅሽ አመለዘውድ ነኝ። ማሚ ሰድሴ፣ እኔ'ኮ በጣም እወድሻለው፣ ግን ደስተኛ አይደለሁም።*

*በተረፈ ቻው*
*ቻው*




አመለዘውድ ትንንሾቹ ህጻናት ወደሚኖሩበት፣ የድርጅቱ ቢሮ ወዳለበት ግቢ ለመምጣትና ለወ/ሮ ገነት ለሰድሴና ቅርብ ለመሆን ከፍተኛ ፍላጎት ነበራት። ወ/ሮ ገነት የአመለዘውድን ፍላጎት ለሰድሴ ነገረቻት። ትንንሾቹ ህጻናት ቢሮው ያለበት ግቢ እንዲኖሩ የተደረገው የቅርብ ክትትልና እንክብካቤ ስለሚያስፈልጋቸው ነው። ሰድሴ አመለዘውድ በጸና መታመሟን ስለምታውቅ በቅርብ ሆነው ለመንከባከብ እንዲመቻቸውም ቢሮው ወዳለበት ግቢ መምጣቷ ተገቢ እንደሆን ስላመነች እንድትመጣ ወሰነች።

«ለሰድሴ ነግሬያት እሺ ብላለች» ብላ ወ/ሮ ገነት የምስራቹን ስትነግራት፣ አመለዘውድ ጋደም ካለችበት ድንገት ተፈናጥራ ተነስታ የወ/ሮ ገነትን አንገት በሁለት እጇቿ እንቅ አድርጋ ይዛ ልጥፍ አለችባት። ወ/ሮ ገነት ያመጣችው ዜና አመለዘውድን ይህን ያህል እንደሚያስደስታት ስላልጠበቀች ተገረመች።





«ገንዬ! በጣም ደ . . . ስ አለኝ!» ዕድሜ የሚቀጥል ዓይነት ደስታ ነበር የተደሰተችው።

ወ/ሮ ገነትም የሷን ደስታ ስታይ ልቧ በሀሴት ተሞላ።

አንድ ክፍል ከተዘጋጀላት በኋላ የአስተዳደር ሠራተኞች ቢሮ ወዳለበት ግቢ እንድትመጣ ተደረገ። አመለዘውድ ወ/ሮ ገነትን እንዲሁም ሰድሴን በየቀኑ ያውም በተደጋጋሚ ማግኘት በመቻሏ ደስተኛ ሆነች። እንዲገዛላት የምትፈልገው ነገር ካለም የድርጅቱ ሹፌር ይድነቃቸው እስኪመጣ ጠብቃ ደብዳቤ መላክ አላስፈለጋትም። ከቻለች ወደ ቢሮ አዝግማ፣ ካልቻለች አጠገቧ ሆነው የሚንከባከቧትን ሞግዚቶቿን ልካ ይሄ ወይም ያ ይገዛልኝ ትላለች። እዚህ መኖር በብዙ መልኩ ቢመቻትም፣ አንዳንዴ ግን በሌላኛው ግቢ ያሉ ልጆች ይናፍቋታል።

*እናቴ ገንዬ፣ እታችኛው ቤት መሄድና መቆየት አልፈልግም። ከአንቺ ጋር እዚህ መሆን ነው የምፈልገው። እዚህ አንቺን ሁሌ አገኝሻለሁ። የኔ ደስታ አንቺን ሁሌ ማየት፣ አንቺ ጋር ቢሮ መሆን፣ ከልጆቹ ጋር መሆን ነው። ግን ይድነቃቸው ሲመጣ አንድ ጊዜ እታች ቤት ልሂድና አይቻቸው ልምጣ፤ ፍቀጂልኝ። ሲመለስ እመጣለሁ። እታገኝና ትነበብን እወዳቸው ነበር። ናፈቁኝ። አንዴ ሄጄ ከይርኔ ጋር ተመልሼ እመጣለሁ። እዚህ መሆን ደስ ይለኛል። ገንዬ፣ ትፈቅጃለሽ? እወድሻለሁ። ደግሞ ማታ አንተነህ* ዳቦ 2 ገዝቶልኛል። አንቺን ላስገዛ ስመጣ የለሽም ነበር። እሱ፣ «እኔ እገዛልሻለሁ» ብሎ ገዛልኝ። ስለዚህ ሳንቲሙን መልሼለት። በተረፈ*

*ቻው*
*ቻው*

**አንተነህ የትንንሾቹ ልጆች መኖሪያ ግቢ የጥበቃ ሠራተኛ ነው።*

ወደ ጓደኞቿ በየጊዜው መሄድ ስለማትችል፣ ከሌላኛው ግቢ እንዲላክላት ወይም እንዲደረግላት የምትፈልገው ነገር ሲኖር ለእነሱም አጠር ያሉ መልዕክቶች ጽፋ ትልክላቸዋለች።

*ለውድ እህቶቼ ትነበብና እታገኝ፣ ከተለያየንበት ጊዜ ጀምሮ ለጤንነታችሁ እንደምን አላችሁ? እኔ በጣም ደህና ነኝ። የፀጉር ጌጥ ማስቀመጫ ውስጥ ያለውን ቃሪያ የሚመስለውን የጆሮ ጌጥ ላኩልኝ። በወረቀት አድርጋችሁ ለይድነቃቸው ስጡልኝ። ደግሞ መነፅሬን ፈልጋችሁ፣ ማለትም ቁም ሳጥኔ ውስጥ ወይም ከአልጋዬ አጠገብ ያለው ሳጥን ውስጥ፣ ፈልጉት። ካገኛችሁት እናንተ ጋር ይቀመጥ። ካላገኛችሁት ፃፉልኝ። ካገኛችሁት እናንተ ጋር አስቀምጡልኝ። በተረፈ ስለትብብራችሁ ጌታ ይባርካችሁ!*



Sample output to test PDF Combine only

## -58-

*«መድኃኒቶቹን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትወስድ እጅግ በጣም ተደስታ ነበር::»*
*ሄኖክ (ወርልድ ዋይድ ኦርፋንስ ፋውንዴሽን)*

በ1997 ዓ.ም. ነሐሴ መጨረሻ ላይ በህጻናት ማሳደጊያው ውስጥ ያሉ ህጻናት በሽታ የመከላከል አቅማቸውን በማጎልበት የጤናቸውን ሁኔታ የሚያሻሽሉ የፀረ-ኤድስ መድኃኒቶች ማግኘት ችለው ነበር:: ለአመለዘውድ ግን መድኃኒቶቹ በጣም ዘግይተው ነበር የደረሱት::

የመኖርና ጤነኛ የመሆን ጉጉቷ ከፍተኛ ስለነበር ለመጀመሪያ ጊዜ በወርልድ ዋይድ ኦርፋንስ ፋውንዴሽን በተባለ የአሜሪካ ድርጅት ኢትዮጵያዊ የህክምና ባለሙያዎች ድጋፍ የፀረ-ኤድስ መድኃኒቶቹን ስትወስድ ፊቷ ላይ ፈገግታ የማይታይበት ጥግ አልነበረም:: እጅግ በጣም ተደስታ ነበር:: ፍንክንክ! ፍንድቅድቅ ብላ ነበር:: እንደምትድን ተስፋ አድርጋ ነበር:: . . . ነበር . . . ነበር . . . ነበር::


በድንገተኛ ኃይለኛ የደም ግፊት ምክንያት እጆቿን መጠቀም አቃታት:: እግሮቿም አልታዘዝ አሏት፤ ያለሰው ድጋፍ መራመድ ተሳናት:: በ1998 ዓ.ም. ጥቅምት መጀመሪያ ላይ ህመሟ ፀንቶባት ዘውዲቱ ሆስፒታል ተኛች::

ደብዳቤ መፃፍ የማይታክቱት ቀጫጭን ጣቶቿ ከአእምሮዋ ጋር ጥሩ ቅንጅት መፍጠር እስኪሳናቸው፤ ብዕሩን ጨብጠው መያዝ እስከሚያቅታቸው ህመሟ ከባድ ነበር:: ከዚህ የሚከተለው አጭር መልዕክት በብዙ ትግልና ስቃይ መስመሮቹን ስታና ቃላቶቹን አደራርባ እንደነገሩ ፅፋዋለች:: ፊደሎቹ ከሌሎች ደብዳቤዎቿ በተለየ ሁኔታ ትልልቅ ናቸው:: ይህቺን አጭር መልዕክት ለመፃፍ ብዙ እንደደከመች በቀላሉ መረዳት ይቻላል:: አንድ ፊደል ለመጻፍ ብዕሯን ወረቀት ላይ ማንሸራተት እጅግ ከባድ ነገር የመግፋት ያህል ፈታኝ እንደሆነባት የፊደል አጣጣሏ ይመሰክራል:: ይህን ያላለቀ መልዕክት ለመጻፍ ያላትን ትንሽ አቅም አንጠፍጥፋለች:: በመጨረሻም አቅቷት ትታዋለች::

*(ተጀምሮ ያላለቀውን የአመለዘውድ ደብዳቤ በሚቀጥለው ገጽ ይመልከቱ::)*







ደርቆ የተጨማተረን አበባ በውሃ የተሞላ የአበባ ማስቀመጫ ውስጥ በማስቀመጥ ውበቱንና ወዘናን መመለስ ለሰዎች እንደማይቻላቸው ሁሉ፣ አመለዘውድ በኤድስ እጅግ ስለተጎዳች ሆስፒታል ተኝታ ያገኘችው የህኪም ዕርዳታ በጤናዋ ላይ የፈጠረው ለውጥ አልነበረም::



Sample output to test PDF Combine only

## -59-

*«ፀጥ ብላለች:: አወቅኩ::»*
*ወ/ሮ ገነት ገብረጻድቅ*
*«ኤድስ ከባድ በሽታ መሆኑን የበለጠ ያወቅኩት*
*አመለዘውድን ካየሁ በኋላ ነው::»*
*ይድነቃቸው አሰለ*

ህዳር 21፣ 1998 ዓ.ም. ጠዋት ነጻ የህክምና ምርመራ አገልግሎት ለልጆቹ በመስጠት ከአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት ጋር በቅርበት የሚሰራው የወርልድ ዋይድ ኦርፋንስ ፋውንዴሽን ሐኪም ዶ/ር ሶፊያ መንግስቱ አመለዘውድን ልትመረምራትና ያለችበትን ሁኔት ልታይ የአልጋ ቁራኛ ሆና ወደተኛችበት የትንንሾቹ ህጻናት ግቢ መጥታ ነበር:: ዶ/ር ሶፊያ ስትመረምራት አመለዘውድ ራሷን አታውቅም:: ዶክተሯ ከክፍሉ ከወጣች ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወ/ሮ ገነት ወደ ክፍሉ ገባች::

«አመለዘውድ፣ እንዴት አደርሽ?» አመለዘውድ መልስ እንደማትሰጣት ብታውቅም ልታናግራት ሞከረች::

ባልተለመደ ሁኔታ ፀጥ ማለቷን አስተዋለች:: የሚከብድና የሚያስፈራ ግርማ ያለው ፀጥታ በአመለዘውድ እጅግ የመነመነ ሰውነት ላይ ረብቧል:: እንደሞተች አወቀች:: ያልጠበቀችው ነገር አልነበረም:: አመለዘውድ የነበረችበትን ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ባለፉት በርካታ ቀናት አይታለች:: ቀደም ሲል አመለዘውድ እግዚአብሔር እንደሚምራትና እንደምትድን ታምን ነበር:: ያ እምነቷ ግን ባለፉት ሳምንታት ባየችው ከቀን ወደቀን እየባሰ በመጣው የአመለዘውድ የጤና ችግር ተሸርሽሯል:: ከአንድ ሳምንት በፊት ዘውዲቱ ሆስፒታል ተኝታ እየታከመች ነበር:: እዚያ ያሉት ሐኪሞች ህይወቷን ማቆየት እንደማይችሉ ስለተገነዘቡ ነበር ከሆስፒታል እንድትወጣ የወሰኑት::

'ጤነኛ ብትሆን ኖሮስ? . . . በሕይወት መቆየት ብትችል ኖሮስ? . . .' ስትል አሰበች::

ለመኖር የነበራትን ጉጉት፣ ለወንድሞቿ የነበራትን ፍቅር፣ ሌሎች ህጻናትንም ለመገሰጽና ጥሩ ልጆች እንዲሆኑ ለማድረግ ምን ያህል ትደክም እንደነበር አስታወሰች:: ሞት ለታማሚዋ ትልቅ እረፍት ቢሆንም አዘነች:: ነፍሷ በዚህች ዕለት ወደ ገነት እንደገባች ከልቧ አመነች:: እምነቷ አጽናናት:: አመለዘውድ ማረፏን ለዶክተሯ ልትነግራት በእርጋታ ከክፍሉ ወጣች::



Sample output to test PDF Combine only



በዶ/ር ሶፊያ መንግስቱ የተዘጋጀው የአሟሟቷን ሁኔታ የሚያስረዳ ሰርተፊኬት አመለዘውድ ከማረፏ በፊት ለሁለት ወራት የፀረ-ኤድስ መድኃኒት እንደወሰደች ይገልጻል:: በተደጋጋሚ በተለያዩ በሽታዎች በመጠቃቷ እጅግ መጎዳቷንና በዚህም ምክንያት መድኃኒቱ ውጤታማ ሊሆን ባለመቻሉ እንዳረፈች ይጠቁማል:: በማጅራት ገትር (ማኒንጃትስ)፣ በሳምባ ነቀርሳ (ቲቢ)፣ እንዲሁም በሌሎች የባክቴሪያ ኢንፌክሽኖች ትሰቃይ እንደነበረ በሰርተፊኬቱ ላይ ተብራርቷል::

* * *

ህዳር 21፣ 1998 ዓ.ም. ረፋድ ላይ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ድህረ ምረቃ ት/ቤት ሆኜ (የመጽሐፉ ፀሐፊ) በአድራሻዬ የተላከልኝን ከስድሴ የተላከ ኢ-ሜይል አገኘሁ:: የአመለዘውድን መሞት የሚያረዳና ቀብሯ በዚያው ዕለት ከሰዓት በኋላ እንደሚፈጸም የሚገልጽ መልዕክት ነበር:: በጽኑ መታመሟን ብሰማም ደነገጥኩ፣ አዘንኩም:: ቀብሯ ላይ ለመገኘት የአፍሪካ ወላጆቻቸውን በኤች.አይ.ቪ. ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት የአስተዳደር ሠራኞች ቢሮ ወደሚገኝበት ግቢ ስደርስ ስምንት ሰዓት አልፎ ነበር::

ከአንድ ወይም ከሁለት ወር በፊት በተከራዩት አዲስ ግቢ በሚገኘው ሁሉንም የአስተዳደር ሠራተኞች በሚይዘው ሰፊ ቢሮ ውስጥ የሃዘን ደመና አንዣብቧል:: ወ/ሪት ስድሴና ወ/ሮ ገነት ሌሎችም የአስተዳደር ሠራተኞች ቢሮ ነበሩ:: ብዙም ሳይቆይ ይድነቃቸው ሚኒባሱን እየነዳ ወደ ግቢው ገባ::

ከግማሽ ሰዓት በኋላ በደማቅ የአበባ ጨርቅ የተለበጠ የሬሳ ሳጥን ይድነቃቸው ከሌላ አንድ ሰው ጋር ይዞ ወደ መኪናው ሲሄድ ላግዛቸው ሮጥ ብዬ የሳጥኑን ግርጌ ያዝኩ:: ባዶውን ሳጥን የመያዝ ያህል እጅግ ቀላል ነበር:: ደነገጥኩ:: ሳጥኑ ባይከብዳቸውም ለሶስት ሚኒባሱ ውስጥ አስገባነው::

ስድሴ፣ ክብነሽ፣ ወ/ሮ ገነት፣ አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ሞግዚቶች ሌሎች የአስተዳደር ሠራተኞችን የያዘው ሚኒባስ መካኒሳ አቦ ቤተክርስቲያን ወሰደን:: ሚኒባስ መኪናው ውስጥ የነበሩት ብዙዎቹ ሞግዚቶች ያለቅሱ ነበር:: የሚኒባሱ ወለል ላይ የተቀመጠውን ሳጥን አንድ ሁለቴ ዞር ብዬ አየሁት:: ሬሳ በተጫነበት መኪና ስሄድ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነበር:: እውስጡ አስደናቂና ውብ ፈገግታ የነበራት፣ ማራኪ ደብዳቤዎችን ትጽፍ የነበረች፣ ኤድስ በተባለ በሽታ ለዓመታት ስትሰቃይ የኖረች ልጅ . . . ሬሳ በፀጥታ መጋደሙን ሳስብ እጅግ አዘንኩ::

ያንን ውብ ፈገግታዋን ደግሜ አለማየቴ ቆጨኝ:: ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ ከተገናኘንበት ቀን በኋላ በህጻናቱና በአመለዘውድ ሁኔታ ተረብሼና ስሜቴ ተነክቶ ነበር:: ይህንኑ የተረዳችው ስድሴ አመለዘውድ ከአንድ ወር በኋላ ዘውዲቱ ሆስፒታል መተኛቷን ሰምቼ ልጠይቃት ብፈልግም፣ «ግድ የለም አሁን ባታያት ይሻላል:: ባይሆን ከሆስፒታል ስትወጣ ታያታለህ::» ብላኝ ነበር:: አመለዘውድ ከዚያ በኋላ ብዙም ጤና አላገኘችም:: እኔም ትምህርት ሲያሯሯጠኝ ዛሬ፣ ነገ ሥል እነሆ በመጨረሻ ሞት ወሰዳት::

መካኒሳ አቦ ቤተክርስቲን የመቃብር ቦታ ስንደርስ በሁለት መቃብሮች መሀል ባለች አንድ ሳጥን ብቻ በምታስቀምጥ ጠባብ ቦታ ላይ ጉድጓድ ተቆፍሮ ነበር የጠበቀን:: ጥቂት ሞግዚቶች ቀድመውን ደርሰዋል:: ትልልቆቹ ልጆች ከሚኖሩበት ግቢ የመጡ ሞግዚቶች ነበሩ:: የአመለዘውድ ታናሽ ወንድም ሚካኤል ከሌሎች ሁለት በህጻናት ማሳደጊያው ከሚኖሩ ወንዶች ልጆች ጋር ከጉድጓዱ ራቅ ብሎ በፀጥታ ቆሟል::

መኪናው ውስጥ ሳጥኑን ያስገባነው ሶስታችን ሳጥኑን ይዘን ወደ ጉድጓዱ ቀረብን:: ሳጥኑ ትንሽ ስለረዘመ ጉድጓድ ቆፋሪዎቹ ጉድጓዱን አስተካክለው ቆፈሩት:: ባልሳሳት ትንሽ ልጅ እንደሆነች ነበር መቃብር ቆፋሪዎቹ የተነገራቸው::

አንድ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር መኪና እኛ ደርሰን ብዙም ሳንቆይ መጣ:: ከውስጡ አንድ ቀይ ረጅም ግርማ ሞገስ ያላቸው ሴት ወጡ:: በወቅቱ ማንነታቸውን ባላውቅም ወ/ሮ ማርታ ነበሩ:: ፀጉራቸውና ሪዛቸው በሽበት ያማረ አንድ ዓይነ-ግቡ አዛውንትም አብረዋቸው ነበሩ:: ባለቤታቸው አቶ ደመቀ ናቸው::

ጥቂት ሞግዚቶች፣ «ወይኔ አመለዘውድ! አመለዘውድዬ!» እያሉ ያለቅሳሉ:: ብዙዎቹ ቀባሪዎች ግን በፀጥታ ነበር ዕንባቸውን የሚያፈሱት::

ግብዓተ መሬቷ ሲፈፀም ከጉድጓዱ ፊንጠር ብዬ ቆምኩ:: በአካፋ የሚወረወረው አፈር የእንጨት ሳጥኑ ላይ ሲያርፍ የሚያሰማውን ድምጽ ጎላ ያለ ለቅሶና መንሰቅሰቅ አጀበው::

ዓይኖቼ ዕንባ ሲያፈልቁ ተሰማኝ::

ተፈፀመ





## ሚካኤልና ታደለ

የአመለዘውድ ታናናሽ ወንድሞች ሚካኤልና ታደለ ማግኘት ያለባቸውን እንክብካቤ እያገኙ አሁንም በአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት የህጻናት ማሳደጊያ ውስጥ ይኖራሉ:: ሁለቱም ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ነው:: ሚካኤል የፀረ-ኤድስ መድኃኒት ይወስዳል፤ በመልካም ጤንነት ላይ ይገኛል:: ታደለም እንደ ወትሮው ጤነኛና ደስተኛ ልጅ ነው::

## ተሾመ

«መማር ትፈልጋለህ?» ብዬ ጠየቅኩት::

«አዎ፣ በጣም! በጣም!» አለኝ ተሾመ ቃላቶቹን እየተጫነ:: በድምጹ ውስጥ ለመማር ያለውን ጽኑ ፍላጎትና ኃይለኛ ጉጉት አዳመጥኩ::

የአመለዘውድ ታላቅ ወንድም ተሾመ በአሁኑ ጊዜ በግንባታ ሙያ ጥሩ ልምድ ያለው ሠራተኛ ሆኗል:: በግቢያቸው ውስጥ ሁለት ክፍል ቤት በራሱ ጥረት በ2002 ዓ.ም. ሰርቷል:: አሁንም ከማንኛውም ሱስ የጸዳ እንደሆነ ይናገራል፤ ለዚህም ሟች እህቱን አመለዘውድን ያመሰግናል:: ከእሷ ሞት በኋላ ሦስት ጊዜ የደም ምርመራ አድርጎ (ስለተጠራጠረ ነበር ደጋግሞ የተመረመረው) ከኤች.አይ.ቪ. ነጻ መሆኑን አረጋግጧል:: ባለመማሩ ከልቡ ይፀፀታል:: ወደፊት መማርና የተሻለ ኑሮ መኖር አብይ ህልምና ዕቅዱ ነው:: ለመኖር ከአዲስ አበባ እየወጣም መሥራት ስላለበት ግን መማር ቀላል አልሆነለትም::

## የአፍሪካ በኤች.አይ.ቪ. ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት

በአፍሪካ በኤድስ ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት በአሁኑ ጊዜ በህጻናት ማሳደጊያው ከሚያሳድጋቸው ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ ልጆች በተጨማሪ በቤታቸው ከቤተሰብ ጋር ለሚኖሩ ጥቂት ህጻናት የምግብና የልብስ፣ የትምህርት መሳሪያዎችን እንዲሁም የነጻ ህክምናና የመጠለያ እርዳታ ይሰጣል:: እንዲሁም በ1999 ዓ.ም. አንድ ተጨማሪ ቤት በአዲስ አበባ ተከራይቶ ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ህጻናት ከቤታቸው እየተመላለሱ ተመጣጣኝ ምግብ፣ የፀረ-ኤድስ መድኃኒትና ነጻ ትምህርት ማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ አመቻችቷል:: ህጻናቱ ቀኑን ሙሉ በዚህ ቤት እየዋሉ ምሽት ላይ ወላጆቻቸው ወይም ዘመዶቻቸው ቤት ድርጅቱ ይመልሳቸዋል::



Sample output to test PDF Combine only

እስከ ነሐሴ 1997 ዓ.ም. በድርጅቱ በህጻናት ማሳደጊያው የነበሩ ህጻናት የፀረ-ኤድስ መድኃኒት አላገኙም ነበር። ዛሬ ደህና የነበሩ ልጆች አስፈላጊው እንክብካቤ ቢደረግላቸውም በሚቀጥለው ቀን ህይወታቸውን ሊያጡ በሚችሉበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ነበሩ። ይህ የሆነው አንዳንዶቹ ልጆች በኤች.አይ.ቪ. ምክንያት በሽታን የመቋቋም አቅማቸውን በመሟጠጡ እንደነበር የድርጅቱ ዳይሬክተር ወ/ሮ ስድሴ ቡሊ ትናገራለች።

«የፀረ-ኤድስ መድኃኒቶቹ በልጆቹ ህይወት ውስጥ በጣም ከፍተኛ ለውጥ አምጥተዋል። አሁን የሚያስጨንቀን ልጆቹ ሲያድጉ ከድርጅቱ ወጥተው ከህብረተሰቡ ጋር እንዴት ያለብዙ ችግር ይቀላቀላሉ? የሚለው ጥያቄ ነው።» ትላለች ስድሴ።

በእርግጥም ከአመለዘውድ በኋላ በጣት የሚቆጠሩ ጥቂት ህጻናት ብቻ መሞታቸው የፀረ-ኤድስ መድኃኒቶቹን ውጤታማነት በግልጽ የሚያሳይ ነው።

ድርጅቱ ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ ልጆች የሚያድጉበትና የሚኖሩበት፣ ከህብረተሰቡ ጋር የሚቀላቀሉበት፣ የወደፊት ህይወታቸውን ለመምራት የሚረዳቸው የተለያየ ሙያና ክህሎት የሚቀስሙባቸው መንደሮች በአዲስ አበባና በክልሎች የማቋቋም ዕቅድ ይዞ እየተንቀሳቀሰ ነው። ለዕቅዱም በተግባር መተርጎም የግለሰቦችን፣ መንግስታዊ የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶችን የገንዘብና የዕውቀት ድጋፍ በእጅጉ ይፈልጋል።

ለድርጅቱ የወደፊት የህጻናት መንደር ግንባታ ገንዘብ መለገስ ከፈለጉ አዋሽ ባንክ፣ አፍሪካ አንድነት ቅርንጫፍ፣ በባንክ የማጠራቀሚያ ሒሳብ ቁጥር:-**0130428279900** በማስገባት የዜግነት ግዴታዎን ይወጡ! ኤች.አይ.ቪ. ፖዘቲቭ የሆኑ ህጻናትን ተስፋ ያለምልሙ! በህይወትዎ ትርጉም ያለው መልካም ሥራ ይስሩ!

የአፍሪካ በኤድስ ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናት እንክብካቤ ፕሮጀክት
(ኤሆፕ ኢትዮጵያ) አድራሻ:-
ኢ-ሜይል:- ahopeethio@yahoo.com
ahopeethiopia@ethionet.et
ፖ.ሳ.ቁ. 647 ኮድ 1033
አዲስ አበባ


Sample output to test PDF Combine only

ይህን እውነተኛ ታሪክ ያነበብኩት እንደ ልብወለድ በልዩ ተመስጦ ነው። መጽሃፉ ራሳችንን፥ ቤተሰባችንንና አካባቢያችንን መለስ ብለን በፅሞና እንድናይ ያነሳሳናል።

ደራሲ ኃይለመለኮት መዋዕል

ይህ መጽሃፍ የአንድ ቤተሰብ ታሪክ ብቻ ሳይሆን የብዙ ኢትዮጵያውያንን የዕለት ተዕለት ኑሮና የጓዳ ምስጢር የሚዳስስ እውነተኛ ታሪክ ነው።

ስድሴ ቡሊ

ታሪኩ እውነተኛ ታሪክ ቢሆንም አቀራረቡ ስነጽሑፋዊ፥ ቃላቱም ጥበባዊ ናቸው።

ደራሲ ማህሌ ሥላሴ ብርሃነ ማርያም

የኢዮብ ጌታሁን ሌሎች መጻሕፍት

49.60 ብር

ሕትመት ፋር-ኢስት ትሬዲንግ ኃ.የተ.የግ.ማህ
0111565352

Sample output to test PDF Combine only